የሕይወት ግብህን ቅረጽ

Sit & Set your goal in life



የሕይወት ግብሃ ቅረጽ



የመጽሐፉ ርዕስ

የሕይወት ግብህን ቅረጽ

SIT AND SET YOUR GOAL IN LIFE

አዘጋጅ

አሰታዝ ያሲን ኑሩ ሊሳ

አትም

የመጀመሪያ አትም

ሚያዚያ 2007

©

የአሳታሚዉ መብት

ከአዘጋጁ የተጠበቀ ነዉ።

የሕይወት ግብህን ቅረጽ

SIT AND SET YOUR GOAL IN LIFE

ያሲን ኑሩ ዒሳ
ዘን - 2,
የቤት ቁጥር - 7
የአልጋ ቁጥር - 1148
ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት

CamScanner

ማስታወሻነቱ

ለትህትና ተምሳሌት፣ ለደግነት ካስማ፣ ለርህራሄ ዓይነታ፣ የህይወት ዘመኔ ልዩ ክስተትና ስጦታ ... ለሆንሽው ... የእናቶች ናሙና። ለእናቴ ሞሚና ይሁንልኝ።

እናቴ ... ታላላቅ የዓለማችን ዑለማዮች በተከበረው የመካ መስጂድ ከሰገዱባት፣ የነቢያት አባት ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) የገነቡትን የአላህን ቤት በህይወትም ሆነ በህልፈት ከረገጠች ... በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ በዕንባና በዱዓው ካስታወሳት ... የነቢዩ ﷺ የትውልድ ሀገርን፣ የመለኮታዊ ራዕይ ምድርን፣ ደጃል የማይረግጣት ቅዱስ ከተማን፣ በዓለም ላይ ያሉ ሙስሊሞች በሶላት የሚቅጣጩትን ሀገር... ቅድስቲቷ መካን ማረፊያዋ ካደረገች ... እኔስ በዚህ ታላቅ ዕድልና ክብር እንዴት አልፅናናም?!

ለመብት ትግሉ ስኬት - የአቅማችሁን ያህል ላበረከታችሁ... ሁሉ ይህ መፅሀፍ ማስታወሻ ይሁንልኝ።

"እነዚያ ያመኑትና መልካሞችንም የሰሩት፣ እነዚያ እነሱ ከፍጥረት ሁሉ በላጭ ናቸው።"

ሁሌም ታሪክ ያወሳችኋል...

"በዚያ ባሰቃቂው በከፋው ዘመን
የነፃነት ትግል እንዲያገኝ ብይን
ለተበደሉና አቅም ላነሳቸው
ጠበቃቸው ሆኜ ሰለቆምኩላቸው
የማያስታውሰኝ የማይጠራኝ የለም
ነገም ከነግ ወዲያ ዛሬም ለዘልዓለም"

(አሌክሳንደር ፑሽኪን)

ሱብሓነከ (ጥራት ይገባህ) - Glory to you

የፍጥረተ ዓለሙ እናፅ ሆይ! ከሁሉም በፊት፣ ከሁሉም በላይ ለአንተ ላቅ ያለ ምስጋና ይድረስህ። በዚህ ስራዬ የአንተ እርዳታ ጠዋትና ማታ አልተለየኝም። ብርታትን ለግሰኸኛል። ነገሮችን ሁሉ አቅልለህልኛል። የተቋጠሩትን ሁሉ ፈተህልኛል... ጥራት ይገባህ (ሱብሓነከ)።

የዓለማት ጌታ ሆይ! - በዚህ ስራዬ አንተን ላወድስህ እንጅ ክፍያ (እጅር) ልጠይቅህ ወኔ የለኝም። ምክንያቱም ይህ ስራ በራሱ ለእኔ የዋልከው ታላቅ ፀጋ ስለሆነ። ለፀጋና ውለታ ምስጋና ይቀርባል እንጅ ክፍያ አይጠየቅበትም።

ጌታዬ - ሙሉ ስራዬን የአንተን ፊት ተፈልጎ የተሰራ ታደርግልኝ ዘንድ በተከበሩና በላቁ ስሞችህ እማፀንሀለሁ።

"... የሰማያትና የምድር ፈጣሪ ሆይ! አንተ በቅርቢቱና በመጨረሻይቱ ዓለም ረዳቴ ነህ፤ ለአንተ እጅ የሰጠሁ ሆኜ ለሀልፊተ ሞት አብቃኝ፤ ወደ መልካም ባሮችህም አስጠጋኝ።"[2]

"...እጅግ በርካታ ከሳይንሱም፣ ከመንፈሳዊውም ዓለም የተቃረሙ አስረጅ ምሳሌዎች፣ ማራኪ አቀራረብ፣...ይህቺ በእስር አጋጣሚ ያዝበኩለት የአስታዝ ያሲን ኑሩ መፅሐፍ ‹ግብን መቅረፅ› የስኬት መነሻም፣ መድረሻም መሆኑን እንዳስብ ረድቶኛል።

...በግጥም እያዋዛ ደራሲውን እና አንባቢውን ቀጥታ በሚያገናኝ አተራረክ የሊቁንም፣ የደቂቁንም ቀልብ የሚገዛው ፍሰቱ ፀሐፊው ‹ለነገሩ ብቻ ሳይሆን ለአነጋገሩም› መጠንቀቁን ያሳያል። አስታዝ ያሲን ምናብ እንደዋዛ በማይሰክንበት፣ ማጣቀሻ የመረጃ ምንጭ በቀላሉ በማይገኝበት፣ በጥሞና ተመስጦ ለመፃፍ በማይመችበት እስር ቤት ውስጥ ለአንባቢዎች መፅሐፎችን ማውጣት መቻሉ ሊያስመሰግነው ይገባል።"

በፍቃዱ ኃይሉ የዞን ዘጠኝ ብሎገር

"በታላቁ ዳኋ ያሲን ኑሩ የተፃፈውን ይህን መፅሐፍ እድሉን አግኝቼ ወደ ገበያ ከመውጣቱ በፊት ቀደም ብዬ ለማየት የቻልኩ እና በህይወቴ ላይ ወደ ስኬት ለሚደረገው ጉዞ መነሻ (Check point) ግብዓት እንዲኖረኝ ያደረገ በመሆኑ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ከመፅሐፉ የሚያገኙት ግብዓት አንዴ ቆም ብለው እንዲያስቡ እና የስኬት መነሻ ምንጭን እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል የሚል እምነት ይሰማኛል።

ከዚህም አልፎ መፅሐፍ ሰዎች ድብቅ ችሎታቸውን (ክህሎታቸውን) አውቀውና ፈትሸው የወደፊት ግቦቻቸውን ካላቸው ችሎታ (ክህሎት) ጋር እንዴት ማስተሳሰር እንዳለባቸው የሚገልፅ እና አንባቢው መፅሐፉን በሚያነብበት ሂደት ውስጥ በምናቡ ችሎታውን (ክህሎቱን) እንዲያስብና እንዲያሰላስል በማድረግ ውስጣዊ ማንነታችንን እንድናነብ እና እንድንፈትሽ በሚያደርግ አኳኋን የተፃፈ ግልፅ እና መሳጭ መፅሐፍ ነው።

በአጠቃላይ መፅሐፍ እራሳቸውን በለውጥ ሂደት ውስጥ ላደረጉ ሰዎች እና በተቃራኒው የህይወት ግባቸውን ሳይቀርፁ እንደ መስኖ ውሃ በተከፈተው በር ለሚሄዱ ሰዎች ሊኖራቸው የሚገባ መፅሐፍ ብቻ ሳይሆን ዘውትር እንደ ማጣቀሻ (Reference) ልንገለገልበት የሚገባ መፅሐፍ በመሆኑ ይህን ታላቅ ስጦታ ላበረከተልን ለያሲን ኑሩ የላቀ ምስጋናዬን

በዚህ አጋጣሚ እያቀረብኩ፣ አላህ ምንዳህን ይክፈልህ እላለሁ።

አብዱረህማን ከማል ሙሳ
(የአሊያንስ ትራንስፖርት ሰርቪስስ አ.ማ ዋና ስራ አስኪያጅ)

"ብዙ መፅሐፍትን አገላብጠህ መፅሐፍን በአዲስ Perspective (The west meets the east) በሚባል Senese ማዘጋጀትህ በጣም ያስክብርሃል።"

ዘላለም ክብረት (የዞን ዘጠኝ ብሎገር)

ይህ መፅሐፍ የህይወት ግባቸው ለጠፋባቸው፣ የመኖር ትርጉሙ ላልገባቸው፣ ስኬት ለናፈቃቸው የተበረከተ ስጦታ ነው። መፅሐፉ ቀልብን እየሳበ፣ ልብን እያንጠለጠለ፣ ውስጥን እያናገረ እንዴት የህይወት ግብ መቅረፅ እንዳለብን እና የስኬት ጫፍ ላይ መድረስ እንደምንችል ያስተምረናል።

ስለ ግብ መቅረፅና ራስን ስለመለወጥ የሚያስተምሩ በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ ሀገር ምሁራን የተፃፉ ብዙ መፅሐፎችን እንብቤያለሁ። ይህ መፅሐፍ ግን ከሁሉም የተለየ እና ሁሉንም የሚያስከነዳ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ኢስማኤል ሀሰን ሌክቸረር (ድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ)

"ዛሬ የምናርበት ደረጃዬ ነገ ልናርበት ለሚገባኝ ደረጃዬ በቂ አይደለም ብሎ ለውጥን ለሚናፍቅ ወጣት ከዚህ መፅሐፍ የተሻለ የማመላክተው ነገር የለኝም። መፅሐፍ ላይ በነበረኝ (የአርትኦት) ተሳትፎ ምክንያት፣ መፅሐፍን ደጋግሜ በማንበቤ ብዙ መልካም ነገሮችን ያበረከተልኝና፣ የራሴን የህይወት ጉዞ በተመለከተ ስሜቴን በመግራት ለተሻለ ህይወት እንድነሳሳ አድርጎኛል።

ጊዜው ሳያልፍ ማቀድ ብልህነት ነው። የቀልድ የሚኖርበት ዘመን አልፏል። አሁን ጊዜው የምር የሚኖርበት ነው። ምድር፣ ለህይወት ፍርፋሪ እንደ ዶሮ ከመናቆር የሰፋች ናት። የዚህ መፅሐፍ አዘጋጅ አሳማም ግለሰብንም ሆነ ማህበረሰብን ከራስ ጠባብ ወሰን አውጥቶ ወደ

ላቀና ሰፊ መስክ ማሸጋገር ነው። ይህም ነው ኢትዮጵያ ሀገራችንም ሆነ እሁን በታላቅቀውስ ውስጥ የምትገኘውን ዓለም የሰላምና የስልጣኔ ቁንፎ ላይ ሊያደርሳት የሚችለው።

እየቀሸነው እንጂ ሀሊናችን ሁሌም የሚነግረን ዕውነት አለ። ከዚህ እውነት ለመድረስ ደግሞ ይህንን መፅሐፍ በጥሞናና ለለውጥ በተዘጋጀ መንፈስ እናንብበው።

እኛ ኢትዮጵያዊያን በአመዛኙ በዘመናዊ አስተሳሰብ ያልታሸን ነን። ከዘመኑ ጋር አብሮ ለመዘመን ደግሞ የህዳሴ ፊር ቀዳጅ (Pionner) መኖሩ የግድ ነው። ምክንያቱም አቅጣጫ ጠቋሚ ሲጠፋ እንደ ማህበረሰብ መጓንት ይከሰታል።

ሀገራችን የለውጥ ሀዋርያዎችን (Change Agents) ሊያፈሩላት የሚችሉ የለውጥ አቀንቃኞችን (Change Catalists) አጥብቃ በምትሻበት በዚህ ወቅት ያሲን ኑሩን የመሰለ ሀገር ወዳድና የለውጥ ቀንዲል የሆነ የህዝብ አስተማሪ በመሀላችን መኖሩ በእርግጥ መታደል ነው።

ጅብሪል ዑመር የኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ተማሪ
(አዋሳ ዩኒቨርሲቲ)

ይህን መፅሐፍ የጀመረ ሰው የሌሊቱንና የቀኑን ማጠር ይበልጥ ይረዳል። ማለቴ - መፅሐፉን ከከፈቱት ሊዘጉት የማይቻል፣ በህይወት ላይ ትልቅ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችል... ዘመን ተሻጋሪ ድንቅ ስራ።

ኤሊያስ ከድር

ይህን መጽሐፍ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ ደጋግሜ አነበብኩት፣ እጅግ አርኔ ወደድኩትም። እንደ ማር በሚያዘንባችው ቃላቶቹ የምናውቀው ውዱ ወንድማችን ኡስታዝ ያሲን ኑሩ ለዚህም ሆነ ለመጭው ዓለም ስኬት የሚረዱንን መልዕክቶች በውብ አጣጣሉ አድርሶናልና እጣችሁን ጊዜ ወስደን እናንብብ።

ሙሐመድ ሰዒድ (ፀሐፊና ተርጓሚ)

ማውጫ

የት እየሔድክ ነው? 15
ትንሽ ስለ መፅሐፉ 18
ከዚህ መፅሐፍ የበለጠ ትጠቀም ዘንድ 20
ኢትዮጵያ አንተን ትጠብቃለች 22
ምኒማ 25
ምዕራፍ አንድ 27
አንዴ ቁጭ በልና ዓላማህን ቅረፅ 28
1.1 ቀስተኛው 28
1.2 የአንበሶቹ ገዳይ 30
- የፖሊሲያችን ውጤት ነው 31
1.3 መቁረጫውን ሳለው 32
ምዕራፍ ሁለት 34
በዓላማ የመንዝ ትሩፋቶች 35
2.1 ግልፅ ህይወትን ከመምራት የሚወለድ ደስታን ለመጎናፀፍ 35
2.2 የራስህ ህይወት ሾፌር አንተው እንድትሆን ያስችልሃል 35
- የአትክልት ስፍራና ጫካ 35
2.3 መርጠህ መስራት እንድትችል ያደርግሀል 36
2.4 ትኩረትህን በመሰብሰብ ውጤታማ ያደርግሃል 38
2.5 ሰው የመሆንህ መገለጫ ስለሆነ 38
2.6 ፅናትን ይለማመዳል 39
- ጥያቄ አለኝ? 39
- የት አለ ሳቅ 40
- ሽሽት 41
2.7 ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም ይረዳናል 42
2.8 ባትደርስበትም ክፍያውን (እጅጉን) ታገኛለህ 44
ምዕራፍ ሶስት 45
የህይወት ግብህ ምንድን ነው? 46
3.1 ባለ ራዕይ ሁን! 46
3.2 ህይወት ያለ ዓላማ 46
- ፕሪሚየር ሊግ 46
- ተራው ሰው 47
- መንገዱ ወደ የት ይወስዳል? 48
3.3 መጪረሻን ወስኖ መንቀሳቀስ 50
- አውሮፕላን አብራሪው 52
3.4 ሁሉም ነገር ሁለቴ ይፈጠራል 53

- ዲዚኔ ላንድ 54
ምዕራፍ አራት 56
ተስፖህን ፈልግ 57
- ለምን ተገርተሃል 58
- ታላቁ ማዕድን 59
- አስላ ስጋ 59
4.1 ተስፖአን መፈለግ ለምን አስፈለገ? 60
4.2 ተስፖአን ለማግኘት የሚረዱን ነጥቦች 61
4.2.1 ጠንካራ ጎኖችህን ለይተህ እወቅ (Identify your strength) 62
4.3 በአጋጣሚ ታገኘዋለህ 64
- ሀገሬን እንዴት ልታደጋት? 65
4.4 ሌሎች ያመላክቱሀል 66
- እይታ ሲስተካከል 66
- ውሻህ ዋና አይችልም 69
- አቡ ሐኒፋ ሆይ! ንግድ አያጠግብህም 71
4.5 ማንነትን ፍለጋ 73
- አንቶኒዮ ሮቢንስ 73
- ዶ/ር ፋይዝ ሰያል 75
4.6 ለብዙ ነገር ፈጣሪ ገርቶህ ቢሆንስ? 77
- ቁንጠኛዋ ዝየ 78
ምዕራፍ አምስት 80
የህይወት አላማችንን እንዴት ማስቀመጥ እንችላለን? 81
5.1 ለምን ተፈጠርን? 81
- አንስታይን 82
- ኢልያ አቡ ማዲ 83
- እንዳይነግርህ አንዳች እውነት 86
5.2 ለአምልኮ 87
- ንግግር ስንል 88
- ድርጊት ስንል 88
5.3 የግቦች ግብ (The Goal of Goals) 90
- ቃሩን (Korah) 91
- ሁሉንም ለዓለማቱ ፈጣሪ አድርግ 93
- ትጋትን ይለግስሀል 94
5.4 ወደ መነሻችን ስንመለስ 95
ምዕራፍ ስድስት 97
መሆን ከምንፈልገው አንፃር 98

6.1 መሆን የምንፈልገውን ነገር ማወቂያ መንገዶች.....98
6.2 ከመወሰንህ በፊት.....101
6.3 አንተ ራስህን ምን ላይ ማግኘት ትፈልጋለህ?.....102
- ከዛሬ በኋላ አልቀጥልም.....103
6.4 አቡ ሐኒፋ የትምህርት መስክ እንዴት መረጡ?.....105
ምዕራፍ ሰባት - ግብህ የተብራራ ይሁን.....109
7.1 ግብህ የስምህን ያህል ግልፅ ይሁን.....110
7.1.1 BMW.....110
7.1.2 معتق (መዕተቅ).....111
7.1.3 ዓላማዬ የነብዩ ሰ.ዐ.ወ. ዱዓ ነው.....113
7.1.4 ሚአተ - አላፊ.....114
7.2 ግብህ ግልፅና የተብራራ ይሁን.....122
- Yole University.....125
ምዕራፍ ስምንት - የህይወት ግብ ለሁሉም.....128
8.1 የህይወት ግብ ለህፃናት.....130
- እንደ ሶሀቦቹ.....131
- ጀምስ አርዊን.....133
8.1.1 እናመላክታቸው እንጂ አንጫናቸው.....134
- ዲግሪው ያባቴ ነው.....134
8.1.2 የልጆች ስንፍና.....136
- ፓብሎ ፒካሶ.....136
- አጋታ ክርስቲ.....137
- አልበርት አንስታይን.....137
- ቶማስ ኤድሰን.....138
8.2 የህይወት ግብ ለጡረተኞች.....140
- እኔ አላረጀሁም 141
- ኪንታኪ.....141
- ለዓለም ማሳየት እፈልጋለሁ.....142
- ህልሜ እውን ይሆናል.....143
ምዕራፍ ዘጠኝ ወደ - ስኬት ስታቀና.....144
9.1 ሚዛናዊ ህይወትን ምራ.....145
- ታላቁ ውርስ.....145
- ራስን በተመለከተ.....148
9.2 ሀብት ስኬት አይደለም.....149
9.2.1 ጥሎህ ይሄዳል.....149
9.2.2 አንተ ጥለኸው ትሄዳለህ.....151
- ታላቁ አሌክሳንደር.....151

9.3 ንብሀ ሁሌም አብሮህ ይሁን 154
- ፊሊፕስ ካምፓኒ 154
- ስቲቭ ጀብስ 155
9.4 ደቻላል 156
- ጥምጥሚ ነጭ ነው 156
- እንጂህ ተብሎ ነበር 156
- የውድድሩ ሻምፒዮን 158
- You Can 161
9.5 ለህይወትህ ራስህ ሀላፊነትን ውሰድ 164
ምዕራፍ አስር - በመንገድህ ላይ 165
10.1 ስራህን ለዓለማት ጌታ ብቻ አድርግ 166
- ባሉን ሻይ 167
10.2 በጌታህ ተደገፍ 168
- ሽልማት ይገባናል 169
10.2.1 በጌታህ የመደገፍ (ተወኩል) ትክክለኛ ገፅታ 171
- ሂጅራ 172
10.3 ጠንካራ ወኔ ይኑርህ 173
- በቀርጥ ፈልገው 176
- ሶስቱ አባ አጥማጆች 177
- ነፍሴ ወኔ የተሞላች ናት 180
- መናኛ ግቦች 182
10.4 አላማህ አስኪሳካ ታጋሽ ሁን 183
- ቶማስ ኤድሰን 184
- የቡሻሪ ፅናት 186
- እንዲታቀም 188
- Don't Quit 190
ምዕራፍ አስራ አንድ 191
የስኬት መርሆች 192
11.1 በአላማ ኑር 192
11.2 የለውጥ ሀግ 192
11.3 በሀብረት ወደ አላማህ ተግዝ 196
11.4 የስኬት ዋጋ 197
11.5 ተግባራዊ እርምጃ 199
11.6 ከፍተኛ ጉጉት ይኑርህ 201
11.7 የንብህን ጉዞ ልመደው 202
11.8 አሻራህን ትተህ አለፍ 203
11.9 ስኬትና ሽንፈት 205
11.10 በስኬትህ አትኩራ 206
11.11 ሰው እንጂ ተቀባይ አትሁን 207
11.12 የማይመለከትህ ነገር ውስጥ አትግባ 209
11.13 እንዳትጠሉኝ 209
11.14 ሁሉም ነገር መፍትሄ አለው 211
11.15 ሁሉንም ማስደሰት አትችልም 213
11.16 ጥበብን ሁሉም ቦታ ፈልገው 219
ምዕራፍ አስራ ሁለት - የስኬት ተምሳሌቶች 221
12.1 ቡሻሪ 226
- ሌሊሁል - ቡሻሪ 229
- ለአላማ ኑር 229
12.2 ሙሐመድ ዩኑስ 229
- የህይወት አጋማሚ 231
- የለውጡ እርሾ 232
- ብድርን ፍለጋ 233
- ሀላፊነትን መውሰድ (Risk Taking) 234
- የግራሚን ባንክ ምስረታ (Grameen Bank) 237
- The Secret of living is Giving 238
12.3 ታላቁ መልዕክተኛ 239
- ብዙ ዘመን ኖሩ 240
- Lead Like Prophets 241
12.3.1 ነብዩ ሙሐመድ ወደ ሰው ልጆች ከመላካቸው በፊት (Before the Advent of the Prophet) 243
12.3.2 የኢስላም ፀሐይ ከአድማሱ ላይ ሲፈነጥቅ 243
- የመልዕክተኛው ﷺ የህይወት ግብ 245
12.3.3 የንቦው ጀማሮ 246
- የግለሰቦች እነፃ 247
- ንዞ ወደ አላማ 247
12.3.4 ለስኬት የተከፈለ ዋጋ (The Price of Success) 249
- ከፍተኛ ግፍ 252
- ማዕቀብ 252
- ሚኢፍ 253
- ስደት ወደ መዲና 254
- ማሳደድ 255
- ሁለንተናዊ ዘመቻ 256
12.3.5 አመርቂ ስኬት (Great Seccess) 263
- መልዕክተኛውን ﷺ በግጥም

መግቢያ

- የት እየሄድክ ነው?
- ትንሽ ስለመፅሐፉ
- ከዚህ መፅሐፍ የበለጠ ትጠቀም ዘንድ
- ኢትዮጵያ አንተን ትጠብቃለች
- ምስጋና

In the Name of Almighty The Merciful The Compassionate

በአላህ ሥም አድማ በጣም ሩህሩህ አድማ በጣም አዛኝ በሆነው።
ምስጋና ፍጥረተ-ዓለሙን አስውቦ ለቀረፀው ጌታ ይሁን። ሰላምና
ደህንነት በዓለማቱ ጌታ መልዕክተኛች ላይ ይስፈን።

የት እየሄድክ ነው?

"ወዴት እንደሚሄድ ለሚያውቅ ሰው ይህች ዓለም መንገዱን ትለቅለታለች።" Emerson

የት እየሄድክ ነው? ወዴት እያቀናህ ነው? የህይወት ግብህስ ምንድነው? በምድራዊ ቆይታህ ምንን ማሳካት ትመኛለህ? ከአስር ዓመት በኋላ ራስህን ምን ቦታ ላይ ደርሰህ ማግኘት ትፈልጋለህ? እየሰራኸው ደስታን የሚለግስህ፣ ባይከፍሉህ እንኳ በነፃ ልትሰራው ፍቃደኛ የሆንከው የስራ መስክ የቱ ነው? በራስህ በማንነትህ) ላይ ደስተኛ ነህን?

በተከፈተው በር ሁሉ ዘው ብለህ የምትገባው፣ ለቀረበው ምግብ ሁሉ እጅህን የምትሰነዝረው፣ ያገኘኸውን ሁሉ ጓደኛህ የምታደርገው፣ ከፊት ለፊትህ በአጋጣሚ ለመጣው ስራ ሁሉ ደፋቀና የምትለው ለምን ይመስልሃል? የአድገት ጉዞህ የኋልዮሽ የሆነበት ምክንያቱ ምንድነው? ጊዜያዊ ደስታን በሰጠህ ጉዳይ ላይ የተጠመድከው ለምን ይሆን? ገቢያ አንድን ነገር ልትገዛ ሄደህ ሌላ ነገር ገዝተህ የምትመለሰው ለምን ይመስልሃል?

ብዙዎቻችን በተለመደ የህይወት አሰልቺ -ሽክርክሪት ውስጥ እንገኛለን። የምንፈልገውን ነገር በሚያጠፋ እንቅስቃሴ ውስጥ ተወጥረናል። እርምጃዎቻችን ቀድመን ካስቀመጥነው ግልፅ ግብ አንፃር የተቃኙ አይደሉም። "ባለህበት ሂድ!" የሚለው ወታደራዊ ትዕዛዝ እንኳን በማይመጥነው ተመሳሳይ

'ታላቅነት ከሌሎች በላይ መሆን አይደለም። እውነተኛ ታላቅነት ከትናንት ማንነታችን የተሻልን መሆን ነው።' የሚለውን የህንዶቹ አባባል ዘላቂ እውነታነት እንዳለው ልብ በል።

አብዛኛው ሰው ተስጥኦውን ባላማከለ የህይወት ጉዞ ላይ እየተንደፋደፈ ነው። የሰውን ልጅ ህይወት፣ የዓለምን ተጨባጭ መለወጥ የሚችሉ እምቅ ሀይሎችና ተሰጥኦዎች እንደዋዛ ሲባክኑ ትመለከታለህ። እነኚህ ተሰጥኦዎች ቆፍሮ አውጥቶ ጥቅም ላይ የሚያውላቸው ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ማህበረሰብ፣ መንግስት... ባለመኖሩ ምክንያት እንዲሁ ሲከስሙ ይታያሉ። ስንትና ስንት ተሰጥኦዎች ለሰው ልጅና ለዓለም መልካምን ነገር ሳያበረክቱና አገልግሎት ሳይሰጡ መቃብር ወርደዋል መሰለህ?! ለዚህም ነው ‹ከርሰ-ምድር ውስጥ ካሉ ማዕድኖች ውስጥ ዋናው የሚገኘው መካነ-መቃብሮች ውስጥ ነው።› የሚባለው።

እንዲሁ እንደዋዛ
አራሹ ሳይለግም
ሳይሰሳ ደመና
ከሀሎት ድርቅ መታው
ዘር መብቀያ አጣና[3]

አሁንም ዳግም ልጠይቅህ - የአንተ ተሰጥኦ ምንድነው? የፈጠረህ ፈጣሪ ለምን ነገር ገርቶሀል? ከዚህ አንፃር የቀረፅከው የህይወት ግብስ አለህ?

እነዚህ ጥያቄዎች ብዙ እንዳማለኑህ እገምታለሁ። ምክንያቱም ይህን መፅሀፍ ከበርካታ መፅሀፎች መሀል መርጠህ ገዝተኸዋልና። "የህይወት ግብህን ቅረፅ" የሚለውን ርዕስ ስታይ፣ ለቀጣዩ ህይወትህ መንገድን እንደሚጠቁምህ ገምተሀልና።

አይዞህ አልረፈደብህም። "መሆን የነበረብህን ለመሆን መቼም ቢሆን አይረፍድም"[4]። ብቻ ለራስህ ትንሽ ጊዜ ስጠው። "ቢዚ ነኝ።" የሚለውን ወንዝ የማያሻገር ምክንያት ለሰነፎቹ ተውላቸው። ደግሞስ "ከስራ ውጪት ብዛት ስለራሳችን የምናስብበት ጊዜ ካጣን፣ ይህ ህይወት ለእኛ ምናችን ነው?"[5]። ይልቅ በል ቆርጠህ ተነሳ። መድረሻህን ወስነህ መንገድህን ጀምር። ራስህን ለመለወጥ ለራስህ እድል ስጠው። በራስ ላይ ለውጥ

---

[3] መነሻ ሀሳብ - የንጥም ስብስብ ከተሰኘው የንጥም መድብል ላይ የተወሰደ
[4] ጸርጀ ክርክበት
[5] ይሰሌው ኢቸ ደቭስ

ማወጅ የውድድሩ ዘመን በእኛ ላይ ግዴታ ያደረገው ጉዳይ መሆኑን አትርሳ። ስለዚህ አንዴ ቁጭ በልና ከራስህ ጋር አውራ። የህይወት ግብህን አስምር።

"SIT ONCE TO SET YOUR GOAL IN LIFE"[6]

[6] በለውጥና ራስን በማብቃት (Change & personal Development) ዙሪያ የሚዳሱ መፅሀፎች ብዙ ጊዜ "ከስኬት" ጋር በተያያዘ መጠሪያቸውን ያገኛሉ። የስኬት መንገድ፣ 17ቱ የስኬት መርሆዎች፣ የስኬት ጥበብ፣ 25 የስኬት ቁልፎች፣ 7ቱ የስኬታማ ሰዎች ባህሪያት... የሚሉት ከብዙው በጥቂቱ ናቸው። እኔም የዚህን መፅሀፍ ርዕስ "ታላቁ ስኬት" ወይም "ስኬታማ ህይወት" ለማለት አስቤ ነበር። ነገርግን አንድ ሰው እንዴት ግብ ሳይቀርፅ ስኬታማ ሊባል ይችላል? የቃጣንለትን አላማ ላይ መድረስ አይደለም እንዴ ስኬት የሚባለው?

አምላ የስኬት መሰረት (foundation) ግብ ማውጣት ሆኖ አገኘሁት። ስለዚህ መፅሀፌም የስኬት መሰረት ከሆነው ከግብ መቅረፅ ስያሜዋን ወሰዳ... "የህይወት ግብህን ቅረፅ" ሆነ መጠሪያዋ።

ትንሽ ስለመፅሐፉ

"እውቀት እስከወዲያኛው ድረስ አለማወቅን እንደገዛው ይኖራል::"
James Madison

ስኬት ላይ የሚያጠነጥን መፅሀፍ ለማዘጋጀት ስነሳ፣ ማህበረሰቡ
ዘንድ እምንታዊ ተፅዕኖን ያስገኛሉ ብዬ ካሰብኳቸው መፅሀፎች ውስጥ
አንዱን ተርጉሜ ለንባብ የማብቃት ሀሳብ ነበረኝ:: "The 8th Habit"
የተሰኘውን የክቬን መፅሀፍ አሳጥሬ ለማዘጋጀት መንገድ ጀምሬ ነበር::
በኋላ ግን የእርሳቸውንና ራስን በመለወጥ (Personal Development) ዙሪያ
የተፃፉ በርካታ መፅሀፍትን እንደ ጥሬ ዕቃ (ግብዓት) በመጠቀም
ከመለኮታዊ እሴቶች ጋር በማዋሀድ የራሴን ወጥ ስራ ማዘጋጀት የተሻለ
ሆኖ ስላገኘሁት ይህችን መፅሀፍ ከተብኩ::

ደግሞም እኛ ኢትዮጵያውያን በትርጉምና በእርዳታ ብቻ መኖር
መምረጥና መውደድ ያለብን አይመስለኝም:: እራሳችን ሰርተን እራሳችንን
መቻል፣ እንዲሁም እራሳችን ፅፈን እራሳችንን መምራት ባህላችን ማድረግ
አለብን:: ... ይህንንም ለማድረግ ደግሞ እንመጥናለን:: አዎ
እንመጥናለን!::

ይህ መፅሀፍ ህይወትህንና የኢኗኗር ዘይቤህን ሙሉ በሙሉ
ይለውጠዋል የሚል ተስፋ ሰንቂያለሁ:: ሌላው ቢቀር ግን ራስህን ቆም
ብለህ እንድታይ፣ ለህይወትህ አዲስ ምልከታን እንድታዳብር፣ አዲስ
የአስተሳሰብ ቅኝት (New paradigm Thinking) እንድታጎለብት እንደሚረዳህ
ግን አልጠራጠርም::

በህይወታቸው አንድ ነገር እንዳጡ፣ በሚመሩት ህዝባዊ እንቅስቃሴ
ላይ አንድ ነገር እንደጎደላቸው ለሚሰማቸው ሁሉ ይህ መፅሀፍ አስፈላጊ
ነው ብየ እገምታለሁ:: ያጡትን ማንነት፣ የጠፋባቸውን አቅጣጫ (True
North) ከማግኘት አንፃር አወንታዊ ሚና ይጫወታል የሚል እምነት
አለኝ:: ታዲያ ህይወትህ ውስጥ ባዶነት ሲሰማህ፣ እንዳልተሳካልህ
ስታስብ፣ በለስ እንዳልቀናህ ስትገምት... ያኔ ይህ መፅሀፍ ያስፈልግህል...
ያኔ እነዚህን ገፆች በደንብ አገላብጣቸው::

በለውጥና ራስን በማብቃት ርዕሶች ዙሪያ ላይ የሚፃፉ መፅሀፎች
የሚያተኩሩት በምዕራባዊያን የስኬት ተምሳሌቶች ተመክሮና ጥበባዊ
ንግግሮች ላይ ብቻ ነው:: በዚህ መፅሀፍ ውስጥ ግን የምዕራባዊያንንም

ሆነ የምስራቃውያንን ታላላቅ ስብዕናዎች በአንድ ማዕድ ታገኛቸዋለህ። ፀሐፊዉ ደግሞ ሙስሊም ላልሆኑ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቼ፣ በዚህ መፅሀፍ ውስጥ እውቅ የምስራቁ ዓለም የለውጥ ቀንዲሎችንና ኢስላማዊ ዮተሀድሶ መሪዎችን እንተዋወቃለን። ቡኻሪ ማናቸው? ታሪክ ልትደግመው ያልቻለችው የፅውቀት ፈር ቀዳጅ ሊቅ አቡሐኒፋ ማን ነበሩ?... ከውስጥ ገፆች የምናነበው ይሆናል።

እም! ምናልባት እስከ አሁን የምናውቃቸው፡- እነ ሶቅራጥስን (469-399 B.C)፣ ቤንጃሚን ፍራንክሊንን (1706-1790)፣ ዊሊያም ዊልበርፎርስን (1759-1833)፣ አብርሃም ሊንከንን (1809-1865)፣ ማንተማ ጋንዲን (1869-1948)፣ ማልኮም ኤክስን (1925-1965)፣ ማርቲን ሉተር ኪንግን (1929-1968)፣ ኔልሰን ማንዴላን (1918-2013)፣ የአሲሲው ፍራንሲስኮን (1182-1226)፣ እማሆይ ቴሬዛ (1910-1997)... ወዘተ ብቻ ሊሆን ይችላል። ይህ መፅሐፍ ግን ገና ያላወቅናቸውንና ያልዘመርንላቸውን የእውነተኛ ስኬት ባለቤቶችን ያስተዋውቅሀል።

በዚህ መፅሀፍ ውስጥ የበርካታ ፈላስፋዎች አባባሎች፣ የህይወት ተሞክሮዎች፣ የታዋቂ ግለሰቦች ጥበባዊ ንግግሮች... ሰፍረዋል። የነዚህ ግለሰቦች ርዕዮተ-ዓለም "ከመለኮታዊ" እሴቶች አንፃር ተቃኝተዋል። ጥበብ የጠፋ ንብረታችን ነውና፣ ካገኘሁበት ቦታ ሁሉ አድኜ ገንቢ አስተምህሮቶቻቸውን በዚህ መፅሀፍ ውስጥ አስፍሬያቸዋለሁ።

የግል ተሞክሮዎቼንና ገጠመኞቼን አልፎ አልፎ ጠቅሻቸዋለሁ። ለዚህ እንደማልመጥን ባውቅም፣ ከቁንፅሏ የህይወት ተሞክሮዬ ትንሽም ብትሆን የሚጠቅምህ ነገር ብታገኝ በሚል ተስፋ አዘል ምኞት ነው። መፅሀፉ ለሁሉም ማህበረሰብ (በተለይ ለተርታው የማህበረሰቡ ክፍል) ይሆን ዘንድ ሀሳቦችንም ሆነ የቃላት አጠቃቀሞችን ቀለል ለማድረግ በጣም ጥረት አድርጌያለሁ። ታሪኮችንና ምሳሌዎችን በመጥቀስ[7] እንዲሁም "የፊት ለፊት ንግግር" የአፃፃፍ ዘይን በመጠቀም የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የቻልኩትን ያህል ጥሬያለሁ።

[7] ታሪክና ምሳሌዎች በሰው ልጆች ልቦና ውስጥ ታትመው፣ በሞንቅላታቸው ውስጥ ተቀርፀው፣ በልቦናቸው ውስጥ ተንቅሰው የሚቀሩ ትዝታዎች ናቸው።
"The picture Created in the heart and Mind of a person by a story is worth ten thousand words" — (Covey — Living the 7 Habit — P. 16)

ከዚህ መፅሀፍ የበለጠ ትጠቀም ዘንድ

"አላህ ሱ.ወ. ከአለምሮ የበለጠ አሱ ዘንድ የተላቀ (የተከበረ) ፍጡር አልፈጠረምነ" ነብዩ ሙሐመድ ﷺ

ከዚህ መፅሀፍ የበለጠ ተጠቃሚ ትሆን ዘንድ የተማርከውን ለሌሎች አስተምራቸው። ከጓደኞችህ፣ ከስራ ባልደረቦችህ እንዲሁም ከቤተሰቦችህ ጋር ተወያዩበት። ይህ የበለጠ የቤተሰብ ትስስርን ያጠናክራል። በልጆችህ እና በባለቤትህ/ትሽ ውስጥ ያለን እምቅ ክህሎት እንድታዳምጥ/ፍኒ እድል ይሰጥሀል/ሻል።

"ለምችን የበለጠ ማስተማር ከፈለክ ወደ መምህርነት ቀይራቸው።" ያለው ማን ነበር?

የተማሩትን ለሌሎች እንዲያስተምሩ፣ ያወቁትን ከሌሎች ጋር እንዲወያዩ አድርጋቸው። ያኔ እያንዳንዱ ተማሪ መምህር ወደ መሆን ሲያድግ፣ እያንዳንዱ መምህር ደግሞ ጥሩ ተማሪ ይሆናል።

በኔ እምነት ማስተማርን የመሰለ የመማሪያ መንገድ አላየሁም። ለሰዎች ባስተማርክ ቁጥር አንተ የበለጠ ትምህርቱ ይገባሃል። ቀድሞ ያላየሀቸው ነገሮች ይገለጡልሀል። ልብስን ለማፅዳት ብለህ ስትነሳ ጥሩ አድርገህ ባጠብክ ቁጥር እጅህ በደምብ እንደሚፀዳው መሆኑ ነው። ስለዚህ በስብስባችህ (በጀመዓችሁ) ውስጥ በጥልቀት ተወያዩበት፣ ተማማሩት፣ ሀሳቦችን በነፃነት ተለዋወጡ።

ጥሩ ምግብን ለማብሰል የምግብ ዝግጅት መማሪያ መፅሀፍ (Cook-book) እንደሚያስፈልግህ ሁሉ፣ ይህም መፅሀፍ የስኬት ማማ ላይ ትወጣ ዘንድ ለስኬት ወሳኝ የሆኑ ቅመማ-ቅመሞችንና የአሰራር ቅደም ተከተሎችን በዝርዝር ያካተተ ነው ብዬ እገምታለሁ። ስለዚህ ገፆቹን በእርጋታ አንብባቸው። እያንዳንዱን ዐረፍተ-ነገር በደንብ አላምጥ። እያንዳንዱን ምዕራፍ ባስተነተንክ ቁጥር አዲስ ነገር ይሰጥሃል የሚል ተስፋ አለኝ። ብትችል እጅህ ላይ ብዕር አይጥፋ። ጠቃሚ ሀሳብ የያዙ ነጥቦችን አስምርባቸው[9]። ቢያንስ በወር አንዴ መለስ ብለህ/ለሽ አላማህን/ሽን ከመፅሀፉ አንባር መቃኘቱን አትርሳ/ሽ።

[8] አትቲርሚዚ እንደዘገቡት

[9] ንዑቀት በርጋፒ አውሬ ነውና ወረቀትን መጋዘን፣ ብዕርን ደግሞ ጠባቂ ዘበኛ አድርጋችሁ አቁሙት። ሙሐያራቱል አደባእ

ይህን መፅሀፍ አንብበህ ህይወትህን ትለውጥ ዘንድ ሁለት ሀሳቦችን መከተል ይኖርብሀል። እነዚህም፡-

የመጀመሪያው ሀሳ - መፅሐፉን በትኩረትና በየልቀት ረጋ ብለህ አንብበው፣ እያንዳንዱን ምዕራፍ ከጨረስክህና ከንደሞችህ (ከጀመንምችህ) ጋር ዘና ብለህ ተወያይበት፣ ወደ ተግባርም አውርደው።

ሁለተኛው ሀሳ - የመጀመሪያውን ህግ አትርሳ!!

"እርግጠኛ ሁን። አንተ ያለምንም ጥርጥር ለስኬት ተፈጥረሃል።"

ኢትዮጵያ አንተን ትጠብቃለች!

"ስኬት ማለት ሀገርህ ለአንተ ከምታደርገው የበለጠ ለሀገርህ ማድረግ ነው።" Henry Ford

ሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ የሰው ሀይልና ያልተነካ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ሀገር ናት። ለም መሬት፣ ሰፊ መልክዓ-ምድር እንዲሁም ለኑሮ ተስማሚ የሆነ የአየር ንብረትን ተችራለች። ውብ የተፈጥሮ መስህቢ የተመልካችን አዕምሮ ስላም ይመግባል። ሀገራችን ውብና ያማረ ምድራዊ ስታዲየም ብትሆንም ጥሩ ተጫዋቾችን ግን አላገኘችም። አጥቂም ኪሷን ወደራሳቸው የግብ ክልል ይጠልዛሉ። የራሳቸውን ተከላካዮች ይኮምካሉ። በራሳቸው ቡድን ላይ "ሀትሪክ" ይሰራሉ።

ይችላል ይሉሀል	-	ፍልሚያ ማዘጋጀት
ያባት አጥንት ወስዶ	-	ሰሎ ጦር ማበጀት
አንተው ጦር ወርውረህ	-	አንተው ቀድመህ ወደቅክ
አካሌ ደረቴ	-	መሆንክን መች አወቅክ[10]

ድህነቷን ታሪክ ያደርጉ ዘንድ ተስፋ የሚጣልባቸው ልጆቿን እስከ አሁን ማህፀኗ ጥቂት እንጂ ሊያመርት አልቻለም። እውነተኛ ለውጧን፣ ሁለንተናዊ እድገቷን ለማምጣት ደፋ ቀና የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው። በአንድ ላይ ለለውጥ የሚዘምሩና አብሮ ለማደግ የወሰኑ አዲስ ትውልዶችን በመጠባበቅ ላይ ናት።... እውቁ ደራሲ አርመን "The Beautiful Once are not Yet born"[11] **"ቆንጆዎቹ ገና አልተወለዱም"** ሲል የፃፈው እኛን አይቶ ይሆን?

አብሮ ለማደግ፣ ተደጋግፎ ለመበልፀግ ከውስጥ ሳንወስን እንዴት "የሀገር ፍቅር አለን" ብለን ማውራት ይቻለናል? ለውጧን እውን ለማድረግ በአንድ ላይ ሳንሰለፍ፣ ሁሉም የቤተሰቢ አባላት በአንድ ላይ እንዲበለፅጉ ሳናልም፣ አንዱ ለሌላው ጉድጓድ መማሱን ሳይተው...

---

[10] በእዉቀቱ ስዩም - የግጥም ስብስብ

[11] The Beautiful once are not yet born.

ስለሀገር ፍቅር ማውራት ምፀት አይመስላችሁም? ማማሸ የቤተሰቧን ክፍል እያገለለች፣ እንደጠላት እየተመለከተችና ውድቀቱን እየተመኘች እንዴት ወደፊት መራመድ ይሳካላታል? እድገቷስ እንዴት ይረጋገጣል?

በእውነት ነው የምላችሁ ይህች ሀገር በስሟና በታሪኳ የሚፎክሩትን እንጂ ለለውጧ ተባብረው የሚሰሩትን አላገኘችም። የቀደምት ገድሏን እያነሱ የሚያቅራሩላትን እንጂ በትጋት ለሀዳሌዋ በአንድነት የቆሙላትን ለማየት አልታደለችም።

የኢትዮጵያ ልጆች

አማማ ተራቁታ አርቃኗን ቢያገኟት
ያብራኳ ክፋዮች ልጆቿ አዘኑላት
አዝነውም አልቀሩ...
መልኳ የጠፋውን ኢትዮጵያን ሊያሰውቧት
ነጠላ አሰርተው ገላዋን ሊያለብሷት
ጥጡን አሰፈልቅቀው - ነድፈው አሰፈትለው
ተደክሞ ሊሸመን - ጥበብ አሰመርጠው
ሸማኔ ፍለጋ ቢሹ ሲያሰፈልጉ
በየሸንተረሩ በየጉራንጉሩ
ሰዎቿ ተገኙ - ጥጡን ወዲያ ጥለው ነገር አያደሩ[12]

ይህቺ ሀገር ታታሪ ልጆቿን በጉጉት ትጠብቃለች። "ድህነትና ኋላቀርነት በትጋትና በጥረት የሚፈወስ በሽታ ነው" ብለው የሚያምኑ የአብራኳቿን ክፋይ ለማየት እንዳቃተተች ነው። ድንግል መሬቷ የሰሪ እጅ ያለህ ሲል ዘውትር ይጣራል።

ይገርማል! እንዴት ብዙ የሰው ሀይል (ህዝብ) ይዘን፣ እንዴት ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ሆነን... ድህነት መገለጫችን ሆነ? "ኢትዮጵያ ከዓለም ስልጣኔ ጅራት ላይ ነች፣ ቀኝ ኋላ ዙር የተባለ ቀን የሚደርስባት የለም" ብለው እንዳሾፉብን አልሰማህም?

Dubai - ዱባይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተመነደገች ያለች ሀገር ናት። የዓለም የንግድ ማዕከል፣ የመካከለኛው ምስራቅ ዋና የቱሪስት መስህብ ለመሆን እየተጋች ነው። ዱባይ በተፈጥሮ ሀብቷ በጣም ደካማ ናት።

[12] የቃየን ፍለጋ - የንጉሡ መድብል

የህዝቦቿ ቁጥር በጣም አናሳ፣ ሀገሯ በረሀማ ነው። ዋና ጥሬ ሀብቶቿ ሶስት ናቸው። Sun (ፀሐይ) Sand(አሸዋ)ና Sea(ወንዝ) ብቻ ናቸው። የእነዚህን የመጀመሪያ ፊደል (Acronym) በመውሰድ 3 s's (ሶስት ኤሶች) ብለው ይጠሯቸዋል።

ታዲያ ይህች ሀገር ያላትን ውስን የተፈጥሮ ሀብት ተጠቅማ ለማደግ ጥረት አደረገች። ፀሐይዋን፣ አሸዋዋንና ወንዟን እንደ ጥሬ እቃ ተጠቅማ ተአምር ሰራች። ወንዟ (Sea) ላይ አሸዋ (Sand) በመጨመር አለምን ያስደመሙ ሰው ሰራሽ ደሴቶችን ገነባች። የዘንባባ ቅርፅ ያለውና ከጠፈር ላይ ሆኖ የሚታየው - Jumeirah - ደሴት ተጠቃሽ ነው። በዚህም የአለምን ትኩረት መሳብ ቻለች። በአሁኑ ሰዓት ዱባይ ከ6 ሚልዮን በላይ ቱሪስቶች ይጎበኟታል። በቅርቡም ይህን ቁጥር ወደ 18 ሚሊዮን ለማሳደግ እየሰራች ነው።[13]

ታዲያ አንተም የህይወት ግብህን ቅረፅና ለሀገርህ እድገት ፈር ቀዳጅ (Pioneer) ሁን። በሀገርህና በሰው ልጆች ህይወት ላይ መልካም አሻራህን ጥለህ አለፍ። የበጎ አስተዋፅኦ ፋናህ አህጉራትን አቋርጦ ያብራ። የመልካም አድራጎትህ ዝና ክፍለ ዘመናትን ተሻግሮ ያስተጋባ። ለሰው ልጆች የመልካም ነገር ተምሳሌት ሁን።... ኢትዮጵያ አንተን እየጠበቀች ነውና።

"ብር የሚገኘው በ20 ዓመት፣ ልብ የሚገኘው በ40 ዓመት" የሚለው ትውፊት አንተን አይመለከትህም። እኛ ህይወታችንን በአላማ ከመራን ብርም ልብም በ20 ዓመታቸው የያዙ ወጣቶችን ፈጥረን ታሪክ እንሰራለን። ያኔም እናት ሀገራችንን እናኮራታለን።

[13] My Vision- Challenges in the race for Excellence, Mohammed bin Rashid Al-Maktoum (20-21) ,
Why Africa is poor- And what Africans can do about it. Greg Mills p-(22-26)

ምስጋና

እናቴ - ከሀመምሽ ጋር እየታገልሽ፣ ከኔ በመሆንሽ የማገኘውን ፅናት ሁሌም ልትለግሽኝ ከሁለት ዓመት በላይ ሀገርሽንና ቤትሽን ጥለሽ ከእኔው ጋር አሳለፍሽ።... ውለታሽን መክፈል ይሳካልኝ ይሆን?

አባቴ - የቤትህን መብራት፣ የትዳርህን ምሰሶ... ከኔ ትሆን ዘንድ ብቸኝነትን ብቻህን ተጋፍጠህ እናቴን ወደ እኔ ስለላክልኝ ለአንተ ያለኝ ክብር ላቅ ያለ ነው።

"ጌታዬ ሆይ! በሀፃንነቴ (በርህራሄ) እንዳሳደጉኝ ሁሉ፣ (አንተም ወላጆቼን) አዘንላቸው።"[14]

በተመሳሳይ ለውዷ እህቴ ሲቲ ኑሩ፣ ለወንድሞቼ ሀሰን (ነጋ) ኑሩ፣ ሰዒድ ኑሩ፣ ሙራድ ኑሩ፣ ፋዒዝ ኑሩ፣ አሚር ኑሩ... ለሁላችሁም አመሰግናችኋለሁ። ከቤተሰቤ ጥግ ላልጠፋህው ኡስታዝ ሙሐመድ ሰዒድ ሰፊውን እቅድህን አላህ ያሳካልህ።

እንዲሁም ገንቢ ትችቶችን፣ አጋዥ ሀሳቦችን፣ ነፃ አስተያየቶችን የለገሱኝን የእስር ቤት ጓደኞቼን በሙሉ ከልቤ አመሰግናለሁ። በተመሳሳይ የአርትኦት ስራው ላይ ለተሳተፋችሁ፣ ሞራል ለለገሳችሁኝ ሁሉ የዓለማቱ ጌታ ሙሉ ክፍያውን እንዲሰጣችሁ እማፀነዋለሁ።

በተለይም ኡስታዝ አቡበክር አህመድ፣ ኡስታዝ በድሩ ሁሴን (ኢንጂነር)፣ ጋዜጠኛ አቡበክር አለሙ፣ ጋዜጠኛ ዩሱፍ ጌታቸው፣ ኡስታዝ ባህሩ ዑመር፣ ኡስታዝ ሰዒድ ዓሊ፣ አርቲስት ሙኒር ሁሴን፣ ጀብሪል ዑመር፣ ኤልያስ ከድር፣ ኢስማኢል ሐሰን፣ ዐብዱረህማን ከማል፣ ኡስታዝ መሐመድ አባተ፣ አህመዲን ጀበል፣ ሸህ መከተ ሙሄ እንዲሁም ለዞን ዘጠኝ ብሎገሮች ዘላለም ክብረት፣ በፍቃዱ ሐይሉ፣ አጥናፉ ብርሃኔ... ለሁላችሁም ላቅ ያለ ምስጋና ይድረሳቹህ።

[14] ቁርአን 17:24

በመጨረሻም - ሶስቱ ልጆቻችንን በብቸኝነት የማሳደግን ሀላፊነት ላለፉት ምስት ዓመት ከመንፈቅ ለብቻሽ ለተወጣሽው፣ እኔ ጋ በመመላለስ ለተንከባከብሽው፣ ይህን መፅሀፍ በመተየብ እንቅልፍ ላጣሽው ለዚህ መፅሀፍ ብቻ ሳይሆን፣ ለሙሉ ህይወቱ ስኬት ሁሌም ከጎኔ ለሆንሽው ውዷ ባለቤቴ ለእንቺ ያለኝ ፍቅርና ክብር የተለየ ነው።

ሀቢዩ - "ከስኬታማ ወንዶች በስተጀርባ ጠንካራ ሴት አለች" የሚለውን እባባል፣ "ከስኬታማ ወንዶች በስተጀርባ ፍቅር ለጋሽና አስተዋይ ሴት አለች" ብሎ ማን ባስተካከለልኝ?...

ያሲን ኑሩ ዒሳ (YN) - ከወህኒ ቤት[15]

[15] ይህችን ፅሁፍ በ 19/3/2007 ዓ.ል በችሎት ላይ እያለሁ ተፃፈች። በዚህ እለት እንደተለመደው ሁሉ በርካታ ሰው ታድሟል። ውዷ ባለቤቴ፣ እህቷ ነፊሳ እንዲሁም ሶስተኛ ልጄ ሩመይሳ ተሳትፈው ነበር።

1

ምዕራፍ አንድ



አንዴ ቁጭ በልና አለማህን ቅረፅ

- ቀስተኛው
- የአንበሶቹ ገዳይ
  - የፖሊሲያችን ውጤት ነው
- መቀረጫውን ሳለው

በአላማ ያልተመራ ህይወት የፈጠረው መተራመስ ነው።

እንቅስቃሴዎቻችንን በእቅድ ሳንመራ የተገኘውን ውጤት ሁሉ (እንዳንደም ያልተረጋገጠ ውጤትን) የእኛ ነው ለያልን መፎከር አራስን ከማታለል የዘለለ አይሆንም። ልክ እንደአንበሶቹ ገዳይ። የአንበሶቹን ገዳይ አወቅካት?። እስቲ ትንሽ ላጫውትህ፦

1.2 <u>የአንበሶቹ ገዳይ</u>

እነሆ በአንድ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ የተለያዩ እንስሳዎች (የዱር አራዊት) በየንሳቸው ተከፋፍለው እየተዝናኑ ነው። ሁሉም መጠጥ ይጎነጫል፤ ጨዋታና ጭፈራውም ደርቷል።

ወደ ሌሊቱ አጋማሽ ላይ ሁሉም አራስን በሚያስት ሥካር ውስጥ ገብቷል። ተፈራርተው የነበሩ እንስሳዎች በሂደት ተቀላቅለው አብረው መጨፈር ጀመሩ። ሌሊቱም ለንጋቱ ተራውን በለቀቀ ጊዜ አዳኝ ከታዳኝ ጋር ተኝተው ተገኙ። ጦጢትም ሳታስበው ከአንበሶች መንጋ መሃል ተኝታ ራሷን አገኘችው። መጀመሪያ ህልም መስሏት ነበር። ነገር ግን እውነታው እንደዛ እንዳልሆነ ቆይታ ተረዳች።

በዙሪያዋ ያሉትን አንበሶች ብትነካካቸውም ሊንቀሳቃሱ አልቻሉም። ማምለጫዋን አመቻችታ እዚህና እዝያ እየሮጠች መቀስቀሷን ቀጠለች። ነገር ግን የአንበሶቹ መንጋ ጥምብዝ ብለው ሰክረው ስለነበረ ሊነቁ አልቻሉም። ጦጢትም የሞቱ መሰላት። ምናልባትም ትናንት ማታ ከእርሷ ጋር በተደረገ ፍልሚያ እንደተሰው አሰበች። "ይህን ሁሉ አንበሳ ብቻዬን ገደልኩኝ እንዴ"? ስትል በአግራሞት ተዋጠች። የስካር አንጎሯር ያልለቀቀው ጭንቅላቷ "ጀግና እኮ ነሽ" ሲላት ፈገግ አለች። ... ወዲያው ጨከታን ለቀቀችው። ከዛፍ ዛፍ እየዘለለች "የአንበሶች ገዳይ" ነኝ እያለችና እየፎከረች ሀገሩን አዳረሰችው።

ይህ ታሪክ ተጨባጭ ያልሆኑ ውጤቶችን እንደ ስኬት ለሚቆጥሩት ሁሉ አይነተኛ ተምሳሌት ነው። ሁሌም ቢሆን የመጣውን ለውጥ የአራሳችን እንደሆነ አድርገን እናስባለን። ማህበረሰቡ ዘንድ የመጣው ለውጥ በእኛ ዳዕዋ (ሰበካ)፤ በህዝቡ ዘንድ የተከሰተው የአስተሳሰብ ለውጥ የጀመዓችን (የማህበረሰባችን)፤ በፖለቲካው ዓለም የታየው ለውጥ የፓርቲያችን፤ በአብዮቱ ላይ የታየው አምርታ የአመራራችን፤

በኢኮኖሚው እድገት ላይ የታየው መሻሻል የፖሊሲያችን... ውጤት ነው ሰንል እንዘምራለን።

የፖሊሲያችን ውጤት ነው

በደርግ ስርዓት ዘመን የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ፣ መንገድ ዘግቶ የነበረን አንድ ትልቅ አለት ድንጋይ ከመንገድ ለማስወገድ ባደረጉት ቁፋሮ በአጋጣሚ ውሃ ይፈልቃል።

በዚህ ድንገተኛ ክስተት በጣም ተደሰቱ። ዓመታት የተጠናወታቸው የውሃ ችግር እልባት እንዳገኘ ተሰማቸው። ምንጩ በሚገባ ተገድቦ አገልግሎት እንዲሰጥ በማሰብ ማህበረሰቡ የገንዘብ መዋጮ በማሰባሰብ ግንባታ ተጀመረ። ሁሉም በገንዘቡ፣ በጉልበቱ አስተዋፅኦ አደረገ። ግንባታውም በተሳካለት ሁኔታ ተጠናቀቀ።

ምንጩ ተገድቦ አገልግሎት በሚሰጥበት የመጀመሪያ ቀን ላይ የአካባቢው አስተዳደር በቦታው በመገኘት ለተሰበሰበው ህዝብ ንግግር አደረገ፡- "መንግስታችን በተገኘው ምንጭ ውሃ እጅግ ደስተኛ ነው። ይህም የአብዮታዊ መንግስታችን ፓሊሲ ውጤት ስለሆነ ኩራት ይሰማናል።... ኢትዮጵያ ትቅደም።" ብሎ አረፈ።

አረዥም ጎዳና	-	ጠመዝማዛ መንገድ
መንደር መሰክ አቋርጦ	-	ተሻግሮ አሚሄድ
አካፋ ወይ ደማ	-	አልነካውም ከቶ
ኮቴ ነው የሰራው	-	መንገዱን አሰፋፍቶ[17]

እውነቱ ይህ ነው። በግለሰብም ይሁን በመንግስት ደረጃ የእኛ ያልሆነን ውጤት እንደራሳችን አድርገን ራሳችንን እናታልላለን። አሁን በመገናኛ ብዙሀን ሁሌ የሚለፈፍልን የሁለት ዲጅት "እድገት"፣ የህዳሴው ጉዞ ውጤት ነው ወይስ የ IMF እና የ World Bank ብድርና እዳ ጥርቅም?... ውጤቱ የማን ነው?

[17] ግጥም - በክፋ ሃይለየሱስ እንደተረጎመው

በየትኛውም የህይወት ጉዟችን በለስ ሲቀናን የእኛ እንደሆነ በማሰብ እንመሻደቃለን። ጉዞው ካልሰመረልን ኪሳችን ወደ ሌላ ለመወርወር መረጃ እንደረድራለን። ማን ነበር "ድል አንድ ሺህ ተጣሪ አላት፤ ሽንፈት ግን አንድም ዘመድ የላትም።" ያለው?

እስኪ አንተም አንዴ ቆም ብለህ አስብ። አልፎ አልፎ የሚያጋጥሙህ ውጤቶች ከተጠና ጉዞ የተወለደ ነውን? እያንዳንዱ እርምጃህ ለዋናው ራዕይህ ግብዓት (Input) እየሆነህ ነው? ያገኘኸው ውጤት የማን ነው?

እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው። ስለራሳችን ለማሰብ ትንሽ ቆም ማለት አልቻልንም። ትንሽ ቁጭ ብለን የህይወት ግባችንን አላሰመርንም። ምናልባትም ጊዜ የለኝም (ቢዚ ነኝ) የሚለውን የተለመደ መፈክር አንግበን ይሆናል።

ይህ መፅሀፍ ግን "ይህ ጉዞህ መስተካከል አለበት፤ በአዲስ ተሀድሶ ህይወትን "ሆ" ብለህ ልትጀምራት ይገባል" ይልሀል። እባክህ አንዴ አረፍ በልና መቁረጫህን ሳለው።

1.3 መቁረጫውን ሳለው

እነሆ ለመናፈስ በዛፎች ወደ ተሞላ አንድ ጫካ ከጓደኞችህ ጋር ጎራ ብለሀል እንበል። በአጋጣሚ ላቡን እያንጠባጠበ በእልህ ዛፎችን ከሚቆርጥ ሰው ጋር ትገናኛለህ።

"ምን እየሰራህ ነው?" ስትል አንተ ትጠይቃለህ።

"ዛፍ እየቆረጥኩ ነዋ!" ሲል በቆረጣ ተመልከቶህ ይመልስልሃል።

"መቁረጥ ከጀመርክ ስንት ሰዓት ሆነህ?" ስትል ጥያቄ ታስከትላለህ። እርሱም፡-

"እስከ አሁን አራት ሰዓት ፈጅቶብኛል። ሆኖም ግን አሁን መሻሻል እያሳየሁ ነው"። ሲል ላቡን ግንባሩ ላይ እየጠረገ ይመልስልሃል።

"ይቅርታ አድርግልኝና... የምትቆርጥበት መጋዝ የደነዘዘ ይመስላል። ለምን ጥቂት ጊዜ እረፍት ወስደህ አትሞርደውም?" ስትል ምክር ቢጤ ትለግሳለህ። እርሱም ቆጣ ብሎ "አልችልም! ምን አይነት የዋህ ነህ! ዛፉ ለመቁረጥ ጊዜ አጥሮኝ እንዴት ስለ መሳል ትመክረኛለህ" ብሎ አራት ሰዓት ሙሉ ወደፈጀበት ዛፍ ያቀረቅራል።

አሁን የዋህ ማን እንደሆነ ዳኝነቱን ለአናንተ ልተወው::[18] ምናልባት ይህ ግለሰብ ሀያ ደቂቃ ወስዶ መጋዙን ቢሰለው በአራት ሰዓት ልፋት ያላጠናቀቀውን ስራ በአንድ ሰዓት ውስጥ ሊያጠናቅቅ ይችል ይሆናል::

ይህ እንግዲህ የአብዛኞቻችንን ህይወት የሚወክል ምሳሌ ይመስለኛል:: ለራሳችን ትንሽ ጊዜ ሰጥተን የአመት፣ የወራት እቅድን አልነደፍንም:: ምናልባት ለዚህ የምናቀርበው ምክንያት - ልክ እንደዛፍ ቆራጩ - ቢዚ ነኝ የሚል የተለመደ መፈክር ይሆናል:: ጥናቱ ግን እንዲህ ይለናል:: "የአንድ ሰዓት እቅድ የማውጫ ጊዜ መውሰድ አስር ሰዓታትን ከማባከን ያድናል::" ህይወትን በአላማና በእቅድ መምራት ጊዜን ከማባከን ብቻ ሳይሆን ውጤትን ከማይወልድ ቢዚነት ያድናል::

"ዘጠኝ ጊዜ ለካ አንድ ጊዜ ቁረጥ::" ይላል ኢትዮጵያዊ ትውፊት:: አምን ከመቁረጣችን በፊት በደንብ መለካት እንዳለብንና የት ድረስ መቁረጥ እንዳለብን የሚያስተምር ነው:: በእርግጥ ይህ አባባል ከአዲሱ ትውልድ መዝገበ ቃላት ውስጥ እንደሌለ አውቃለሁ::

የዚህ መፅሀፍ አላማም ዘጠኝ ጊዜ ባይሆንም አንድ ጊዜ ለክተን አንድ ጊዜ እንድንቆርጥ ማስታወስ ነው:: ከሁከት ከፀዳ ቦታ ሆነን እራሳችንን ማዳመጥ አስፈላጊ መሆኑን መጠቆም ነው:: አንዴ ቁጭ ብለን የቀጣዩ ህይወታችንን ጉዞ ማስመር ለስኬታማ ህይወት መሰረት መሆኑን ማመላከት ነው::

አሰኪ አንዴ አንቅሰቃሴህን Pause (ገታ) አድርገውና አላማህን ቅረፅ።

" SIT AND SET YOUR GOAL IN LIFE "[19]

[18] Sean P. 206

[19] በትዕምርተ ጥቅስ ተቀምጠው፣ጥቅሶቹ የማን እንደሆኑ ካልተገለፀ ጥቅሶቹ የመፅሐፉ አዘጋጅ ሀሳቦች ናቸው::

2

ምዕራፍ ሁለት



በአላማ የመኝዝ ትሩፋት

- ግልፅ ህይወት ከመምራት የሚወለድ ደስታን ለመጎናፀፍ
- የራስህ ህይወት ሾፌር አንተው አንድትሆን
- መርጠህ መሰራት አንድትችል ያደርግሀል
- ትኩረትህን በመሰብሰብ ውጤታማ ያደርግሃል
- የሰውነትህ መገለጫ ስለሆነ
- ፅናትን ይለግስሃል
- ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም
- ባትደርስበትም ከፍያውን (አጅሩን) ታገኛለህ

በአላማ መኖር በርካታ ትሩፋቶች አሉት። ከእነዚህም ውስጥ፥-

2.1 ግልፅ ህይወትን ከመምራት የሚወለድን ደስታ ለመጎናፀፍ

መዳረሻን አውቆ እንደመራመድ የውስጥ ሰላም የሚሰጥ የለም። ህይወትን በአላማ መምራት ኑሮን ዝርና ቀላል ያደርጋታል። ይህም ውስጥን ሰላም ያላብሳል።

አንድ ጥናት እንደሚያመላክተው የህይወት ግባቸው ግልፅ የሆነላቸው ሰዎች 70% ደስተኛ ሲሆኑ፣ በተቃራኒው ግልፅ የህይወት አላማ የሌላቸው ሰዎች ደግሞ70% ደስታን የተነፈጉና የተሳከረ ህይወት የሚመሩ ናቸው[20]።

ስለሆነም "በአላማ ያልተመራ ህይወትን እየገፋህ ለውጥ በሌለው ተደጋጋሚና አሰልቺ የኑሮ ሽክርክሪት ውስጥ እራስህን ብታገኘው አይግረምህ።"

2.2 የራስህ ህይወት ሾፌር እራስህ እንድትሆን ያስችልሀል

አንተ እራስህ ባወጣኸው አላማ ህይወትህን የማትመራ ከሆንክ ሌሎች ወደሚፈልጉት ይመሩሀል። እነሱም ጎደኛ፣ ቤተሰብ አልያም የመገናኛ ብዙሃን ሊሆኑ ይችላሉ። በተለይ መገናኛ ብዙኃን አላማ የሌላቸው ብዙሃንን ወደሚፈልጉት አቅጣጫ የሚነዱበት መሳሪያ ነው። ለዚያም ነው "mass media is mass manipulation" - "ብዙኃን መገናኛ ብዙኃንን የምትቆጣጠርበት ነው" የተባለው።

የራሱ ህይወት ሾፌር ያልሆነ ሰው በሌላው ህይወት ላይ ተሳፋሪ መሆኑ አይቀርም። ይህን ጉዳይ ለማስረዳት ዶር ፋይዝ የአትክልት ቦታንና ጫካን በማነፃፀር አንድ ቆንጆ ምሳሌ ይጠቅሳሉ።

የአትክልት ስፍራና ጫካ

በአትክልት ስፍራና በጫካ መሀል ሰፊ ልዩነት አለ፣ ልክ በአላማ በሚመራ ህይወትና በመርህ የለሽ ህይወት መሀከል ልዩነት እንዳለው ሁሉ።

[20] Life teachs me - Dr. Tarik Assuwaidan

•ጫካ በደመነፍስ የሚበቅል ሲሆን የአትክልት ቦታ ግን በቀለምና በአይነት ነው የሚተከለው።

•የአትክልት ቦታውን ባለቤቱ ውሃ በማጠጣት፣ በመኮትኮት፣ከበሽታ በመጠበቅ፣ አረሙን በማስወገድ ሲንከባከበው፣ ጫካ ግን ሀላፊነት የሚወስድለት አካል የለም።

•በአትክልት ስፍራ ምን መብቀል እንዳለበት የሚወስነው ባለቤቱ ነው። በተጨማሪም ምን አይነት ዘር ቢዘራ ጥሩ እንደሆነም የሚወስነው እርሱ ነው። ጫካ ግን ማንኛውም ነርፍ የሚያመጣውን ዘር ሁሉ ያፈራል። አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርቦ ያለ መርህ ይበቅልበታል[21]።

ይህ ቀላልና ግልፅ ምሳሌ ነው። ህይወትን በአላማና በእቅድ ካልመራኸው የሌሎች ተከታይ ነው የምትሆነው። በሌሎች ፕሮግራም ላይ ተሳፋሪ ሆነህ ህይወትን ትገፋለህ። በራሳችን ህይወት ላይ የመረጥነውን የራሳችንን ዘር ካልዘራን፣ ካልኮተኮትን፣ ካልተንከባከብን፣ ውሃ ካላጠጣ ልክ እንደጫካው መርህ የለሽ ሆኖ ይበቅላል። ህይወታችን በዙሪያችን ባሉ ነገሮች መዋጡን ይቀጥላል። የህይወት ግብ ማውጣት የራስ ህይወት በራስ እጅ እንዲሆን ያግዘናል።

2.3 መርሐህ መሰራት አንድትችል ያደርግሃል

የግልፅ አላማ ጠቀሜታ በህይወት ጠቃሚና አስፈላጊ ናቸው ብለህ ያመንክባቸውን ነገሮች እንድትለይና እነሱንም ለመተግበር እንድትነሳ አድሱን ይሰጥሃል። ህይወት ብዙ ጊዜ መንታ መንገድ ላይ ትጥለናለች። በዚህ ጊዜ ግልፅ አላማ ያላቸው ሰዎች ወደ ግባቸው የሚያደርሳቸውን መንገድ ሲመርጡ ሌሎች ግን ብዥታ ውስጥ ይገባሉ።

ጓደኛ - ጓደኞችን በምን መስፈርት ነው የምትመርጠው? አላማ ያለው ወጣት ከህይወት ተልእኮው አንፃር ጓደኞቹን ይመርጣል። ጓደኛ ሀይል ነውና ለአላማው መሳካት ጉልህ ሚና ይጫወታል ያለውን ግለሰብ ሲመርጥ፣ ያለ አላማ የሚንዘው ግን በየትኛውም የህይወት አጋጣሚ የተዋወቀውን ሁሉ የልብ ወዳጅ አድርጎ ይይዛል።

[21] The Road to success – Dr. Faiez Seyal

ለዚህም ነው ታላቁ መልዕክተኛ መሐመድ (በእርሳቸውና በሌሎችም ነብያቶች ላይ ሰላም ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ የመከሩን፡- "አንድ ሰው በንደኛው እምነት (አመለካከት) ውስጥ ነው ያለው። ስለዚህ አንዳችሁ ማንን ንደኛ አድርጎ እንደሚይዝ ይመልከት"[22]

ይህ ግልፅ መልዕክት ነው። አላማ ያለው ሰው ለአላማው መሳካት አጋዥ የሆነን ባልንጀራ ይመርጣል።

መፅሐፍ - እንበል በአንድ ትልቅ ቤተ-መፅሐፍት ውስጥ ትገኛለህ። ወደ መፅሐፍ መደርደሪያው እንደቀረብክ በርካታ መፅሃፍትን ተመለከትክ... የትኞቹን ትመርጣለህ?። አልያም አንድ ካፌ ላይ ቁጭ ብለህ ሻይ እየጠጣህ ነው እንበል፣ ከፊትህ አንድ ወጣት መፅሀፎችን ይዞ እንድትገዛው ቀረበህ... የትኞቹን መፅሀፍ ትገዛለህ?። ርዕሶቹ የሳቡህን? ወይስ ቀለሞቹ ያማሩትን?

አየህ ግልፅ የህይወት አላማ ያለው ሰው ለመምረጥ አይቸገርም። በቀጥታ እጁን በመስንዘር ለቀረበው የህይወት ግብ መጋቢ የሚሆኑትን መፅሀፎች በቀዳሚነት ያነሳል። ከዚያም ለጠቅላላ እውቀት የሚያግዙትን ያስከትላል።

በርካታ ሰዎችን ተመልክቻለሁ፣ ያገኙትን መፅሀፍ እንዳመጣጡ ያስተናግዱታል። አንዳንዶችማ ከተመረቁበት የትምህርት መስክ ውጭ ያሉ መፅሀፍት ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋሉ። የአንድ ሰው 70% የንባብ አትኩሮት በተመረቀበት የትምህርት መስክ፣ እንዲሁም 30% በተለያዩ መስኮች ላይ ሊሆን ይገባዋል የሚል ጥናታዊ ፅሁፍ ማንበቤን አስታውሳለሁ።

የህይወት አላማ ያላቸው ሰዎች የመምረጥ ችግር የለባቸውም። ከፊት ለፊታቸው አማራጮች ሲደረደሩ፣ ቀድመው ለቀረቡት አላማ መጋቢ የሆነውን መርጠው ያነሳሉ። ወደ አላማቸው የሚያደርሰውን ጎዳና ይከተላሉ።

---

22 ቲርሚዚና አቡዳውድ ዘግበውታል።

2.4 ትኩረትህን በመሰብሰብ ውጤታማ ያደርግሀል።

የህይወት ግብ ያለው ሰው የሚፈስበትን ቦይ፣ የሚንዠበትን ጎዳና፣የሚቆምበትን መዳረሻ ያውቃል። ይህም ትኩረቱን ሁሉ፣ሙሉ ህይሉን በሙሉ በዚህ ላይ እንዲያውል ያደርገዋል።

ሺቭ ኬራ እንዲህ ይሉናል፦ "ፀሐዩ በበረታበት አንድ ቀን እጅህ ላይ የሌንስ መስታወት ይዘህል እንበል። ይህን ሌንስ አርግተህ ካልያዝከው ብርሃኑ ያረፈበትን ወረቀት የማቃጠል አትም አይኖረውም። ነገር ግን የሌንሱን ብርሃን አንድ ቦታ ላይ እንዲያርፍ አድርገህ ከያዝከው ብዙም ሳይቆይ ወረቀቱ ይቃጠላል። This is the power of concentration- ይህም አንድ ነገር ላይ የማተኮርን ሃይል ይጠቁመናል።"[23]

የአላማ ግልፅነት የትኩረት መሰብሰብን ይወልዳል። የትኩረት መሰብሰብም ወደ ውጤት ያመራል።

2.5 የሰውነትህ መገለጫ ስለሆነ

በህይወቱ አላማ የሌለው ሰው ከእንስሳ በምን ይለያል? መብላትና መጠጣት ከሆነ የሰውነት መገለጫው እንስሶችም ከእኛ በተሻለ መልኩ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ።

ሰው ከእንስሳ የሚለየው የተፈጠረበትን አላማ፣ የሚኖርበትን ምክንያት፣ የሚንዠበትን መነሻና መድረሻ በአግባቡ መረዳቱ ነው።

ምድር ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ የሰው ልጅን ለማገልገል ተፈጥረዋል። ተፈጥሮ ለሰው ልጅ አገልግሎት ተገዥታለች። ይኸው ፈረስን ይጋልባል፣በግና ዶሮ አርዶ ይበላል፣ ፍራፍሬ ከማሳው ለትሞ ይመገባል፣ ከላሚቱ ወተት አልቦ ይጠጣል፣ ከምንጪ ጠልቆ ይጎነጫል። ሁሉ ነገር የሰውን ልጅ ሊያገለግል፣ የሰው ልጅ ደግሞ ለአለማት ጌታ አገልጋይ (ባሪያ) ሊሆን ተፈጥሯል።

እንስሳዎች በአጠቃላይ ለሰው ልጅ አገልግሎት እያደሩ የሰው ልጅ ግን የተፈጠረበትን ዋና አላማ ከዘነጋ ከእነሱ በታች ሆነ ማለት ነው። እንስሳት አንተን በማገልገል አላማ ላይ ተፈጥረዋል። ይህን ተልዕኳቸውንም

[23] You can win: Shiv Khera

በእግዙ ተወጥተዋል። አንተ ደግሞ የሁለት ዓለም ስኬትን ለመቆናጠጥ ተፈጥረሃል። ህይወትን በአላማና በእቅድ በመምራት ልታሳካቸው ግድ ይላል። ይህም ነው ከአንገት የተሻልክ የሚያደርግህ፣ ይህም ነው የሚመጥንህ።

"የሚሞትለት አላማ የሌለው ሰው ለመኖር ብቁ አይደለም" ይለናል ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር።

2.6 ፅናትን ይለግስሃል

"የአላማ ግልፅነትና ጥንካሬ ነገሮችን በፅናት እንድናልፋቸው ብርታትንና ሞራልን ይለግሱናል"

እንደምታውቀው ህይወት ፈተና ይበዛታል። የሙከራ ሜዳ ስለሆነች ውጣ ውረዶች መገለጫዎቿ ናቸው። የሰውም ልጅ በዚህ ውስጥ ነው የተፈጠረው።

"የሰውን ልጅ በአርግጥ በልፋት ውስጥ ሆኖ ፈጠርነው።"
(አል-በለድ፣ 4)

ምናልባት ባለቤትህ አልፎ አልፎ ትነጫነጫለች፣ ሽረ እንዳንድ ሚስቶችማ በቀን ውስጥ ባህሪያቸው ሁለቴ የሚለዋወጥ አሉ። ወዴ እንዳይመስልህ ያ ገጣሚ ጥያቄ አለኝ ያለው። እስኪ ጥያቄውን አብረን እንስማው፦

ጥያቄ አለኝ?
መምህሬ እንዳሉኝ_
የመሪት ክብነት የሚረጋገጠው
ቀኑ ፀሐይ ውሎ ግቶ ሲጨልም ነው
የኔ ፍቅር ነገር?
ጠዋት ልሟ መልካም
አመሻሽ ጠማማ
ንጋት ፊቷ ፀሐይ
ምሽት ላይ ጨለማ

ፀባይዋ ሚት ማታ
የሚቀያየረው
ለመሬት ክብነት
ማረጋገጫ ነው?

ልጆችህ ደግሞ በዚህ ሳምንት ያመጡት ባህሪ አሰልቺ ሆኖብህል፣የንረቤቶችህ ባህሪ የማይቻል ሆኗል፣ስራህም እንዳሰብከው እየሄደ አይደለም፣ያመንከው ጓደኛህ አንተን ክዶ ከአንተ አንሣር ተሰልፏል፣ የወላጆችህ ህክምና አረፍት ነስቶሀል... ህይወት ውስጥ ደስታ አጥተሀል።

አምን የብዙዎቻችን ህይወት እንደዚህ ነው። አውነተኛ ደስታን እያጣጣምን አይደለም። ጥርሶች አውነተኛ ሳቅ ናፍቋቸዋል። አውነተኛን ሳቅ ጎምጅተዋል።

የት አለ ሳቅ

ካንገት በላይ ሰንሰቅበት - የዘመኑ ጥርስ አረጀ
ሳቅ ራሱ ጥርስ ናፈቀ - ጥርስም ፈገግታን ጎመጀ
ምነው ሰው ሁሉ ሳቅ ራቀው
ምነው ሰው ሁሉ ጥርስ አጣ
ቁም ነገር ዳዋ ለበሰ - ህይወት ሆነ የለበጣ
ጥርስ መሳቂያ ጊዜ አጣ - ማንክ ብቻ ሆነ ሰራው
ከልክ በላይ መብላት ለምደ - ሆዳችን እያሰፈራራው።

ይህ ግጥም የአብዛኞቻችንን ህይወት ያሳብቃል። አንዳንዶችማ ያለአላማ የመሩት ህይወት ያመጣባቸውን መመሰቃቀል ለመሸሽ ራሳቸውን በመጠጥ በማደንዘዝ ጭንቀታቸውን ለመርሳት ይሞክራሉ። እነዚህ ሰዎች በማዕበል እየተወሰዱ የወንዙን አረፋ ይዘው ለመዳን በሚሞክሩ የዋሆች ይመሰላሉ። ሌሎች ደግሞ ከተሳከረው ኑሮአቸውን ለመራቅ እንቅልፍን መሸሸጊያ አድርገውታል። ፀሐይ እንደ አዲስ ወጥታ የተለመደውን አሰልቺ ህይወት ከመግፋት፣ በዚያው ቢያሸልቡ ይመርጣሉ።

" የጋዜጠኛዉ ማስታወሻ - ትግሊ ምስ ሀዉቱ
(በዚህ መፅሐፍ የሰፈሩ ግጥሞችን አልር አልር ትምህርቱ ከተፃፉበት ጓራ አውተቹ እንደምጠቀምባቸው ልብ ይሏል)

ግጥም

ጀምበር ከአድማስ ግዞ ከመጋረጃዋ
ሙቀት ብርሃኗን ስትከት ከጉያዋ
ከሀይወት ከኑሮ ከቀትር ፀሐዩ
ከድካም ከልፋት ከምድር ከሰማዩ
ያስጨነቁኝ ሁሉ ሳይሰሙ ሳያዩ
በጨለማ አምልጠው እንደተኙሁ ካልጋ
ምናለ ባልገኝ ምናለ ባይነጋ።

ሀይወት እንዲህ በችግሮች ስትናጥ ፅናትን የሚለግስህ ያ ያስቀመጥከው አላማህ ነው። እውነቱ ይህ ነው። የህይወት ግብ ያላቸው ሰዎች (በተለይ አላማቸው ቀጣዩን አለም ያማከለ ከሆነ) በህይወት ውጣ ውረዶች ቶሎ አይሸነፉም። የህይወት የመከራ ንፋስ ያመጣውላቸዋል እንጅ ከስር አይነቅላቸውም። ምክንያቱም አላማቸው ስሩ የጠለቀ፣ ላዩም የዘለቀ ነውና።

"ለህይወቱ መሪ ቃል ያለው ሰው በስሮቹ መሬትን በደንብ ቆንጥጦ ይዞ ዛፍ ይመስላል። ተረጋግቶ የቆመና ከቆመበትም በምንም መልኩ የማይንቀሳቀስ ከመሆኑም በላይ ህይወት ያለውና ያለማቋረጥ የሚያድግ ነው።" ይለናል ሲን።

አላማ ፅናትን ይመግባል። ዛሬ ባይሳካልኝ ነገ ይሳካልኝ ይሆናል ብለህ እንድታስብ እድል ይሰጥሀል። ከደከመህ ታርፍ ይሆናል እንጂ እዚያው አትቀርም። ምክንያቱም ያስቀመጥከው አላማህ ላይ ለመድረስ እንደገና ጉዞህን መቀጠል ስላለብህ። በአርምጃህ ላይ በፀናህ ቁጥር ደግሞ ውጤት ላይ ትደርሳለህ።

"ዓለም ፊቷ ዞሮ
ዕድልህ ቢከፋ
አትበል መአት መጣ
ይልቅስ
ጠብቃት ዞራ አሰክትመጣ"

. . . ሲል ያስተጋባል ያ ግልፁ የህይወት ግብህ።

* የሊያ ሙሉ - የተተ መድብል

2.7 ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም ይረዳናል

"ዛሬ ከቀረችው የህይወት ቀኔዎች የመጀመሪያዋ ቀን ናትና ተጠቀምባት።"
ሐሰን አልበሰሪ

በተለምዶ "ጊዜ መርቅ ነው" ይባላል። ጭሩ ግን ጊዜ ከእንቁም ከአልማዝም በላይ ውድ ነው። እንድን ቀን ሊገዛልን የሚችል ምንም ሀብት የለም። በእጭሩ "ጊዜ ህይወት ነው"። የሰው ልጅም የቀናት ጥርቅም ነው። ታሪክ (ምድራዊ ቆይታው) ሲዘገብም "ከዚህ እሰት ተወለደ በዚህ እሰት አረፈ" ተብሎ ነው።

ያደጉ ሀገሮች ለጊዜ ትልቅ ዋጋ ይሰጣሉ። እንደ ጀርመን ያሉ ሀያላን ሀገራት የጊዜ ሚኒስትር እስከማቋቋም ደርሰዋል። "ኢትዮጵያዊው ሳሚ ለኢድም በሀገራችን የጊዜ ባንክ ለማቋቋም አየሳሬ ይሸኛል"። በእርሱ እምነት ሀገራችን ከሚገስጓት ጥሬ ሀብቶች ሞኖው ጊዜ ነው። የሳሚን ሀሳብ ለመረዳት አንድ ምክሌ ልስጥህ፣ እንበል "ጊዜ" የተሰኘ ባንክ አለህ። በዚህ ባንክ ውስጥ በየቀኑ 24 ሰዓታት ይፈሰስሩልሃል። እነዚህን ሰዓታት በዚያኑ ቀን ካልተጠቀምክባቸው ለነገ አይዘዋወሩም ብትባል ምን ታደርጋለህ?

ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም ግልፅ ግብ የአለመኖር ውጤት ነው። ፍንትው ያለ አላማ ያለው ሰው ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል። ጊዜውን በአግባቡ የሚጠቀም ሰው ደግሞ አላማውን ጥግ ያደርሳል።

ዛሬ የኛን መሰረት ነው። ዛሬ ላይ ያለንው ራዕይ ነው ነገ ላይ እውን ሆኖ የምናገኘው። ዛሬን በአላማ ሳንመራ ነገን ብንጠብቅ ነገ ላይ ጠፋ የሚል ነገር የለም።

ከሱ በስተጀርባ ምን አለ ሳትቸኩሉ?
ነገን ምትጠብቁት ዛሬን ረስታችሁ።

---

[42]

በስልክ ደውለህ "ስንት ሰዓት እንገናኝ?" ስትለው፣ "በፈለከው ሰዓት" የሚልህ ሰው የህይወት አላማውን ያላሰመረ ነው። እንዲሁም ራሱን በተለያየ መዝናኛ ውስጥ ከቶ ታገኘውና "ምን እያደረክ ነው?" ስትለው፣ "ጊዜ ለመግደል" ካለህ ይህም የህይወት አላማውን ያልቀረፀ ሰው መሆኑን ተረዳ።

በእርግጥ የሰው ልጅ ራሱን እድጉን ይወዳል። ከሌሎችም በላይ ራሱን ያስቀድማል። እንኳን ሞት ችግር እንዲቀርበው አይፈልግም። ነገር ግን ጊዜን መግደል ራስን መግደል መሆኑን በመዘንጋት "ጊዜ አንግደል" ሲል ይደመጣል። እነዚህ ሰዎች፦ "ህይወትህን የምታፈቅር ከሆነ ጊዜህን አታባክን፣ ህይወት ተቀመረችው ከጊዜ ነውና" የሚለውን የሐሰን አልበስሪን ምክር ልብ ያላሉ ናቸው።

"ወደ ነገ ስትሮጥ ልትተዋወቀው
ያወከውን ዛሬህን ጨፍልቀህ ገደልከው"

እንደሚባለው ጊዜ ደግና ቸር ነው*፣ ለሁሉም እኩል እድልን ይሰጣል። ጊዜ ቆጣኒም ነው፣ ላልተጠቀመበት ሰዎች ምህረትንና ሁለተኛ እድልን አይሰጥም። "ጊዜ እንደሰይፍ ነው። በስራ ካልቆረጥከው እርሱ ይቆርጥሃል" ይላሉ ዐረቦቹ።

በአላማ ህይወታቸውን የሚመሩ ሰዎች በድንገተኛ ገጠመኞች አይወሰዱም። ገጠመኞችን ከቀረፁት የህይወት ግብ አንፃር ይቃኟቸዋል።

"ከፊት ለፊትህ በኢጋማሚ ለመጣው ፕሮግራም እሺ ስትል ቀድመህ ላወጣህው እቅድ እምቢ ማለት መሆኑን አትዘንጋ።" የሚለውን ምክር ጠንቅቀው የተረዱ ናቸው።

ግልፅ የህይወት አላማ ጊዜን በአግባቡ እንድንጠቀም ያግዘናል። ጊዜያችንን በአግባቡ ስንጠቀም ለስኬት እንዘጋለን።

" Killing time is not Murder, It's sucide " Anthony Robbins

* ያው ፈጣሪ ደግ ቸር ነው ለማለት ነው።

2.8 ባትደርስበትም ክፍያውን (አድሩን) ታገኛለህ

እራስህን፣ ቤተሰብህን፣ ሀገርህን... ለማሳደግ፣ የሰው ልጆችን ካሉበት የተሳከረ ህይወት ለማውጣት፣ አለምን ከጥፋት ለመታደግ ይህንንም በማድረግ የፈጣሪን ውዴታ ለማግኘት አስበህ ያወጣህው ግብ፣ሳትደርስበት ብታልፍ እንኳ ክፍያውን የአለማት ጌታ ይሰጥሀል። በዝህች ምድር ክብርና ውዳሴን፣ በቀጣዩ አለም ጀነትና ውዴታን።

አስልምና ለቁርጥ አላቤ (ኒያ) ክፍያ የሚሰጥ ድንቅ እምነት ነው[31]። አንድ ሰው አንድን ራዕይ ሰንቆ፣ ሳይተገብረው ምድርን ቢሰናበት እንኳ የተገበረው ያህል ክፍያ ይሰጠዋል።

እንበልና በሁለት ሺህ ሀያ (VISION 2020) ኢትዮጵያን ከድህነት ማውጣት አለብኝ ብለህ እርምጃ ጀመርክና ሳትጨርሰው ምድርን ተሰናበትክ፣አልያም ደግሞ መቶ መርከቦችን (የሀይማኖት ትምህርት የሚሰጥባቸው ማዕከሎችን) ገንብቼ በእምነት አሌቶች የጎለበተና በስነምግባር የተዋበ ትውልድ መፍጠር አለብኝ ብለህ አቅድ አወጣህና ሳትተገብረው ሞት ቀደመህ... የአለማት ጌታ ግን ልክ እንደተገበርከው አድርጎ ክፍያውን ይሰጥሀል። አትጠራጠር!

"ስራዎች ሁሉ በአላቦት ፅዳታቸው (በንያቸው) ነው ዋጋ የሚሰጣቸው። ለእያንዳንዱም ሰው ያሰበው አለው (ባሰበው ልክ ክፍያ አለው)" ይሉሀል ታላቁ መልዕክተኛ ነብዩ ሙሐመድ[32] ﷺ

በእቅዱ ልክ እንደሚከፈለው እያወቀ ከማያቅድ ሰው በላይ ለነፍ የት ይገኛል? በራዕዩ ምጥቀት ልክ የጀነት ደረጃው ከፍ እንደሚል እያወቀ ትልቅ ራዕይ ካልሰነቀ ሰው በላይስ ማን ደካማ አለ?

---

[31] ይህ ለሱችም ሰማያዊ ሀይማኖቶች የሚጋሩት ሀሳብ ነው።

[32] ቡኻሪና ሙስሊም በተሰኙ አለማዊ ድርሳናት ውስጥ ተዘግቧል።

3

ምዕራፍ ሶስት



የህይወት ግብህ ምንድነው?

- ባለ ራዕይ ሁን
- ህይወት ያለ ዓላማ
- መጨረሻን መሰኖ መንቀሳቀስ
- ሁሉም ነገር ሁለቱ ይፈጠራል

አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ፡- ለወደፊት ምን ለመሆን ትመኛለህ? ከአመታት በኋላ ራስህን ምን ላይ ማግኘት ትፈልጋለህ? ራእይህ ምንድን ነው? ግብህስ የት መድረስ ነው?

3.1 ባለራዕይ ሁን

ውድ የሀገሬ ልጆች፡- ራዕይ ማለት የምንፈልገውን ነገር ቀድመን በአይነ-ህሊናችን መመልከት ማለት ነው። ተሳክቶ ማየት የምንፈልገውን ነገር ቀድመን መወሰን ነው። ያለ ራዕይ፣ ያለ አላማ የሚንገዘገዝ ሰው አቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስ ሳይኖረው ውቅያኖስ ውስጥ በሚቀዝፍ መርከበኛ ይመሰላል። ካፒቴኑም ሆነ ተሳፋሪዎቹ የት ለመድረስ እንዳሰቡ ግልፅ አይሆንላቸውም። ከሄደት በኋላ አይደለም ወደፊት መቀጠል ወደ ነበሩበት ቦታ እንኳን እንመለስ ቢሉ ትክክለኛውን አቅጣጫ ማግኘት አዳጋች ይሆንባቸዋል። አም መድረሻቸውን ብቻ ሳይሆን መነሻቸውንም ሊያጡ ይችላሉ።

3.2 ህይወት ያለ አላማ

ህይወትን ያለ አላማ የሚኖር ሰው እንዲህ ይመስላል፡-

ፕሪሚየር ሊግ

እንበልና በአንድ የፕሪሚየር ሊግ ላይ አንቱታን የተቸሩ ታዋቂ ተጫዋቾችን የያዙ ሁለት ቡድኖች ለከባድ ፍልሚያ ወደ ሜዳ ገብተዋል። ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት የጎሉን ብረቶች፣ መረቡን እንዲሁም የጎሉን መስመሮች ብናነሳቸው (ብናጠፋቸው) ምን ሊሆን ይችላል? ተጫዋቾችስ እንዴት ጎል ማግባት ይችላሉ? ካሲኒስ ወደምን ይመታታል? ተከላካይና አሰልጣኝስ አጥቂ የሚባል ነገርስ እንዴት ይኖራል? የበረኛ መኖርስ ምን ትርጉም አለው?

አም! ይህ የመላምት ህይወት ለሚገፉ ሰው የቀረበ ምሳሌ ነው። አብዛኛው ሰው ያለአላማ ተራ ህይወትን እየገፋ ይገኛል። "በምድራዊ ቆይታዬ ማሳካት የምፈልገው ምንድነው?" ብሎ ራሱን ጠይቆ የማያውቀውንማ ቤት ይቁጠረው።

ሌሎቹ ደግሞ ላንኳኳው ሁሉ በር ይከፍታሉ፣ ለደወሰው ሁሉ ይመልሳሉ። ወደነሱ ለመጣው ነገር ሁሉ ክፍት ናቸው። ነገሮችን ከአላማቸው አንፃር የመቃኘት አድል የላቸውም። ምክንያቱም ማንነፀሪያና መመዘኛ የሚሆን አላማ ቀድመው አላስቀመጡምና።

ማህተማ ጋንዲ "የየእለት ተግባራችን በህይወታችን ቀዳሚነት የሰጠነውን ነገር ጠቋሚ ነው።" ማለታቸውም ለዚሁ ነው።

ነገር ግን ከፊት ለፊት የመጡ አጋጣሚዎችን ተከትለን የምንፈስ ከሆነ በህይወታችን ቅድሚያ የሰጠነው ነገር እንደሌለ ይጠቁማል። ህይወታችን ከአላማ አንፃር ያልተቃኘ መሆኑን ያመላክታል።

ለዚህም ነው የተሳከረ ህይወት እየገፋን በአንድ ወገን የገንባነውን በሌላው ወገን የምናፈርሰው። ከወደፊት ይልቅ ወደኋላ የምንራመደው። ከትናንቱ ህይወታችን ያልተሻለ ህይወት የምንፈልገው። ለንመታት ጉልበታችንን፣ ጊዜያችንን እንዲሁም ገንዘባችንን ያፈሰስንበትን ቁምነገር ለጊዜያዊ ስሜት/ደስታ/ ስንል አፈር ድሜ የምናበላው። ለዘመናት የገነባነውን ንደኛነት የምንንደው፣ የሞቀውን ትዳራችንን የምንበትነው። ይገርማል! በተከፈተው በር ሁሉ ዘው ብለን እንገባለን፣ የተገኘውን ሁሉ እንመገባለን፣ ፊትለፊት የመጣውን ስራ ሁሉ እንሰራለን.... ይህ ነው መር- የለሽ ህይወት የምንለው።

ተራው ሰው

ስለተራው ሰው ሰምተህ ታውቃለህ? እርሱ ማን እንደሆነ ምን አሳወቀህ? ነገሩ ወዲህ ነው። ይኸው አሜሪ የህይወት ታሪኩ- ተራው ሰው በህይወታቸው ለየት ያለ ግብ ካልነበራቸው ሁለት ወላጆች ተወለደ። ያለ አላማም አደገ። በሂደትም እንደማንኛውም ህፃን ልጅ ትምህርት ቤት ገባ። ከዚያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቀቀ... ትንሽ ቆይቶም ተራ የሆነ ስራ ፈልጎ ተራ ህይወትን መምራት ጀመረ... በሂደትም ብቸኝነት ስለያዘተው ተራ ሚስት አግብቶ ተራ የሆኑ ልጆችን ወለደ። እነሱንም ያለ አላማ ተራ ህይወትን እንዲኖሩ አደረጋቸው... እድሜውም በዚህ መልኩ ገፋ... በመጨረሻም ተራው ሰው ተራ ህይወት (life of mediocrity) ኖሮ ተራ አሟሟት ሞተ።[33]

[33] በለመትጎል-ሐያት - ዶር ማሪቅ ሰመይዳን

ይህ የብዙዎቻችንን ህይወት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መነፅር ይመስለኛል። ታዲያ አንተስ ማነህ? የት ነው መድረስ የምትፈልገው? በህይወትህ ምን አላከተህ ማለፍ ትፈልጋለህ? አሁን የያዝከው መንገድ ወደየት ያደርስሃል?

መንገዱ ወዴት ይወስደኛል?

ከረዥምና አሰልቺ ጉዞ በኋላ ኤሊ ሁለት መንታ መንገድ ላይ ደረሰች። "የትኛውን መንገድ መከተል ይሻለኛል?" ስትል ራሷን ጠየቀች። ጥሩ አጋጣሚ ሆነና ከመንታ መንገዱ ዳር ድመትን ከስጋ ጋራ እየተላፋ አገኘችው።

"እባክህ ከዚህ ተነስቼ በየት በኩል መሄድ እንዳለብኝ ልትነግረኝ ትችላለህን?" ስትል ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ኤሊ ለድመት ጥያቄ አቀረበች።

"ይህንን የሚወስነው የት ልትሄጂ እንደፈለግሽ ስትነግሪኝ ነው።" ሲል የነጨውን ስጋ እያኘከ ድመት መለሰ።

"እኔ ወዴትም ብሄድ ግድ የለኝም።" አለች ኤሊ በድካም መንፈስ ተውጣ።

"እንዲህ ከሆነማ ሁሉም መንገድ ወደምትፈልጊው ያደርስሻል።" አለና ወደ ስጋው ተመለሰ ድመት!!

"When you don't know where you are going, any road will take you there." እንደሚባለው መሆኑ ነው።

አንተስ የት እየሄድክ ነው? ራስህን ከአስር አመት በኋላ ምን ላይ ማየት ትፈልጋለህ? ልታሳካው የምትገሰግስለት የህይወት ግብ ቀርፀሀል? እያንዳንዱ እንቅስቃሴህ ከዚህ አላማህ አንፃር የተቃኘ ነው? ዛሬህ ለነገ ለቀረፅከው አላማህ ግብአት እየሆነህ ነው?

ስቴቨን ኮቪን "የስኬታማ ሰዎች 7ቱ ልምዶች (The 7 habits of Highly Effective people) በተሰኘው መፅሀፋቸው ዓለም ያውቃቸዋል። በታሪክ ላይ የስኬት ሻኛ የሆኑትን ግለሰቦች ለአመታት እንዳጠኑና እነዚህ ታላላቅ ስኬታማ ሰዎች የሚያመሳስላቸው ሰባት ልምዶች (ባህሪያት) እንዳላቸው

በመፅሀፉ በስፋት አትተዋል::[34]

ከእነዚህ ስባት ልምዶች ውስጥ የመጀመሪያው ተነሳሽ ሁን (Be pro-active) - ማለትም ለህይወትህ ሀላፊነት መውሰድ አለብህ፣ አንተ የህይወትህ ሹፌር እንጅ ተንሻፎ መንገደኛ አይደለህም፣ ሲሉ ሁሉም ሰው ነፃ ምርጫ እንደተሰጠውና ለውድቀቱም ሆነ ለስኬቱ ራሱና ራሱ ብቻ ተጠያቂ እንደሆነ አመላክተዋል::

"መንገድ ላይ እየተጋፋህ ስትሄድ ሰዎች ምን ያህል ጊዜ ገፍተውሃል ወይም ረግጠውሃል? በዚህ ጊዜ ምንድነው የምታደርገው? መጥፎ ቃል ትመልሳለህ? ቀኑን ሙሉ እንደተናደድክ ትውላለህ? ወይስ ችላ ብለህ በፈገግታ አልፈሃቸው መንገድህን ትቀጥላለህ? አሁንም ምርጫው የአንተው ብቻ ነው::" ሲሉ ያነሳሉ::

"መበሳጨት አልያም በትዕግስት ማለፍ ምርጫ ነው:: ተራን ህይወት መግፋት አልያም ወደ ስኬት ማቅናት ምርጫ ነው:: ህይወትን በአላማ መርቶ የስኬት ማማ ላይ መውጣት አልያም ትርጉም የለሽ ኑሮን መግፋት ምርጫ ነው:: ለፈጣሪህ ትዕዛዝ ማደር አልያም ከትዕዛዙ ማፈንገጥ ለአንተ የተተወ ምርጫ ነው::

"የሻም ሰው ይመን ! የሻም ሰው ይካድ"[35]

የፊጠረን ፈጣሪ ለውጫዊ ተፅዕኖዎች (External factors) እውቅና አልሰጠም:: ሰይጣን አሳስቶኝ፣ ነፍሴ ገፋፍታኝ፣ ምድራዊ ንዋይ አማሎኝ፣ ጓደኞቼ አዘናግተውኝ፣ ያደግኩበት አካባቢ ተፅዕኖ ፈጥሮብኝ... የሚሉ ምክንያቶች በትንሳኤ ቀን (የውመል ቂያማ) ተቀባይነት የላቸውም:: ሁሉም ሰው በነፍስ ወከፍ ተጠያቂ ነው::

---

[34] ክቡ ይህን መፅሀፍ በ1970ዎቹ አጋማሽ አካባቢ እንደፖሩት ይገልፁ:: ለፖክተሬት ድግሪ መመረቂያ ይሆን ዘንድ የ 200 ዓመት የስኬታማ ሰዎችን ታሪክ ሲያጠናው እነዚህን ስባት ባህሪያት(ልምዶች) እንዳገኙ ጠቅሰዋል::

[35] ቁርአን - 18:29

"የሰው ልጅ በዚያን ቀን ባስቀደመውና ባስቆየው ሁሉ ይነገራል። በእርግጥም ሰው በነፍሱ ላይ አስረጅ ነው (አካሉቹ ይመሰክሩበታል) ምክንያቶቹን ሁሉ ቢያመጣ እንኳ (አይሰማም፤ ተቀባይነት የለውም)።"*

ለህይወትህ ተጠያቂው አንተው ነህ። ለውድቀትህ ሀላፊነት የምትወስደው አንተው ነህ። ጓደኞችህ፣ የስራ ባልደረቦችህ፣ ሚስትህ፣ ልጆችህ፣ ጎረቤትህ... ሊያበሳጩህ መበሳጨት መብትህ ነው። አለመበሳጨትም በእጅህ ነው። "የምትሞትበትን ቀጠሮ መወሰን አትችልም። የኑሮህን ሁኔታ የመምረጥ እድል ግን በእጅህ ነው።" ይሉናል ጀን ቤነር።

በአጭሩ አንተ የህይወትህ ሾፌር እንጅ ተሳፋሪ አይደለህም።

ሁለተኛው የስኬታማ ሰዎች ልማድ (ባህሪ) ደግሞ - አእምሯችን ከቋጨው ስዕል እርምጃችንን መጀመር (Begin with the End in Mind) ይሉታል ኮቪ። ወይም በቀላል አገላለፅ (to start with a clear understanding of your destination) መጨረሻህን ወስነህ እርምጃህን መጀመር ማለት ነው።

በዚሁ ነጥብ ላይ የህይወታችን ሾፌር እኛው እንደመሆናችን መጠን የት እንደምንሄድ እንድናውቅና የመንገዳችንን ካርታ ቀድመን እንድንነድፍ ይመክሩናል።

3.3 መጨረሻን ወስኖ መንቀሳቀስ

ሲን ኮቪ የአባቱን መፅሀፍ ለወጣቶች የበለጠ በሚገባ መልኮ አዘጋጅቶታል። በእርሱ እምነት የአባቱ መፅሀፍ ለወጣቶች ከባድና አሰልቺ እንደሆነ ያምናል። ነገር ግን የአባቱ መፅሀፍ ካለው ፋይዳ አንፃር በመፅሀፍ የተቀመጡ መርሆችን በቀላል አቀራረብ ቢቀርቡ፣ ህይወት እንደቀድሞው የመቦረቂያ መስክ መሆኗ ቀርቶ ጥቅጥቅ ያለች ደን ለሆነችባቸው ወጣቶች አቅጣጫ ጠቋሚ ሊሆን ይችላል ብሎ ያምናል።

በዚህም መሰረት "መድረሻህን ወስነህ እንቅስቃሴህን ጀምር" ለሚለው መርህ እንዲህ ሲል ቀለል ያለ ምሳሌን ያቀርባል፡-

* ቁርአን - 75 : 13-15

በርካታ ቁርጥራጭ እንጨቶችን አጣጥመህ አንድ ስዕል የመፍጠር ጨዋታ እንድትጫወት ተጠይቀሃል አንበል። እንዲህ ዓይነቱን ጨዋታ ብዙ ጊዜ ስለተጫወትከውና ስለምታውቀው ጨዋታውን እስክትጀምር ቸኩለሃል። ቁርጥራጭ እንጨቶቹን የያዝውን አነስተኛ ሳጥን በትልቅ ጠረጴዛ ላይ ስትገለብጠው 1000 ቁርጥራጭ እንጨቶች ይዘረገፋሉ። እንደተለመደው እንጨቶቹ ተጣጥመው የሚሰጡት ምስል በሳጥኑ የውስጠኛው ክፍል ላይ ታትሞ መገኘት ነበረበት። የሳጥኑን መዘጊያ ከፍተህ የውስጠኛውን ክፍል ስትመለከት ግን አለመታደል ሆኖ አንድም የስዕል ዘር የለም።

ቁርጥራጮቹ ተጣጥመው ምን ዓይነት ምስል እንደሚሰጡ ሳታውቅ እንጨቶቹን እንዴት ልትጣጥማቸው እንደምትችል ግራ ይገባሃል። ያኔ የምትመኘው ያችን ስዕል ለአንድ አፍታ እንኳን ብታያት ነው። ያቺን ስዕል አንዴ ብታገኛት የምታስገኘህ ሰውጥ እንዴት ትልቅ ነበር! ካለዚህች ስዕል ግን እንጨቶቹ ትርጉም የላቸውም። ማጣጣጠም ለመጀመር እንኳን ምንም ምንጭ ሊኖርህ አይችልም።

ይህን ምሳሌ ተከትሎ እንዲህ ይሰናል ሲን ኳቬ- አሁን ደግሞ ያንተን ህይወት እንደኘህ 1000 ቁርጥራጭ እንጨቶች አድርገህ አስበው። መድረሻህን ለይተህ ታውቃለህ? ከአንድ ዓመት በኋላ ምን አይነት ሰው መሆን እንደምትፈልግ ጥርት ያለ ስዕል በአዕምሮህ ውስጥ አለ? ከአምስት ዓመት በኋላስ? ወይስ ምንም ሳትረዳ ያለአላማ ዝም ብለህ እየተንዘፈ ነው?

እኔ ደግሞ ለላ ምሳሌ ልጨምርላችሁ- እንበልና የኢድ አል-አድሀን (አረፋን) በአል ለመቀበል ሽር-ጉድ እያልክ ነው። ከአምስት ዓመት በፊት የገዛኸው የቴሌቪዥን ማስቀመጫ ስላረጀ ለመቀየር ከባለቤትህ ጋር ተስማማህ። አብራችሁ ጎራ አላችሁና በጣም ዘመናዊ ተጣጣሚ የቴሌቪዥን ማስቀመጫ ላይ አይናችሁ አረፈ። ቤት ውስጥ ገጣጥማችሁ ላሉን ላይ ለማስቀመጥ ትወስኑና ገዝታችሁ ወደ ቤት ትመለሳላችሁ። ቤት ደርሳችሁ የማስቀመጫውን ቁርጥራጭ ክፍል የያዘውን ካርቶን ስትከፍቱት ግን እንግዳ ነገር ታያላችሁ። አዎን እንጨቶቹና ብሎኖቹ እንጅ እንዴት እንደሚገጣጠሙ የሚያስረዳው መመሪያ መፅሐፍ (Manual) የለም። የትኛው ብሎን ከየትኛው እንጨት ጋር እንደሚገናኝ ይጠፋባችኋል። ታዲያ አንተ በድፍረት ተነሳስተህ ስትሞክረው... እንዴ

የወንበር ቅርፅ ይመጣብሀል...

ሌላ ጊዜ ጠረጴዛ ይመስልሀል... ምን ታደርጋለህ? እርግጠኛ ነኝ ወደ ገዛበት ድርጅት ባስችኳይ ተመልሰህ መመሪያውን (Manual) መጠየቅህ አይቀርም። ሊሰጠህ ካልቻሉ ደግሞ አቃውን መመለስህ የግድ ነው።

ህይወትም እንደዚሁ ናት። የምንመራበት መመሪያ (Manual) ያስፈልገናል። የምንሄድበትን አቅጣጫ ማወቅ ይጠበቅብናል። መድረሻችንን ወስነን መንቀሳቀስ የስኬት ቁልፍ ነው። ግባችንን አውቀን መነሳት የስራችንን ብዙ ክፍል ማጠናቀቅ መሆኑን አንዘንጋ። ግባችን ህይወታችን ምን መምሰል እንዳለበት የሚነግረን የግል መፈክራችን ነውና።

አለበለዚያማ እንደዚያ አውሮፕላን አብራሪ ሆንክ ማለት ነው።

አውሮፕላን አብራሪው

አንድ የአየር መንገድ ቴክኒሽያን ሰራተኛ አውሮፕላኑን ፍተሻ እያደረገ እያለ አውሮፕላኑ ውስጥ አንድ መፅሀፍ ያገኛል። መፅሀፉ የሚያትተው ስለ አውሮፕላን የማብረር ቴክኒክ ነበር። በኢጋጣሚ አውሮፕላኑ ውስጥ ሌላ ሰራተኞች ስላልነበሩ ቁጭ አለና መፅሀፉን ገልበጥ ገልበጥ አደረገው። የበረራ ሙያ ባይማርም መፅሀፉ ላይ የተጠቀሱት ሀሳቦች ግን ለእርሱ እንግዳ አልነበሩም። ብዙዎቹን ከሙያው አንፃር ያውቃቸዋል።

ድንገት አንድ ሀሳብ መጣለት... "ለምን ይህን መፅሀፍ እንደመመሪያ እያነበብኩ ለማብረር አልሞክርም!" ሲል ራሱን ጠየቀ። ውስጡም ትችላለህ ሲል ገፋፋው። በጣም ከባድ ፍላጎት ውስጥ ገባ። ይህ ጥበብ ፍላጎቱና ጉጉቱ አውሮፕላኑን ያለሙያውና ያለፍቃድ በማብረሩ የሚያስከትልበትን ተጠያቂነት ጋረደበት።

ኮፓይለቱ ወንበር ላይ ተቀመጠና በመፅሐፉ መሰረት በሮችን ዘጋ! ሞተሩንም አስነሳ፣ አውሮፕላኗን ለማብረር መሮጥ ጀመረ... በሂደትም ወደ ላይ አነሳት... አውሮፕላኗ አድማሱ ውስጥ ነጎደች... እንዴ የማብረሪያ መመሪያ መፅሀፉን ሌላ ጊዜ ከሰሩ የተንጣለለውን ጉም እያየ በሀሴት ሀዋው ላይ ዋኘ።

ከአንድ ሰዓት በረራ በኋላ ወደ ተነሳበት አየር ማረፊያ አቀና። እንዴት ማረፍ እንዳለበት ለመመልከት አይናቹን ከጉሙ ነቅሉ ወደመፅሀፉ መለሳቸው። ከመፅሀፉ የቀረችው ግን አንዲት ገፅ (ወረቀት) ብቻ ነበረች።ገልበጥ አድርጎ ሲያነባት... በጣም አስደንጋጭ ነገር ተመለከተ... ፍርሃትም ወረረው... አይናቹ ፈጠው ቀሩ... እንዲህ የሚል ነገር ነበር ያነበበው... "ስለ አውሮፕላን አስተራረፍ የሚያሳየውን መመሪያ ከሚቀጥለው መፅሀፍ ላይ ይመልከቱ።" በጣም አሳሳቢው ደግሞ ይህ መፅሀፍ አውሮፕላኑ ውስጥ አለመኖሩ ነው። ግለሰቡ ሀዋ ላይ እየተዘፈ ነው፣ ነዳጅም እየጨረሰ ነው.... ምን ያድርግ? እርስዎስ ምን ይመክሩታል?

መልሱን ለእናንተ ልተወው። ነገር ግን መጨረሻን ወስኖና ተዘጋጅቶ እርምጃን መጀመር ምን ያህል አስፈላጊና ውጎ እንደሆነ የተረዳን ይመስለኛል።

ስኬታማ ሰዎች በሀሳቡት ራዕይ ጉልበትና ጥልቀት ይመዘናሉ። መልካቸውን በመስታወት እንደሚመለከቱ ሁሉ ራዕያቸውን በአይነ ህሊናቸው የገሀዱን ያህል ይመለከቱታል። ታዲያ የአንተ ራዕይ ምንድን ነው? የት መድረስ ትፈልጋለህ? ምድር ላይ ጥለኸው ማለፍ የምትፈልገው በጎ ነገር (legacy) ምንድን ነው? መጻረሻህን ወስነህ ነው ጉዞህን የጀመርከው? ምን መሆን ትፈልጋለህ?

3.4 ሁሉም ነገር ሁለቴ ይፈጠራል

አእምሮህ ከቋጨው ስዕል እርምጃህን ጀምር የሚለው አባባል የመነጨው፣ ሁሉም ነገር ሁለቴ ይፈጠራል ከሚለው መርህ ነው። መጀመሪያ አዕምሮ ውስጥ (Mental Creation) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በገሀዱ ዓለም በድርጊት ይፈጠራል (Physical Creation).

ለምሳሌ ቤት ለመስራት ብንነሳ፣ መሀንዲሱ መጀመሪያ የቤቱን ዲዛይን አእምሮው ውስጥ ይቀርፀዋል፣ ከዚያም አእምሮው ውስጥ የተቀመጠውን ንድፍ (Blue Print) ወረቀት ላይ ያሰፍረዋል፣ ከዚያም ምድር ላይ ግንባታው ይጀመራል (Physical Creation).

መርፌና ክሩ ከልብሱ ጋር ከመገናኘታቸው በፊት የልብሱ አይነትና ቅርፅ ልክ ለፊው ቀድሞ ይወስናል። ሚስማሩና መዶሻው ከመገናኘታቸው በፊት የቤቱ ካርታ ይነደፋል። እምን ይህ ጉዳይ በአለት ተአለት ጉዟችን የምንተገብረው መርህ ነው። ጉሞ ለማድረግ ስትነሳ የት ሀገር የሚለውን ትወስናለህ፣ ከዚያም ትኬት ትቆርጣለህ፣ ለጉዞህ የሚያስፈልጉህን ነገሮች ይዘህ እየር ማረፊያ ትገኛለህ...።

አሁን በተጨባጭ ምድር እውን ሆኖ የምናያቸው ነገሮች ቀድመው ሞንትላት ውስጥ ተነድፈው የነበሩ ነገሮች መሆናቸውን ታውቃለህ? ስለ ዋልተር ዲዝኒ ትንሽ እንበል።

ዲዚኒ ላንድ

"የወደፊቱን የሚወርሱ ሰዎች ሁኔታዎች እውን ከመሆናቸው በፊት እንደሚቻሉ አስቀድመው የሚያዩ ሰዎች ናቸው።" ጀን ስኩሊይ

ዲዚኒ ላንድ፡- እውቅ የመናፈሻ ቦታ ነው። ይህ መናፈሻ ስያሜውን የወሰደው ዋልተር ዲዚኒ ከተባሉ አሜሪካዊው ባለራዕይ ግለሰብ ነው። ግለሰቡ በህይወት እያሉ አዕምሮአቸው ውስጥ የፀነሱትን ራዕይ ለማየት ሳይታደሉ ቢያልፉም፣ ራዕያቸውን አብራቸው በስንቀችው ባለቤታቸው አማካኝነት አብሯቸው ወደ መቃብር ከመውረድ ድኗል።

ደግሞስ ጥሩ መሪ ማለት ራሱን በብቃት መተካት የቻለና እርሱ እንኳን ቢያልፍ ራዕዩን ባልደረቦቹ ተተክተው ወደ መሬት እንዲያወርዱት አድርጎ የቀረፃቸው ማለት አይደለምን?

ይህ ሊያዩት አእምሮን ሰላም የሚመግብ የህፃናት መናፈሻ በተመረቀበት ቀን በዘግጅቱ የታደመ አንድ ጋዜጠኛ በማዕናናት ቃና ምኞቱን ለባለቤታቸው እንዲህ ሲል ገለፀ፡-

"ዋልተር ዲዚኒ በህይወት ኖረው ይህን መናፈሻ አይተውት ቢሆን ናሮ ምንኛ አስደሳች ነበር?" ብሉ ንግግሩን ከመጨረሱ አመቤቲቱ እንዲህ ሲሉ ታሪካዊ መልስ ሰጡት፡- "በጣም ተሳስተዋል ጌታዬ... ባለቤቴ እኮ ይህን የህፃናት ገነት ያየው ራዕዩን የሰነቀ ዕለት ነው"

አምን! ስኬታማ ሰዎች የተጠናቀቀን ውጤት በአእምሮአቸው ውስጥ ቀድመው የፀነሱ ናቸው። ሆኖ ማየት የሚመኙትን ውጤት ቀድመው መመልከት የቻሉ ናቸው።

ዛሬ እውን ሆኖ የምናየው ታላላቅ ግንባታ ሁሉ በአንድ ወቅት ታላላቅ ባለራዕዮች በአእምሮአቸው ውስጥ የሳሉት ንድፍ ውጤት ነው"

ይሁናል Black

አንተስ ምን ሰንተህል? አሁን የያዝከው መንገድ ወደየት ነው የሚያደርስህ? አእምሮህ ላይ የተቋጨው የወደፊት አላማህ ምንድን ነው? የህይወት ግብህስ ምንን ማሳካት ነው?

4 ምዕራፍ አራት



ተሰጥኦህን ፈልግ

- ተሰጥኦን መፈለግ ለምን አስፈለገ?
- ተሰጥኦን ለማግኘት የሚረዱን ነጥቦች
- በአጋጣሚ ታገኘዋለህ
- ሌሎች ያመላክቱሀል
- ማንነትን ፍለጋ
- አብዙ ነገር ፈጣሪ ገርቶህ ቢሆንስ?

"ሁሉም ሰው ብልህ ነው። ነገር ግን አሳን ዛፍ ላይ በማውጣት ችሎታውንና ብቃቱን ከመዘንከው፣ ይህ አሳ እድሜውን በሙሉ ደደብ ነኝ ብሎ በማመን ይኖራል።" Albert Einstein

እነሆ በዱር ውስጥ ይኖሩ የነበሩ እንስሳት ተሰባስበው ትምህርት ቤት ሊከፍቱ ይወስናሉ። ተማሪዎቹ ዓሳ፣ ጥንቸል፣ ውሻ፣ ወፍ፣ ቀንድ አውጣ ነበሩ። የሚሰጡ ትምህርቶች ሁሉን አቀፍ እንዲሆን ከሞላ ጎደል ተስማሙ። መቆፈር፣ መዋኘት፣ መብረርና ዛፍ ላይ መውጣት... የትምህርት ቤቱ ሥርዐተ-ትምህርት (Curriculum) እንዲሆን ተወሰነ። ሁሉም ተማሪ ሁሉንም አይነት የትምህርት ዘርፎች እንዲከታተሉ ቦርዱ በአንድ ድምፅ አፀደቀ።

ትምህርቱን ለአመታት ከተከታተሉ በኋላ ሁሉም ለፈተና ቀረቡ። በመብረር ረገድ የተዋጣለት ሆኖ በበረራ ትምህርት "A" ያገኘው ወፍ በቁፋሮ ትምህርቱ ላይ ግን መንቆሩና ክንፎቹ እየተሰባበሩበት ስለተቸገረ አመርቂ ውጤት ማምጣት አልተሳካለትም። በቀጣዩ ሴሚስተርም ክንፎቹ በቁፋሮው ስለተጎዱ የበረራ ውጤቱ አሽቆልቁሎ "C" ተከናነበ። የዛፍ መውጣትና የዋና (መዋኘት) ትምህርቶች ላይ እንዲትም ነጥብ ሊያመጣ አልተቻለውምና "F" ተሰጠው።

በዋና የሚስተካከለው ያጣው ዓሳ ለህይወቱ አስጊ በመሆኑ ከውሃ ውስጥ መውጣት አልቻለምና የሌሎች ትምህርቶች ውጤቱ "F" ሆነ። በአንፃሩ ቀንድ አውጣ ደግሞ በዛፍ መውጣት ትምህርት "A" ሲያገኝ በዋናው ትምህርት ነጥብ ማምጣት ተስኖት ወደቀ።

ውሻው ከመጀመሪያውም በትምህርት ቤቱ ሥርዐተ-ትምህርት (Curriculum) ደስተኛ አይደለም። ከትምህርት ቤት የቦርድ አባላት በተገኘባቸው መድረኮች ላይ ሁሉ (የእርሱን ተሰጥኦ ያማከለውን) መፍሀን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይካተት ዘንድ መሟገቱን አልተወም። ጥንቸሉ በቁፋሮ ትምህርቱ "B" ሲያስመዘግብ የዛፍ መውጣቱ ጉዳይ ግን ያላሰበውን ችግር ፈጠረበት። አንድ ጊዜ ያደረገው ሙከራ በጭንቅላቱ እንዲከሰክስ አድርጎት የአዕምሮ መዛባት ጉዳት ስላደረሰበት በሂደት የቁፋሮ ትምህረቱ ውጤቱም ወደ "D" ወረደ።

"ወፍ በበረራ ውጤቱ "A" ያመጣው፤ አሳ በዋና "A" ያገኘው... ተሰጥኦቸውን ያማከለ ትምህርት በሥርዐተ-ትምህርት (Curriculum) ስለተካተተላቸው ነው። ስለዚህ ለኔም "ሩጫ" እንደ አንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ይካተትልኝ" ብሎ ጥንቸል ያቀረበው አቤቱታ እስከአሁን ምላሽ አላገኘም።

ታዲያ አንተስ "A" የምታመጣበት የህይወት መስክህ የቱ ነው?... ተሰጥኦህን ፈልገው።

ለምን ተገርተህል?

"ሁሉም ነገር ለተፈጠረለት ነገር (ጉዳይ) የተገራ ነው።" ነቢዩ መ.ሐመድ[37] ﷺ

ይህ ትልቅ ነቢያዊ ንግግር ነው። ሁሉም ነገር (ሰው፤ እንሰሳና በአጠቃላይ በፍጥረተ-ዓለሙ የሚገኝ ነገር ሁሉ) ለተፈጠረበት ነገር ተገርቷል። ሁሉም ሰው የተገራበት ችሎታ አለው።

ህይወት አምራና አሸብርቃ ትቀጥል ዘንድ ፈጣሪ ለሰው ልጆች የተለያዩ ክህሎቶችን ሰጥቷቸዋል። አብረውን የተወለዱ ተሰጥኦዎች (Endowments) አሉ። ታዲያ ቁም ነገሩ እነዚህን ተሰጥኦዎች ፈልጎ ማግኘቱ ላይ ነው። በምድር ቆይታህ ላይ ለምን እንደተገራን መረዳት የስኬት መሰረት ነው።

ሚካኤል አንጀሉ አንድ የሚያምር ሐውልት ከቀረፀ በኋላ እንዴት አድርጎ እንዲህ የተዋጣለት ስራ ሊሰራ እንደቻለ ተጠይቆ ነበር። እርሱም "ሐውልቱ መጀመሪያም ድንጋዩ ውስጥ ነበር- እኔ ያደረኩት በሀውልቱ ዙሪያ የነበሩ አላስፈላጊ ነገሮችን ፈልፍዬ ማስወገድ ነው።" ሲል መልስ ሰጠ።[38]

---

[37] ﷺ - ይህ አባባል የአላህ መልዕክተኞች በተጠቀሱበት ቦታ ሁሉ አብሮ ይጠቀሳል። ትርጉሙ- የአላህ ሰላምና ደህንነት በመልዕክተኞች ላይ ይሰፈን ማለት ነዉ።

[38] ሀውልት ቀረፃን እስልምና በጥብቅ የኮነነው ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ሰዎችን ላያስቡት ወደ ባዕድ አምልኮ ሊመራ ስለሚችል። ከዚህ ጋ የተፈለገው የሚካኤል አንጀሉን ጥበባዊ ንግግር ነው። ጥበብ ከተገኘበት ቦታ ሁሉ በላልነት ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ መመሪያም ነው። "ጥበብ የጠፋች የሙሚን ንብረት ናት። ከየትም ካገኛት ይጠቀምባት።" ነብዩ መ.ሐመድ ﷺ ስለዚህ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የተጠቀሱና ከመለኮታዊው መመሪያ ጋር የማይጣሙ ነገሮች ካጋጠሟችሁ በዚሁ ሃሳብ ይታዘቡኝ።

አዎ! ሁላችንም ውስጥ የተለየ ችሎታ አለ። ብንገፋበት ከማንም በላይ ስኬታማ የምንሆንበት የህይወት መስመር አለ። በታሪክ የሚጠቀሱ ታላላቅ ስብዕናዎች (great personalites) የታላቅነታቸው ምስጢር ተስፋዎቻቸውን ያማከለ የህይወት ጎዳና መከተላቸው ነው።

ታላቁ ማዕድን

"ብርካታ ሰዎች በውስጣቸው ያለውን ዜማ አንድም ቀን ሳይዘፍኑት ወደ መቃብራቸው ይዘውት ይወርዳሉ።" (Oliver Wendall)

አብዛኛው የሰው ልጅ ከህይወት ጥሪው ጋር አልተገናኘም። ከትክክለኛ እርሱነቱ ጋር ሳይተዋወቅ የምድራዊ ቆይታውን አጠናቆ ያልፋል። ብዙ ተስፋዎች አገልግሎት ላይ ሳይውሉ ወደ መቃብር ወርደዋል። ለዚህም ነው ምድር ውስጥ ካሉ ውድ ማዕድናት ውስጥ ዋነኛው የሚገኘው ቀብር ውስጥ ነው የሚባለው። ከርሰ ምድር ውስጥ ወርቅ፣ አልማዝ፣ ነዳጅ... ብዙ ማዕድናት ይኖራሉ። ነገር ግን እነዚህን ማዕድናት ለተሻለ ነገር የመጠቀም ብቃት ያለው የሰው ልጅ ከነተስፋው አፈር ውስጥ ገብቷል። ለዚህም ነው የምድራችን ዋና አንጡራ ሀብት የሚገኘው መቃብር ውስጥ ነው የተባለው።

ሁሉም ሰው በእለት ተእለት ህይወቱ ላይ የጠፋውን ነገር ለማግኘት ይማስናል። ውዴ እህቴ ቤት ውስጥ እቃ ቢጠፋሽ ለማግኘት ቤቱን ከላይ እስከታች ምስቅልቅል ታደርጊዋለሽ። አንተ ደግሞ መንገድ ላይ ብር ቢጠፋህ ጎዳናውን ሁሉ እየተመላለስክ ትፈልገዋለህ... ታዲያ እኛንታችንን በተገቢው ለማወቅ... ተስፋዎቻችንን ፈልገን ለማግኘት... የውስጥ ጥሪያችንን ለማዳመጥ ለምንድነው ሰራላችን ጊዜ ያልሰጠነው?

ስጋቸው ከሰውነታቸው ላይ አልቆ በአጥንታቸው የቆሙ ህዝቦች ያደረጉትን የስጋ ፍለጋ ሰምተሀል? "ማን ይሆን እንዲህ መጥምጥ የበላን?" ብለው ጉሀ ይምረዋል። ይሳካላቸው ይሆን?

አሰሳ ስጋ

ዕልፍ ከሲታዎች - ቀጥነው የሞጉ
ስጋችን የትሄደ - ብለው ሲፈልጉ
በሆሽንተረሩ - በሆጋጥጉ

አስሰው አስሰው - በምድር በሰማይ
አገኙት ቦርጭ ሆኖ - በአንድ ሰው ገላ ላይ[39]

ከአልህ አስጨራሽ ፍለጋ በኋላ እንደ ሰም አቅልጠው፣ እንደ ብረት ቀጥቅጠው ከገዟቸው መደብ ባላባቶች ሰውነት ላይ አገኙት። የእነሱን ላብ አንጠፍጥፈው ከተጠቀሙ ጥቂት ባለፀጎች ቦርጭ ላይ አገኙት። በሙስና የህዝብን ንብረት ካወደሙ ባለስልጣናት ሰውነት ላይ ተመለከቱት።

አዎን! የሰው ልጅ ብዙ ነገር ለማግኘት ይማስናል። የራሳችን የውስጥ ተሰጥኦ ለማግኘት እንደመጣር ግን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነገር የለም።

4.1 ተሰጥኦን መፈለግ ለምን አስፈለገ?

"ስኬት የተሰጥኦና መሆን የምንፈልገው አላማ ውህደት ውጤት ነው"

የምንቀርፀው የህይወት ግብ ተሰጥኦዎቻችንን ያማከለ መሆን አለበት። ራዕያችን ፈጣሪ ከገራን ማንነት ጋራ መዋሀድ ይኖርበታል። ይህ ውህደት ታላቅነትን ይወልዳል። ታላቅነት (greatness) ከተሰጥኦና ከአላማ ጋብቻ የሚወለድ ብርቅየ ልጅ ነው።

ተሰጥኦን ያላማከለ የህይወት መንገድ ብንከተል ምናልባት የተወሰነ ውጤት እናመጣ ይሆናል። ነገር ግን ታላቅ ስኬት ላይ አንደርስም። እስኪ አስቡት ፈረስን በውሻ ቦታ ተክተን የቤትና የግቢ ጥበቃ ሃላፊነት ብንሰጠው... ሲጠብቅ ነቅቶ ያድራል ወይስ ተኝቶ? አልያም ፍየልን በውሻ ቦታ ተክተን ያለ ተሰጥኦዋ ለአደን ይዘናት ብንወጣ ... ራሷ ትታደን እንደሆን እንጅ ለአደን አትጠቅመንም። በተጨማሪም በጎችን በከብቶች ቦታ ተክተን (ፈጣሪ ባልገራቸው መስክ) እርሻ ላይ ብናሰማራቸው ውጤቱ ምን ይሆናል? ... ተሰጥኦን ያላማከለ ሀላፊነት ውጤቱ አመርቂ አይሆንም። ፈጣሪ ከገራን መንገድ ውጭ በመንዝ ታላቅ ስኬትን መቆናጠጥ አይታሰብም።

ነገር ግን ፈረስ ፈጣሪው የሰጠውን የመሮጥ ተሰጥኦን ያማከለ ግብ ቢያወጣ ለስኬት የቀረበ ይሆናል። በፈረስ ግልቢያው ውድድር ላይ

[39] ግጥም በአውተሩ ሰፈም

ሻምፒዮን መሆን አለብኝ ቢል አልተሳሳተም። እንዲሁም ውሻ ያሳዳሪዎቹን ግቢ ሌት ተቀን በትጋት በመጠበቅ ከሰፈሮቹ ካሉት ውሻዎች የተሻልኩ መሆን አለብኝ፣ አሳዳሪዎቼንም ማስከበር አለብኝ የሚል ግብ ቢያወጣ ይሳካለት ይሆናል። ልብ በሉ! ግቦቻችን በተስፋዎቻችን ቦይ መፍሰስ ይጠበቅባቸዋል።

ተስፋን ፈልጎ ማግኘት የስኬት መሰረት ነው። "እውነተኛ ማንነታችንን እስከምናውቅ ድረስ መሆን ወደሚገባን ሁኔታ መራመድ አንችልም።" Charlotte P.Gilman. ማለታቸው ለዚሁ ነው።

ምናልባት አሁን እራስህን አንድ ጥያቄ እየጠየክ ይሆናል። እንዴት ተስፋዬን ማግኘት እችላለሁ? እኔን ፈጣሪ ለምን ጉዳይ ነው የገራኝ? በየትኛው የህይወት መስክ ብሰማራ ነው የተሻለ አስተዋፅኦ ማበርከት የምችለው?... ቆይ እትጨነቅ ከዚህ በታች መንገዶችን ልጠቁምህ እሞክራለሁ።

4.2 ተስፋን ለማግኘት የሚረዱን ነጥቦች

እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ችሎታ፣ የራሱ የሆነ ተስፋ፣ የራሱ የሆነ ብቃት አለው። የአንተ ችሎታ ምንድነው? ተከታዮቹ ነጥቦች እገዛ ያደርጉልሃል ብየ እገምታለሁ።

1. ተስፋን ያማከለ ስራ ቀልቡን ስለምንተገብረው በደስታ እንሰራዋለን። ታዲያ አንተ ባይከፈልህ እንኳ በነፃ ልትሰራው ፍቃደኛ የሆንከው የስራ መስክ የቱ ነው? በደንብ ጊዜ ሰጥተህ በማሰብ ቢያንስ ሶስቱን ጥቀስ።

1.----------

2.----------

3.----------

2. የተፈጥሮ ችሎታን ያማከለ ስራ በብቃትና በጥራት እንሰራዋለን። ታዲያ አንተ ከምትሰራቸው ስራዎች ሁሉ የትኞቹን ነው በጥራትና በብቃት የምትሰራቸው?

1. ----------

2. ----------

3. ----------

3. እየሰራኸው ደስታን የሚመግብህ የህይወት መስክ (ስራ) የትኛው ነው? ለምን ደስታን የፈጠረልህ ይመስልሀል?

1. ----------

2. ----------

3. ----------

4.2.1 ጠንካራ ጎኖችህን ለይተህ ማወቅ
(Identify Your Strength)

እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ፈጣሪ የቸረው ክህሎት (ችሎታዎች) አሉት። ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውስጥ የአንተ ችሎታ (ክህሎት) የትኛው ነው?

1. --- የመናገር ችሎታ
2. --- የማንበብ ችሎታ
3. --- ስብሰባን የመምራት ችሎታ
4. --- ነገሮችን በፍጥነት የማከናወን ተሰጥኦ
5. --- በጥሞና የማድመጥ ክህሎት
6. --- የመፃፍ ተሰጥኦ
7. --- የማስተዋል ችሎታ
8. --- ከሰው ጋር የመግባባት ክህሎት
9. --- የማስታወስ ችሎታ
10. --- ሰዎችን የማስታረቅ ክህሎት
11. --- የስዕል መሳል ብቃት
12. --- የቃላት ተሰጥኦ
13. --- የሂሳብ ተሰጥኦ
14. --- ውሳኔ የመስጠት ችሎታ
15. --- የስነ-ፅሁፍ ተሰጥኦ

16. --- የመምራት ክህሎት
17. --- የጥሩ ድምፅ ተሰጥኦ
18. --- አንድን ነገር እያሰሩ ሳይሰለቹ ለሰዓታት የመቆየት ችሎታ
19. --- ስዎችን የማሰልጠን ችሎታ
20. --- የማስተማር ክህሎት
21. --- የማንባታ ተሰጥኦ
22. --- የኪነ-ጥበብ ችሎታ
23. --- የቴክኒካዊ ነገሮች ችሎታ
24. --- የአትሌቲክስ ችሎታ
25. --- የመምከር ችሎታ (የምክር አገልግሎት መስጠት)
26. --- የነሺዳ (የመዘመር) ችሎታ
27. --- የጨዋታ አዋቂነት ተሰጥኦ
28. --- አዲስን ነገር የመፍጠር (Creativity) ክህሎት
29. --- የወደፊቱን የመገመት ተሰጥኦ
30. --- ለረዥም ሰዓት ስብሰባን የመታደም ችሎታ
31. --- ነገሮችን በቀላሉ የመረዳት ተሰጥኦ
32. --- የስነ-ግጥም ክህሎት
33. --- ጉዳዮችን የማስፈፀም ክህሎት
34. --- ህፃናትን የመንከባከብ ችሎታ
35. --- በፍጥነት የመናገር ተሰጥኦ
36. --- የአናፂነት ችሎታ
37. --- ሰውን በቀላሉ የመማረክ ተሰጥኦ
38. --- ዜማ የማውጣት (የመፍጠር) ተሰጥኦ
39. --- የሰዎችን ተሰጥኦ የመረዳት ተሰጥኦ
40. ---

ከላይ ያልተጠቀሱ ተሰጥኦ (ችሎታ፣ ክህሎቶች) ካለህ ካለሽ/ ከዚህ በታች ዘርዝሪ/ዝው፡-

1. _____
2. _____
3. _____
4. _____
5. _____
6. _____

ከላይ ያስፈርናቸው ነጥቦች ግባችንን ከማውጣት አንፃር ወሳኝ መስረቶች ናቸው። የምናወጣው ግብ ያለንን ጠንካራ ጎን (Strength) ማለትም ክህሎቶቻችንን ያማከለ ሊሆን ይገባል።

ለምሳሌ አንድ ሰው ታዋቂ የሀዲስ ሊቅ፣ የቁርአን ሀፊዝ (ቁርአንን በቃሉ የሸመደደ) ሰው ለመሆን ካሰበ የማስታወስ ችሎታ ሊኖረው ይገባል። በተመሳሳይ የታሪክ ተመራማሪ መሆን ከፈለገ፣ መጀመሪያ ክስተቶችን የመሸምደድ፣ ድርጊቶች የተፈፀሙበትን ዘመናት የማስታወስ ችሎታ እንዳለው ራሱን መፈተሽ ይጠበቅበታል።

እንዲሁም አንድ ሰው አንቱታን የተቸረ ታዋቂ ኡዲተር መሆን አለብኝ የሚል ግብ ከመቅረፁ በፊት የሂሳብ ችሎታውን በሚገባ መፈተሽ ይኖርበታል። በኢንጂነሪንግና በሂሳብ የትምህርት ዘርፎች ከመሰማራቱ በፊት ለቁጥር ያለውን ዝንባሌ መፈተሽ ተቀዳሚ ተግባር ነው።

እውቅ ፀሀፊና ደራሲ መሆን የሚፈልግ ሰው የስነ-ፅሁፍ ክህሎቱን በደንብ መፈተሽ ይኖርበታል። የንባብ ፍቅሩን መገምገም ይጠበቅበታል።

ታዋቂ ነሺዳ ባይ (ዘማሪ) መሆን የፈለገ ሰው የድምፅ ተሰጥኦውን መፈተሽ ተቀዳሚ ጉዳይ ነው። ለበርካታ ሰዓታት ልምምድ የማድረግ ትግስቱን ማጤን ይኖርበታል።

በተመሳሳይ አንድ ሰው እውቅ አትሌት መሆን ቢፈልግ ወይም ይህን ግብ ቢያወጣ ቀድሞ የአትሌቲክስ ችሎታውንና በየትኛው የአትሌቲክስ ዘርፍ የበለጠ ተሰጥኦ እንዳለው መፈተሽ ይጠበቅበታል።

ሁላችንም አላማችንን ከመቅረፃችን በፊት በየትኛው የህይወት መስክ ፈጣሪ እንደገራን መፈተሽ አለብን። ተሰጥኦዎቻችን ግባችንን የምንቀርፅባቸው መስረቶች ናቸው። ታላቅነት (Greatness) የክህሎትንና የአላማን መሰላል በመውጣት የምንደርስበት ማማ ነው።

ታዲያ እነዚህ ተሰጥኦዎቻችንን በህይወት አጋጣሚ ድንገት የምናገኛቸው እምቅ ሀይሎቻችን ሊሆኑ ይችላሉ። አልያም አንዳንድ አስተዋይ ግለሰቦች፣ ወላጆች፣ ልሂቃን የሚያመላክቱን አጋጣሚ ይፈጠራል።

4.3 በአጋጣሚ ታገኘዋለህ

ተሰጥኦዎችህን በአንድ የህይወት አጋጣሚ ታገኛቸዋለህ። በዙሪያህ ያለን ማህበራዊ ችግር ለመቅረፍ ቆርጠህ ስትነሳ ድንገት ከውስጥ ከሱትህ ጋር ትተዋወቃለህ። የዶር አሩና ፕራግሻን ተሞክሮ አብረን እንመልከት፦

ሀገሬን እንዴት ልታደጋት?

እነሆ ህንዳዊቷ ምሁር ዶር አሩና ፕራግሻ በህንድ ጎዳና ላይ መንገራደድ ይዘዋል። ከቅርብ ርቀትም በርካታ ቁጥር ያላቸው ወጣቶችን ሰልፍ ይዘው ተመለከቱ። ወጣቶቹ ሰንዶችን (ዶክመንቶችን) በእጃቸው ይዘው ይተራመሳሉ።

ሁኔታውን ለማጣራት ወደ ቦታው ዶር አሩና ተጠጉ። ድርጅቱ ባወጣው ማስታወቂያ መሰረት ስራ ለመቀጠር የተሰበሰቡ ስራ ፈላጊዎች መሆናቸውን ተረዱ። የተሰበሰቡት ስራ ፈላጊ ወጣቶች ቁጥር ተቋሙ ከሚፈልገው ቁጥር በላይ ነበር።

ከተወሰኑ ደቂቃዎች ቡኋላ ግን በህይወታቸው የማይረሱትን አንድን ክስተት ተመለከቱ። እምነ የተፈጠረውን ትርምስ ለማረጋጋት ስርዓት አስከባሪዎች በወሰዱት እርምጃ ተሰልፈው ከነበሩት ወጣቶች መሀል አንዱ ቦጥይት ተመትቶ ሲወድቅ አዩ። ያዩትን ማመን አቃታቸው። ይህ ለዓመታት በዩኒቨርሲቲ የተማረና ሀገሩን ይረክባል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ወጣት መሬት ላይ ደም ለብሶ ሲዘረር ተመለከቱ።

ያዩት ክስተት በቀላሉ ከአእምሯቸው ሊፋቅ አልቻለም። ለብዙ ጊዜ አብሯቸው ቆየ። የተሰማቸውን ጥልቅ ሀዘን ወደ መኖሪያ ቦይ አፈሰሱት። ለሀገራና ለህዝቤ ምን ላድርግ ብለው ማሰላሰል ያዙ። ለሀገሬ ህዝብ የኑሮ ዋስትና ምንድነው? ህዝቤን እንዴት ከስራ አጥነት መታደግ እችላለሁ? ሲሉ አሰቡ። አራሳቸውንና ሌሎችንም አማከረው መጨረሻ ላይ አንድ መፍትሄ ላይ ደረሱ። ይኸውም "ሕንድን በኢንተርፕርነርሺፕ ሀይል በቂ ማድረግ አለብኝ።" የሚል ራዕይ ሰንቁ።

በዚህም መሰረት የህንድ ኢንተርፕርነርሽፕ (የስራ ፈጠራ) ብሔራዊ ንቅናቄ ጀመሩ። ይህንንም በዝርዝር የሚያብራራ "Everyday Entrepre

neur" የሚል የተቀጣለት መጽሀፍ ጸፉ። በዚህ ብሔራዊ ንቅናቄ ፕሮግራም መሰረት ሀንድ አንድ ሚሊዮን ወጣቶቿን አሰልጥናና አስተምራ ኢንተርፕርነሮች ብታደርግ ኋላቀርነቷ ተረት ይሆናል ብለው ወደ ቢሊዮን ከሚቆጠረው የህንድ ህዝብ አንድ ከመቶ ኢንተርፕርነር ለመፍጠር ፕሮጀክቱን ጀመሩ።

ብዙ ጊዜ ተሰጥኦዎቻችንንና ግባችንን ለማህበራዊ ችግር መፍትሄ ለመስጠት ስንጨነቅና ስናማክር እናገኛቸዋለን። ለሰው ልጆች መልካም ነገርን ለማበርከት ራእይን ስንቆ የተነሳን ግለሰብ ፈጣሪ ይረዳዋል። ሰኬት እንዲከተለው ያደርጋል።[40]

"ከሰዎች ሁሉ የተሻለው ለሰዎች ጠቃሚ የሆነው ነው።" ሲሉ ታላቁ መልዕክተኛ ነብዩ መሐመድ ﷺ ለለውጥ ያነሳሱሀል።

4.4 ሌሎች ያመላክቱሀል

አንዳንዴ በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ተሰጥኦዎቻችንን እንድንገልፅ፣የህይወት ጥሪዎቻችንን እንድናገኝ ይረዱናል። "አብዛኛው ሰው ለራሱ ባዕድ ነው።" እንደሚባለው ሁሉ ከራሳችን ጋር ሳንተዋወቅ፣ ውስጣዊ ክህሎቶቻችንን ሳንገልፅ ህይወትን እንገፋ ይሆናል። አንድ ቀን ግን ይህን ችሎታችንን ያስተዋሉ ሰዎች ጎዳናውን ሊያመላክቱን ይችላሉ። የቱን መስመር ብንከተል የበለጠ ውጤታማ እንደምንሆን ይጠቁሙናል። ይህን ነጥብ በደንብ ለመረዳት እንዲረዳህ የተወሰኑ የህይወት ገጠመኞችን እስኪ ልጥቀስልህ፦

እይታ ሲስተካከል

እነሆ አንድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተማሪዎቻቸው ቅርብ ጓደኛ እንደሆኑ ከሚታወቁት ተወዳጅ አስታዝ ጋር አየተዘዋወረ ነበር። በመንገዳቸውም ላይ ከመንገዱ ዳር የተቀመጠ አንድ አሮጌ ጥንድ ጫማ ይመለከታሉ። ጫማው የማን እንደሆነ ለማወቅ ብዙም ጊዜ አልፈጀባቸውም። ጫማው ከመንገዱ ዳር በቀን ስራ ላይ የተሰማራ የአንድ ወዛደር ነበር። ግለሰቡ ለስራው አመች ስላልሆነ ነበር ጫማዎቹን ያወለቃቸው። ይህንንም ተማሪውና መምህሩ ተገንዝበዋል።

[40] ስለአስቴ ግንጪ መሐመድ የጉብ እንዴት የህይወት ግቡን በኢጋሚ እንዳገኘና እንዴት የሚያተተውን ክፍል ይመልከቱ - (ምዕራፍ 12 - የስኬት ተምሳሌቶቻችን)

ወጣቱ ተማሪም ወደ ኡስታዙ (ፕሮፌሰሩ) እየተመለከተ "እስኪ ይህንን ጫማ እንደብቀውና ሰውየው ክቦታው ሲያጣው የሚፈጠርበትን ስሜት እዚያ ዛፍ ስር ተደብቀን እንመልከት።" ሲል ሀሳብ አቀረበ።

መምህሩም ትልቅ ቁምነገር የሚያስተምሩበት አጋጣሚ እንደተፈጠረላቸው ተገነዘቡ። ይህን አጋጣሚ የዚህን ወጣት አይታ (Attitude) ለመቀየር ተጠቀሙበት። አጋጣሚውም የወጣቱን ግንዛቤ ያሰፋ፣ ከተሰጥኦው ጋር እንዲተዋወቅ ያደረገ ሆኖ አለፈ።

ኡስታዙም "አንተ ወዳጄ ሆይ! በዚህ ድሃ ሰው ላይ እየቀለድን ራሳችንን ለማዝናናት መሞከር አይገባንም። ይልቁንስ ሌላ መልካም ነገር በመስራት በዋጋ የማይተመን ደስታን ማግኘት የምንችልበትን መንገድ ማሰብ ነው የሚሻለው።" የሚል ሀሳብ አቀረቡ። አስከትለውም፦ "አንተ ምንም ተማሪ ብትሆንም ከኪስህ የሆኑ ሳንቲሞች አይጠፉም። በእነዚህ ሁለት እግር ጫማዎች ውስጥ የተወሰኑ ሳንቲሞችን አስቀምጥ። ከዚያም እነዚያ ዛፎች ውስጥ እንደበቅና ሰውዬው ሳንቲሞቹን ሲያይ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚፈጠርበት እንመልከት።" ሲሉ ሀሳብ አቀረቡለት። ወጣቱም ሀሳቡ ከተለመደው አስተሳሰብ ቅኝት (Pattern of thought) ውጣ ያለ ስለነበር ሀሳቡን ወዶታል። ለመስማማት ጊዜ አልወሰደበትም። ከኪሱ ሳንቲሞችን በማውጣት ጫማዎቹ ውስጥ ጨመራቸው። ሰውየው ላይ የሚፈጠረውን ሁኔታ ለማየት በዛፉ ተከልለው መመልከት ጀመሩ።

ስራውን ያጠናቀቀው ወዲያርም እግሮቹንና እጆቹን ታጥቦ ወደ ልብስና ጫማው አቀና። ኮቱን እየለበሰ አንድ እግሩን ጫማው ውስጥ አጠለቀ። አንድ ነገር እግሩን ሲቆረቁረው ተሰማው። ጫማውን በማንሳት አራገፈ። ነገር ግን ከጫማው የወጣው እንደተለመደው ጠጠርና አፈር ሳይሆን ሳንቲሞች ነበሩ። አይኖቹ የማያምኑትን ነገር ተመለከቱ። እጆቹ ያልጠበቁትን ነገር ዳበሱ... በቀን ውስጥ ከሚያገኘው ገቢ በላይ የሆነ ሳንቲም ከጫማው ውስጥ ተንጠባጠቡ። ፊቱ ጥርስ ወጥርስ እንደሆነ በሀሴት ተሞልቶ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ቢመለከት የሰው ዘር በአካባቢው አያታይም።

ፈጣሪውን እያመሰገነ እንደቆመ ሁለተኛውን እግሩን ወደ ጫማው ሰነዘረ። ተመሳሳይ ነገር ገጠመው። ደስታው ወደር አልነበረውም። ይህ የፈጣሪዬ ሲሳይ ነው ሲል አሰበ። ፈጣሪውንም ለማመስገን አይኖቹን

ስማዩ ላይ ተከሉ ውዳሴውን ያለማቋረጥ አቀረበ። ቤተሰቡ በእይን ሀሊናው መጠበት። ለስራ ያልደረሱ ለምግብ ያላነሱ ልጆቹን አስታወሰ... ጠግበው ሲቦርቁ ታየው። የህዘና ገንዘብ እጥታ አልጋ ላይ የወደቀችው ባለቤቱም ታዘማ ስትድን ታስበው። "ፈጣሪዬ ምስጋና ይድረሰው አሁን የታመመችው ሚስቱ መታከም ትችላለች፣ የተራቡ ልጆቼም ጠግበው ያድራሉ።" ሲል ለብቻው አወራ።

ከደስታ ብዛት የፈሰሱ እንባዎቹን እየጠራረገ ቀበቶውን ማጠባበቅ ጀመረ። በሀሊናው ውስጥ የሳላቸውን ልጆቹን በአካል ለማግኘት ወደ ቤቱ አቀና።

ከወላደሩ በላይ ግን በነገሩ የተደመመው ወጣቱ ተማሪ ነበር። ሰዎች በትንሽ ገንዘብ እንዲህ በሀሴት ሲዋጡ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር የተመለከተው። "እንዴት አየኸው"? የሚለው የኡስታዙ ንግግር ከግርምት ማዕበል ውስጥ ወጣቱን አወጣው። "አንተ ካሰብከውና አሁን ካየኸው የቱ የተሻለ ነው? ሚማዬ ጠፋኝ ብሎ ሲደነግጥና ሲዋከብ ማየት ወይስ እንደ አሁኑ በደስታ ሲፈነድቅ መመልከት"? ሲል አስታትሎ ጠየቀው። ወጣቱ ተማሪ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ጊዜ አልወሰደበትም። "መቼም ልረሳው የማልችለውን ትምህርት ነው ከአርስዎ ያገኘሁት። እውነት ለመናገር በዩኒቨርስቲው የዓመታት ቆይታየ ካስተማሩኝ በላይ በዚህች ሰዓት የተማርኩት ይበልጥብኛል። ከዚህ በፊት ልገነዘባቸው ያስቸገሩኝን እውነታዎች ተረድቻለሁ። የመኖር ሚስጥሩ መልካሙን ነገር ለሰዎች ማበርከት መሆኑን ተገንዝቤያለሁ።" አላቸው።

ይህ ወጣት ይህን ራዕይ ሰንቆ ትምህርቱን አጠናቀቀ። ከዓመታት በኋላም እንቱታን የተቸረ የበጎ አድራጎት ድርጅት በመክፈት የብዙዎችን ችግር ለመታደግ በቃ።

እይታ ሲስተካከል በርካታ አውብ ድንቅ የተሰኙ ለውጦች ይከሰታሉ።

ለዚህም ነው - "Attitude determines Altitude" "አስተሳሰብ የምንደርስበትን ርቀት ይወስናል" የሚባለው።

አዎ! የምንወጣበት የለውጥ ከፍታ ከአስተሳሰባችን ይመነጫል።

እንዳንዴ በዙሪያህ ያሉ የቅርብ ወዳጆች ተስፋህንና አላማህን እንድታገኝ ይረዱሀል። ለአንተ ጥሩና መልካምን ነገር የሚመኙ ሰዎችን ምክር ከልብህ አድምጥ። ለውጥህን የሚመኙ ጓደኞችህን አስተያየት ከልብህ ተቀበለው። በእርግጥ ለውጥህን የሚመኙ፣ ለችሎታህ እውቅና የሚሰጡ፣ ጓደኞችን ማግኘት ቀላል ላይሆን ይችላል። ውሻህ ወንዝ ላይ ሲራመድ እያዩት ባለመዋኘቱ ሊተቹት ልታገኝ ትችላለህ።

ውሻህ ዋና አይችልም

አንድ እረኛ ከውሻነቱ ባህሪ በዘለለ እንደወፍ የሚያደርገው ውሻ ነበረው አሉ። ውሻው ያው በአፈጣጠሩ እንደማንኛውም ውሻ ቢሆንም፣ ከሌሎቹ የሚለየው በውሃ ላይ መራመድ መቻሉ ነበር።

ታዲያ ይህ እረኛ ይህን የውሻውን የተለየ ተሰጥኦ ለጓደኞቹ ለማሳየት ፈለገ። አንድ ቀን አንዱን ጓደኛውን ጫዙ ለማጥመድ አብረው እንዲሄዱ ጋበዘው። በርካታ ጫዙዎችንም እያስወነጨፉ ገደሉ። እረኛው ወንዙ ላይ ተገለው የሚንሳፈፉትን ጫዙዎች እንዲያመጣላቸው ውሻውን አዘዘው። ውሻውም በውሃው ላይ እየተራመደ ጫዙዎችን እያንጠለጠለ መሰብሰብ ያዘ። ነገሩ አስገራሚ ነበር። ውሻው መሬት ላይ እንደሚራመደው ነበር በውሃውም ላይ የሚራመደው።

አዳኙም ጓደኛው ስለውሻው የሆነ የአድናቆት አስተያየት ይለግሰኛል ብሎ ቢጠብቅም ጓደኛው ምንም ያለው ነገር የለም። እደናቸውን ጨርሰው ወደቤት የመልስ ጉዞ ሲያደርጉ አዳኙ ጓደኛውን ከውሻው ያስተዋለው ያልተለመደ ነገር ካለ እንዲነግረው ይጠይቀዋል። ጓደኛውም "አምን ያልተለመደ ነገር አይቻለሁ። ታውቃለህ በጣም ዝሞኝ ነበር። ያየሁት ያልተለመደና የገረመኝ ነገር... ውሻህ ዋና አለመቻሉን ነው።" ብሎ አረፈ... አይገርምም!!!

ቆይ በዙሪያህ ያሉት ጓደኞችህ፣ የስራ ባልደረቦችህ፣ ጎረቤቶችህ... ላለህ ተሰጥኦ እውቅና ላይሰጡ ይችላሉ። ሁሌም ድክመትህን ብቻ ነቅሰው የሚተቹ ሆነው ብታገኛቸው አይገርምህ።

በተለይ እንደበለጥካቸው ከተሰማቸው አንተን በመተቸት ወደታች እውርደሀ ከአንተ ጋር በቁመት አንድ እንደሆኑ ማሰብ ይፈልጋሉ። ያኔ በመከከላችሁ ያለው የብልጫ ርቀት እንደጠበበ ስለሚሰማቸው በተበላሞነት ስሜት አይንገላቱም። በአርግጥ ይህን አኩይ ስሜት አነሱም በውል ላይረዱት ይችላሉ።

"ጸጸላው ደስ የሚላቸው ወላጅና መምህር ናቸው።" የሚለውን አባባል ስምተህ ታውቃለህ? ወላጅ ምንም ያህል ከአርሱ ርቀህ ከኖ ብትል፣ ደስታው እየጨመረ ነው የሚሄደው። ምክንያቱም ልጁ ነህና። በተመሳሳይ መምህርም በበለጥከው ቁጥር ደስታው ይጨምራል። ምክንያቱም ተማሪው ነህና። አንተ የምታገኘው ዝናና ክብር ወደርሱም ተመላሽ ነው።

"እንትና እኮ የኔ ተማሪ ነበር።" ብሎ መፎከር ያስደስተዋል። ምክንያቱም ይህ የእርሱን ታላቅነት ዞሮ የሚያነላ ስለሆነ።

ታዲያ አንተም በዙሪያህ ያሉ ሰዎች ለተሰጥኦህ ቦታ ባይሰጡ እይግረምህ... ውሻህ ወንዝ ላይ ሲራመድ እያዩት ባለመዋኘቱ ሲተቹት ቢታገኝ አይድነትህ።

ብቻ "ቀናተኛ ሰዎችን አትጥላቸው የሚቀኑብህ አንተ ከእነሱ የተሻልክ ነህ ብለው ስለሚያስቡ ነው።" ፓውሎ ኮሊዬ

ነገር ግን ይህን ስልህ ጨለምተኛ እንድትሆን አይደለም። በተለይ እንደኔው አድለኛ ከሆንክ በርካታ ለውጥህን የሚናፍቁ፣ ለተሰጥኦህ አውቅና የሚሰጡ ጓደኞች ሊኖሩህ ይችላሉ። ካገኘህቸው ምክራቸውን ከልብህ ተቀበላቸው። አቡ ሐኒፋም ያደረጉት ይህንኑ ነው። አስቲ ስለአርሳቸው ደግሞ ትንሽ ላውጋልህ።

አቡ ሐኒፋ ሆይ! ንግድ አያጠግብህም

ምድር ላይ ካለፉ ታላላቅ ሊቆች ውስጥ ኢማሙ አቡ ሐኒፋ[41] አንዱ ናቸው። እኒህ ታላቅ ሰው ገና በለጋ እድሜያቸው በንግድ ላይ ተሰማርተው ነበር። ንግድ ላይ የነበራቸው ትጋትና ብስለት በትርፍ እንዲንበሸበሹ አደረጋቸው። በወጣትነታቸው በንግድ ጉዟቸው ላይ አንዳንድ ከንግድ ጋራ የተያያዙ ኢስላማዊ ጥያቄዎች ሲኖራቸው ታላላቅ የሀይማኖት ምሁራኖችን ይጠይቁ ነበር። (ያው እንደሚታወቀው ንግድ በኢስላም የራሱ የሆነ ሰፊ ሃይማኖታዊ ድንጋጌዎችን የያዘ መስክ ነው። በሸሪዓውም አጠራር "ቡዩዕ" ይባላል። ክባድና ጥልቅ የዕውቀት ዘርፍ ነው። ስለሆነም ጥቂት ሊታውንት አንጂ ሌላው በቀላሉ ሊካንበት ይከብዳል። ምክንያቱም የንግድ ሂደት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተለዋዋጭ ስለሆነ፣ ሁሌም ከዘመኑ ጋር የኢስላምን የንግድ መርሆዎች ማዋሃድ ስለሚጠይቅ)። አቡ ሐኒፋም በንግድ ጉዟቸው ላይ የቸገራቸውን ጉዳይ የሚያማክሩዋቸው ሸዕቢ የሚባሉ ታላቅ የኢስላም ሊቅ ነበሩ።

ሁሌም ከንግዱ ጋር በተያያዘ ለሚከብዷቸው ጥያቄዎች ሸዕቢን ይጠይቁ ነበር። እኚህ ታላቅ ሊቅ የአቡ ሐኒፋን ፍጥነት፣ ብስለትና ትጋት ሲመለከቱ፣ የዚህን ወጣት አርቆ አስተዋይነት፣ ነገሮችን በጥልቀት የመረዳት ክህሎት፣ ለዕውቀትና ለመረዳት ያለውን ጉጉት ንግድ ብቻ እንደማያረካው ተረዱ። ይህን የመሰለ ትጋትና ብስለት በንግድ ብቻ መባከን የለበትም ብለው አሰቡ። ከዚያም አቡ ሐኒፋን አንድ ጥያቄ ጠየቁት "ማን ዘንድ ነው እውቀትን የምትማረው?" አሉት። እርሳቸውም "እኔ ከንግድ ውጭ ሌላ የማውቀው የለኝም፣ ከማንም አልማርም።" አሉት። ሸዕቢም "ከንግድህ ጎን ለጎን እውቀትን ብትቀስም መልካም ነው። እውቀቱ ለንግድ ጉዞህ ያግዝሃል።

የእውነት ነው የምንግርህ ንግድ ብቻ ያንተን ጭንቅላት ማርካት አይችልም። አንተ ታላቅ የግንዛቤ ምጥቀት ያለህ ሰው ነህ።" አሏቸው።

ታላቁ አቡ ሐኒፋ እንዲህ ይሉናል፡- "የታላቁን ሊቅ ምክር ስሰማ ንግግራቸው ውስጤ ገባ፣ እድሜ ልኬን የማልረሳው ምክር ነበር"። ከዚህ በኋላ አቡ ሐኒፋ የሚወዱትን የትምህርት መስክ (Departement)

[41] ኢማሙ አቡ ሐኒፋ - ኑዕማን መሐመድ ቢን ሀይሉት ከ 100 ዓመት በኋላ ወደ ምድራችን ብቅ ያሉ ታላቅ የኢስላም ምሁር ናቸው። ይህን የወደፊት ታላቅነታቸው ታሳቢ በማድረግ የወጣትነት እድሜያቸውን በእንቁታ እንተርከዋለን።

መርጠው ገቡበት[ሀ]። ሐማድ ከሚባሉ ሊቅ ዘንድ ሄደው ለ18 ዓመታት ፊቅህ የተሰኘውን የትምህርት ዘርፍ ተማሩ። ምድር ካወቀቻቸው ጥቂት ሊቆችም ግንባር ቀደሙ ለመሆን በቁ።

ከእርሳቸው የትምህርት መስክ (School of thougt) የተማሩ ብዙ ሊቆች የዓለም ታሪክን ለውጠው አልፈዋል። ዓለም እስከአሁን አቡ ሐኒፋን የሚያህል ሊሂቅ ማየት አልተሳካላትም። የእውቀት ማህፀናች የአቡ ሐኒፋን አይነት ልጅ መውለድ ተስኗቸዋል። በቃ እንዲህ ነው የህይወት አላማህ ከተስጦህ ጋር ሲዋሀድ።

ሸዕቢ በአቡ ሐኒፋ ህይወት ላይ የፈጠሩትን አምንታዊ ተፅዕኖ ተመልክት። የአቡ ሐኒፋን ተሰጥኦ በጥልቀት ተመልክተው መስመሩን ጠቆሙት። የአዕምሮው በላልነት፣ የአመለካከቱ ጥልቀትና ትጋት በንግድ ብቻ እንደማይረካና ንግድም እንደማያጠግበው ተረዱ። ዘርፈ ብዙ ከሆነው የኢስላም የእውቀት ማዕድ እንዲመገብ አባታዊ ምክራቸውን ለገሱት።

አቡ ሐኒፋም በዚህ ተሰጥኦዋቸውን ባማከለ መስክ (አላማ) ላይ ተሰማሩ። ምድርም ልትደግመው ያልቻለችውን ሰው ተመለከተች።

አዎ! ተሰጥኦህን አንዳንዴ በአጋጣሚ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አንተን በጥልቀት የተመለከቱህ ሰዎች በሚሰጡህ ጥቆማ ታገኘዋለህ። እስከ አሁን ባለኝ መረጃ መሰረት የትኛውም ሀገር ላይ "ተሰጥኦ ፍለጋ ላይ ስለሚሰራ ሚኒስትር መስሪያ ቤት" ሰምቼ አላውቅም። እንደ ጀርመን ያሉ ሀገራት "የጊዜ ሚኒስትር" እንዳቋቋሙ አውቃለሁ። ይህ ድርጅት ማህበረሰቡ ጊዜውን በአግባቡ ከመጠቀም አንፃር ሊከተለው የሚገባውን መርህ ዘርግቷል። ውጤቱም አመርቂ ሆኗል። በእኔ ግምት ግን ተሰጥኦን ፍለጋ ከዚህ በላይ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል እላለሁ።

ኢትዮጵያ ሀገሬም ይሀን የተሰጥኦ ሚኒስትር መስሪያ ቤት አቋቁማ አንድ ቀን ሀልማችንን አውን ታደርገው ይሆናል።

[ሀ] አቡ ሐኒፋ እንዴት የትምህርት መስክ እንደመረጡ "የህይወት አላማህን ከምትወደው መስክ አንፃር አስምር" የሚለውን ይመልከቱ።

4.5 ማንነትን ፍለጋ

ማንነትን ፍለጋ ከማዕድን ቁፋሮ በላይ ትኩረትን ይሻል። ጥቂቶቹ በዕናት ተጉዘው ከውስጣዊ ክህሎታቸው ጋራ ተገናኝተዋል። ክህሎቶቻቸውን (ተሰጥኦዋቸውን) ያማከለ አላማ ቀርፀውም የስኬትን አፀድ ረግጠዋል። የስኬት ዝናቸው ከአዕናፍ እስከ አዕናፍ አስተጋብቷል። ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች መልካምን ነገር አበርክተዋል።

አንቶኒዮ ሮቢንስ

እውቁ አለማቀፋዊ አሰልጣኝ አንቶኒዮ ሮቢንስ የበርካታ ሰዎችን ህይወት እንደለወጡ ይነገርላቸዋል። አሁን ለደረሱበት ደረጃ ደግሞ መሰረቱ ውስጣቸው ያለን ተሰጥኦ ፈልገው ማግኘታቸው እንደሆነ ራሳቸው ይናገራሉ።

እንደሳቸው አባባል ውስጣቸው ያለን ተሰጥኦ ለማግኘት ከ 700 በላይ መፅሐፍትን አንብበዋል። በተጨማሪም በርካታ ተሞክሮዎችን ከተለያዩ ምንጮች ለማግኘት ማስነዋል። ከዚህም በላይ ብዙ ጠቃሚ ፊልሞችን ተመልክተዋል። ከበርካታ ጥረቶች በኋላ ውስጣቸው የተቀመጠውን የታላቅነት መነሻ አገኙ። ሙሉ ኃይላቸውን፣ ጊዜያቸውን እንዲሁም ዕውቀታቸውን ሁሉ ተሰጥኦዋቸውን ባማከለው አላማ ላይ አዋሉት።

ግለሰቡ በ24 ዓመታቸው ከሚሊየነሮች ተርታ ለመሰለፍ በቅተዋል። ጉዟቸውን በዚሁ ቀጥለው በቀጣይ አመታትም የዘጠኝ ካምፓኒዎች ባለቤትና ስራ አስኪያጅ ለመሆን ችለዋል።

አንቶኒዮ ሮቢንስ ራስን ፈልጎ ለማግኘት የጎላ ሚና ይጫወታል ተብሎ በሚነገርለት Awaken the giant with in — "ውስጥህ ያለውን ታላቅነት ቀስቅሰው"- በተሰኘው ውድ መፅሀፋቸው ላይ፡- "በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ከሶስት ሺህ በላይ አዳዲስ ነገሮችን መፍጠር የሚያስችል ከህሎት አለ።" ሲሉ ፅፈዋል።

እንዲሁም ስለራሳቸው ስኬት መሰረት ሲናገሩ "እኔ ዛሬ የዘጠኝ ካምፓኒዎችና የአንቶኒዮ ፋውንዴሽን ባለቤት ለመሆን የቻልኩት

እያንዳንዱ ሰው[43] ውስጥ ከተቀመጡት ከሶስት ሺህ ችሎታዎች ውስጥ አንዱን በማግኘቱ ነው። ይህ ብዙ ማስኜ ያገኘሁት አንዱ ችሎታዬ (ተሰጥኦዬ) ግን በሀገሬ ውስጥ በድሎት የምኖር ባለሀብትና በአለም አቀፍ ደረጃ የታወቅሁ ግለሰብ ከመሆን አልፌ ሌሎች ውስጣቸው ያለን ታላቅነት በማግኘት ባለሀብት እንዲሆኑ ምክንያት የሆንኩ መምህር፣ አማካሪና አሰልጣኝ እንድሆን አድርጎኛል።" ይሉናል።

ግለሰቡ ከበርካታ አሰሳ በኋላ ያገኙት እምቅ ከሀሎታቸው የተዋጣላቸው የአመለካከት አሰልጣኝ መሆናቸውን ነበር። ሰዎችን ማስተማር፣ ማማከር (Counselling)፣ እንዲሁም ውስጣቸው ያለን ታላቅነት ፈልገው እንዲያገኙ ማመላከት የህይወት ጥሪያቸው (ተሰጥኦዋቸው) መሆኑን ተረዱ... በዚህ መስክ ላይ ገፉበት። ከተሳካላቸው አሰልጣኞች አንዱ ለመሆን በቁ።

ከአሜሪካዊያን በተጨማሪ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ በርካታ ተቋማትንና ግለሰቦችን ብሩህ ተስፋ እንዲሰንቁ፣ በውስጣቸው ያለውን ያልተገደበ ሀይል (Unlimited Power) እንዲያዩ ለማድረግ የሚጥሩ አስተማሪ፣ አሰልጣኝና አማካሪ ሆነዋል።

በበርካታ የአሜሪካ ከተሞችና በተለያዩ የአውሮፓ፣ የእስያ እንዲሁም የመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች ላይ በመዘዋወር ሰፊ ስልጠናዎችን ሰጥተዋል። በመደበኛ አውሮፕላኖች የሚያደርጉት ጉዞና በጉዞው ላይ (አውሮፕላን የመጠበቅ፣ ፍተሻ፣ ሻንጣ ማስረከብና መረከብ እንዲሁም መሰል የጉዞ ስነ-ስርዓቶች) የሚወስዱትን ጊዜ ካላቸው በርካታ የስልጠና ፕሮግራሞች ጋር ባለመጣጣሙ የግል ጀት አውሮፕላን ለመግዛት ተገደዋል። በአሁኑ ሰዓት በግል ጀታቸው ከዓለም አጥናፍ እስከ አጥናፍ ይዘዋወራሉ።

አንቶኒዮ ሮቢንስ ወደ ተለያዩ ሀገሮች በሚጓዙበት ወቅት የርሳቸው አውሮፕላን በሚያርፍበት አካባቢ አልፎ አልፎ ለእርሳቸው አቀባበል ለማድረግ የተሰበሰቡ ሰልጣኞች የአውሮፕላን ማረፊያውን ከመሙላታቸው የተነሳ አውሮፕላኑ አየር ላይ እንዲቆይ የሚነገራቸው

[43] በእኔ እይታ እያንዳንዱ ሰው ፈጣሪ የለገሰውና የተገራበት ተሰጥኦ አለው። ይህን ተሰጥኦ በቀና ለመገንዘብ ግን ሰማያዊም ሆነ ጥናታዊ መረጃ የለም።

ተፅዕኖ ፈጣሪ ለመሆን በቅተዋል። ከአውሮፕላን ማረፊያው ጀምረው ወደ ማስልጠኛ ስፍራቸው ሲጓዙ በአድናቂዎቻቸው እንደ ፕሬዝዳንቶች በክብር ታጅበው ነው።

ኮሚሰሙት ስልጠና ጎን ለጎን የሚሰጧቸው Unlimited power "ያልተገደበ ሀይልና" Awaken the giant within — "ውስጥህ ያለውን ታላቅነት ቀስቅሰው" የተሰኙት መፅሀፎቻቸው በብዙ ሚሊየን ኮፒዎች ታትመው በአለም ተሰራጭተዋል።

በጣም የሚገርመው ግለሰቡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ብቻ ነው ያጠናቀቁት። የኮሌጅ በር አልረገጡም። ሆኖም በርካታ ፕሮፌሰሮች ኮሚሰሙት ትምህርት በላይ የእርሳቸው ትምህርትና ስልጠና የበለጠ የተወደደ ነው።

አየህ! ዋናው ነገር የትምህርት ደረጃ አይደለም። ቁም ነገሩ ያለው እራስንና ተሰጥኦን አውቆ ወደ አላማ መንዙ ላይ ነው። ተሰጥኦን ያማከለ ጉዞ ወደ ስኬት ያደርሳልና። ... ታዲያ አንተስ ተሰጥኦህን ለመፈለግ ጊዜው አሁን አይመስልህም?

ዶ/ር ፋይዝ ሰያል

አውቁ ፓኪስታናዊ ምሁር፣ አስተማሪ፣ አሰልጣኝ እንዲሁም አማካሪ የሆኑት ዶ/ር ፋይዝ ገና በለጋ እድሜያቸው ስኬትን የተቆናጠጡ ወጣት ነበሩ። በ30 ዓመታቸው የሂሳብና የምክር አገልግሎት በሚሰጥ ተቋም ውስጥ እንደ አጋርና የበላይ አመራር በመሆን ይሰሩ ነበር።

በዚህ ተቋም ውስጥ ብዙ መልካም ነገሮች ተመቻችተውላቸው ነበር። ትልቅና ውብ የመኖሪያ ቤት፣ በዚህ ቤት ውስጥ የሚያገለግሉ ከአምስት ያላነሱ የቤት ሰራተኞች፣ ድርጅቱ የሰጣቸው ዘመናዊ መኪና፣ የሚያምር ሰፊ ቢሮ፣ በርካታ የውጭ ሀገር ጉዞ እንዲሁም ዳጎስ ያለ ወርሃዊ ደሞዝ... ሁሉም በዚያ በወጣትነታቸው ዘመን የደረሱበት ደረጃ ነበር።

ይህ ሁሉ ድሎት አብሯቸው ቢሆንም ደስታ ግን ሊፈጥርላቸው አልቻለም። "ለምን ይሆን?" ብለው ራሳቸውን መፈተሽ ጀመሩ። ይህም

" የሰሟቸውን ስልጠናዎች በከፊል በቪዲዮ ተከታትያቸዋለሁ እጅግ ማራኪ ናቸው።

ጥረታቸው ራሳቸውን ፈልገው እንዲያገኙ መንገድ ከፈተላቸው። "በህይወቱ ትልቅ ዋጋ የምሰጣቸውን ቁም ነገሮችን (Core Values) ዘርዝሬ ፃፍኳቸው። ገንዘብን ግን ከዝርዝሩ ውስጥ ላገኘው አልቻልኩም።" ይሉናል። ገንዘብ ከእርሳቸው ዘንድ ትልቅ ቦታ አልነበረውም። እርሳቸው በህይወታቸው ትልቅ ዋጋ የሚሰጡት ነገር "የሰዎችን አመለካከት በመቀየር ህይወታቸውን መቀየር ላይ" መስራት መሆኑን ተረዱ።

ብዙም ሳይቆዩ ብዙዎች የሚቋምጡለትን ስራ ለቅቀው ተሰጥኦዋቸው በሆነው መስክ ላይ ለመስራት ወሰኑ። የስራ መልቀቂያ ደብዳቤ ሰተቋሙ አስገቡ። ይህን ጉዳይ ግን ማንም ለማመን አልቻለም። ያበዱም መሰላቸው። "ሁሉም ሰው የሚመኘው የህይወት ተጨባጭ ውስጥ እያሉ እንዴት ስራውን ለመልቀቅ ይወስናሉ?" ሲሉ ተገረሙ። ካምፓኒውም ይሕፍላቸው ከነበረው ደሞዝ እጥፍ ሊሕፍላቸው ዝግጁ እንደሆነ ነገራቸው። እርሳቸው ግን በአቋማቸው ፀኑ።

ከዚህ ውሳኔ በኋላ ከእውነተኛ ማንነታቸው፣ ከውስጣዊ ተሰጥኦዋቸው ጋር ሆነው እንደ አዲስ ህይወትን "ሀ" ብለው ጀመሩ። "በጣም ትንሽ ገንዘብ እየተከፈለኝ እንኳ ስልጠናዎችና የሰዎችን ህይወት የሚለውጡ ምክሮችን ሰጥቼ ስመለስ የሚሰማኝ ደስታ ወደር አልነበረውም። ምክኒያቱም ይህ በህይወቴ ትልቅ ዋጋ የምሰጠው ቁም (Core Value) ነገር ስለሆነ።" ይላሉ

ዶ/ር ፋይዝ ከዚህ ከስተት ጀምሮ እንደ አዲስ ተወለዱ። ሌሎችም ራሳቸውን በመፈለግ እንዲያገኙና እንደ አዲስ እንዲወለዱ የሚያግዝ "Born again" "ዳግም ተወለድ" የተሰኘ መፅሐፍ አበረከቱ።

ግለሰቡ ዘመናዊውን ትምህርት ከቁርዓንና ከነቢዩ መ.ሐመድ ስ.ዐ.ወ. አስተምህሮት ጋር በማዋሀድ በተለያዩ የዓለም ሀገራት በመዘዋወር የበርካቶችን ህይወት ለውጠዋል። ብዙ ሺሕ ድርጅቶችን በማሰልጠንና በማማከር ለስኬት አብቅተዋል። በተጨማሪም በእንግሊዝኛና በኡርዱ ቋንቋዎች በርካታ መፅሐፍትን ከትበዋል። እንዲሁም በኦዲዮና በቪዲዮ ካሴቶቻቸው ብዙ ትምህርቶችን ሰጥተዋል።

ከባሏቸው የእንግሊዘኛ መፅሐፎች ውስጥ Born Again, 30 second Manager, Change Your lens Change Your world, Please Mind Your Manners, Leadership 63;Traits of Global Leaders, Fast T. R. A. C. K እንዲሁም ስለ ተቃራኒ ጾታዎች ግንኙነት የሚያትተው Together Forever የሚሉት ይገኙበታል።

የዚህ ሁሉ ስኬታቸው መሰረት የውስጥ ዝንባሌያቸውንና ተሰጥኦዋቸውን ባማከለ የስራ መስክ መሰማራታቸው መሆኑን ልብ በሉ። ዶ/ር ፋይዝ ዳግም ለመወለድና ከውስጣዊ ማንነታቸው ጋር ለመተዋወቅ ብዙ ማስነዋል። ይህን እልህ አስጨራሽ ጉዞ እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል፦

"The longest Journey I can ever remember is the Journey to self discovery"

"በህይወቴ የማስታውሰው ረዥሙ ጉዞ ራሰን ለማግኘት ያደረኩት ጉዞ ነው"

አንተስ ተሰጥኦህ ምንድነው! ፈጣሪ ለምን ነገር ገርቶሀል?

"የሒሳብ ስሌቶች (መደመር፣ መቀነስ፣ ማባዛት...) ሳንችል የሂሳብ መልመጃዎችን መስራት እንደማንችል ሁሉ፣ ተሰጥኦዎቻችንን ያማከለ ዓላማ ሳንቀርፅ ስኬት ላይ መድረስ አዳጋች ነው።"

4.6 ፈጣሪ ለብዙ ነገር ገርቶህ ቢሆንስ?

ኢማሙ አዝ-ዘሀቢ "ሲየር አዕላመ አን-ኑበላእ - "የታላላቅ ሰዎች ታሪክ" በተሰኘው ባለብዙ ጥራዝ መፅሀፋቸው ውስጥ ዓለም ላይ ተፅዕኖ ፈጥረው ያለፉ የሙስሊሙ ዓለም ነገስታትን፣ የብዕር ሰዎችን፣ ገጣሚዎችን፣ የሀይማኖት ሊቃውንትን፣ የጦር መሪዎችን፣ የቋንቋ ምሁራንን፣ ለአምላካቸው ባላቸው ክብርና ፍርሀት የሚታወቁ ግለሰቦችን... በዝርዝር ጠቅሰዋል።

ከጠቀሷቸው ታላላቅ ስብዕናዎች ውስጥ የተወሰኑት በበርካታ የህይወት ዘርፍ ላይ አንቱታን የተቸሩና የብዙ ተሰጥኦዎች ባለቤት ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ አብዱላህ ኢብኑል መባረክ ይጠቀሳሉ።

ኢብኑል ሙባረክ በርካታ ተሰጥኦዎችን የተቸሩ የሁሉም መስክ ሰው ናቸው። የነቢዩን ሀዲሶች (አስተምህሮዎች) ከ700ሺ በላይ በቃላቸው የሸመደዱ ሊቅ ነበሩ። ከዓለም የተለያዩ ቦታዎች እየመጡ የእምነቱ ተከታዮች ከእርሳቸው ይማራሉ። የቁርዓን እውቀት ምጥቀታቸው ግንባር ቀደም ያደርጋቸዋል። በፊቅህ (Islamic Jurisprudence) ላይ ጥልቅ እውቀት ነበራቸው። የፊቅህ እውቀት ዘርፍ አዋቂዎች "ከባባድ የፊቅህ ጥያቄዎች ሲኖሩን የኢብኑል መባረክን መፅሀፎች እናገላብጣለን።" ሲሉ በዚህ የትምህርት ዘርፍ ላይ ያላቸውን ጥልቅ ግንዛቤ ይመሰክራሉ። በስነ-ግጥም ዘርፍም የሚስተካከላቸው አልነበረም። ግጥሞቻቸው በዐረብኛ ባይሆኑ ኖሮ ትንሽ አስነብባችሁ ነበር። በተጨማሪም ተፋላሚ የማይደፍራቸው የጦር ሜዳ አርበኛም ነበሩ።

በዚህ ላይ የኢኮኖሚ ነፃነታቸውን (Financial Freedom) ያረጋገጡ መልቲ ሚሊየነር፣ ገንዘባቸውን ለችግረኞች የሚለግሱ ቸር፣ ቀኑን በፆም ሌሊቱን በስግደት የሚያሳልፉ ፈሪሀ-አላህ ነበሩ።... የእነዚህና የበርካታ ተሰጥኦ ባለቤት ነበሩ።... ታዲያ አንተም ብዙ ተሰጥኦዎች ውስጥህ ሊኖሩ ይችላሉ። በደንብ ፈትሻቸው።

ነገር ግን ስለብዙ ተሰጥኦዎች ስናወራ በመስኩ ላይ እንደሻኛ ጎልተን የወጣንበት መስክ ማለታችን መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። ሁሉን መነካካትና አንዱንም አለማድማት ስኬት አይደለም። እንዲህማ ከሆነ እንደ ዝየ ሆንን ማለት ነው። እስቲ ከዝየ ጋር ደግሞ ጥቂት ቆይታ እናድርግ፦

ቁንጠኛዋ ዝየ

ጌብራን የተባለ እውቅ ፀሀፊ በዝየና በፈረስ መሀከል የነበረውን ውይይት እንዲህ ሲል አስፍሮታል፦

"... ከእለታት አንድ ቀን አቶ ፈረስ ከሃይቅ ዳርቻ ሳር እየጋጠ ነበር። ወይዘሪት ዝየ በተለመደው ቁንጥኛ አረማመዷ እየተንጎራደደች ወደ ፈረስ ተጠጋችና እንዲህ አለችው።

"ስማ አቶ ፈረስ! አንተ በምድር መጋለብ ብቻ ነው የምታውቀው። እኔ ግን ሎሌት ሙያ አለኝ፣ እዋኛለሁ፣ እበራለሁ፣ እጋልባለሁ (እሮጣለሁ)።"

አቶ ፈረስ ሳር መንጨቱን በመተው በመገረም እንዲህ አላት፦

"ከሎሌት አንዱን ባግባቡ ብትፈልሚው በተሻለሽ። ከበረሩ አይቀር እንደ ንስር ነበር። ከዋኙ አይቀር እንደ አሳ። ከጋለቡ አይቀር እንደ እኔ። አንቺ አንዱን እንኳ በትክክል አትፈልሚም። መጋለብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቂያለሽ? ተመልከች እንግዲህ..."

አቶ ፈረስ ተናግሮ ሁዳዱ (መስኩ) ላይ እንደጉድ ቢሸመጥጥ ከአድማሱ ሆድ ገብቶ ተሰወረ[46]...

አዎ! ሁሉን ከመነካካት በአንዱ መዝለቅ ይመረጣል። ተስፖአዎቻችንን ባማከለው መስክ አንቱታን ማግኘት ነው ወሳኙ።

አሁን ዳግመኛ ልጠይቅህ። ተስፖህ ምንድን ነው? የዓለማት ጌታ ለምን ጉዳይ አግርቶሃል?

እስከ አሁን በስፋት የህይወት ግባችን የምንቀርፅበት አንዱን መሰረት (ተስፖአን ለይቶ ማወቅን) ተመልክተናል። በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ ሌላ መሰረታዊ ነጥቦችን እናያለን።

[46] የስደተኛው ማስታወሻ - ተስፋዬ ገብረአብ

5

ምዕራፍ አምስት



የህይወት አላማችንን እንዴት ማለስቀመጥ እንችላለን?

- ከምን ተፈጠርን?
- ከአምልኮ
- የግቦች ግብ
- ወደ መነሻችን ስንመለስ

ምናልባት ለአብዛኛው ሰው ይህን ጥያቄ መመለስ ብዙም ከባድ ላይሆን ይችላል። "የህይወት ግባችንን ለወደፊት መሆን የምንፈልገውን ነገር ወረቀት ላይ ማስፈር" የሚል ሊሆን ይችላል። በተለይ ደግሞ ከሀሉትና ተሰጥኦዎቻችንን ባማከለ መልኩ ግባችን ማስቀመጥ። ሙሉ ስኬትን (የሁለት ዓለም ስኬትን) እንደሚመኝ አንድ የለውጥ ግለሰብ ግን ይህ በቂ አይደለም። የህይወት ግባችን የሚጣልበት ሌላ መሰረት አለ። ይህም መሰረት ለምን እንደተፈጠርን መረዳት ነው። ይህን በግልፅ ከተረዳን በኋላ ከዚህ ተነስተን የህይወት ግባችንን እንቀርፃለን።

5.1 ለምን ተፈጠርን?

ይህ ጥያቄ የብዙ ፈላስፋዎችን ጭንቅላት ያናወዘ ጥያቄ ነው። ለእነዚህ ጥያቄዎች መለኮታዊ መፅሀፍት አንጅ ሌላ ፍልስፍናዎች መልስ ሊሰጡበት አልቻሉም።

በጥልቀት ከተመራመሩት ፈላስፋዎች ውስጥ አንዱ የሆነው አፍላጦ እንዲህ ነበር ያለው፡-

"ፈጣሪ ፍጥረተ ዓለሙን ፈጥሮ ረስቶታል"። ይገርማል!... ለዚህ የተሳሳተ ድምዳሜ ቁርአን እንዲህ ሲል መልስ ይሰጣል፡-

"ጌታህም ረሽ አይደለም...."

ማርክስም "ፈጣሪ ፍጥረተ-ዓለሙን የፈጠረው ሊጫወትበት ነው።" ሲል ግርምት ውስጥ የሚከት ንግግሩን ያስነብበናል። በእርግጥ ለዚህ የተሳከረ አይታ ቁርአን ውስጥ ጥርት ያለ ምላሽ እናገኛለን፡-

[7] ቁርአን 19:64

የፈጠርናችሁ ለከንቱ መሆኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መሆናችሁን ጠረጠራችሁን? (ለከንቱ የፈጠርናችሁ መሰላችሁን?)[፡፡]

በአርግጥም ፈጣሪ ምድርን ፈጥሮ አልረሳትም፣ለመጫዎታም አልፈጠራትም። የሰው ልጅ ለታላቅ ቁምነገር ተፈጥሯል። መጀመሪያ ወደፈጠረው ጌታ ይመለሳል። ሁሉም ነገር ወደ ሀያሉ ጌታ ተመላሽ ነውና።

"መጨረሻውም ወደ ጌታህ ብቻ ነው።"[፡፡]

አንስታይን

አውቁ ላይንቲስት አልበርት አንስታይን ትልቅን ነገር ለዓለም አበርክቶ አልፏል። በተለይ በ Modern Physics ዘርፍ ላይ የማይተካ ሚና ተጫውቷል።

ለአለም ትልቅ ነገር አበርክቶ ቢያልፍም፣ ምንም እንዳልሰራ ነው የሚያስበው። ሁሌም የማይረሳት እንዲህ የምትል መፈክር አለችው። "የውስጣዊም ይሁን የውጫዊ ህይወቴ በሌሎች ላብ (አስተዋፅኦ) ላይ የተመሰረተ መሆኑን ሁሌም ለራሴ አስታውሰዋለሁ። ከህዝቡ ያገኘሁትን ያህል አገልግሎት እኔም መስጠት እንዳለብኝ ስለሚሰማኝ ሁሌም በጣም ጥረት አደርጋለሁ... ነገር ግን አሁንም ከምድር ተገልጋይ ነኝ"[፡፡]

እንዲህ አይነት እይታ የነበረው ታላቅ ሰው ግን የተፈጠረበትን መሰረታዊ አላማ እንዳልተረዳ ራሱው ይናዘዛል። ህይወት እንቆቅልሽ እንደሆነችበት ነበር ያለፈው።

አንዱ አንድ ሰው "ፈጣሪን አንድ ጥያቄ የመጠየቅ እድል ብታገኝ ምን ብለህ ትጠይቀው ነበር?" ሲል ጥያቄ አቀረበለት። እርሱም "ፍጥረተ አለሙን እንዴት እንደ ጀመረ እጠይቀው ነበር። ምክንያቱም ከዚህ በኋላ ያለው ነገር ሁሉ የሂሳብ ስሌት ነው" ሲል መለሰ። ከዚያም ቆም ብሎ

[፡፡] ቁርአን 23:115
[፡፡] ቁርአን 53:42
[፡፡] Entrepreneurship - Werotaw Bezabih (PHD)

ትንሽ አስላስለና ሀሳቡን ቀይሮ እንዲህ አለ "ለምን ፍጥረተ-ዓለሙን እንደተፈጠረ አጠይቀው ነበር። ምክንያቱም የህይወቴን (የመፈጠሬን) ትርጉም በውል እንድረዳ ስለሚያደርገኝ"

ይገርማል! በቴክኖሎጂው አድገት ላይ ትልቅ ሚና የነበረው ሳይንቲስት ለምን እንደተፈጠረ፣ ፈጣሪ ፍጥረተ-ዓለሙን ለምን እንደፈጠረ፣ ለምን ወደ ምድር እንደመጣ አልተረዳም። የመፈጠሩን ሚስጥር በወጉ ሳይረዳ ነፍሱ እንደቃተተች ምድርን ተሰናበተ።

በእርግጥ አንስታይን ትልቅ ግብ ነበረው። ምድር የሰጠችኝን ያህል ልስጣት ይገባል፣እንዲሁም ከሰዎች ያገኘሁትን አገልግሎት ሁሉ መክፈል አለብኝ የሚል ትጋት ነበረው። ነገር ግን የግቦቹ ግብ አልነበረውም። የተፈጠረበትን አላማ አልተረዳም ነበር። የህይወቱ (የመፈጠሩ) ትርጉም ግልፅ ሳይሆንለት የምድራዊ ቆይታውን አጠናቋል።

ኢልያ አቡማዲ

እንደ ብዙ ፈላስፋዎች ሁሉ ኢልያም የተፈጠረበት አላማ አልገባውም ነበር። ይህን ስሜቱንም "ጦላሊም" ብሎ በሰየመው ስንኙ ገልፆታል።

"መጣሁ፤ ከየት እንደሆነ ግን አላውቅም፤ ነገር ግን ወደ ምድር መጣሁ። ከፊት ለፊቴ መንገድን ተመለከትኩ... ተራመድኩ። ወደድኩም አልወደድኩም በህይወት ጎዳና ላይ ጉዞዬን እቀጥላለሁ። እንዴት ወደ ምድር መጣሁ?... እንዴትስ መንገዴን ተመለከትኩ?... እኔ አላውቅም!

ለዚህ አለም አዲስ ነኝ? ወይስ የቆየሁ?
ነፃ ነኝ? ወይስ የታሰርኩ እስረኛ?
የህይወቴ መሪ እኔ ነኝ? ወይስ ሌላ የሚመራኝ ሀይል አለ?
ባውቅ ደስ ይለኝ ነበር። ነገር ግን... በጭራሽ አላውቅም!
የህይወት መንገዴ... ምንድን ነው መንገዴ? አጭር ነው
ወይስ ረዥም?
የህይወትን አቀበት እየወጣሁ ነው ወይስ እየወረድኩ?
እኔ በእርምጃዬ ላይ እየተንገዘገዝኩ ነው ወይስ እርምጃዬ
እየተንገዘገዘኝ ነው?

[1] The 8th habit from effectiveness to Greatness p . 71-72

ወይስ እኔና አርምጃዬ ቆመን ፣ ጊዜ አራሱ እየተራመደ ነው?
በጭራሽ አላውቅም!
ተስተካክዬ ሰው ሆኜ ከመፈጠሬ በፊት
ማኅፀን ውስጥ የታዘልኩ ነበርኩ? ወይስ ሌላ ነገር?
ለዚህ ሁሉ እንቆቅልሽ መፍትሄ አለው ወይስ ለዘልዓለም
ይቀጥላል?
እኔ በጭራሽ አላውቅም... ለምንድን ነው የማውላቀው? ... እኔ
አላውቅም!

ይህን መርህ የለሽና ግራ የተጋባ ህይወት ...ይህን የተሳከረ ህይወት ቁርአን እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡-

"በፊቱ ላይ ተደፍቶ የሚሄድ ሰው ይበልጥ የቅናቻን ጎዳና የተመራ ነውን? ወይስ በቀጥተኛ መንገድ ላይ ተስተካክሎ የሚሄድ?"

ይህ እንግዲህ የህይወት አቅጣጫ ጠፍቶት፣ ከህይወት ግንብ ጋር እየተላተመ፣ ለምን እንደተፈጠረ፣ ወዴት እንደሚሄድ ስላልተረዳ ሰውና የህይወት ግቡ ግልፅ ስለሆነለት ግለሰብ በእንዛራዊነት የቀረበ ምሳሌ ነው።

ለዚህ እንቆቅልሽ መፍትሄውን ፍለጋ የሰው ልጅ የተለያዩ የፍልስፍና መፅሀፍትን ቢያገላብጥም ሊያገኘው አልቻለም። ምክንያቱም እነዚህን መፅሀፍት የፃፉ ፈላስፋዎች ራሳቸው ለዚህ ጥያቄ መልስ አላገኙምና።

ይህ እንግዲህ የህይወት አቅጣጫ ጠፍቶት፣ ከህይወት ግንብ ጋር እየተላተመ፣ ለምን እንደተፈጠረ፣ ወዴት እንደሚሄድ ስላልተረዳ ሰውና የህይወት ግቡ ግልፅ ስለሆነለት ግለሰብ በእንዛራዊነት የቀረበ ምሳሌ ነው።

[52] ኢማንና ህይወት - ፕ/ር አል-ቀርዳዊ
[53] ቁርአን 67 : 22

መፅሀፋቸውን ባነበብክ ቁጥር ሌላ ብሽቦታ ውስጥ ይከቱሀል። ከራስህ ጋር ለመታረቅ አስበህ ስታገላብጣቸው ከራስህ ጋር ተጣልተህ ታገኘዋለህ።

የአንድ እናት ልጆች
በአስተሳሰብ ተጣልተው
በአመለካከት ተለያይተው
የሚያስታርቅ ጠፍቶ
የአብድ ገላጋይ በዝቶ[54]

እነዚህ የፍልስፍና መፅሐፍቶች የአብድ ገላጮች ናቸው። ለማንነትህ መልስ ሊሰጡህ አይችሉም። አንተነትህን ሊያመላክቱህ አቅም የላቸውም። ከማንነትህ ጋር ያጣሉህል እንጂ አያስታርቁህም። የአንድ እናት ልጅ ከሆናችሁ ከአንተና ከማንነትህ ጋር ያራርቁሃል እንጂ አያቀራርቡህም።

እውቁ ጀርመናዊው ፋላስፋ ኒቼ[55] በአንድ ወቅት "እምላክ የሚባለውን ሀይል የፈጠሩት ድሆች ናቸው።" ሲል። በሌላ ክፍለዘመን የመጣው የሶሻሊስቱ ርዕዮተ-ዓለም መስራች ማርክስ ደግሞ "እምላክ የሚባለውን ነገር የፈጠሩት ሀብታሞች ናቸው።" ሲል ሌላ የተቃርኖ ዋልታ ላይ ሆኖ ይፈላሰፋል። ታዲያ አንተ የቱን ትይዛለህ?... አየህ በእውነትም የአብድ ገላጮች ናቸው። ባነበብካቸው ቁጥር አዲስ የአስተሳሰብ መዋዥቅ ውስጥ ራስህን ታገኘዋለህ።... እውነቱ ግን ወዲህ ነው። ለዚህ የማንነት ብሽቦታ ነልሱ ያለው ካልተበረዘው መለኮታዊ መፅሀፍ ውስጥ ብቻ ነው።

አብዛኛው ሰው የጠፋ ማንነቱን በማሰብ መረበሽ፣ የህይወት ተልኮውን በማሰላሰል መጨነቅ አይፈልግም። አፅምሮአቸው ፅረፍት ካገኘ የሚያነሳው ጥያቄ እንዳለ ያውቃሉ። ለምን ተፈጠርክ? ለምን ትኖራለህ? መመለሻህ ወዴት ነው?..... የሚሉት እውነታዎች ሁሌም ያቃጭሉባቸዋል። ይህን አፅምሮአቸው ውስጥ ሁሌም የሚመላለስና መልስ ያጡለትን ጥያቄ ለመርሳት መጠጥና መሰል አደንዛዥ ሱሶች ውስጥ ይደበቃሉ። ጭፈራ ውስጥ ይሸሸጋሉ። ጫት ውስጥ ይወሸቃሉ። አፅምሮአቸው ነፃ ከሆነ የሚነግራቸው እውነት እንዳለ ስለሚያውቁ፣ ቀጣይዋን ግጥም እንደመፈክር አንግበዋል። ግጥሟ እንዲህ ትላለች፦

[54] ግጥም - በአሉ ግርማ - የጋዜጠኛዉ ማስታወሻ - ተስፋዬ ገ/አብ
[55] God is dead — Fredrich Nitzsche

አንዳይነግርህ አንዳች አውነት!

ደንስ ጎበዝ! ደንስ ጀግና
ከራቫትክን አውልቅና
ሀሳብክን ልቀቀውና
ኮትክን ሸሚዝክን ጣልና
አርገጥ ጨፍር ደንስ ጀግና!
ያን የሙዚቃህን ናዳ የኮንትራባሱን መብረቅ
ልቀቀውና ይደብለቅለቅ
ምድር በሆይታ ይጥለቅለቅ!
ምንም ምንም አንዳታስብ ሁሉን ሁሉን አንድትረሳ
ደንስ! ካካታው ይነሳ
ጨፍር ወለሉ አስኪበሳ....
ሃይ-ሃይ! ዋይ! ሃይ-ሃይ! በልበት
የጃዝ ፍንፍር አንኳኳበት
ራስክን አንዳታስብበት
ሆ! በል አሪ! በል ምታበት
ፎክርበት አቅራራበት
አናፋበት ሸልልበት
የሲቃ ሳቅ አሸካካበት
ሆያ ሆዬ! በል ጩኽበት
ኑኡታህ መንኮራኩርክን አስኪያሰጥመው አጓራበት
ጭንቅላትክን ግዘፍበት ውቀጥበት ውገርበት...
ዝማ ብሎማ ያሰበ ቀን ይነግርህል አንዳች አውነት!![56]

በቃ! ይህ ነው ጉሏቸው አዕምሮአቸውን ቢዚ በማድረግ መልስ ካጡለት ጥያቄ ይሸሻሉ። ደስታንና መረጋጋትን ለማግኘት ይማስናሉ። የውስጥ ሰላምና ደስታ ዱርዬ ይመስል በየጭፈራ ቤቱ ይፈልጉታል።

የዘወትር ዜማቸውም ይህ ነው፡-

ፀጉሩን አንጨብሮ ሺሙን አጎፍሮ
ጥማ ተቀምጦ ለሚታየኝ ወጣት
ሂድና ታዘዘው ሰጠው አንድ ድራፍት
ቅዳለት አንድ ጂን ሃሳቡን ይርሳበት

[56] አሳት ወይ አበባ - ከፀጋዮ ገብረ መድህን

በጄሙ መንፈር በፀንፋ መንጨበረር
ቁጥር ፈታ በሚል በግንባሩ መሰመር
ይታየኛል ቋንቋ ይታየኛል ነገር

፡ ፡ ፡

ኮረዳዋንም፡ ፡ ፡

አዛም ከጨለማው · ብሮንነት ወጣት
ሲንፈዋን ይዛ · ለቆመችው ወጣት
ሂደና ታዘዛት · የሚጠጣ ሰጣት
ምን በተፋችው · በጭሶቹ መሃል
ሊትነት ሊበደል · አሀትነት ሊጣል
አናትነት ሊንደል
ይታየኛል ቋንቋ ይታየኛል ፊደል

እውነቱ ግን ይህ አይደለም። ሲጋራ ውስጥ መያዘቅ አያጭማም።መጠጥ ውስጥ መሸሸግ አያሳልቅም። ደስታ ያለው የተፈጠርክበትን ምድራዊ ተልዕኮ ከመረዳትና በአርሱው መስመር በመንዝ ውስጥ ነው። የደስታ አዝመራ የሚበቅለው የህይወትን አላማ በግልፅ ከማወቅ መስክ ላይ ነው።

5.2 ለአምልኮ

ለአለማት ፈጣሪ ምስጋና ይግባውና ይህ ጥያቄ አንተን አያስጨንቅህም። ለምን እንደተፈጠርክ በአንዲት አንቀፅ ተቀምጧልሀል። እስኪ የአለማት ጌታ ምን እንደሚለን እንስማው፡-

"የሰውን ልጅም ሆነ አጋንንትን እኔን ሊገዙኝ ቢሆን እንጂ አልፈጠርኋቸውም"[57]

በአጭር ቃል የሰው ልጅ የተፈጠረበት መሰረታዊ አላማ የፈጣሪው አገልጋይ፣ በስርአቱ የሚያድር... ለትዕዛዙ እጅ የሰጠ ይሆን ዘንድ ነው። በአሳቡ፣ በንግግሩ፣ በድርጊቱ ሁሉ የፈጣሪውን ውዴታ ለማግኘት

[57] ቁርአን 51 : 56

የሚጥር ክንውን መሆን ነው ኢባዳ ማለት።... እንግዲህ ከዚህ መሰረት ላይ የህይወት አላማችን ይገነባል።

ነገር ግን ፈጣሪን መገዛት ማለት ምን ማለት ነው? መስገድና መፆም ብቻ ነው? ወይስ ምዕዋት መስጠትና ችግረኞችን መርዳት ብቻ? ምን ማለት ነው መገዛት ማለት?

እውቁ ምሁርና የተህድሶ ቀንዲል ኢብኑ ተይሚያህ[58] እንዲህ ሲሉ የተብራራ ምላሽ ይሰጡናል፡-

"ኢባዳ (አምልኮ) የወል ስም ሲሆን ፈጣሪ ቢተገበር የሚወደውን ነገር ሁሉ ያጠቃልላል። ይህም የውስጥም ይሁን የውጭን፤ ንግግርም ይሁን ድርጊትን ያካትታል"[59]

ንግግር ሰንል፡- ሰዎችን መልካም ነገር ማስተማር፤ ከመጥፎ መከልከል፤ የምክር አገልግሎት መስጠት፤ ነሺዳ (መዝሙሮችን) መዘመር፤ ግጥሞችን ማነብነብ፤ ስልጠና መስጠት፤ መብቱ ይከበር ብሎ ጎዳና ላይ ወጥቶ መጮህ፤ የተጣላን ማስታረቅ፤ ሰዎችን በንግግር ወደ መልካም ስብዕና መጥራት፤ መለኮታዊ መፅሀፍትን (ቁርዓንን) ማንበብ፤...።

በአጭሩ የሰው ልጅ አንደበቱን በመጠቀም የሚሰራቸውን ሠናይ ስራዎችን ሁሉ ይመለከታል።

ድርጊት ሰንል፡- ለራስህ፤ ለቤተሰብህ፤ ለሀገርህ ለሰው ልጆች የሚጠቅሙ ሰናይ ተግባሮች፤ መፃፍ (የተለያዩ የህትመት ውጤቶችን... ጋዜጣ ላይ፤ ፌስቡክ ላይ፤ የተለያዩ መፅሀፍትን...) የተለያዩ ሀይማኖታዊ (መስገድ፤ምዕዋት መስጠት፤ ችግረኛን መርዳት...)፤ ሀላል (በተፈቀደውና በተገቢው መንገድ) ነግዶና ሰርቶ በላብ ማደር፤ መለኮታዊውን መመሪያ መሰረት አድርገህ ካገባሀት ባለቤትህ ጋር ግንኙነት ማድረግ...። በአጠቃላይ ፈጣሪ የሚወደውን ሰናይ ነገርን ሁሉ ያመላክታል። አምልኮ በአስልምና ትልቅና ሰፊ መልዕክት ያዘለ ነው።

---

[58] ኢብን ተይሚያ - ከ800 ዓመት በፊት ወደዚህች ምድር ብቅ ብለው የነበሩ የተሃድሶ ሰው።

[59] ከተውሒድ እድማስ - አዘጋጅ ያሲን ኑሩ ዒላ (YN)

ስለዚህም አንድ ሰው ልጆቹን በጥሩ ስነምግባር ኮትኩቶ ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው ብሎም ለሀገር የሚጠቅሙ አድርጎ ማሳደግ ራሱን የቻለ የአምልኮ (የኢባዳ) ተግባር ነው።

የማህበረሰቡንና የሀገሩን ችግር ለመቅረፍ ማህበረሰቡን በአንድ አላማ አስልፎ መንቀሳቀስ ኢባዳ (ፈጣሪን ማምለክ) ነው።

በተለያዩ የሚዲያ ውጤቶች ላይ በመግፍ ሀገር ላይ ፍትህ እንዲሰፍን፣ ዲሞክራሲ እንዲያብብ፣ ነፃነት እንዲጎለብት መታገል ኢባዳ ነው። ጠዋት ማታ ጠንክሮ በማጥናት የተሻለ ውጤት ለማምጣት መትጋት ኢባዳ ነው...።

አዎ ኢባዳ ጥቅል የሆነ የወል ስም ነው። በአጭሩ የፈጣሪን ውዴታ ሊያተርፍልን የሚችሉ ነገሮች በአጠቃላይ ኢባዳ ውስጥ ይካተታሉ። አንድን ነገር አስብ ወይም ተናገር አልያም አድርግ፣ ያ ነገር ፈጣሪህ የፈቀደውና እርሱን በማድረግህ ላይ የፈጣሪን ውዴታ ፈልገህ ያደረከው ከሆነ ኢባዳ እንለዋለን።

የሰው ልጅ የተፈጠረው ለኢባዳ ነው። ወደዚህች ዓለም ያመጣው አንዱና ብቸኛው ጌታ ነው። ምድራዊ ቆይታውን ሲያጠናቅቅም ወደ እርሱ ይመለሳል። ይህን ጉዳይ በአግባቡ የተረዳ ሰው የአስተሳሰብ መዋዠቅ ውስጥ አይገባም። ለምን ተፈጠርኩ?፣ ለምን እኖራለሁ?፣ ወደ የትስ እመለሳለሁ፣ የሚሉት ጥያቄዎች ዕረፍት አይነሱትም።

አዎ! የተፈጠርንበት መሰረታዊና ዋናው አላማ የፈጣሪን ትዕዛዝ በመፈፀም የእርሱን ውዴታ መሻት ነው። ሁለንተናችን የእርሱን ውዴታ በማግኘት ላይ ልናሰልፈው ነው። ይህ የግቦች ሁሉ ግብ (Goal of Goals) ነው። ስለዚህ ከዚህ ጠንካራ መሰረት ላይ (ምድራዊ ተልኳችን ላይ) የህይወት ግባችን ይገነባል።

5.3 የግቦች ግብ (The Goal of Goals)- The A Goal

ምድር ላይ ስማቸው የገነነ ስብዕናዎችን ታሪክ ስታገላብጥ አንድ መሰረታዊ ልማድ (Habit) አላቸው። ሁሉም ምድር ላይ ሊያሳኩት ሊጥሩለት፣ ሙሉ ጊዜያቸውን የሰውለት ግብ ነበራቸው።

"የዓለም ቁጥር አንድ ሀብታም መሆን አለብኝ" ብለው ተነስተው በጥረት ተሳክቶላቸዋል፣ አንቱታን የተቸረው ቁጥር አንድ ስፓርተኛ ለመሆን ጥረው የአላማቸው ጥግ ላይ ደርሰዋል፣ አውቅ አርቲስት ለመሆን አልመው ኢላማቸውን መተዋል፣ ታዋቂ ሰው ለመሆን ባደረጉት ጥረት የዝና ማማ ላይ ወጥተዋል፣ ሌት ተቀን ማሰነውና ጠላት ከሚሉት ሀይል ጋር ተፋልመው የጠላትን ጦር ደምስሰው ሀገራትን ተቆጣጥረዋል፣አውቅ ፀሀፊና ገጣሚ መሆን አለብን የሚል የህይወት ግብ አውጥተው በጥረት ተሳክቶላቸዋል፣ በፓለቲካው ምህዳር ላይ ለአመታት በመታገል ህዝባዊ ምርጫን አሸንፈው ወደ ቋመጡለት ዙፋን ወጥተዋል... እነዚህ ታላላቅ ሰዎች ለቀረፁት አላማ በመኖር አላማቸውን አሳክተው በታሪክ መዝገብ ላይ በደማቁ ሰፍረዋል።

ነገር ግን ለአንድ ሁለንተናዊ ስኬት ለሚያልም ሰው ይህ በቂ አይደለም። ከላይ የጠቀስናቸው ምድራዊ ግቦች ከተፈጠርንበት መሰረታዊ ግብ (የፈጣሪን ውዴታ ማግኘት) ጋር መጣጣምና ለዋናው ግቡ ግብነት መሆን ይኖርባቸዋል።

ቆይ አንዴ እድል ስጠኝና ሀሳቤን በደንብ ለማብራራት ልሞክር። እንበልና የዓለም ቁጥር አንድ ሀብታም መሆን አለብኝ ብለህ የህይወት ግብ አውጥተሃል፣ ይህ መልካም ነገር ነው። ነገር ግን አንድ ሌላ ነገር ይቀርሀል። ከዋናው የመፈጠር አላማህ ጋር አላስተሳሰርከውም። እራስህን አስክትስህ አንድ ጥያቄ ልትጠይቀው ይገባል። ለምንድነው ቁጥር አንድ ሀብታም መሆን የምፈልገው? መልሱም:- ራሴንንና ቤተሰቤን ጥሩ ኑሮ ላኖራቸው፣ ሀገሬን ላለማ፣ ችግርተኞችንና ድሆችን ልረዳ፣ የእምነት ተቋማትን ልገነባ... ይህንም በማድረጌ የፈጣሪዬን ውዴታ ላተርፍ... አሁን የተሟላ ግብ ቀርፀሀል ማለት ነው።

ሌላ ልጨምርላችሁ። ታዋቂ ፀሀፊና ገጣሚ የመሆን ግብ ቀርፀሀል እንበል። ግን ለምን ታዋቂ ደራሲ ለመሆን ፈለክ? አንቱታና ክብርን ለው

ሁሉ እንዲቸርህ? ዓለም እንዲያደንቅህ? ከመፅሀፍ ሽያጮችህ ጸሃፌ ያሰ ኝ ለማግኘት?... ይህ ያልተሟላ ግብ ነው። ታዋቂ ያሬሲ በመሆን እጣ አደርጋለሁ፣ በዚህ ምክንያት ያገኘሁትን መልካም የሆ ዓለም ላይ በጎ ነገር ለማድረግ እጠቀምበታለሁ... በዚህ ስራዬ የፈጣሪዬን ውዴታ አኛለሁ ስትል... አሁን የተሟላ ግብ ቀረፅክ ማለት ነው።

"ለአንድ ሙስሊም ሁሉም ምድራዊ ግቦች መዲረሻ (Means) እንጂ መድረሻ አይደሉም"። እነዚህ ምድራዊ ግቦች ሲላ መሰረታዊ የተፈጠርንበትን ዋና ግብ ሊያገለግሉ ይገባል። ምንም አይነት የህያወት ግብ ስንቀርፅ "ይህን በማድረጌ የአለማትን ጌታ ውዴታ ላገኝበት" ከሚለው መሰረታዊ ሀረግ ጋር ልናዋህደው ይገባል።

ዓለም ላይ ያለፉ ታላላቅ ሰዎች አብዛኛዎቹ ግቦች ነበራቸው። ነገር ግን የግቦች ግብ አልነበራቸውም። ምድርን መሻገር ያልቻለ፣ ሮድራዊ ቆይታ ብቻ የታጠረ፣ በሞት የሚጠናቀቅ... ግብ ነው የነበራቸው።[ሠ]

"Effective people have goals, where as, great personalities have a goal of goals"

"ስኬታማ ሰዎች ግቦች አሏቸው። ነገር ግን ታላላቅ ስብዕናዎች የግቦች ግብ አላቸው።" ... የሚለው አባባል ገሸር ይመስለኛል።

ሁለንተናችንን የአለማትን ፈጣሪ ውዴታ በማግኘት ላይ ልናፈሰው ይገባል። ሙሉ ተሰጥኦዎቻችንን አንዱንና ብቸኛውን ጌታ በማገልገል ላይ ማዋል ይኖርብናል።

ቃሩን (Korah)

ቁርዓን ውስጥ ቃሩን[ሠ] ስለተባለ ባለፀጋ አላህ ይተርክልናል። ግለሰቡም

[ሠ] በአርግጥ የእነዚህን ሰዎች የስኬት ጉዞ በዚህ መፅሀፍ ውስጥ በአፋት ተጫኗል። ዋኔ ተኖር እንደምታገኝበትም እምታለሁ። አንተ የምደራዊ ስኬታቸውን እንደአስተምህሮት መከተል ልኖው ግብህ አጋሯ ታደርገዋለህ በሚል ተስፋ ነው።

[ሠ] የነብዩ ሙሳ የአጎት ልጅ ነው። በርካታ ሀብትና ለቀጥር የሚታክቱ ደልቦች ተሰጥቶት ነበር። የሀብቱ መጠን ስፍር ቁጥር አልነበረውም። የገምጃ ቤቶና የካዝናዎቹን ቁልፍ የሀያል ዓለፈቶች የሆኑ ጭፍሮች (ጉልበታም የሆኑ ጋርዶች) ሊሸከሙት የሚከብዳቸው ያህል ነበር። ቁልፎቹን መክፈት ሰብዙ ሰራተኞች የማይቻል ከሆነ ሀብቱ ምን ያህል እንደሆነ አስቡት። እነዚያ የሀይሎት አላማቸው ግልፅ የሆነላቸው ወገኖቹ ይህን ፀጋ የቀባቸን አለም ስኬት በማትረፍ ላይ እንዲሰውለው መከሩት። ይህን ምድራዊ ስኬት (ሀብት) ለቀባቸ ዓለም ስኬት ግብዓት እንዲሆኖርገው አሰታወሱት... ነገር ግን አልተቀበላቸውም።

ከፈጣሪ ትዕዛዝ ያፈነገጠ ስለነበረ ወገኖቹና የሙሳ ተከታዮች ምክር ሰግሰውታል። ጌታ የሰጠውን ፀጋ የቀጣዩን ዓለም ስኬት ማግኛ እንዲያደርገው ጠቁመውታል። ቁርኣን እንዲህ አስፍሮታል፦

"አላህም በሰጠህ ፀጋ የመጪረሻይቱን አገር (የቀጣዩን ዓለም) ፈልግ፣ ከቅርቢቱም ዓለም ፋንታህን (ድርሻህን) አትርሳ፣ አላህም ወደ አንተ መልካምን እንዳደረገልህ (ለሰዎች) መልካምን አድርግ፣ በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ፣ አላህ አጥፊዎችን አይወድምና" (አሉት ህዝቦቹ)::[62]

ትልቅ ምክር ነበር የለገሱት። አላህ በሰጠህ ፀጋ የመጪረሻይቱን ዓለም ስኬት ፈልግበት። የሰጠህን ችሮታ የዓለማትን ጌታ ውዴታ በማግኘት ላይ አሰልፍና... በዚህች ምድር ድሎትና ክብር፣ በቀጣዩ ዓለም ልቅናና ስኬትን ተቆናጠጥ። የሁለት ዓለም ስኬትን የግልህ አድርግ።

አላህም መልካምን ነገር ለአንተ እንዳደረገልህ ሁሉ አንተም (ለሰው ልጆች፣ ለሀገርህ፣ ለዓለም) መልካምን አድርግ። የበጎ ስራ አሻራህ አህጉራትንና ክ/ዘመናትን ተሻግሮ ያብራ፣ የደግነት ዝናህ ትውልድን ተሻግሮ ያስተጋባ። "በምድር ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ"፣ ገንዘብህን ለጥፋት አትጠቀምበት። የሰው ልጆችን ስብእና በማርከስ ላይ ኢንቨስት አታድርገው... አላህ አጥፊዎችን አይወድምና።

በአርግጥ ቃሩን (Korah) ይህን የህዝቦቹንና የወገኖቹን ምክር ለመቀበል ዝግጁ አልነበረም። የደረሰበት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ስኬት የሰዋዊ ጥበቡ ውጤት እንደሆነ በማሰብ ተመላደቀ፣ ለቀረበለትም ጥሪ አሻፈረኝ አለ። አላህም ምድር ከነሙሉ መኖሪያው እንድትውጠው አደረገ። ቃሩን (Korah) የወገኖቹን ምክር ሰምቶ ቢሆን ናሮ የሁለት አለም ስኬትን

[62] ቁርኣን 28:77

ምንኛ ያማረ ምክር ነበር የለገሱት፡- "አላህም በስጠህ ፀጋ የመጨረሻይቱን አገር (የቀጣዩን ዓለም) ስኬት ፈልግበት።" አም ለቀጣዩ ዓለም ስኬት ግብአት ያልሆነ ስኬት ቁንፅል ስኬት ነው፤ ያልተሟላ ግብ ነው። ስለዚህ የምንቀርፃቸው ግቦች ለዋናው ግባችን ግብአት መሆናቸውን ልብ ልንል ይገባል።

እስኪ አሁን ውዷ እህቴን በቀጥታ ልጠይቅሽ "ለምን ትወልጃለሽ?"... በልጆችሽ ለመደሰት?፤ አይንሽ የሚያርፍባቸው ተተኪዎችን ለማግኘት?፤ ወራሽ ለማዘጋጀት?፤ ግርማና ክብር እንዲሆኑሽ?፤ አብረውሽ አደባባይ የሚታዩ አበቦች እንዲሆኑ?...። ይህን ካልሽ በእርግጥ አልተሳሳትሽም። ነገር ግን ይህ የተሟላ ግብ አይደለም። ይህ ምድር ላይ ብቻ የሚቆም ግብ ነው። ነገር ግን ልጆችን የምወልደው (ከላይ የጠቀስናቸው ምድራዊ ቱሩፋታቸው እንዳለ ሆኖ)... በጥሩ ስነምግባር ኮትኩቼ በማሳደግ ለራሳቸው፤ ለቤተሰባቸው፤ ለሀገራቸው ለእምነታቸው፤ ለሰው ልጆች ሁሉ... መልካም ነገር የሚያበረክቱ አድርጌ ልኮተኩታቸው፤ ይህን በማድረጌ የጌታዬን ውዴታ ላገኝበት... ብለሽ ትልቅ ግብ ካወጣሽ፤ የሁለት ዓለም ትርፍ አገኘሽ ማለት ነው። የግቦችን ግብ ተቆናጠጥሽ ማለት ነው።

ሁሉንም ለአለማት ፈጣሪ አድርግ

መለኮታዊው መመሪያ ሁለንተናችንን ለዓለማቱ ፈጣሪ እንድናደርግ ያዘናል። ሀይማኖታዊ ክንዋኔዎቻችን (ሰላት፤ ፆም፤ ምፅዋት...)፤ ትዳራችን፤ስራችን፤ ህይወታችን፤ ሞታችን... ሁሉም እርሱ በፈቀደውና የእርሱን ውዴታ በምናገኝበት መንገድ ላይ ማድረግ እንዳለብን ቁርዓን እንዲህ ሲል ያዘናል፡-

"ሰግደቴ፣ መገዛቴም፣ ህይወቴም፣ ሞቴም፣ ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው።" በል[63]።

ሁሉ ነገራችንን ለዩኒቨርሱ አስገኚ ማድረግ ይኖርብናል። የምናወጣቸው ግቦች ሁሉ የእርሱን ውዴታ በማግኘት ላይ ልናውላቸው ይገባል። አም! ስግደትህ፤ ጋብቻህ፤ መማርህ፤ መስራትህ፤ ገንዘብህ፤

[63] ቁርአን ም. 6 ቁጥር-162

ልጄ... ሁሉም መዳረሻ ግቦች ናቸው። ሁሉም የዓለማትን ፈጣሪ ውዴታ ለማግኘት የምትጠቀማቸው ጥሬ እቃዎች ናቸው። በራሳቸው የተሟሉ ግቦች አይደሉም።

ያወጣኸውን የህይወት አላማ ለማሳካት ሌት ተቀን መጣር ይኖርብሃል። የደረስክበትንም ምድራዊ ስኬት በደንብ አጣጥመህ ልትኖረው ይገባል። ነገር ግን የሁለት ሀገር ትርፍ እንድታገኝ ከዋናው ግብህ (The goal of Goals) ጋር ማዛመዱን አትርሳ።

ትጋትን ይለማመዱ

ምድራዊ ግቦች ለዋናው ግባችን (ለቀጣዩ ዓለም ስኬት) ግብአት ነው ብሎ ማሰብ ትጋትን ይለግሳል። እስኪ አስቡት ወደ ስኬታማ ምድራዊ ህይወት (ገንዘብ፣ እውቀት...) የምናደርገው እርምጃ ኢባዳ (አምልኮ) ነው፣ ለቀጣዩ ዓለም ስኬትም ግብዓት ነው ብሎ የሚያስብ ሰው ምን ያህል ታታሪና ደስተኛ እንደሚሆን።

እያንዳንዱ የህይወት እርምጃው ወደ አለማቱ ጌታ እንደሚያቀርበው የሚያስብ ሰው ነገሮችን በትጋት ያከናውናል። የቀረፅኩት አላማ ኢባዳ ነው፣ ከምድራዊ ዓለም ጎን ለጎን ለቀጣዩ ደዓለም ይጠቅመኛል፣ በህይወቴ ከማገኘው ስኬት በተጨማሪ የጌታዬን ውዴታ አገኝበታለሁ ብሎ የሚያስብ ሰው.... ምን ያህል ትጉና ታታሪ ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም።

"To aim to be a great person is a goal but, to attain the love of the Almighty by being great is the goal of goals"

"ታላቅ ሰው ለመሆን ማለም ግብ ነው። ነገር ግን ታላቅ ሰው በመሆን የዓለማትን ጌታ ውዴታ ለማግኘት ማለም የግቦች ግብ ነው።" በሚለው አባባል ሀሳባችንን ብንቋጨውስ?

ስለዚህ እውቀትህን፣ የስራ ድርሻህን፣ ስልጣንህን፣ ዝናህን... ሁሉንም የአላህን ውዴታ በማግኘት ላይ አውላቸው። የህይወት አላማህን ስትቀርፅ ዋናውን ግብህን አትርሳ።

5.4 ወደ መነሻችን ስንመለስ

የህይወት ግባችንን ስናስቀምጥ ከተፈጠርንበት አብይ ምክንያት በመነሳት ሊሆን እንደሚገባን ተመልክተናል። ምድራዊ ግቦችን ስንቀርፅ ቀናውንና ሰማያዊ ግባችንን መርሳት የለብንም ስንል በስፋት አይተናል። የዓለማቱን ፈጣሪ ውዴታ ለማግኘት መንቀሳቀስ የግቦቹ ሁሉ ግብ (The goal of goals) መሆኑን በስፋት ተመልክተናል። እንደ አንድ ሀገሩ እንደምታሳስበው ዜጋ ምድር ላይ ብቻ የሚጠናቀቅ፣ ቱሩፋቱ ወደ ቀጣዩ ዓለም የማይሻገር፣ በምድራዊ ቆይታችን ብቻ የሚቋጨ አልያም ከሞትን በኋላ ዝናን ብቻ የሚያተርፍልን ግብ ማውጣት እንደማይመጥነን ተወያይተናል። የምንቀርፃቸው ምድራዊ ግቦች (ሀብት፣ እውቀት፣ ...) ሁሉም የፈጣሪን ውዴታ ለማግኘት፣የቀጣዩን ዓለም ስኬት ለመቆናጠጥ ጥሬ እቃዎች ሊሆኑ ይገባል ስንል ጠቁመናል። እንዲህ ብሎ ማሰቡ (ምድራዊ ግቦች ለቀጣዩ ዓለም ስኬት ግብአት ናቸው ብሎ ማሰቡ) የበለጠ ትጋት እንደሚሰጠንም አትተናል።

አም ፈላስፋዎቹ፣ ሳይንቲስቶቹ እንዲሁም አንቱታን የተቸሩ ታላላቅ ሰዎች ለምን እንደተፈጠሩ፣ለምን እንደሚኖሩ፣ ወደ የት እንደሚሄዱ፣ ከሞት በኋላ ምን እንደሚገጥማቸው... አብዛኛዎቹ ሳይረዱ አልፈዋል። ቢሆንም አብዛኛዎቹ "በምድር ላይ ልናሳካ ይገባናል::" የሚሉትን ግብ ቀርፀውና እልህ አስጨራሽ ትግል አድርገው የዝና ማማ ላይ ወጥተዋል። በህይወት እያሉ ላቅ ያለን ክብር፣ ሀብት፣ ዝናን ተጎናፅፈዋል። ከሞቱም በኋላ ሚዲያዎች ስለእነሱ በስፋት ለፍፈዋል። ጎዳናዎች፣ የጥናት ማዕከሎች፣ የሽልማት መጠሪያዎች.... በስማቸው ተሰይመዋል።

በምድራዊ ስኬቶች ብቻ መወሰን ግን አንተን አይመጥንህም። ከሞት በኋላ የቀብር ስነስርዓቱ ላይ ታላቅነቱ የሚነበብለት ሰው ብቻ ለመሆን ማለም ትልቅ ቁም ነገር አይደለም። አንተ ከዚህ የተሻልክ ነህ። አም! እነዚህ ጫማዎችና ሱሪዎች ላንተ አይበቁህም። ልክህም አይደሉም። አንተ ከዚህ የገዘፍክ፣ ከዚህ ለተሻለ አላማ የተፈጠርክ ነህና።

በህይወት ቆይታህ ልታሳካቸው የምትፈልጋቸው አላማዎችህ የቀጣዩንና የዘልአለማዊውን ህይወት ስኬት የሚያስገኙልህ ሊሆኑ ይገባል። ምድርን የሚያልፍ፣መቃብሮችን የሚሻገር አላማ ሊኖርህ የግድ ነው። እውነተኛው ስኬት የመጭው አለም ስኬት ነውና።

"_ ይህም እርሱ ታላቅ በኪት ነው።"[1]

የህይወት አላማችንን ከምንቀርፅባቸው መስረቶች አንዱና ዋነኛው፤ ከተፈጠርንበት አላማ አንፃር ሲሆን እንደሚገባው በስፋት ለይተናል። በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ ሁለተኛው መስረት ላይ ሰፊ ዳሰሳ እናደርጋለን....።

[1] አል-ተውባ - 9:111

6

ምዕራፍ ስድስት



መሆን ከምንፈልገው አንጻር

- መሆን የምንፈልገውን ነገር ማወቂያ መንገዶች
- ከመወሰንህ በፊት
- አንተ ራስህን ምን ላይ ማግኘት ትፈልጋለህ?
- አቡ ሐኒፋ የትምህርት መሰከ እንዴት መረጡ?

6

ምዕራፍ ሰድስት



መሆን ከምንፈልገው አንጻር

- መሆን የምንፈልገውን ነገር ማወቂያ መንገዶች
- ከመወሰንህ በፊት
- አንተ ራስህን ምን ላይ ማግኘት ትፈልጋለህ?
- አቡ ሐኒፋ የትምህርት መሰከ እንዴት መረጡ?

መሆን ከምንፈልገው አንፃር

ተስፖእን ያማከለ የህይወት ግብ ለከፍተኛ ስኬት እንደሚያነሳሳ ተመልክተናል። የህይወት ግባችን ከተፈጠርንበት መሰረታዊ አላማ አንፃር መቃኘት እንዳለበትም በስፋት አይተናል። ምድራዊ ግቦች ለተፈጠርንበት መሰረታዊ አላማ መዳረሻ (means) እንጂ መድረሻ (final destination) እንዳልሆኑም አትተናል። አሁን ደግሞ ሌላ መሰረታዊ ነጥብ እንዳስሳለን።

የህይወት አላማን ስንቀርፅ መሆን ከምንፈልገው አንፃር ሊሆን ይገባል። እያንዳንዱ ሰው መሆን የሚፈልገው ነገር አለው። ለወደፊት ራሱን ሆኖ ማየት የሚመኘው ነገር ውስጡ አለ። አንተ ምን መሆን ትፈልጋለህ? ምድር ላይ ምንን አላክተህ ማለፍ ታልማለህ?።

አሁን ውስጥህ አንድ ነገር እየተመላለሰ እንደሆነ እገምታለሁ። አዎ መሆን የምትፈልገውን ነገር በትክክል የምታውቅበትን መንገድ እያስተነተንክ ነው አይደል? ግድ የለም አንዴ ታገለኝ መንገዱን ልመራህ እሞክራለሁ። መሆን የምትፈልገውን ነገር በግልፅ እንዲታይህ ጎዳናውን እጠቁምሃለሁ።

6.1 መሆን የምንፈልገውን ነገር ማወቂያ መንገዶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች አራስህን ጠይቅ። በደንብ አስተንትናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስህን ወረቀት ላይ አስፍር። በትክክል ለወደፊት መሆን የምትፈልገውን ነገር ለመረዳት በጣም ያግዙሃል ብዬ አስባለሁ።

1) በህይወትህ እንደ ሞዴል የምታየው ሰው ማን ነው? ለምን የምታደንቀው ይመስልሃል? እንደሱ አይነት ለመሆን በአርግጥ ትመኛለህ?

1. _____

2. _____

3. _____

2) በርካታ መፅሀፍ የሚኖሩበት መፅሀፍ መደብር ውስጥ ብትገባ የትኞችን መፅሀፍ ትገዛለህ? ለምን የገዛሀቸው ይመስልሃል?

1. _____

2. _____

3. _____

3) ምንም ነገር ቢያስከፍልህ እንኳን (At any cost) ለማሳካት የምትመኛቸውን ሶስት ነገሮችን በዝርዝር አስፍራቸው።

1. _____

2. _____

3. _____

4) የዓለማትን ፈጣሪ አንድ ነገር ጠይቀኸው፣ እርሱም ወዲያውኑ የሚሰጥህ ቢሆን ምንን ትጠይቀዋለህ?

1. _____

2. _____

3. _____

5) በህይወትህ ትልቅ ቦታ (ትልቅ ዋጋ) ከምትሰጣቸው ነገሮች (core values) ሶስቱን ጥቀስ።

1. _____

2. _____

3. _____

6) ከአስር ዓመት በኋላ በቴሌቪዥን እንግዳ ሆነህ ተጋብዘህ ቀርበህል እንበል፤ ጋዜጠኛው አንተን ምን ብሎ ቢያስተዋውቅህ ነው ደስ የሚልህ?

1. _____

2. _____

3. _____

7) ከ 20 ዓመት በኋላ አንድ መፅሄት ከቅርብ ሰዎችህ ሶስቱን (አባትህን፤ ወንድምህንና የስራ ባልደረባህን ወይም ጓደኛህን) ስለ አንተ አስተያየት እንዲሰጡ በሚያዘጋጀው መፅሄት ላይ ቢጋብዛቸው፤ስለ አንተ ምን ብለው ቢናገር ነው ደስ የምትሰኘው?[1]

1. _____

2. _____

3. _____

8) ከአመታት በኋላ (እድሜህን ከመልካም ስራ ጋር ያርዝምልህና) ምድርን በሞት ብትሰናበት ስለ አንተ የመገናኛ ብዙሀን ምን ብለው ቢዘግቡ ትመኛለህ?

1. _____

2. _____

3. _____

ከላይ የጠቀስናቸው ነጥቦች መሆን የምታልመውን፤ በምድር ቆይታህ ማሳካት የምትፈልገውን፤ ምድርን ከተሰናበትክ በኋላ ህዝብ ስለአንተ ቢያወራ የምትመኘውን፤ በቀጣዩ ዓለም ፈጣሪ ዘንድ የተሻለ ቅርበትን

[1] እነዚህና መሰል ጥያቄዎች የውስጥ ፍላጎታችንን እንድንረዳ የሚያግዙና መሆን የምንፈልገውን ነገ ለመፈተሽ ይጠቅማሉ ተብለው በመሰኩ ምሁራን የቀረቡ ናቸው እንጂ ዝናን ስለመናፈቅ ለማውራት አይደለም::

ሚለጥህን.... ዓላማ ለመቅረፅና በተገቢው መንገድ ለመረዳት ያገዙሀል። በደንብ አስላስላቸው፤ መልሶችን በዝርዝር ፃፋቸው... ያኔ መሆን እምትፈልገው ሰው በአይነ-ህሊናህ መመልከት እንድትችል ያደርግሀል። የህይወት ግብህም ግልፅ ብሎ በተገቢው መንገድ ይታይሀል። ፍላጎታችንን በተገቢው ሁኔታ ማወቅ የስኬት መሰረት መሆኑን ልብ በል።

"ሌሎችንና ራስን ማወቅ አንድ መቶ ፍልሚያዎችን ተፋልሞ ሁሉንም ማሸነፍ እንደማለት ነው። ሌሎችን አለማወቅና ራስን ማወቅ አንዴን ፍልሚያ አሸንፎ እንደናውን ደግሞ አንደመሸነፍ ነው። ሌሎችንም ሆነ ራስን አለማወቅ ፍልሚያዎችን ሁሉ አንደመሸነፍ ነው።" Sun Tzu

6.2 ከመወሰንህ በፊት

አብዛኞቻችን በትምህርት ቤት ህይወት አልፈናል። ምናልባትም "ስወደፊት ትልቅ ስትሆን ምን መሆን ትፈልጋለህ?" ተብለን የመለስንን መልስ ሰጥተን ይሆናል። ዶክተር፤ ኢንጅነር፤ ፓይለት፤ ማናጀር፤ ሳይንቲስት... መሆን እንፈልጋለን ብለን ይሆናል። ይህ የልጅነት ምኞት ሆኖ ያልፋል። ይህን ፍላጎታችን ተከታትሎ እንዲያብብና እንዲያፈራ የሚያደርግልን ሰው ማግኘት አይቀልም። በአብዛኛው ምኞት ሆነው ያልፋሉ።

ካደግን በኋላ የከፍተኛ ትምህርታችን ለመከታተል ወደ ዩኒቨርሲቲዎች እናቀናለን። ያኔ ክባድ ፈተና ይገጥመናል። የትኛውን ፊልድ (Department) ልምረጥ? ስንል ግራ እንጋባለን... በመጨረሻም ነደኖቻችን የመረጡትን ፊልድ እንመርጣለን። አልያም ፍላጎታችንን ያላገናዘበ መስክ (ፊልድ) መርጠን ለአመታት በወደቀ ሞራል ትምህርታችንን እንከታለን። ታዲያ የትምህርት መስክህን ከመወሰንህ በፊት ውስጥህን ልታዳምጠው ይገባል። በየትኛው የትምህርት መስክ (ፊልድ) ነው መሰማራት የምትመኘው? ምን መሆን ትፈልጋለህ?

በአብዛኛው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከተመረቁ በኋላ፣ በዚህ የትምህርት መስክ (ፊልድ) መማር አልነበረብኝም ሲሉ ይደመጣሉ። እንዴ

* በዚህ ዙርያ የበለጠ ለመረዳት "ህይወት ግብ ለሌለው" የሚለውን ክፍል በደንብ ተመልከተት ልጆችን እንዴት ከልጅነት ደምረን ልክታቸዉና የህይወት ግብ እንዲኖረው ልናደርጉው እንደሚገባ ቴክኒኮችን ያስጨብጠናል። (ምዕራፍ - 8)

በኢንጅነሪንግ የተመረቀ ወንድሜ "እኔኮ ኢንጅነሪንግ ማጥናት አልነበረብኝም::" ማለቱን ሰምቻለሁ:: በቅርብም እንደማውቀው አብዛኛውን ህይወቱን የገፋው በቤተሰቡ የህትመት ካምፓኒ ውስጥ የስራ ሀላፊ ሆኖ ነበር:: የሁለተኛ ድግሪውንም በማኔጅመንት ላይ እንደተማረ አስታውሳለሁ::

6.3 አንተ ራስህን ምን ላይ ማግኘት ትፈልጋለህ?

2002 መጀመሪያ አካባቢ "የህይወት ግብህን አስምር" የሚል ትምህርት ለህዝብ ለቅቄ ነበር:: በተመሳሳይ 2003 ላይ "የት እየሄድክ ነው?" የሚል ተመሳሳይ ትምህርት ዱባይ ላይ አስተምሬ ነበር::[67]

ይህን ፕሮግራም የተከታተሉ ወጣቶች የተለያዩ ጥያቄዎችን ያቀርቡልኝ ነበር:: አንዳንዶቹ "እንደዚህ መሆን እንፈልጋለን::" እያሉ ሀሳባቸውን በስልክ፣ በፅሁፍ፣ በግጥም ይልኩልኝ ነበር:: የህይወት ግቡን በግጥም ከሸኖ የላከልኝን ወጣት በቀጣዩ ምዕራፍ ከነግጥሙ አስነብባችኋለሁ::

ትምህርቱን ለተከታተሉ አብዛኛው ህዝብ ቆም ብለው እራሳቸውን እንዲጠይቁ እድል የሰጠ እንደነበር አገምታለሁ:: ልክ አሁን አንተ ይህን መፅሀፍ ስታነብ የተሰማህን አይነት እንግዳ ስሜት ፈጥሮባቸው ነበር:: የህይወት ግቤ ምንድነው? ለወደፊት ምን መሆን እፈልጋለሁ? ሲሉ እራሳቸውን እንደጠየቁ አጫውተውኛል:: በዚህ የተነሳ በርካታ መልዕክቶችና አስተያየቶችን ተቀብያለሁ:: በትንሿ አቀሜም ምክሬን ሰግሻለሁ:: (ያው ጋኖች ሲጠፉ ምንቸቶች ጋን ይሆናሉ አይደል ሚባለው)

ይህ ጥያቄ ከታሰርኩም በኋላ ከሸቦ ጀርባ ሊጎበኙን ከሚመጡ ወጣቶች አልፎ አልፎ ይቀርብ ነበር:: አንዱ በትምህርቱ በጣም ጥሩ ውጤት ያመጣ ተማሪ "የትኛውን የትምህርት መስክ እንድማር ትመክረኛለህ?" ብሎ ጠየቀኝ:: ልጁ ጥሩ ውጤት አምጥቶ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት እየተሰናዳ የነበረበት ወቅት ነው:: እኔም ካሉን ወደ አርሱ መልሼ ከራሱ ሜዳ ላይ አጫወትኩት:: 'አንተ ለወደፊት ምን መሆን ትፈልጋለህ?' ስል እራሱን እንዲያዳምጥና ውስጣዊ ፍላጎቱን እንዲፈትሽ እድል ሰጠሁት::

[67] ትምህርቶች በCD፣DVD፣AUDIO CD፣በ MEMORY CARDS በቴፕ ካሉቶች ወደ ህዝብ በስፋት ተሰራጭተው ነበር:: www.yassinnuru.com

እራሱን እያወላወለና እየተቅለሰለሰ በፈገግታ ምንም ነገር እንዳልወሰነ ገለፀልኝ። የበለጠ ግልፅ እንዲሆንለት የተወሰኑ ጥያቄዎችን ጠየኩት። ለወደፊት የሚመርጠውን የትምህርት መስክ ለመለየት እንዲችል እንዲህ አልኩት፡- "አንተ ለወደፊት ራስህን ምን ላይ ማግኘት ታልማለህ? ታዋቂ የህግ ባለሙያ ሆነህ፣ ጥቁር ጋወን ለብሰህ፣ ለፍትህ መሰፈን የምትሟገት ሰው መሆን ትፈልጋለህ? ወይስ ቀና ብለህ የምትመለከተው ሰማይ ጠቀስ ፎቅ የነባ ታዋቂ መሀንዲስ መሆን ነው የምትመኘው? ወይስ ደግሞ የበርካታ ህመማንን ህይወት የሚታደግ (በአላህ ፍቃድ) እውቅ ዶክተር መሆንን ነው ውስጥህ የሚነግርህ? ወይስ ደግሞ ድርጅቱን ለትልቅ ትርፋማነት ያበቃ እውቅ ማኔጀር መሆን ነው የምትመኘው?... የተለያዩ ጥያቄዎችን አከታትዬ ጠየኩት። አሁንም መልስ አልሰጠኝም በፈገግታ እንደተዋጠ እራሱን እያወላወለ ይመለከተኝ ይሄል። እነዚህን ጥያቄዎች ውስው እያመላለሰ እንደሆነ ገምቻለሁ። በውስጥ ኮምፓሱ የህይወት ጥሪውን (True north) እየፈለገ እንደነበር ለጋ ፊቱ ያሳብቅበታል። ብቻ ይህን ጥያቄ ወዲያውኑ እንደማይመልሰው ስለገመትኩ፤ ውስጡን በመጠየቅ ምርጫውን እንዲወስን ሀሳቤን ለግሼ ተሰናበትኩት።

በተመሳሳይ በትምህርቱ አራት ነጥብ ያመጣ ወጣት ተመሳሳይ ምክር ለግሼዋለሁ። ተሰጥኦውንና ፍላጎቱን ያማከለ መስክ እንዲመርጥ ጠቁሜዋለሁ። "ጋዜጠኛ መሆን እፈልጋለሁ ምን ትመክረኛለህ?" ብሎ ለጠየቀኝም ወጣት ተመሳሳይ ሀሳቦችን ሰጥቻዋለሁ[88] ። ለትክክለኛና ለአመርቂ ስኬት እንድንበቃ በምንወደው የህይወት መስክ መሰማራት ግድ ይለናል።

"ከልብ በምንፈልገውና በምንወደው ተግባር ላይ ስንሰማራ ውጤታማነታችን በጣም የጎላ ነው።" ጀርጅ ግሪተር

ከዛሬ በኋላ አልቀጥልም!

አብዛኞቻችን ሳናስበው አልያም በጓደኞቻችን ፍላጎት ወይም የምንመርጠውን የትምህርት መስክ ካለማግኘት አንፃር (በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ደሀ ሀገራት) በምንመርጠው ፊልድ መማር የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ያጋጥማሉ። እንዳንድ ተማሪዎች ተገደው

[88] እነዚህና መሰል ጥያቄዎች ይህን መፅሀፍ እንዲፅፍ መንስኤ ሆነውኛል።

በማይፈልጉት መስክ እንደገቡ አውቃለሁ። ለበርካታ አመታት በማይወዱትና ተስፋአምቻቸው ባልሆነ መስክ ላይ ይሰማራሉ።

ዶ/ር ጢሪቅ ስወይዳን እውቅ ሰባኪ፣ በማኔጅመንትና በሊደርሺፕ መስክ ላይ አንቱታን የተቸሩ አሰልጣኝ፣ እንዲሁም የበርካታ መፅሀፍት ደራሲ ናቸው። ይክትሬት ዲግሪያቸውን በነዳጅ ምህንድስና (Petroleum Engineering) አሜሪካ ከሚገኝ አንድ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል። ነገር ግን ይህ አመታት ሀገራቸውን ጥለው በስደት የተከታተሉት የትምህርት መስክ የማይወዱትና መሆን የማይፈልጉት፣ እንዲሁም ከተስፋአቸው ጋር እንደማይሄድ ተገነዘቡ። በሚማሩት ትምህርት የመጨረሻ አመት ላይ የገጠማቸውን እንዲህ ሲሉ ያጫውቱናል፡- "የሶስተኛ ድግሪዬን በምከታተልበት የመጨረሻ አመት ላይ ይህ የትምህርት መስክ ፍላጎቴ እንዳልሆነ ተረዳሁ። በዚህ መስክ ላይ የመማሬት ወኔ አጣሁ። ክፍል ውስጥ ትምህርት እየተከታተልኩ ተቀምጬ ባለሁበት ለራሴ እንዲህ ስል ቃል ገባሁ፡- "ከዛሬ በኋላ ይህ ክላስ (የትምህርት ክፍል) ከተለመ ትምህርቴን አተዋለሁ"። በዚህ ውሳኔዬም ቁርጠኛ ነበርኩ። በጣም የሚገርመው ይህች ቀን ትምህርት የምናጠናቅቅበት የመጨረሻ ቀን ነበረች[69] ።

ዶ/ር ጢሪቅ ከዚህ በኋላ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እየገቡ የማኔጅመንትና የሊደርሺፕ ኮርሶችን መከታተል ጀመሩ። ይህን ትምህርት የሚከታተሉት ሲመረቁበት አልነበረም። ትምህርት ቤቱም በዚህ ፊልድ አልመደባቸውም። ብቻ ኮርሱ አለ በተባለበት ክፍል እየገቡ በርካታ ትምህርቶችን ተከታተሉ። "በነዳጅ ምህንድስና (Petroleum Engineering) ከወሰድኳቸው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በላይ በማኔጅመንቱ መስክ የወሰድኳቸው ኮርሶች በቁጥር ይበልጡ ነበር።" ይላሉ። አምላክ ከፍላጎትህ ጋር ትምህርትህ ሲዋሀድ በፍቅር ትማረዋለህ።

በአሁኑ ሰዓት ዶ/ር ጢሪቅ ዓለም ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሚባሉ ግለሰቦች አንዱ ናቸው። በማኔጅመንትና በሊደርሺፕ መስክ የበርካታ ሀገራት ሚኒስትሮችን አሰልጥነዋል። ወጣቱን ትውልድም በሊደርሺፕ መስክ ላይ በስፋት በማሰልጠን ላይ ናቸው። በበርካታ አልበሞቻቸውና በሳተላይት ቴሌቪዝን የሚሰጧቸው ትምህርቶች የበርካታ ሰዎችን ህይወት

[69] ዶ/ር ጢሪቅ ስወይዳን - እንዳዲል ቃላህ - /Making Leaders/

ለውጠዋል። እኔ ራሴ ከ200 በላይ ትምህርታቸውን ተከታትያለሁ። ህይወቴ ላይ አወንታዊ ተፅዕኖ ከፈጠሩ ግለሰቦች ውስጥ አንዱ ናቸው።

6.4 አቡ ሐኒፋ የትምህርት መስክ እንዴት መረጡ?

ታላቁ ሊቅ አቡ ሐኒፋ በለጋ ወጣትነታቸው የተዋጣላቸው ነጋዴ ነበሩ። ብልጠቱንና አስተዋይነቱን የተመለከቱ ሽዕቢ የሚባሉ ትልቅ ሊቅ በሕውቀት ዘርፍ ቢሰማሩ የተሻለ እንደሆነ መከሯቸው። ምክራቸው ውስጣቸው ጠልቆ ገባ። ከዚያም አቡ ሐኒፋ እንደ ታላቁ ምሁር ሽዕቢ ለመሆን ቆርጠው ተነሱ። ከኢስላም ዘርፈ ብዙ የእውቀት ወንዝም[70] ጨልፈው ለመጠጣት ወሰኑ።

ከሰፊው የኢስላም የእውቀት ማዕድ ለመገዘን ወደ ትምህርት ማእከሉች መጡ። ነገር ግን ኢስላም ዘርፈ ብዙ የእውቀት ማዕድ ነው ያለው፤ የትኛውን ይማሩ? የትኛውን ፊልድ (Department) እንደሚመርጡ ግራ ገባቸው። ምሁራኖቹን ቀርበው አያንዳንዱን ፊልድ በዝርዝር እንዲያብራሩላቸውና እነሱንም በመማሩ ምን እንደሚያገኝ ጠየቋቸው። እነሱም ሁሉንም የትምህርት ዘርፍ በዝርዝር ተነተኑለት። እርሳቸውም እያንዳንዱን የትምህርት ዘርፍ በስም እያነሳ የበለጠ ማብራሪያ ጠየቁ።

ለምሳሌ አሉ አቡ ሐኒፋ፦ ቁርአንን ብማርና ባጠና እንዲሁም ተፍሲሮችን (የቁርዓን ማብራሪያዎችን) ጠንቅቄ ባውቅ መጪረሻዬ ምን ይሆናል? ያኔማ "ቁርዓንን ታነባለህ፤ ለሀዘብ ታሳውቃለህ፤ ህፃናትን ታስተምራለህ።" አሏቸው። ከዚህስ በኋላ ምን ይሆናል? ሲሉ ጥያቄ አቀረቡ። እነሱም "ያው ስታረጅ ካንተ የተሻለ ተማሪ፤ ከአንተ የሚበልጥ ታወጣለህ።" አሏቸው። አይ ይህ ዝንባሌዬ አይደለም አሉ። እሽ ሀዲስን (የነብዙን ንግግሮች፤ ትምህርቶች፤ ትዕዛዞች... እንደማለት ነው። ከነብዩ

[70] ዶር ግሪት ሱወይዳን - ኢስላሚክ ስተዲስ - Making ኢስላም በርካታ የትምህርት ዘርፎችን ያቀፈ የህይወት መንገድ ነዉ። እነዚህ ከዘረዉ የእዉቀት ዘርፎች ዉስጥ የተወሰኑትን እንጥቀስ- 1) ቁርዓን ተፍሲር (Quran and its exegesis) 2) ፊቅህ (Islamic Jurisprudence) 3) ነህዉ (Arabic Grammar and syntax) 4) ሶርፍ (Morphology) 5) Tewhid (Theology) 6) ባላጋ (rhetoric) 7)መንጢቅ (logic) 8) መኻኒ (prosody) 9) በያን (eloquence) 10) በዲዕ (The science of Metaphors or of good style) 11) ኡሱል ኢል-ፊቅህ (The principle of law) 12) ሐዲስ (The study of the traditions of prophet Muhammed) 13) ሲራ (The legacy of the prophet Muhammed)... ምንጭ - Pro.Hussein Ahmed ,Islam in Nineteenth century wallo,Ethiopia)

የተነገሩ በሚሊየን የሚቆጠሩ ትምህርቶች በተከታዮቻቸው ተላልፏል። ይህ የኢስላም ትልቅ የአውቀት ዘርፍ ነው።) ይህን በመማሬ ምን አገኛለሁ? መጨረሻዬ ምን ይሆናል? አላቸው። ያኔማ "ሀዲስን በቃልህ ትሸመድዳለህ[71] ለምችንም ታስተምራለህ፤ ታላቅ የሀዲስ ሊቅ ትሆናለህ..." አሏቸው። ይህን እንኳ ብዙም ፍላጎቴና ዝንባሌዬ አይደለም አሉ።

አቡ ሐኒፋ አሁንም የሚወዱትን የህይወት መስክ በማፈላለግ ላይ ናቸው። ጥያቄዎችን እያቀረቡ ውስጣቸውን ማዳመጥ ቀጥለዋል። ተሰጥኦዎቸውንም መፈተሽ ይዘዋል።

ከዛም አስከትለው ስለ ስነ-ግጥም ጠየቁ። እርሱን በመማሩ ምን ላይ እንደሚደርስ ጠየቁ። "ብዙ ግጥሞችን የሸመደድክ እውቅ ገጣሚ ትሆናለህ" አሏቸው። እሺ እንበልና ብዙ ግጥሞችን በቃሌ አጠናሁ፤ ታዋቂ ገጣሚም ሆንኩ፤ ከዛ በኋላስ ምን ይሆናል? ምን እሆናለሁ? አሏቸው። እነሱም "ገንዘብ የሰጠህን በስንኝህ ታወድሰዋለህ፤ ያልሰጠህን ትወርፈዋለህ[72] አሏቸው። ከሊቆቹ የሰሟቸው ምክሮችና ሀሳቦች ሁሉ ከውስጥ ጥሪያቸው ጋር ሊዋሀድላቸው አልቻለም። ይህን ፊልድም (የትምህርት መስክም) ለማጥናት አልፈለጉም። መሆን የሚፈልጉት ይህን አይደለም።

ምሁራኖቹ ለአቡ ሐኒፋ በርካታ የአውቀት ዘርፎችን ዘረዘሩላቸው። ሁሉም የተከበሩ የትምህርት መስኮች ቢሆኑም አርሳቸውን ግን ውስጣቸውን ሊንጣቸው አልቻሉም። በመጨረሻም "ፊቅህን" (የኢስላማዊ ሸሪዐ ድንጋጌዎችንና መመሪያዎችን የሚያጠና የአውቀት መስክ...) ተማር አሏቸው። ፊቅህን ተምሬ ምን እሆናለሁ? ለህዝቤ ምን አበረክታለሁ? መጨረሻው ውጤቱ ምንድነው? ሲሉ ጠየቁ። እነሱም "ሰውን ታስተምራለህ ፤ለሰዎች የቸገራቸውን ጥያቄ ትመልስላቸዋለህ፤ ፈትዋ (ኢስላማዊ ብይን) ትሰጣለህ፤ ሀዲስና ቁርዓንን እያጣቀስክና ከተጨባጩ ጋር እያጣመድክ ለማህበረሰቡ ችግር መፍትሄ ትፈልጋለህ..." አሏቸው።

---

[71] ከሚሊዮን የሚበልጡ የጎበዙን ሀዲሶች የሸመደዱ ምሁራን በታሪክ አልፈዋል።

[72] የጎረቤን ትውልድ በንግም የሚስተካክላቸው የሰም። በተለይ በዚያን ዘመን ገጣሚዎች እደግ የተከበሩ ነበሩ። በአንድ ንግም የሚፈልጉትን ነገ ያንገላሉ፤ የጠሉትን ደንም ያረክሳሉ። ነገስታቶችም እውቅ ገጣሚዎች ነበራቸው። በጥሩ ስንኝ ያወደሳቸውን ዳጎስ ያለ ስጦታ ይሰጡት ነበር።

እቡ ሐኒፋ ልባቸው ተከፈተ፤ የተመኙትንና የሚወዱትን መስክ አገኙ። ከትክክለኛ ፍላጎታቸው ጋር የሚታረቅ የእውቀት መስክ (Department) ጋር ተዋወቁ። መጀመሪያ ሀሳቡን ወዳቀረቡለት ታላቅ ሊቅ ሻፅቢ ዘንድ ተመልሰው የፊትህን የእውቀት ዘርፍ መምረጣቸውን ነገሯቸው። ምርጫዬስ ትክክል ነው? በትክክል የምወጣው ይመስልዎታል? ሲል ጠየቋቸው። ታላቁ ሊቅ ሻፅቢም "እርሱን ነበር እኔም ላንተ ይስማማል ብዬ ያሰብኩት" ሲሉ አፀደቁላቸው።[73]

በመቀጠልም እቡ ሐኒፋ ይህን የትምህርት ዘርፍ በተገቢውና በጥራት ሊያስተምራቸው የሚችል ሰው ማፈላለግ ጀመሩ። የተለያዩ ሰዎችን ማጠያየቅ ቀጠሉ። በመጨረሻም ሀማድ አቢ ሱለይማን ከተባሉ ሊቅ ጋር ተገናኙ። ታዋቂ የፊትህ ሊቅ ነበሩ። እቡ ሀኒፋ ለ18 ዓመት ከርሳቸው ትምህርት ቤት እውቀትን አከበቱ። በተጨማሪም ከበርካታ የኢስላም ሊቃውንት ዘንድ እየሄዱ እውቀትን ቀሰሙ። ጃዕፈር አስሷዲቅ ከተባሉ ዐሊም (ሊቅ) ጋርም በርካታ እውቀትን ወሰዱ።

ከዓመታት የእውቀት ፍለጋ ልፋት በኋላ እቡ ሐኒፋ ታላቅ ሊቅ ለመሆን በቁ። በሙሉ ፍላጎት በርካታ ተማሪዎችን ሰብስበው ያስተምሩ ጀመር። በኢስላም ታሪክ ውስጥ እንቁታ ያገኘውን እና በስማቸው የተሰየመውን "የሀነፍይ መዝሀብ" (School of thought) መሰረቱ። የአስተምህሮታቸው ብቃት፤ ያተኮሩባቸው ምጥቀት፤ የእውቀታቸው ጥልቀት... እስከአሁን አምሳያ አልተገኘላቸውም። የዓለምን ታሪክ ለውጠውና ለሰው ልጆች ችግር መፍትሄዎችን አስቀምጠው አልፈዋል።[74] ላህ እቡ ሐኒፋን ይዘንላቸው።

አዎ! መሆን የምንፈልገውን ነገር ያማከለ አላማ (Goal) ለከፍተኛ ስኬት መሰረት ነው። የምንቀርፃቸው ግቦች ከፍላጎታችንና ነገ ራሳችንን ሆነን ማየት ከምንፈልገው አንፃር የተቃኙ መሆን ይኖርባቸዋል። እቡ ሐኒፋ መሆን የሚፈልጉትን ነገር በትክክል ለማግኘት ምን ያህል እንደማሰኑ አይታችኋል። የሚፈልጉትን መልስ ካገኙም በኋላ ይህን እውቀት በደንብ ሊያስጨብጧቸው የሚችሉትን ምሁራን አሳይው አግኝተዋል (ያው በዘመናችን ምርጥ ትምህርት ቤትና ዩኒቨርሲቲ

[73] ዘወቢ ሊያር አአላመንፀላል

[74] አቡ ኸዚር - አልቢዳያ ወኒሃያ. ዶር ዐምር ንሊድ- ጻዕውቱን ሊተወሽ

እንደምንለው አይነት ነው)። ለዓመታትም ከምሁራኖቹ እውቀትን ቀስመዋል።

አሁን ደግሞ አንተን ልጠይቅህ "ምን መሆን ትፈልጋለህ?" "ከዓመታት በኋላ ራስህን ምን ላይ ማግኘት ያስደስትሃል?"። መሆን የምንፈልገውን ነገር በትክክል መረዳት ይጠበቅብናል። ምክንያቱም የህይወት ግባችን የሚገነባበት መሰረታዊ መሰረት ነውና።

7

ምዕራፍ ሰባት



ግብዝ ግልፅና የተብራራ ይሁን

- ግብዝ የሰምሀን ያህል ግልፅ ይሁን
  - BMW
  - ዓለማዬ የንብዩ ሰ.ዐ.ወ. ዱዓ ነው
  - ሚስተ - አለፈ
- ግብዝ የተብራራ ይሁን

እስከ አሁን የህይወት አላማችንን ስንተርፅ ከተፈጠርንበት፣ ከተሰጥኦዎቻችን እና መሆን ከምንፈልገው አንፃር ሊሆን እንደሚገባ አይተናል። ተሰጥኦን ያማከለ አላማ ለከፍተኛ ስኬት እንደሚያበቃም ተመልክተናል። አሁን ደግሞ አላማህ ግልፅና ሰቁጥጥር በሚያመች መልኩ የተብራራ ይሁን እልፃለሁ/እልሻለሁ። ሁሌም ቢሆን የስግችን ያህል የምናውቀው፣ በዝርዝር የተብራራ፣ እንዲሁም የጊዜ ገደብ የተበጀለት መሆን ይናርቢታል።

7.1 ግብህ የስምህን/ሽን ያህል ግልፅ ይሁን

የምንተርፀው ግብ ከግልፅነቱ የተነሳ እንደስግችን የምናውቀውና ብንጠየቅ በፍጥነት የምንመልሰው ሊሆን ይገባል። ለክ "ስምህ ማን ነው?" ስትባል በፍጥነትና በቀላሉ እንደምትመልሰው ሁሉ፣ "ግብህ ምንድነ ነው?" ተብለህም ስትጠየቅ በቀላሉ ልትመልስ ይገባል። አብዛኛው ሰው "የህይወት ግብህ ምንድን ነው?" ሲባል፣ አልያም "ለወደፊት ምን መሆን ትፈልጋለህ?" ሲባል ዶክተር፣ኢንጅነር፣ ሳይንቲስት፣ማናጀር፣ፓይለት... ሲል ይመልሳል። በተለይ ይህ አባባል በልጆች ላይ ይስተዋላል። ነገር ግን አብዛኞቻችን ከአንድ በላይ ልናሳካቸው የምንፈልጋቸው አላማ ይኖሩናል። እንዲህ አይነት አላማዎች ለመግለፅ ደግሞ የአላማዎቻችን የየመጀመሪያ ፊደላት በመጣመርም መጠሪያ እናውጣላቸዋለን። ይህ የአላማችን የመጀመሪያ ፊደል በመጣመም የፈጠርነው ቃል (Acronym)[75] ሊተነተን በህይወት ቆይታችን ልናሳካ የምንፈልገውን ነገር በግልፅ ያሳየናል። እስኪ የተወሰኑትን እንመልከት፡-

7.1.1 BMW

ከላይ ርዕሱን አያችሁት? BMW ይላል። በእርግጠኝነት ወደ አዕምሯችሁ የሚመጣው ስዕል የታዋቂው BMW መኪና ምስል ነው አይደል? አም BMW የዘነጋው መኪና መጠሪያ ስም ነው። ታዲያ እንድ ጓደኛዬ ይህን መጠሪያ የህይወት ግቡን መግለጫ አድርጎታል።

---

[75] Acronym - የእንደን ነገር መጠሪያ ቃላት መነሻ ፊደሎችን በመጣመም የሚፈጠር አዲስ ቃል (Best English — Amharic Dictionary — by Daniel worku p.6)

BMW የራሱን ሰምና ወርቅ ይሟል። ሰሙ (የላይ ትርጉሙ) ምቾት፣ ፍጥንትና ጥንካሬ ያለው ውብና ውድ መኪና ሲሆን የውስጥ ትርጉሙን (ወርቁን) ደግሞ እንዲህ ይብራራል፦

B - የሚለው "ቢሊየነር" የሚለውን ቃል ይወክላል። በህይወት ቆይታው ማሳካት የሚፈልገው አንዱ ነገር እንቁታን የተቸረ ባለፀጋ መሆን ነው። ሰርቶ፣ ጥሮ ግሮ፣ ላይ ታች ወጥቶ ወርዶ በላቡ የከበረ ባለሀብት።

M - "ማሂር" የሚለውን የዐረብኛ ቃል ይወክላል። ትርጉሙም ጥልቅ አዋቂ፣ ነገርን በደምብ የተረዳ፣ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ምልከታ ያለው ማለት ነው። ስለዚህ ሁለተኛው ግቡ፣ በያዘው የትምህርት መስክ፣ የእውቀት ዘርፍ አልያ በያዘው ጉዳይ ላይ ጥሩ ግንዛቤን የያዘ፣ ነገሮችን በጥልቅ የተረዳ መሆን ነው።

W - "ወልዩላህ" - የሚለውን የዐረብኛ ቃል ይወክላል። ትርጉሙም - የአላህ ታማኝ ባሪያ፣ ደግ ሰው፣ የፈጣሪን ትዕዛዝ የሚያከብር ጥንቁቅ (Pious) ማለት ነው። ስለዚህ ከላይ ያሰፈራቸውን ሁለት መዳረሻ ግቦች ተጠቅሞ ሶስተኛውን ግብ ማሳካት ይመኛል። ያለውን ሀብትና ጥልቅ እውቀት ተጠቅሞ የፈጣሪውን ውዴታ ያገኘ ተወዳጅ ባሪያ መሆን ይፈልጋል።

7.1.2 معنّق (ሙዕተቅ)

ይህ የዚህ መፅሀፍ፡ ፀሀፊ የትርብ ወዳጅ ከንመታት በፊት የቀረፀው የህይወት ግቡ ነው። ቃሉ ሰምና ወርቅ የያዘ ነው። ምክንያትም የሰሙና የወርቁ ጭብጥ ተመጋጋቢ የሆኑበት ነው። አልያም ሰሙ የወርቁን የመጨረሻ ውጤት የሚያመላክት ነው። ግለትም የወርቁ ድምር ውጤት ሰሙን ይወልዳል። "ሙዕተቅ"- የሚለው የዐረብኛ ቃል ትርጉሙ ነፃ የወጣ ማለት ነው። አም የላይ ትርጉሙ (ሰሙ) ነፃነቱን ያወጀ ማለት ነው። ሲተነተን (ወርቁ) ደግሞ እንደሚከተለው ነው፦

የመጀመሪያዋ ፊደል " , " ሚም - ሚሊየነር ሚለውን ትወክላለች። አም፣ በትጋት ሰርቶ፣ ጥሮ ግሮ ለበጎ ነገር የሚያውለውን ፀጋ ያገበተ፣ ከሰዎች እጅ የተብቃቃ፣ ሰጭ እንጂ ተቀባይ ያልሆነ ባለፀጋ መሆን ነው አንደኛው አላማዉ ይለናል።

ሁለተኛዋ ፊደል "ع" "ዐይን"- "በሊም" ወይም አዋቂ ማለት ነው ትርጉሙ። በመረጥኩት የአነጋገሜ ይዘት የህይማኖታዊ የእውቀት ዘርፍ፣ እንቱታን የተቸርኩ ልሂቅና ሊቅ መሆን። ትውልድን የሚቀየረ በርካታ መፅሀፍትን የሚፅፍ ፣ በርካታ ትምህርቶችን የሚሰጥ፣ ግቤ ስልጠናዎችን የሚያዘጋጅ፣ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ ምሁራዊ ትንታኔዎችንና አስተያየቶችን በመስጠት የማህበረሰቡን ስብዕና የሚገነባ በበርካታ የህትመት ውጤቶች ላይ መጣጥፎችን በማስነበብ የህዝብን አመለካከት የሚቀርፅ... ምሁር (Intellectual) መሆን። ይህንም በማድረጌ ሀገሬንም ህዝቤንም አጠቅማለሁ። የጌታዬን ውዴታም አገኛበታለሁ።... ይህ ሁለተኛው ግቤ ነው ይሰኛል።

* ى * - የምትለው የዐረብኛ ቃል ደግሞ - "ተቅይ" የሚለውን ይወክላል። አላህን የሚፈራና የሚጠነቀቅ (Pious) መሆን ነው። ከሰይጣን የጠቀስኳቸው ሁለት መዳረሻ ግቦች (ሀብትና እውቀት) የተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ካልታከለባቸው ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ሊያመዝን ይችላል። በገንዘቡ ብዛትን የሚያስፋፋ ከሆነ፣ በእውቀቱ የሰውን ልጅ አመለካከት የሚያንቅዝ ፅሁፍ የሚፅፍ ከሆነ ትልቅ ኪሳራ ነው። ስለዚህ ሀብትና እውቀት ገቢተቅዋ ካልታጀቡ ትርጉም የላቸውም። በተቅዋ ልንም ካልተያዙ የሚያስከትሉት አደጋ የከፋ ነው ሊል ያስጠነቅቃል።

* ق * - የሚለው ፊደል ደግሞ "ቃኢድ" የሚለውን ዐረብኛ ቃል ይወክላል። "ቃኢድ" ተፅኖ ፈጣሪ መሪ (Influencial leader) ማለት ነው። ይህ ደግሞ አራተኛ ግቤ ነው። ነገር ግን ለእኔ ተፅኖ ፈጣሪ መሪ ማለት የፓለቲካ መሪ ብቻ ማለቱ አይደለም። መሪነት ዘርፈ ብዙ ነው። የእውቀት መሪ፣ የአስተሳሰብ ቀማሪ፣ የሰውን ልጅ ስብዕና ወደ ተሻለ ደረጃ የሚያሳድግ መሪ፣ ምድር ላይ እምነታዊ ለውጥ የሚያስገኝ የለውጥ ቀማሪ (Change-catalyst)፣ ፈርቀዳጅ የተሀድሶ ሀሳብ የሚያመነጭ መሪ (Pioneer)... ማለቱ ነው። በእጥሩ ኔሎቹ "Making a difference" እንደሚሉት፣ በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ አዲስ ለውጥ የሚያመጣ ተፅኖ ፈጣሪ መሪ መሆንን መመኘት ነው።

" I am not here just to make a living. I am here to make a difference "

"እኔ ምድር ላይ የምኖረው ለመበላትና ለመጠጣት ሳይሆን ለውጥን ለማምጣት ነው" የሚለውን አባባል ዘውትር መናገር ነው።

ለእኔ መሪነት ይህ ነው። የማህበረሰቡን አመለካከት መገራት፣ የሰውን ልጅ ወደተሻለ አስተሳሰብ ማመላከት፣ ስብእናቸውን ማነፅ፣ ለራሳቸውና ለሀገር መልካም አበርካች ዜጋ እንዲሆኑ ማገዝ... ነው ትክክለኛ መሪነት። አሁን ምድር በምትናጥበት የተሳከረ የፓለቲካ መስመር ውስጥ ገብቶ መንደፋደፍ እኔ ዘንድ ብዙም ቦታ የለውም ይለናል።

በአጭሩ ትርጉሙ (ወርቁ) ይህ ነው። ሰርቶ የከበረና ለሌሎች የስራ እድል የከፈተ ባለፀጋ፣ በመረጣቸው የእውቀት ዘርፎች ላይ በጥልቀት የተረዳ ልሂቅና ሊቅ፣ የፈጣሪውን ትዕዛዝ የሚጠብቅ ተቅይ እና በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ ለውጥን የሚያመጣ ተፅዕኖ ፈጣሪ መሪ ማለት ነው- መዕተቅ። ታዲያ ሰሙ ከወርቁ ጋር ያለውን ተዛምዶ አያችሁ? ሰሙ ነፃ የወጣ ማለት ነው። በዘህች ምድር ላይ ከድህነት፣ ከመሀይምነት፣ ከተዛባ አስተሳሰብ... ነፃ የወጣ ባሪያ መሆን ማለት ነው። ታዲያ ከላይ የተዘረዘሩት አራቱ ነጥቦች (Acronyms) ሰሙ ላመላከተው ነፃነት ምን ያህል ግብዓት እንደሆኑ ተመለከታችሁ?... አላህ እንዲያሳክለት እመኛለሁ።

7.1.3 አላማዬ የነቢዩ ﷺ ዱዓ ነው

ከዓስር ዓመት በፊት ማለትም ዘጠናዎቹ አጋማሽ አካባቢ "ጎልድ ኩዌስት" ፋሽን ሆኖ ነበር። ለማናውቀው ካምፓኒ ወርቅ ለመሸጥ ጥድፊያው ለጉድ ነበር። በስራችን ተከታዮቻችንን ለማብዛት የነበረን ትጋት አይረሳኝም!! እኔና ሙሳ ታጄም (የሀሰን ታጄ ወንድም) ቢሮ ከፈትንና የስልጠና ቁሳቁሶችን (በርካታ አግዳሚ ወንበሮች፣ ጠረጴዛ፣ ሰሌዳ...) አሟልተን ሌሉችን ለመሳብ የነበረኝ ትጋት አሁን ድረስ ይታወሰኛል። ያኔ ወራው ሁሉ ስለ "Success" ስለ "Time management"፣ ስለ "Goal setting" ... ነበር። "The road to success የተሰኘውን የዶ/ር ፋይዝ ሰያልን መፅሀፍም ያኔ ነበር የተዋወቅነው። እንዴ ታዲያ ሙሳ የህይወት ግብ ስለማውጣት እየተወያየን ባለንበት፣ ስለ አንድ ልጅ የህይወት ግብ ነገረኝ። የልጁ የህይወት ግብ የተመዘዘው ከነብዩ ሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ. አስተምህሮት ነው።[76]

[76] የነብያን ﷺ አባባሉችን የሚያውና ተቀም በህገራችን አለማቻችን ያሳክሉ። ይህ እንቁራ ህፀት በተጨመ ሁኔታ ወንጠቀምበት የአለምን ችግር እንፈታው ነበር። "ሙሐመድ በህይወት ዚናር ናር አለም አሁን ካለችበት ውጥንቅጥ ያወጣት ነበር። አውቀ አሜሪካ ፈላስፋ ሚርነንድ ሾው አንዳለው።

ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ስለ ሁሉም የህይወት ጉዟችን መመሪያን ሰጥተውናል። በየትኛውም አርምጃችን የሚባሉ ውዳሴዎችንና ፀሎቶችን በዝርዝር አስተምረዋል።

የአላህ መልዕክተኛ ሲዐወ. አንድ ሰው አዲስ ልብስ ለብሶ ሲታዩ ይህን ዱዓ (ፀሎት) አድርጉለት ብለዋል፦

البس جديداً ، وعش حميداً ، ومت شهيداً

ትርጉሙ፦ "ሁሌም አዲስ ልብስ ልበስ፣በህይወትህ አስካለህ ድረስ ለአላህ ፀጋዎች ተገቢውን ምስጋና የምታደርስ ሁን፣ስትሞት ደግሞ በአላህ መንገድ ላይ በሚደረግ ትግል ሰማዕት ሆነህ ተሰዋ።"[1]

ይህ አንድ ሰው አዲስ ልብስ ለብሶ ስናየው የሚደረግ ዱዓ ነው። ታዲያ ይህ ወጣት ይህን ዱዓ የህይወት ግቡ አደረገው። እስኪ ዱዓዎችን በዝርዝር እንተንትናቸው፦

• البس جديداً "- "አልበስ ጀዲደን" - ሁሌም አዲስ ልበስ - ይህ ልደ ሁሌም አዲስ ልብሶችን የሚለብስ፣ንፅህናውን የጠበቀ፣ሲታይ ለሰዎች አእምሮ ሰላምን የሚመገብ... መሆን ይፈልጋል። ይህን ለማሳካት ደግሞ ሀብት ወሳኝ መሆኑንም ያረዳል። ስለዚህ ጥሩ የኢኮኖሚ ደረጃ ይርሶ በብሩ መልካምን ነገር የሚለብስና የሚጫማ ውብ መሆን ነው እንዴ ግቡ።

• وعش حميداً "- "ወዒሽ ሐሚደን" - በህይወት እስካለህ ድረስ ለአላህ ፀጋዎች ተገቢውን ምስጋና የምታደርስ ሁን - ይህ ደግሞ በህይወቱ የሚኖርለት ሁለተኛው አላማ ነው። ጌታው ለዋለለት ውለታ ተገቢውን ምስጋና ያደርሳል። ለጌታ የሚቀርብ ምስጋና ማለት አሁን እንደምናየው ጥሩምግብ ተመግቦ ሲያበቃ እጁን እየጠራረገ "አልሀምዱሊላህ" ማለት ብቻ አይደለም። እንደ ኢስላም አስተሳሰብ ምስጋና ማለት አንድን ነገር ለተፈጠረበት አላማ ማዋል ማለት ነው። ጤናማ አይን የተሰጠው ሰው ምስጋናው ጌታው የሰለሰውን ነገር አለመመልከት ነው። ጆሮ የመሆን

---

[1] አቡ ዒየሕ - ሐዲሱል ሙስለም - ትርጉም ዐሊን ታጂ - ገፅ 31

[2] አስላም እንዲት የወንድማማችነትን ተስዕር ለማጠንከር እንደሚቀጋ በዚህ ዱዓ እናያለን። አንድ ሰው እንዲህ ባለ ዱዓ ሲታደርግለት ወይም በሰሌት ይሆናል። ለወንድሙ ያለው አክብሮትና ፍቅር ይጨምራል። የወንድማማችነት ተስዕሩም ይጠነክራል።

ፀጋ የተሰጠው ሰው በፍትህ መፍረዱ ነው ምስጋናው። የመሪነት ስልጣንን አላህ የሰጠው ሰው በፍትህ ማስተዳደሩ ነው ምስጋናው። ሀብት የተሰጠው ሰው ምስጋናው ገንዘቡን አላህ በሚወደውና በፈቀደው ቦታ ማዋል ነው... ሁሉን ነገር ፈጣሪ በሚወደው መስመር ስታውለው ለተሰጠህ ፀጋ አመስጋኝ ሆንክ ማለት ነው።

ታላቁ ሊቅ አቡ ሐኒፋ አንድ ልብስ ለራሳቸው ሲገዙ ለድሆችም አንድ ልብስ ይገዙ ነበር። ተገቢው ምስጋና ማለት ይህ ነው። ይህም ወጣት እንደዚህ አይነት አመስጋኝ ባሪያ መሆን ይፈልጋል። አዲስ ሰብሶና አምሮበት መኖር ግቡ እንደሆነ ሁሉ ለሌሎችም መልካም የሚውል፣ ለጌታው ፀጋ ተገቢውን ምስጋና የሚያቀርብ መሆንን እንደ ሁለተኛ ግቡ አስቀምጦታል።

- وفيه شهيد". "ወሙት ሸሂደን" - ስትሞት ደግሞ በአላህ መንገድ ላይ በተደረገ ትግል መሰዋዕት ሆነህ ተሰዋ - ይህ ሶስተኛ የህይወት ግቡ ነው። በአላህ መንገድ መሰዋትን አልሟል። በህይወት እስካለ ድረስ ሁሌም አዲስ እየለበሰ አምሮበት ህይወትን መግፋትን፣ ለጌታውም ፀጋ ተገቢውን ምስጋና እያቀረበ መኖርን ተመኝቷል። ይህ ያማረ ህይወት ግን የሚያምር መቋጫ ያስፈልገዋል። በአላህ መንገድ ላይ ከመሰዋት በላይ ደግሞ ምጡቅ ደረጃ የለም። ጥሩ አማኝ፣ በጌታው መንገድ ላይ መሰዋትን (ሸሂድ መሆንን) ሁሌም ይመኛል። ምክንያቱም ትልቅ ውጤት አለውና። ሸሂድ መሆን (በአላህ መንገድ መሰዋት) በርካታ ደረጃዎችን ከአላህ ዘንድ ያሰጣል። እነዚህም፦

"በመጀመሪያ የደም ጠብታው ሙሉ ሀጢያቱ ይለርያለታል። ከተባር ቅጣት አላህ ይጠብቀዋል፣ በትንሳኤ ቀን የክብር ዘውድ ይጠለትለታል፣ 70 ሁረል ዐይን[1] አላህ ይድረዋል፣ለ 72 ቤተሰቦቹ አማላጅ እንዲሆን አላህ እድል ይሰጠዋል (አላት ውስጥ የገቡ ካሉ ለማስወጣት፣ከጀነት ከታችኛው ደረጃ ካሉ ከፍ ወዳለው ለመውሰድ)። መሰዋዕት ሲሆን

---

[1] አቡ ሐኒፋ - ታላቅ ኢስላም (ቀደምት) ምሁር ነበር። አቡ ሐኒፋ እንዴት የተምሀርት መስክ መረጡ? እና "አቡ ሐኒፋ ሆይ! ንገድ አያጠፉህም" የሚሉትን ክፉዎች ይመልከቱ።

[2] የሰው ልጆች ፍትህን እንዲያገኙ፣ ነጥቃቸውን እንዲያውቁ፣ የእምነት ነጥቃቸው እንዲከበር መዋደቅ በአላህ መንገድ ከሚደረግ ትግል ውስጥ ይከተታል።

[3] ሑረል አይን- የጀነት አማላይ ውብ ኢረዲኖች- እንዴ በዕሀይ መውጫ ቀትመጣ የወሀይን ወርሀን ታደገኘው ነበር፣ ምራቂ ወንዞች ላይ ቢጨመር የምናር ውሀዎች ጥፍጥና ፀተቀየረ ነበር... ተባሉታል በነብዩ ሙሀመድ ሰለይ ዉ እንደጠቀ።

የፈለሰው ደሙ እንደ ሚስክ (መልካም መዓዛ) እያወደ የትንሳኤ ቀን እሰ
ፊት ይቀርባል...::"

ይህን ደረጃ ለማግኘት ሁሉም ሰው ይንገበገባል። ይህ ውጣት ይህን እንደ ለስተኛ አላማ ቀርጿል። እምርበት መናር፣ አመሲጋኝ ባሪያ ሆኖ ህይወትን መግፋት፣ መስዋዕት ሆኖ ምድርን መልቀትና የቀጣዩን አለም ለሊት መቆናጠጥ። ... ታዲያ እንተስ የህይወት ግብህ ምንድን ነው? የስምህ ያህል ግብህን ታውቀዋለህ?

7.1.4 ሚስተ - አላፊ

2002 አፕቢያ ላይ ከደሴ የተወለነ ርቀት ወደምትገኘው ወልላ ከተማ[80] ለፕሮግራም ተጋብዤ ሄጀ ነበር። በርካታ ህዝብ በታደመበት ማዕከል በተለይ ውጣቱ ህይወቱን በአላማ እንዲመራ በመጠቆም ትምህርት ለመስጠት ሞክሬ ነበር። ከወልላያ ስመለስም በደሴ አረብ ገንዳ መስጅድ ላይ "የህይወት ግብህ ምንድን ነው?" በሚል ርዕስ ትምህርት ሰጠሁ። በማግስቱ ደግሞ ሸዋ በር መስጅድ ውስጥ ሌላ ትምህርት አቀረብኩ። ኡስታዝ አቡበክር አህመድ[81] በጀመረው ትውውቅና መከፈቻን ተስተካ "ለአምነትህ ምን እየሰራህ ነው?" በሚል ርዕስ ላይ ዳሰሳ አደረኩ።

ሁሌም ታዲያ አንድን ፕሮግራም ስናቀርብ ከታዳሚው የተለያ ጥያቄዎች በወረቀት መላክቸው የተለመደ ነው። ጥያቄዎችን፣ ምስጋናዎችን፣ ትችቶችን፣ አስተያየቶችን፣ የግል ሀሳቦችን... የያ ወረቀቶች ሁሌም ወደ መድረክ ይላኩሉኝ። ትምህርቱን ጨርሼ ከኡስታ አቡበክር አህመድ ጋር ከሸዋ በር መስጅድ ስንወጣ በርካታ ሰው እየመ ይጨብጠን ነበር። ድንገት ኮሜን እንደሆነ የማላቀው አንድ ወረቀት እጄ ላይ አረፈ። የወረቀቱን ይዘት ለማየት ፋታ አላገኘሁም። ብቻ የተለመዱ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ይሆናሉ የሚል ግምት ነበረኝ።

ከመስጅድ ወጥተን ወደ እነ አቡበክር ቤት አቀናን። ትንሽ እረፍት ከወሰድኩ በኋላ እጄ ላይ ያሉትን ወረቀቶች ማንላበጥ ጀመርኩ። አንደኛው ወረቀት ትኩረቴን ሳበው። ስለ አላማ ማስተመጥ፣ ስለ ግብ መኖ

---

[80] በወልላያ ከተማ አንድ ተልቅ የአምነት ማዕከል ይኖራል። ማዕከሉ የመጀ አልላ ሙስሊ መንዘዘሪያ ቦታ፣ መናሙ ቤት፣ የአርሻ ቦታ ሆቴል... ሰውሰው አቅፏል።

[81] ኡስታዝ አቡበክር አህመድ- ታላቅ ዳኢና ሀገሀ መሰረሙ 2004 ላይ ይህት የተነሳው ጥ ተከትሎ በተመረጠው ኮሚቴ ላይ የመሪቱው አባልና ሰብዓዊ።

ያትታል። በተለይ ደግሞ ወጣቱ የህይወት አላማውን በግጥም አስቀምጦት ነበር። ትናንት ማታ ዐረብ ገንዳ መስጅድ ላይ በተረበው ትምህርት ላይ "ጉብዝ የስምህን ያህል ግልፅ ይሁን" ስል አስተምሬ ነበር። ቢ ኤም ደብሊው (BMW)" እና "ሙዕተቅ" የሚሉትን ግቦች እንደ ምሳሌ እንስቼ ነበር። እርሱም ይህን ነው በግጥም የላከልኝ። ግጥሙን እንደወረደ እነሆ፦

"አሰላሙ ዐለይኩም ወረህመቱላሂ ወበረካቱሁ
ለአላህ ስል የምወድህ
እኔ ደካማ ወንድምህ
አላህ ሁሉንም ይጨምርልህ
ከመጥፎ ነገር ይጠብቅህ
ጀነተል ፈርደውስን[1] አላህ ይስጥህ
እያልኩ ሀሳቤን ገለፅኩልህ
ትናንት ያልከውን ተረድቼ
ለዛች ለቀልቤ አስረድቼ
አላማሽ እኮ ምንድን ነው ስላት
ከሁሉ መርጣ የሚሻላት
ይህ ነው አለች አላህ ያሳካላት
ሚአተ አላፈ ማለት ተሸላት
ይህን ሀሳቧን ያሳካላት
እያልክ ወንድሜ ዱዓ አድርግላት
ምን ማለትሽ ነው ብዬ ስላት
ሚሊየነር እኮ አህለል ኸይራት[2]
አሊም መሆን አውቆና ሰርቶ ማነው ነው
ተቅይ[3] መሆን ነው ላንድ ለጊታው
አሚር[4] መሆን ለነቢ ኡመት[5]
ላኢላህ ኢለላህ ሊሆናት ምት[6]

---

[1] የላይኛውና ዋናው የጀነት
[2] አህለል ኸይራት-ብጎ ሰረ፣መልካም አደራጊ... ወገንህ ውስጥ ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋሞችን የሚሰራ፣እርዳታ የሚሰጥ፣ንጠቁን ለበጎ አደራጅት የሚያውል ሰው።
[3] ተቅይ አላህን የሚፈራ ጥንቁቅ ሰው (Pious)
[4] አሚር - መሪ (Leader)
[5] የነቢ ኡመት - ነብዩ መሀመድ ﷺ ይምር ያሉው የአለም ህዝብ።
[6] ላ ኢላህ ኢለላህ - የእስልምና ምስክርነት ቃል ነው። ትርጉሙ- አንዱና ብቸኛው አላህ ዉጭ

ፈርደውለል አልሓ ሊያስገባት
ብላለችኝ ያሳነሳት
ውድ ወንድሜ ዱዓ አርግላት
ያረቢ ያአላህ አሳነሳት

አተማሪ -
ለውድ ዳዒ[ያ] ያሲን ኑሩ
ስሜን ደብቅልኝ
03/01/2002 አ.ል"

እጅግ በጣም የሚያምር አቀማመጥ ነው ያለው። ወጣቱ አላማውን በቀላል አቀራረብ ብቻ ሳይሆን በግራኪ ግጥም አስቀምጦታል። እስኪ ትንሽ ግጥሙን ተንተን እናድርገው።

"ሚአተ አላፌ ማለት ተሻላት" ይላል። ከዚህ ስንኝ ነን ባለፈራት ፅሁፍ ጥሬ ትርጉሙ፡- "ንፍሴ ከመቶ ሽህ በላይ እድሜ ተመኝቶ ማለት ነው" የሚል ፅሁፍ አስፍሯል። እም! ሚአተ አላፌ - ማለት 100 ሺህ ማለት ነው። ሬዥም እድሜን ነፍሱ ተመኝታለች። ይህ እንግዲህ ሰሙ ነው።

በመቀጠል እያንዳንዱን ፊደል በየስንኙ የመጀመሪያ ፊደል ላይ እያደረኩ ወርቁን እኔው ራሴ ልተንትንለት፡-

ሚ - "ሚሊየንር እኮ አህለል ኸይራት" ሲል ይጀምራል። በህይወቱ ጥር ግር፣ ለፍቶ፣ ላይ ታች ወጥቶ ወርዶ... ሚሊዬኖችን ያካበተ ባለፀጋ መሆን። ግን ይህ በቂ አይደለም፣ ሀብት መዳረሻ (Means) እንጅ መድረሻ (የጉዟችን ማብቂያ) አይደለም። ይህን ሀብት ለዋናው ጎላችን ግብዓት (Input) ልናደርገው ይገባል። ይህንም በአግባቡ የተረዳው ተማሪ "ሚሊየንር እኮ አህለል ኸይራት" ሲል ስንኙን ጨረሰው። አህለልኸይር ማለት በጎ አድራጊ፣መልካም ሰሪ፣ ማህበራዊ ችግርን ቀራፊ፣ ድሆችን

በአውነት የሚሹት ጌታ የለም ማለት ሲሆን የህይወት ፍተሄውም በዝህች ታል የሰንሰለት ሰው ይንትን ይወርሳል።

[ii] ፈርደውለል አልሓ የላይኛው ይንት፣ንብያቶችና አላህ ዘንድ እጅግ የተከበሩ ባሮች የሚኖሩት ዓለም።

[iii] ወደ አላህ መንገድ ተጣሪ፣ ወደ መልካም ስብዕና፣ወደ በጎ ነገር ተጣሪ።

ደንብ... ማለት ነው። ስለዚህ የልጅነት በርካታ ሚስጥሮችን ለበጎ አድራጎት ስራ የሚያውል ሰው መሆን ነው።

ሁለተኛው ስንኝ ደግሞ እ - "እሊም መሆን እውቀትና ሰርቶ ማሳወቅ ነው" ይላል። እውቀት ትልቅ ቁም ነገር ነው። ከድርጊት በፊት እውቀት ይቀድማል። ነገር ግን ጥሩ የእውቀት ደረጃ ላይ መድረስ በራሱ በቂ አይደለም። እውቀትን የጋን መብራት ከሆን ትርጉም የለውም።[1] እንዲሁም እኛ አራሳችን የምንናገረውን የማንተገብር ከሆን ግወቃችን ትርጉም ያጣል። በእንደበታችን ብቻ ሳይሆን በድርጊታችንም ማስተማር አለብን። ድርጊት ከቃላት በላይ ንልተው ይሰማሉ (Actions speak louder than words)። አልያ እኛ እየሰበክን፣ እያስተማርን፣ ሰዎች መልካም እንዲሰሩ እያዘዝን፣ ከመጥፎ ነገር እንዲርቁ እያስጠነቀቅን... እኛ የማንተገብረው ከሆነ ትርጉም አይኖረውም። ተፅዕኖውም የጠፋ ያህል የወረደ ነው። Walk as you talk (ንግግርህን ተራመደው) እንደሚባለው፣ በተግባር ያልታደበ ንግግር ልብ ውስጥ ቦታ የለውም። ከጆሮ ኪላ አያልፍም።

ታዲያ ይህ ተግሪም ይህችን ሀሳብ በአንድ ስንኝ ቋጠራት። እውቅ ምሁር መሆን፣ እንዲሁም በንግግሩ ብቻ ሳይሆን በድርጊቱም የሚያስተምር መሆን የሚል ጥቅል ግብ ቀረፀ። ጀግናና ሰርቶ ሚለየነር ሆኖ በጎ ስራን መስራት እንደሚፈልገው ሁሉ፣ እውቀትን ሸምቶ በእንደበቱ ብቻ ሳይሆን በድርጊቱም ሌሎችን ማስተማር ይፈልጋል። ይህ ነው ሙሉ አላማ። እውቀ ማሳወቅ፣ በንግግሩም በስራውም ተምሳሌት መሆን።

ቲ - "ተቅይ መሆን ለአንድ ለጊታው" ያለል ሶስተኛ ስንኙ። ተቅይ ማለት ጥንቁቅ፣ጊታውን የሚፈራ ማለት ነው። ከላይ ሚለየነር ስለመሆንና አዋቂ ስለመሆን ተናግረናል። ነገር ግን ሀብትና እውቀት በተቅዋ ልንም ካልተያዙ የሚያስከትሉት አደጋ ከባድ ነው። በሀብቱ ብዛለትን የሚያስፋፋ፣ፍትህን የሚያዛባ፣ ሙስናን የሚያስራፍ... ከሆነ ሀብት ጥፋት ነው። እንዲሁም በእውቀቱ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ የሚያነቅዝ፣ ስብዕናቸውን የሚያበላሽ ትምህርቶችን የሚሰጥ፣ ወደ ሴራና ተንኮል የሚጠሩ መፅሀፍትን የሚፅፍ፣ ሰዎች እውነትን እንዳይረዱ ብሽቃ የሚፈጥር... ከሆን እንደዚህ አይነት እውቀት ምን ዋጋ አለው?

[1] To know and not to do is really not to know - The 8th Habit P.33

ለዚህም ነው ተግሪው ከላይ ከቀረፃቸው ሁለት አላማዎች አስተሳ "ተቅይ መሆን" ሲል የከተበው። እውቀትና ሀብት በተቅዋ (አለመ በመፍራት) ሲታደሉ ውጪታቸው አመርቂ ይሆናል።... ይ እንዴት ያለ አስተዋይ ወጣት ነው።

አስከትሎም እ - "አሚር መሆን ለነጪ ኡመት" ብሏል። ይህ ጠ ወኔ ነው[80]። ታላቁ አሚር (Leader) መሆንን ተመኝቷል። ለነ ሙሀመድ ሰ.ዐ.ወ. ኡመት (ተከታይ አልያም እርሳቸው ከተላኩበት ጊ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍፃሜ ያለ ትውልድ) በሙሉ መሪ መሆን አለብኝ ሲል አራተኛ ግቡን አስፍሯል። ምድርን ወደተሻለች ደረጃ ለማሸጋገር ቀርሳ ተነስቷል። ከላይ ሀብትን፣ እውቀትንና ተቅዋን ጠቅሶ ነበር። አሁን ደግሞ እነዚህን ሁሉ ዓለምን ወደተሻለች ሁኔታ ለመቀየር ሊጠቀምባቸው ይፈልጋል። ታላቅ መሪ መሆን አለብኝ ሲል አላማ ቀርጿል።

ብዙ ጊዜ ሰዎች መሪነትን (ስልጣንን) የሚፈልጉት የተሻለ ኑሮ ለመኖር፣ ቤተሰብን ወደሚፈልጉት ሀገራት ለመላክ፣ በስብሰባ ሰዎ በየሀገሩ እየሄዱ ለመዝናናት...ነው። ኾነ እንሩ የቤተመንግስት ባር እንደረገጠ የህዝብ ንብረት መጨበጥ ይጀምራል። ይህን አይነት ችግ ለመቅረፍ ታስቦ ነው አሜሪካ ውስጥ ፕሬዝዳንት ለመሆን፣ የተወሰነ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ መድረስ ግድ የሆነው። አሜሪካ ውስጥ የሚመረ መሪዎች የኢኮኖሚ ደረጃቸው አብሮ ግምት ውስጥ ይገባል።

በተጨማሪም በአውቀት መንሰበት የብቁ መሪዎች መገለጫ ነው አመራር ጥበብን ይጠይቃል። ይህም ወጣት ሀብትንና እውቀትን ቀደየ እንደ መዳረሻ አላማ አስቀምጧል። አሁን ደግሞ የጎለም የአመራር መዘውር እጁ ውስጥ ማድረግን ይመኛል። ስልጣኑም እንዳያሸነገለው "ተቅይ መሆን ለአንድ ለጌታው" የሚለው ግቡ ጠባቂ ይሆነዋል። ስልጣን ያለ አግባብ ከመጠቀም የሚያግደውና የሚጠብቀው ይህ ለጌታው ያለው ፍራቻ ነው። ይህ በአርግጥ የትልቅ መሪ መገለጫ ይመስለኛል። ከህዝብ ንብረት የማይፈልግ ባለፀጋ፣ የአመራር ብቃት ያለው አዋቂ (አሊም) እንዲሁም ለፈጣሪው ታማኝና ጥንቁቅ የሆነ ሰው እንዴት አይነት መሪ ሊሆን እንደሚችል አስቡት።

---

[80] "ወኔ ወኔ ይነርሆ የሚለውን ይመለከቱ። ትልቅ አስብ ትልቅ ሰው ላይ እንደምንረዳ ወሎ ያስተምረናል። "If You Dream, Dream big" ምንለት ወሎ ወኔ ስሜት ያማከለ ተሞክሯል።

ላ - "ላ ኢላህ ኢለላህ ሊሆናት ሞት" ያለል እምስተኛው ስንኝ። ላኢላህ ኢለላህ (ከአንድ አላህ ውጭ በእውነት የሚገዙት ጌታ የለም ማለት ነው)። ይህ አንድ ሰው ወደ እስልምና እምነት ሲገባ የሚናገረው የሚለው የምስክርነት ቃል ነው። ይህች ቃል የመጨረሻው የሆንችለት ሰው ጀነትን ይወርሳል[94]። ምድርን ከመልቀቁ በፊት የመጨረሻ ንግግሩ ይህች ቃል የሆነችለት ሰው ስኬትን ያገኛል።

ይህ ወጣት የምድራዊ ቆይታው በፀጋ፣ በእውቀት፣በአላህ ፍራቻና በጥሩ አመራር እንዲሆን ይፈልጋል። አሁን ደግሞ የምድራዊ ቆይታው ባማረ መልኩ እንዲጠናቀት ተመኝቷል። "ላ ኢላህ ኢለላህ የምትለውን የምስክርነትን ቃል በመጨረሻው የህይወት ቅፅበት ተናግሮ የሁለት ዓለምን ስኬት መቆናጠጥን አልሟል። በዝህች ምድር መሪነትን በቀጣዩ አለም ጀነትን ማግኘት አለብኝ የሚል ወኔ አንግቧል። በአርግጥም እንድ ሰው ምድር ላይ የትኛውም አይነት ደረጃ ቢደርስ፣ የቀጣዩን አለም የሚክስር ከሆነ ምን ትርጉም አለው!። በዝህች አለም ስኬት ላይ ደርሶ የቀጣዩን ዓለም ዋና ስኬት (The goal of goals) ከረሳ ምን ቀጋ አለው?

ፊ - "ፊርደውሰል አዕላ አላህ ሊያስገባት" ሲል ይቋጫል የህይወት ግቡን ትንተና። ከላይ እንዳየነው የመጨረሻ ንግግሩ "ላ ኢላህ ኢለላህ የሆነለት ሰው ጀነትን ይወርሳል። ነገር ግን ጀነት የተለያዩ ደረጃዎች አሏት። ትልቁና ዋነኛው "ፊርደውስ" የሚባለው ነው። ከሰምንቱ የጀነት ዓለም ውስጥ ያማረውና የተዋበው ፊርደውስ ይባላል። ከእሱ በላይ ርርቯ የሚባለው ግዙፍ ዓለም ብቻ ነው ያለው። የጀነት ወንዞች የሚመነጩት ከፊርደውስ ነው[95]። በፊርደውስ ዓለም ውስጥ የሚኖሩት የአላህ የቅርብ ባለሟሎችና ነብያቶች ናቸው። ታዲያ ይህ ወጣት አሁንም ወኔው ከፍተኛ ነው። በቀጣዩ ዓለም የነብዩ ጎደኛ፣ የሰማዕታት ጎረቤት መሆን አለብኝ ሲል ግብ ቀርጿል። "በዝህች ምድር መሪነትን፣ በቀጣዩ ዓለም የላይኛውን ጀነት" ማግኘት አለብኝ ሲል አላማውን አስፍሯል።

ከላይ መጀመሪያ ላይ እንዳየነው "ሚእተ-አላፊ" (100 ሺህ) የሚለው የላይ ትርጉሙ (ለመ) ሲሆን፣ በዝርዝር ያብራራነው ጉዞም ደግሞ ወርቁ ነው። የዚህን ወጣት አስተዋይነት ተመልከቱ ስድስት ቃላቶችን በሰምና

[94] ኩቱቡል ሐዲስ- የነብዩ መሀመድ ﷺ ንግግር
[95] ነብዩ መሐመድ ሰ.ዐ.ወ. ብኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት።

ወርቅ አስተላስሮ የህይወት አላማውን ቀርጿል። የሁለት ዓለም ስኬት የሚያገኝበትን አላማ አስቀምጧል። የሚዝም ውጣት ነው።

አሁን በእርግጠኝነት ይህ ወጣት ማን ነው? ማን ይባላል? አሁኪ አስተዋውቀን እያላችሁ እንደሆን እገምታለሁ። እኔም ባስተዋውቃችሁ ደስ ባለኝ ነበር። ነገር ግን ንግግሩን ሲጨርስ "ስሜን ደብቅልኝ" ብሏል። በዚህ ሰዎች ዝናን ለማግኘት በሚግስንብት ዘመን ይህ ድንቅ ወጣት "ስሜን ደብቅልኝ" ማለቱ የልቤን ምጡት ስብዕና ያመላክታል። ስለዚህ እኔም ተማፅኖውን ተቀብየዋለሁ። ስሙንም ለመደበቅ ግድ ይለኛል። ግን እንደ እውነት ልንገራችሁ። ይህን ተማሪ እኔም በአካል አላውቀውም። እምናለሁ እኔና የኢትዮጵያ ህዝብ ባናውቀውም የአላዮች አላኝ አላህ ግን ያውቀዋል። የዚህን ወጣት አላማ ለወደፊት እንዲያሳክለት የዐለማትን ጌታ አማፀናለሁ።

ደብዳቤውን ሲጨርስ "ለአላህ ስል እወድሀለሁ" ሲል ፅፏል። ታዲያ እኔም በህዝብ ፊት እንዲህ ልበልህ "ለአርሱ ስትል እንደወደድከኝ አላህ ይውደድህ"[36]። ለውጥ ያደብህ፣ እድገት አብሮህ ይሁን፣ ስኬት ይከተልህ።... አሚን።

ስለዚህ እኛም የምናውጣው ግብ ግልፅና የተብራራ መሆን ይኖርበታል። ግባችንን የስግችን ያህል መመለስ ይኖርብናል። እስኪ አሁን ዳግም ልጠይቅህ፡- ስምህ ማን ነው? _____ ። የህይወት ግብህስ ምንድን ነው? _____። እርግጠኛ ነኝ ከፍት ቦታው ስምህን በፍጥነት እንደምትሞላው ሁሉ፣ ግብህንም በፍጥነት እንደምትሞላው አልጠራጠርም። ከላይ የጠቀስነው የደሴ ወጣት ግብ ምንድን ነው? ቢባል ግልፅ ሳያስፈልገው "ሚስተ-አላፊ" ይል ነበር። አንተም የስምህን ያህል የምታውቀው ግብ ይኑርህ።

7.2 ግብህ የተብራራ ይሁን

"የዓላማ ግልፅነት የሥራ ፅዳትን ብቻ ሳይሆን የቁጥጥር ስርዓትንና የአተገባበር ፍጥነትንም ይወልዳል"

[36] ነብዩ መሐመድ ﷺ - አቡ ዳዉድ- ሐሰንል መልም- ገ - 206

የለንቅከው ራዕይ፣ ያወጣኸው ግብ ግልፅ፣ ሊለካ የሚችል ተጨባጭ የሆነና ጊዜ የተገደበለት መሆን እንዳለበት አትርሳ። ሰራውን ራዕይህን ግልፅ አድርገህና በጊዜ ገድበህ ስትተገብረው ይቀልሀል።

"Life is hard by yard
But by the inch
It's cinch" Gean Gorden

""ህይወት በስፋቷ
ከብደቷ
ከፋፍለህ ስትመራት
ምንኛ ቀላል ናት" ሂኒ

ብዙ ሰዎች በደፈናው ሲያልሙ ታገኛቸዋለህ። "ህያወቴ ስኬታማ መሆን እፈልጋለሁ" ሲሉ ትሰማቸዋለህ። "ብዙሃን የሚኝኑት ድራጅ መክፈት እፈልጋለሁ" ሲል ታደምጠዋለህ "እንደ እገሌ መሆን አለብኛ ሲሉ ታገኛቸዋለህ። ይህ ግን ምኞት ከመሆን የዘለለ አይደለም።

የምንቀርባቸው ግቦች የዘመኑን የግብ አወጣጥ መስፈርት የተከተሉ መሆን ይኖርባቸዋል። "SMART" የተሰኘውን የግብ አወጣጥ መመዘኛ ማለፍ ይኖርባቸዋል።

SMART - የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የመጀመሪያ ፊደል (Acronym) በመጠቀም ግብን መተንተን የዘመናችን የአመራር ሳይንስ መገለጫ ነው። Smart የሚለው የፊደላቱ ትርጉምም እንደሚከተለው ይተነተናሉ።

Smart - ከሚለው ቃል የመጀመሪያዋን ቃል (ኤስን) በማብራራት እንጀምራለን፡-

1) S - Specific - ግልፅና አሞር - ያወጣነው ግብ በግልፅ ከተቀመጠ ከብዥታ ከመፅዳቱም አልፎ ለአፈፃፀም ቅልጥፍናና ጉልህ ሚና ይጫወታል። የአላማ ግልፅነት የስራ ፅዳትንና የአፈፃፀም ፍጥነትን ይወልዳል። ለምሳሌ አንድ ሰው ጉብደት መቀነስ አለብኛ ቢል ይህ ምኞት ነው። አላማ ይሆን ዘንድ ግልፅና የተብራራ መሆን ይኖርበታል። ነገር ግን "በ 3 ወር ውስጥ በአምንት 3 ቀን

እስፓርት እየሰራሁ 10 ኪሎ መቀነስ አለብኝ ቢል አሁን Specific ሆነ ማለት ነው።

2) M – Measureable - ሊለካ የሚችል። ግባችን ግልፅና እጥር ከሆነ በኋላ መለካት፣ መሸራር፣ መመዘን በሚቻል መልኩ መቀመጥ ይኖርበታል። ይህም ለቁጥጥርና በቀላሉ ለመምራት ያረዳናል።

"If You cannot measure it, You cannot acomplish it"
"ልትመዝነውና ልትለካው ያልቻልከውን ነገር ልትፈፅመው አትችልም።"

ለምሳሌ፦ አንድ ደራሲ "ለወደፊቱ በርካታ መፅሐፍ እፅፋለሁ" ቢል ይህ ምኞት ከመሆን አይዘልም። ነገር ግን በ20 ዓመት ውስጥ 30 መፅሐፍ እፅፋለሁ፣ በየስምንት ወሩ አንዳንድ መፅሐፍ ማሳተም ይጠበቅብኛል፣ በየሳምንቱ አስር ገፅ እፅፋለሁ፣ የእያንዳንዱ መፅሐፍ የገፅ ብዛት ከ300-350 መሆን አለበት... በሚል መልኩ ሲቀመጥ ለለካ የሚችል (Measurable) ሆነ እንላለን። በዚህ መልኩ የተቀመጠ ግብ ለክትትል አመች ከመሆኑም በላይ የእለት ከእለት ሰውጤን ለመመዘን ዕድሉን ይሠጠናል። ለአላማችን መሳካት ያለንን ርቀትና ቅርበት በግልፅ ያሳየናል።

3) A – Attainable /Achievable - ሊተገበርና ሊደረስበት የሚችል። ግባችን ከፍ ያለና ወኔን የሚወልድ መሆን ቢኖርውም፣ የማይደረስበት ሆኖ ተስፋ የሚያስቆርጥ መሆን የለበትም። የመጠቀ ግብ ይኑርህ፣ ነገር ግን በሠዋሚ ጥረትህ የምታሳካው መሆኑን እርግጠኛ ሁን።

4) R – Realistic / Relevant - እውነት ላይ የተመሰረተ (ለዋናው ራዕይ ግብነት የሚሆን) ያወጣነው ግብ ከእውነታው የራቀ፣ መተግበሩ የሚሳን መሆን የለበትም። በፈጣሪ ተዐምር ካልሆነ በስተቀር ሊሆን የማይችል አላማ መቅረፅ የዋህነት እንጂ ሌላ ምን ሊባል ይችላል።

Relevant - ለዋናው ራዕይ ግብዐት የሚሆኑ መሆን ይኖርበታል። ከታች ያሉት ትናንሽ አላማዎች መሳካት ለዋናው ራዕይ መፈፀም

አብላራዎች ናቸው። የቋናው ራዕይ የበኬት መንገዝ የሚዋቀረው ከትናንዝ የድረት ግቦች መሳካት ነውና። የመጀመሪያዋ እርምጃህ የአላማህ ጥግ ለመድረስ አብይ ግብንት ናት። አንድ እርምጃ ስትራመድ ለአንድ ሺህ ሜትር ርቀት 999 ቀረህ ማለት ነው።

እንደዚህ በግልፅ ከፋፍለህ የምታውጣው ግብ ለዋናው ራዕይ መጋዚ (Relevant) መሆኑን አስተውል።

5) T – Time Bound - በጊዜ የተገደበ

በእያንዳንዱ እርምጃህ መንገና መድረሻ የጊዜ ገደብ ልታበጅለት ይገባል። የጊዜ ገደብ ያልተቀመጠለት እርምጃ እድገቱ በትክክል መለካት አይችልም። እስኪ ልጠይቅህ "ይህ አሁን የምትመራው ድርጅት ውጤታማ የሚሆነው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ነው?፣ "አሁን የምትማረውን (የምትቀራው) ኪታብ መቼ ነው የምታጠናቅቀው?" በዚህ መልኩ በጊዜ ተተንትኖ የቀረበ አላማ ለስኬት የቀረበ ነው። እስከ አሁን በገርገር ያየናቸውን በደንብ ትረዳ አንድ ምሳሌ ልጥቀስልሁ

Yole university

እነሆ 1953 በዮል ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እየተመረቁ ነው። የማህበራዊ ሳይንስ አጥኝዎች ለእነዚህ ተማሪዎች መጠይቆችን አቀረቡላቸው። የጥናታዊው መጠይቅ አላማ አንድና አንድ ነው። ለወደፊት ምን መሆን ትፈልጋላችህ? የነገ ህያወታችሁ ምን እንዲመስል ትመኛላችሁ? ራሳችሁን ከዓመታት በኋላ ምን ላይ ብታገኙት ታልማላችሁ? የሚል ነበር። ከነዚህ ተመራቂዎች መሀከል ግልፅ የህይወት ግብ የነበራቸው ሶስት በመቶዎች ብቻ ነበሩ። (ልብ በሉ የዩኒቨርሲቲ አመታትን ተምረው የተመረቁት ምንን ለማሳካት ነበር? አያስብልም!!!)

ከ20 ዓመት በኋላ 1973 እነዚህ ተመራቂ ተማሪዎች ከየቦታው ተፈልገው እንደ አዲስ ጥናት ተደረገ። ውጭም የሚገርመው የተብራራ የህይወት ግብ የነበራቸው ሶስት በመቶዎች ከቀሪዎች ብጠና ሰባት በመቶዎች የተሻለ የተሳካለት ህይወት እየመሩ ነበር።

ወንድሜ ግልፅ ግብ ከሌለህ ትሰራ ይሆናል ነገር ግን እታከናውንም ትለፋ ይሆናል ነገር ግን ውጤት አታይም። ለዚህ ነው "Don't work hard but work smart" የሚሉን የለውጥ ሊይንስ ተማሪዎች። አላማህን በጊዜ ከፋፍለህ፣ ግልፅና ዝርዝር አድርገህ፣ ሊለኩ በሚችል መልኩ አስቀምጠህ ተግዝ... ውጤቱን በትርብ ታየዋለህ። እትጠራጠር!!

"ህይወትን በኪሎ
ግን ችሎ
በግራም ስትለካት
ምን አላት" ሂክ

"ከእንቅል ምኖትና በአላማ መሀከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት፣ አላማ በጊዜ የተገደበ መሆኑ ነው" ጂይ ፎርፊስ ማሊታቸውም ለዚሁ ነው።

ብዙ ሰው ባለፀጋ መሆን ይፈልጋል። መሆን የፈለጉትን ነገር ዝርዝር የስራ እቅድ (Activity) አውጥቶ መተግበር ግን የጥቂት ስኬታማ ሰዎች መገለጫ ነው። ዝርዝር የስራ እቅዶች (Activities) ወደ ግባችን የሚያደርሱንን ተግባራት ሳናስናውን ጊዜ እንዳያልፍብን የምንቆጣጠርበት ዘዴ ከመሆኑ ጎን ለጎን ግዙፍ የሆኑ አላማዎች ለመተግበር ያቀሉልናል።

ዝርዝር እቅዶችና ክትትል የስኬት ወሳኝ እርምጃዎች ናቸው። እነዚህ ዝርዝር እቅዶች በተሳኑ ቁጥር ወደ ዋናው አላማችን እየቀረብን መሆኑን ልብ እንበል። እነዚህ በጊዜ የተገደቡ ዝርዝር እቅዶች በጡብ ይመሰላሉ፣ ዋናው ግባችን ደግሞ በህንፃ ይመሰላል። የእነዚህ ጡቦች ድርደራ በተገቢው መንገድና በተወሰነላቸው ጊዜ መጠናቀቅ የህንፃውን መጠናቀቅ አብሳሪ ናቸው። አልያም እነዚህ ዝርዝር እቅዶችና ተግባራዊ እርምጃዎች በዝናብ ጠብታ ይመሰላሉ። ግባችን ደግሞ በትልቅ ወንዝ ይመሰላል። እነዚህ ጠብታዎች በሂደት ትልቁን ወንዝ ይፈጥራሉ።

"ግብ ግለት ቀን የተቀጠረለት ህልም ግለት ነው።" ናፖሊዮን ሂል

ግብና ወደ ግቡ መዳረሻ የሆኑት ዝርዝር እቅዶች፣ በገጠመኝ ስራዎች እንዳንወሰድ ይጠብቁናል። ነገሮችን መርጦ የመስራት እድልን ይሰጡናል። ብዙ ሰዎች "እንደዚህ አይነት ሰው መሆን እፈልጋለሁ፣ ለወደፊት እዚህ እደርሳለሁ"... ሲሉ ልትሰማቸው ትችላለህ (ያው እንዲህ የሚሉት ሰዎች

ቁጥራቸው ጥቂት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ግለቱ ነው። እንጂ አብዛኛው ሰው እንዲህ እሆናለሁ የሚለው አላማ የለውም)... ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በየቀኑ፣ በየሳምንቱ፣ በየወሩ ምን ሰርቼ ነው ወደ ግቤ የምደርሰው? የሚል ዝርዝር እቅድ አላስተመጡም።

ስኬት የግልፅ አላማ፣ ወደ አላማ የሚያደርሱን ዝርዝር እቅዶችን የመተግበርና እነሱን በአግባቡ የመቆጣጠር ድምር ውጤት ነው።

"የምትፈልገውን ነገር ካልተከታተልከው አትጨብጠውም። ካልጠየክ መልሱ ሁልጊዜ አሉታ ነው። ወደፊት ካልተራመድክ ዘውትር ራስክን ባለህበት ታገኘዋለህ።" ኖራ ሮበርትስ

እንበልና ለወደፊት ትልቅ የህዲስ (የንብዩ ሲ.ዐ.ወ. አስተምህሮቶችና አባባሎች) ሊቅ መሆን ፈልገሀል። ይህ ትልቅ ግብ ነው። ነገር ግን የዝርዝር ዕቅድ ወይም እርምጃ ያስፈልግሀል። በየቀኑ ስንት ህዲሶችን ትማራለህ (ትቀራለህ)? በወር ውስጥ ስንት ትቀራለህ? ስማን ትማራለህ? ዛሬ መማር የሚገባህን ህዲስ በአጋጣሚዎች ሳትማር ቢያልፍ፣ መች ታካክሰዋለህ? በዓመት ውስጥ ስንት መፅሀፍን (ኪታብን) ትማራለህ (ትቀራለህ)?.... እኒህና መሰል ጥያቄዎች የተግባር እርምጃዎች (Activities) መገለጫ ናቸው።

በጊዜና በቦታ ያልተገደበ ግብ ህልም እንጅ ሌላ አይደለም። ግብ መዳረሻ ዝርዝር እርምጃዎች ያስፈልጉታል። የስምህን ያህል ቢጠይቁህ የምትመልሰው ግልፅ አላማ እንዳለህ ሁሉ ወደዚህ አላማህ የሚያደርስህ ዝርዝር እቅድም (የተግባር እርምጃ) ያስፈልግሀል።

8

ምዕራፍ ስምንት



የህይወት ግብ ለሁሉም

- የህይወት ግብ ለሀፃናት
- አናመላለቷቸው አንጂ አንጫኗቸው
- የልጆች ሰንፍና
- የህይወት ግብ ለጡረተኛች

ምድር የሁሉም መኖሪያ ናት። በመሆኑም የሁሉም አስተዋፅኦና ተሳትፎ ያስፈልጋታል። የሰው ልጅ በዚህች ምድር ላይ የፈጣሪ አምባሳደር ሆኖ ተሹሟል። ይህን ሀላፊነቱን መለኮታዊው መፅሐፍ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፦

" (ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ለመላእክት - "እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ" ባለ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)_"[97]

አዎ! የሰው ልጅ የፈጣሪ አምባሳደር ነው። በፍትህ ሊመራ፣ ሰላምን ሊያስፍን፣ ፈጣሪን በብቸኝነት ሊያመልክና ምድርን ሊያለማ ምድር ላይ የፈጣሪ አምባሳደር ሆኗል። ይህን ምድርን የማልማት ተልዕኮውን ቁርኣን እንዲህ ይገልፀዋል፦

"_አላህ ከምድር ፈጠራችሁ፣ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ_"[98]

የአደም ልጅ ምድርን የማልማት ሀላፊነትን ተሸክሟል። ይህን ሀላፊነቱንም በብቃትና በጥራት እንዲወጣም ታዟል፦

"ያ የትኛችሁ ሰራችሁ ያማረ መኾኑን ሊሞክራችሁ፣ ሞትንና ህይወትን የፈጠረ ነው። እርሱም አሸናፊው መሀሪው ነው"[100]

[97] ቁርኣን 2 : 30
[98] ቁርኣን 11 : 61
[99] Who amongst you do the good deeds in the most perfect manner
[100] ቁርኣን 67 : 2

ታዲያ ተልዕኮውን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የሰው ልጅ በአላማ የተመሩ ህይወትን መኖር ይጠበቅበታል። ያለ ግልፅ አላማ ተልዕኮው በሚፈለግበት መልኩ መወጣት ይሳነዋል።

አምነ በብቃትና በጥራት (ኢህሳን) ይሰራ ዘንድ በግልፅ የተቀመጠ የተበራራ፣ ሊለካ የሚችልና በጊዜ የተገደበ የህይወት ግብ ወሳኝ ነው።

ስለዚህም ለሁሉም የምድር ነዋሪ ያለምንም የእድሜ ገደብ የህይወት ግብ ያስፈልጋቸዋል። ምናልባትም ግብን ስለመቅረፅ ሲነሳ በአዕምሮአችን ላይ የሚመጣው፣ ወጣቱን ትውልድ ለቀጣይ ህይወቱ ግብ እንዲቀርፅ ማስታወስ ይሆናል። ነገር ግን የህይወት ግብ ለህፃናት፣ ለወጣቶች፣ ለጎልማሶች፣ ለሽማግሌዎች፣ ለአረጋዊያን...ለሁሉም ያስፈልጋል። ምድር የሁሉም ቤት ናት፣ የቤተሰቡ አባሎች ሁሉ ለቤቱ ልማት በነፍስ ወከፍ አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

8.1 የህይወት ግብ ለህፃናት

ህፃናት በሊጋና ለም ጭንቅላታቸው ሊተክል፣ በንፁህና በብሩህ አዕምሯቸው ሊታተም የሚገባው የህይወት ግብ ያስፈልጋቸዋል። ከደማቸው ጋር ተዋህዶ፣ ከመንፈሳቸው ጋራ ተዛምዶ የሚያድግ የህይወት ግብ እንዲቀርፁ ማገዝ የወላጆች፣ የአስተማሪዎች፣ እንዲሁም የማህበረሰቡም ሀላፊነት ነው።

በዩ. ኤስ አሜሪካ ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ ት/ቤቶች ህፃናት ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ በአላማ የተመሩ ህይወት እንዲመሩ ያስተምሯቸዋል። ገና የሰባት ዓመት እድሜ የሆናቸውን ህፃናት በሳምንት አንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ እንዲማሩ ይደረጋል። ይኸውም "የህይወት አላማህን ቅረፅ"[101] የሚል ነው። ልጆቹ በየሳምንቱ አላማን ስለመቅረፅ ይማራሉ። ምናልባት እነዚህ ህፃናት በዚህ እድሜያቸው በደንብ ላይረዱት ይችላሉ፣ ነገር ግን ሁሌም ሲደጋገም በሂደት ውስጣቸው ይሰርፃል። የከረምት እረፍት ለመውሰድ ወደ ቤተሰብ ሲመለሱ ለቤተሰቦቻቸው ደብዳቤ ይላክላቸዋል። "ልጃችሁ በህይወቱ መሆን የሚፈልገውን አላማ

[101] ልክ እንደ ባሎሊ፣ ኪሚስትሪ፣ ፊዚክስ...ሁሉ ይህም አንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ተሰጥቶ ይማራሉ።

ስለቀረፀ በደንብ ተከታተሉት፣ አግዙት" የሚል መልዕክት ለወላጆች ይላካል::[102]

እንደ ሶሃቦቹ

ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአንዱ ይማር ስለነበረ አንድ ህፃን ሁሌም የሚነገር ታሪክ አለ::

ነገሩ እንዲህ ነው:- በምድረ አሜሪካ ከሚኖሩ ሙስሊም ቤተሰቦች ውስጥ የተገኘ አንድ ልጅ ለመማር ወደ ትምህርት ቤት ይለካል:: የዓመቱ መጀመሪያ መግቢያ ስለነበር ሁሉም ተማሪ ራሱን እንዲያስተዋውቅና ለወደፊት ምን መሆን እንደሚፈልጉ እንዲገልፁ እድል ተሰጥቷቸው ነበር:: ሁሉም ህፃናት እየተነሱ ስማቸውንና ሲያድጉ መሆን የሚፈልጉትን ነገር መተንተን ይዘዋል:: "ዶክተር፣ ፓይለት፣ ኢንጂነር፣ ሳይንቲስት፣ አስተማሪ፣ ማኔጀር... መሆን እፈልጋለሁ" የሚሉ አባባሉች በህፃናቶቹ በተደጋጋሚ ይገለፁ ነበር:: ነገር ግን አንድ ህፃን ከልጆቹ ሁሉ በተለየ መልኩ አንድ ለየት ያለ (odd) አላማ ተናገረ:: "እንደ "ሶሓቦች"[103] መሆን እፈልጋለሁ" ሲል ስሙን አስከትሎ አላማውን ተናገረ :: መምህሯ በአመታት የመምህርነት ቆይታዋ ሰምታው የማታውቀው ነገር ስለነበር፣ ህፃኑን ተጠግታ "ሶሓባ" ማለት ምን ማለት ነው? ስትል አይን አይኑን በትኩረት እየተመለከተች ጠየቀችው:: ህፃኑም "የዚህ መልስ ያለው እናቴ ጋር ስለሆነ "ኡሚን" ጠይቂያት" ሲል መለሰ::

ይህን ጉዳይ ለማጣራት መምህሯ ወደ ልጁ እናት በቀጥታ ደወለች:: "ልጅሽ ለሶሓባ መሆን እፈልጋለሁ ብሏል" ሶሓባ ማለት ምን ማለት ነው? ስትል ሰላምታን አስከትላ ጥያቄዋን አቀረበች:: የልጁ እናትም "ይህ በእልክ የምነግርሽ ጉዳይ አይደለም፣ ከስራ ስትወጪ ወደቤት ነይና እንጨዋወታለን" ስትል ወደ ቤት ጋበዘቻት:: መምህርትም ነገሩን ለማወቅ ከነበራት ጉጉት የተነሳ ስራ እንደጨረሰች ወደ ልጁ ቤት አቀናች:: እናቱም በመልካም መስተንግዶ ተቀበለቻት:: ዘርዘር አድርጋም የዚያን ምጡቅ ትውልድ ታሪክ ነገረቻት:: ምድር ላይ ፍትህን ያሰፈኑ፣ምጡቅ አመለካከት

---

[102] ዶር ዓምር ካሊድ - ሐታ የገደሉ ማቢአንቶሊሞ ገፅ -270

[103] የነብዩ ﷺ ባልደረቦች:: የለሊት ሲጋደች፣ የቀን ጋላቢዎች:: ምድር ላይ ፍትህንና መልካምን ስብዕና ተክለዉ የሄዱ፣ዓለም ዛገም ልታያቸዉ ያልተሳካላት ዘላቂ ህዘቦች:: ለበለጠ ግንዛቤ "ሐያቱ ሶሓባ" የተሰኙትን 3 ተከታታይ ጥሪቶች ይመልከቱ::

የነበራቸው፤ከራሳቸው በላይ ለህዝብ የኖሩ፤አዛኝና ደጎች፤ምድር ላይ ተበትነው ለሰው ልጆች የኢስላምን መልዕክት ከሜፍ እስከ ሜፍ ያዳረሱ፤ የዚህች ምድርንም የቀጣዩ ዓለምንም አላማ አሳክተው ምድርን የተሻገሩ ብርቅየዎች። ምድር ዳግም ሊደግማቸው ያልቻላቸውና እኔ ያልተገኘላቸው ህዝቦች... እንደነበሩ በሚገባ አብራራችላት።

በህይወቷ ሰምታው የማታውቀው ታሪክ ነበር። ምድር ላይ እንደነዚህ አይነት ስብዕና የነበራቸው ትውልዶች መኖራቸውን ስትሰማ ለመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር። ይህን ድንቅ ታሪክ ባለቤቷም እንዲሰማው ፈለገች። ከልጂ አባት ጋር የመምህሯ ባለቤት ተገናኝተው ተወያዩ። ባሏም በጉዳዩ እጅግ ተገረመ። እርሱ እስከዛሬ የሚያውቃቸው የተለያዩ ፈላስፋዎችንና የለውጥ አራማጆችን ብቻ ነበር። አዎ! እርሱ እንደሞዴል የሚከተላቸው እነ፡-ሶቅራጥስን (469-399B.C)፤ ቤንጃሚን ፍራንክሊን (1706-1790)፤ ዊልያም ዊልበርፎረስን (1759—1833)፤ አብራሀም ሊንከን (1809-1865)፤ ማኑተማ ጋንዲን(1869-1948)፤ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየርን (1929-1968)፤ ማልኮም ኤክስን (1925-1965)፤ኔልሰን ማንዴላን (1918-2013)፤የአሲሲው ፍራንሲስኮን (1181-1226)፤እማሆይ ቴሬዛን (1910-1997)... ብቻ ነበር።

አሁን የሰማው ነገር ግን ከሁሉም የተለየ ሆነበት። "እውነት በምድር ላይ እንደነዚህ አይነት ትውልዶች አልፈዋልን?" ሲል ራሱን ጠየቀ።... ከባለቤቱም ጋር በነገሩ ላይ በስፋት ተወያዩ፤ በዚህ (በሰሐቦች) ዙሪያ የተከተቡ መፅሀፍትን አነበቡ። በመጨረሻም ይህን አይነት ስብዕና ኮትኩቶ ያመረተውን መንገድ ለመከተል ወሰኑ። ልክ እንደሶሓቦቹ ለሰው ልጆች ሁሉ መልካም አርአያ ለመሆን ቆርጠው ተነሱ።

ወላጆች ሆይ! ልጆቻችንን ከስረ መሰረቱ ልንንከባከባቸው ይገባል። ለልጆች ከምንሰጠው እንክብካቤ ዋነኛው፤ ልጆች ለወደፊት መሆን የሚፈልጉትን ዓላማ ፈልገው እንዲያገኙ መርዳት፤ ተሰጥኦዎቻቸውን እንዲፈትሹ ማገዝ ነው። ማልበስና መመገብ ብቻ ትልቅ ቁም ነገር አይደለም። ትንሽ ቁጭ ብለን የውስጣቸውን እንዲነግሩን እድል ልንሰጣቸው ይገባል። አላማቸውን እንዲቀርፁ ልናግዛቸው ግድ ይላል።

ጀምስ ኦርዊን

ጀምስ እራቱን በደንብ ከበላ በኋላ በመለስተኛ ላሉናቸው ውስጥ መረቁን ይሟል። ከተለመደው የመኝታ ጊዜው እንዲለፈ የተረዳችው እናቱ ሰዓቷን ከተመለከተች በኋላ መኝታ ቤት ሄዶ እንዲተኛ አዘዘችው። ብቸኝነት እንዳይሰማው በማሰብ ስራዋን እንደጨረሰች ቶሎ ወደ መኝታ ክፍሉ እንደምትመጣ አባብላ ነገረችው።

ጀምስ የእናቱን ትዕዛዝ ተቀብሎ ወደ መኝታ ቤት የሚወስደውን ደረጃ መውጣት ጀመረ። ክፍሉ ውስጥ እንደገባም በመስኮቱ በኩል ደማቅ ብርሃን መግባቱን አስተዋለ። ወደ መስኮቱ በመጠጋት ወደ ውጭ አማተረ። ጨረቃ ከወትሮው በተለየ መልኩ ወለል ባለው ሰማይ ላይ ብርሃኗን እየረጨች ነበር። በተመስጦ ተመለከታት። ለረዥም ጊዜም በአትኩሮት አስተዋላት። እናቱ ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ወደ መኝታ ቤቱ ስትመጣ ጀምስን በመስኮቱ እያማተረ አገኘችው። "ምን እያደረክ ነው እስከ አሁን? የመኝታ ሰዓትህ አኮ አልፏል" ስትል ግርምትም ቁጣም በተቀላቀለው አንደበት ጠየቀችው። "ጨረቃዋን እየተመለከትኩ ነው" ሲል አንዴ ወደእናቱ ሌላጊዜ ወደ መስኮቱ እያማተረ መልስ ሰጠ። "በል ይበቃል የመኝታ ሰዓትህ አልፏል ግባና ተኛ" አለችው። እርሱም በዘገምተኛ እርምጃ እግሩን እየጎተተ እንዲህ ሲል ህልሙን ነገራት፡- "አንድ ቀን በጨረቃ ላይ እራመዳለሁ"።

ካደገም በኋላ ይህን ህልሙን ሊያሳካ የሚችልበትን የትምህርት መስክ ተማረ። በበረራ ስልጠና ተመረቀ። በመስኩም ለዓመታት ገፋበት። በጣም የሚገርመው ለእናቱ ህልሙን ከተናገረ ከ32 ዓመታት በኋላ ጨረቃን ለመርገጥ በቃ። ድሮ ምድር ላይ ሆኖ ነበር ጨረቃን ያያት አሁን ደግሞ ጨረቃ ላይ ሆኖ ምድርን ተመለከታት።

ሀሳብ በለጋ እድሜያቸው የህይወት ግብ እንዲቀርፁ ማገዝ ይኖርብናል። ከደማቸው ጋር ተዋህዶ ያደገ አላማ ተፈፃሚነቱ የጎላ ነው። እንዲሁም የቀረፁትን ግብ እውን እንዲያደርጉ ሁሌም የወላጅ እገዛ ያስፈልጋቸዋል። በመረጡት የህይወት መስክ እንዲሄዱ ሙሉ ነፃነታቸውን ልንሰጣቸው ይገባል።

8.1.1 እናመላክታቸው እንጂ እንጫናቸው

እያንዳንዱ ልጅ የራሱ የሆነ ተሰጥኦና ፍላጎት ይኖረዋል። ልጁን ወደሚፈልጉበት የህይወት መስመር እንዲያቀኑ ወላጆች ግገዛ ይጠበቅባቸዋል።

አውቁ ምሁር ዶ/ር ጣሪቅ አስ-ሰወይዳን ልጃቸው መሐመድ ጣሪቅ እርሱው በወደደው መስክ እንዲቀጥል ምርጫውን ለልጃቸው እንደተውለት ይናገራሉ። እንደላቸው ፍላጎት ቢሆን ኖሮ ልጃቸው በ"Management" ና በ " Leadereship" መስክ ትምህርቱን በከታተል ይመርጡ ነበር። ልጃቸው የትምህርት መስክ (Departement) ከመምረጡ በፊት ሰፊ ውይይት እንዳደረጉ ያወሳሉ። በመጨረሻ ግን ልጃቸው ማጥናት የሚፈልገው በህክምናው ዘርፍ መሆኑን ነገራቸው። እርሳቸውም ለመረጠው መስክ እገዛ አደረጉለት።[104]

አንዳንድ አባቶች ለልጆቻቸው ልክ ልብስና ጫማ መርጠው እንደሚገዙላቸው ሁሉ፤ የትምህርት መስክም ለልጆቻቸው ሊመርጡላቸው ይፈልጋሉ። አንዳንዶቹማ እነሱ ድሮ ተመኝተው ሊያሳኩት ያልቻሉትን የትምህርት መስክ ልጆቻቸው እንዲማሩ ይጫኗቸዋል። እራሳቸው የህክምና ዶክተር መሆን ፈልገው ካልተሳካላቸው ልጃቸው የህክምና ዶክተር እንዲሆን ይጫኑታል። ምናልባት ሁሌም የምንሰማው አንድ ታሪክ አለ። እንዲህ ይነበባል፡-

ዲግሪው ያባቴ ነው

አንድ አባት በወጣትነት የትምህርት እድሜያቸው አንድ ምኞት ነበራቸው። ትምህርታቸውን ጠንክረው ተምረው ጥሩ የህክምና ዶክተር መሆን፤ ወላጆቻቸውንም በማህበረሰቡ ዘንድ "የዶክተር አገሌ ወላጆች" እየተባሉ ሲከበሩ ማየትን ይመኙ ነበር። ጥሩ ውጤት አምጥተው ወደ ዩኒቨርሲቲ አቀኑ። ነገር ግን መሆን የሚፈልጉትን የትምህርት መስክ (ፊልድ) ሊያገኙ አልቻሉም። ያለ ፍላጎታቸውና ያለ ተሰጥኦዋቸው በመምህርነት ትምህርታቸውን አጠናቀው ተመረቁ። በእንካሳ ወኔ የመምህርነትን ህይወት ገፉበት። ያ በልጅነት የሰነቁትን ዶክተር የመሆን

[104] ዶ/ር ጣሪቅ አስ-ሰወይዳን - ሂዋር መው ዶ/ር ጣሪቅ

ፍላጎታቸውን ሁሌም በተማሪዎቻቸው ላይ ያንፀባርቁት ነበር። "ስታድጉ ጀኔራር ነው መሆን ያለባችሁ" ሲሉ ይመክሩ ነበር።

በዚህ የወጣትነት ጊዜያቸው አይናቸው ከሌላ መምህርት ላይ ያርፍና ትዳር ይመሰርታሉ። በአመቱም ልጅ ይወለድላቸዋል። በእርሳቸው እውን ያልሆነው ህልማቸው በልጃቸው እውን እንደሚሆን ይገምቱ ነበር። ገና በልጅነቱ ሲጠሩትም "ዶክተር" እያሉ ነበር።

ልጃቸው እደገና ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግብ ጎበዝ ተማሪ ሆነ። በተለይ የሂሳብ ተሰጥኦው የሚደንቅ ነበር። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በጥሩ ውጤት አጠናቀቀ። ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመሄድ በተዘጋጀበት ወቅት አባቱ መጡና የትኛውን የትምህርት መስክ (ፊልድ) መምረጥ እንደሚፈልግ ጠየቁት። "ኢንጅነር መሆን እፈልጋለሁ" ሲል ለአባቱ መለሰ። አባቱም ቆጣ ብለው "የለም አንተ ልትሆን የሚገባህ የህክምና ዶክተር ነው" አሉት። ከአባቱ ጋር ለሰዓታት ቢወያዩም ሊግባቡ ግን አልቻሉም። በመጨረሻም ልጃቸው አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ። አባቱ ለእርሱ እንደሌሎች አባቶች አይደሉም። ለጥሩ ውጤት እንዲበቃ ምን ያህል እንደ ደከመለት ያውቃል። ቀን ሲያስተምር ውሎ ማታ ደግሞ እርሱን በማስጠናት እንደሚያመሹ ያውቃል። የአባቱን ውለታ መክፈል እንዳለበት አመነ። የህክምና ፊልድን መርጦ አምስት ዓመት ሙሉ በወደቀና እንደበረዶ በቀዘቀዘ ወኔ ተምሮ አጠናቀቀ።

ዛሬ የልጁ ቤተሰቦች ደስተኛ ሆነዋል። በተለይ አባቱ የሚጨብጡትን አጥተዋል። በምረቃ በዓሉ ላይ በርካታ የቤተሰቡ አባላት ተገኝተዋል። ልጁ ከምረቃ አዳራሹ እንደወጣ፣ ቤተሰቡ ሁሉ በጉንጉን አበባ ተቀበሉት። በካሜራዎችና በሞባይሎች ፎቶግራፎችን አስቀሩ። ከቆይታዎች በኋላ ልጁ የዲግሪውን ካርድ ከወረቀቶች መሀል አመጣና ለአባቱ ሰጠው። "አባቴ ሆይ! ዲግሪው ለአንተ ነው። እኔ ተሰጥኦዬና ፍላጎቴ ባልሆነ የህይወት መስክ ላይ መቀጠል አልፈልግም" አለው። "ይህን ትምህርት የተማርኩት የአንተን ትዕዛዝ ለመጠበቅ ብቻ ነው። እኔ መሆን የምፈልገው ኢንጅነር ነው" ሲል አቋሙን ገለፀ።...

አሁን ልጁ እንደ አዲስ የኮሌጅ ትምህርት ቀጥሏል። ኢንጅነር ለመሆን በትጋት እየተማረ ነው። የሂሳብ ተሰጥኦውም ለዚህ እንደሚያግዘው እርግጠኛ ነው።

ስንትና ስንት ልጆች ይሆኑ ፍላጎታቸው ባልሆነ መስክ እየተማሩ ያሉት? አንዳንዴ በቤተሰብ ተፅዕኖ ሌላ ጊዜ የሚመርጡት ጉ የትምህርት መስክ በማጣት። ልጆቻችን በሚወዱት መስክ ላይ እንዲገ ልናግዛቸው ይገባል። እንደ ወላጅ ከእኛ የሚጠበቀው እያንዳንዱን ፊልድ ቢማሩ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ማብራራት ብቻ ነው። ስለሚመርጡት መስክ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማገዝ ነው። በመጨረሻ ምርጫውን የምንተወው ለራሳቸው ለልጆቹ መሆን ይኖርበታል።[106]

"የተወደዳችሁ ዜጎች! ግን ለምንድ ነው ሀብት ንብረት ለማፍራት እያንዳንዱን ድንጋይ ስትፈነቅሉ ይህን የምታፈሩትን ሐብት ለምትተውላቸው ልጆች ሰብዓዊ ብልፅግናና ዕድገት ተገቢውን ጥንቃቄ የማታደርጉት?" ሶቅራጥስ

8.1.2 የልጆች ስንፍና

ምናልባት አንዳንድ ልጆች በህፃንነታቸው ቶሎ ትምህርት የማይገባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ታዲያ ወላጅ መጨነቁ አይቀርም። "ልጄ ሰነፍ ሆነብኝ" ብሎ ማሰቡ የተለመደ ነው። ነገር ግን ወላጆች ልብ ማለት የሚገባቸው አንዳንድ ልጆች ምናልባትም ትልቅ ተሰጥኦ ይኖራቸውና የሚማሩት ትምህርት ላይመጥናቸው ይችላል። ይሄኔ ህፃናት የሚመርጡት ዝምታን ሊሆን ይችላል። በጣም የሚገርመው ጥቂት የማይባሉ ዓለም ላይ አንቱታን ያተረፉ ታላላቅ ሰዎች በልጅነታቸው ሰነፍ ተማሪ መሆናቸው ነው። የተወሰኑትን እናንሳ፦

ፓብሎ ፒካሶ

የስዕል ጥበብን ወደ አዲስ ደረጃ እንዳሳደገ የሚነገርለትን ፓብሎ ፒካሶን "ኦልድ ማን ዊዝ ጊታር"፣ "ዝ ያንግ ሌዲስ ኦፍ አቪንን" ፣ "ጉዌርኒካ" እና በሌሎችም ድንቅ ስራዎቹ አለም ታውቀዋለች። ይህ ሰው በልጅነት እድሜው ትምህርት የመቀበል ስንፍና ነበረበት። ይህ ሁኔታው የትምህርት ቤት ህይወቱን አስቸጋሪ አድርጎበት ነበር።

---

[106] <እሱ ሐኒፋ እንዴት የትምህርት መስክ መረጡ? የሚለውን ይመልከቱ - ምዕራፍ 6

ቢሆንም ፒካሶ እንድ ተሰጥኦ ነበረው። እም! ሰዎች እንዴት ሊታዩ እንደሚፈልጉና ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚያዩዋቸው የመገንዘብ ልዩ ክህሎት ነበረው። ይህን ክህሎቱን በስዕል ንድፍ ላይ አዋለው። ይኸው ዛሬ ስሙ ናኝቶ ይገኛል።[106] ስለተቆናጠጠው ስኬት ሲናገር እንዲህ ይላል፡- "እናቴ - ወታደር ብትሆን ጀኔራል ትሆናለህ፡መነኩሲ ብትሆን ደግሞ ጳጳስ ወደ መሆን ታድጋለህ አለችኝ። እኔ ግን ሰዓሊ ሆንኩና ፒካሶ ሆንኩኝ።"[107]

አጋታ ክርስቲ

በልጅነቷ ትምህርት የመቀበል ስንፍናዋን ያዩ ቤተሰቦቿ እንደ ደካማ ይመለከቷት እንደነበር ትናገራለች። እያደገች ስትሄድ ግን ከትከሰኛ የስነ-ፅሁፍ ተሰጥኦዋ ጋር ተዋወቀች። እንግሊዛዊቷ አጋታ ክርስቲ በአሁን ሰዓት እውቅ የረጅም ልብ-ወለድ ፀሀፊ ናት። 14 የአጭር ልብወለድ መፅሀፍትን ለህትመት አብቅታለች። ከ66 በላይ የሚሆኑ የወንጀል ምርመራ መፅሀፍትን ለዓለም አበርክታለች።

እንደ ጊነስ ቡክ አፍ ወርልድ ሪከርድስ መረጃ መሰረት ድርሳናቶቿ በዓለም ዙሪያ ከ4 ቢልዮን ቅጅ በላይ የተሸጠላትና ተፎካካሪ የሌላት ብቸኛ ደራሲ ነች።

አልበርት አንስታይን

ለብዙዎቻችን የአንስታይን ስም ሲነሳ አለምን የቀየሩት የፊዚክስ ቀመሮች ወደ አእምሮአችን ይመጣሉ። የበርካታና ምጡቅ ቀመሮች ቀማሪ መሆኑ ይታወሰናል። በሰው ልጆች የቴክኖሎጂ እድገት ላይ እምንታዊ ተፅዕኖ የፈጠረው "ሞደርን ፊዚክስ" አባት ምናባችን ላይ ይከሰታል።

ነገር ግን ይህ ሳይንቲስት በለጋ እድሜው እንዲህ ፈጣንና ንቁ አልነበረም። ማንበብ የጀመረው እንኳ በሰባት አመቱ፣ መናገር ደግሞ የጀመረው በአራት ዓመቱ ነበር። አስተማሪዎቹና ወላጆቹ የአእምሮ

---

[106] Richard Carlson- Don't Sweat the Small Stuff... and it's all Small Stuff. አፍሪም እንዳ - የስኬታማነት ጥበብ

[107] ይኸው አሁን ደግሞ "ጥበብ የጠፋች የሙዕሚናኖች ንብረት ናት። ካገኙት የትም ቦታ ይውሰዱት" የሚለውን ነብያዊ ሰ.ዐ.ወ ምክር ተከትለን የፒካሶን የልጅነት ስንፍናንና የጌላ ስኬትን እንደ ማሳያ አውስተናል።

እድገት ዝግመት ያለበት፣ ለገምተኛና ዳተኛ፣ ለማህበራዊ ኑሮ የማይመች ግላዊ እንደሆነ ይናገሩ ነበር። በትምህርቱ እጅግ ሰነፍ ስለነበር በተደጋጋሚ ተመክሯል። የተሰጠውም ምክርና ማሻሻያ ሊለውጠው አልቻለም። በመጨረሻም ከትምህርት ቤት ተባረረ።

ቤተሰቡ የሙያ ትምህርት ቢገባው ብለው ወደ ፓሊቴክኒክ ትምህርት ቤቶች ወሰዱት። የዙሪክ ፓሊቴክኒክ ትምርት ቤትም እንዲህ አይነት ሰነፍ ልጅ አንቀበልም አለ። ... ነገር ግን በቤተሰቡ ብርቱ ድጋፍ ተሰጥኦውን ባማከለው የጥናት መስክ ሌት ተቀን ይለፋ ጀመር። በተለይ የፊዚክስ ምርምሩ የበለጠ ደስታን ሰጠው። በመስኩም ይበልጥ ገፋበት። በሂደትም የአለምን የፊዚክስ መስክ አንድ እርምጃ ለማራመድ ቻለ። ለአስተዋፅኦውም የኖቬል ሽልማት ለመቀበል በቃ።

ቶማስ ኤድሰን

1847 እ.ኤ.አ ለምድራችን ታላቅ የእድገት አስተዋፅኦ እንዲበረክት የሚነገርለት አውቱ ሳይንቲስት ቶማስ ኤድሰን የተወለደበት ዓመት ነው። ቶማስ በልጅነቱ እጅግ አስቸጋሪና ሰነፍ ልጅ ነበር። መናገር እንኳን የጀመረው አራት ዓመት ሲሞላው ነበር። መናገርም እንደጀመረ ጥያቄዎችን ያበዛ ነበር። በተለይ መምህሮችን በበርካታ ጥያቄዎች ማስልቸት የዘወትር ተግባሩ ሆነ። በዚህ የተነሳ ከትምህርት ቤት ተባረረ። እናቱም በ12 ዓመቱ የተለያየ ምርምር የሚያደርግበት ላብራቶሪ (Science lab) ከቤታቸው ስር ከፈተችለት። ጊዜውን በምርምሩ ላይ ማሳለፍን ተያያዘው።

ከቤት ውስጥ ከሚያደርገው ምርምሩ ጎን ለጎን ጎዳና ላይ ጋዜጦችንና ከረሜላዎችን እያዞረ በመሸጥ ወላጆቹን ያግዝ ገባ። ታዲያ አንዴ በአንድ ባቡር ጣቢያ አካባቢ እየተዘዋወረ ሲሸጥ አንድ በባቡር ተገጭቶ ሊሞት የነበረን ህፃን ሮጦ በመድረስ አዳነው። የህፃኑ ቤተሰብም በጣም ደስ ስላላቸው ቶማስን ለመሸለም ወሰኑ። የባቡሩ ጣቢያ የሚጠቀመው Morse Code የሚባል መልእክቶችን ወደ ቃላት የሚለውጥ የስልክ መገናኛ ነበራቸው። ይህን መሳሪያ ኤድሰን በጣም ወዶት ስለነበር፣ የህፃኑን አባት ይህን መሳሪያ እንዲሸልመው ጠየቀው። ግለሰቡም ልጁን በማዳኑ በጣም ደስተኛ ስለነበር መሳሪያውን ሸልሞ አጠቃቀሙንም አስተማረው።

ይህ መሳሪያ ለቶማስ ኤድሰን የምርምር እይኑን የከፈተለትና ከእምቅ ሀይሉ ጋር ያስተዋወቀው አጋጣሚ ሆኖ አለፈ። በምርምሩ ላይ አመታትን አሳለፈ። በሂደትም የኤሌክትሪክ መብራትን ለዓለም አስተዋወቀ። ይህ የኤሌክትሪክ መብራት በ September 4, 1882 ነበር ስራ ላይ የዋለው። ይህ መከራውም በኒዎርክ ከተማ አንድ Square Mile በሚሸፍን ጎዳና ላይ ተተገበረ። ያኔ ኒውዮርክ አሸብርቃ አደረች።

በሂደት KinetoScope የተባለና ፊልሞችን የሚቀርፅ ካሜራ ለዓለም ገበያ አበቃ። ከተጨማሪ ጥናት በኋላ በርካታ ሰዎች በህብረት ተሰብስበው ፊልም ሚመለከቱበት Vitascope የተባለ ትልቅ እስክሪን ያለውን መሳሪያ አበርክቷል። ... ኤዲሰን በህይወት እያለ ከ 1000 በላይ ግኝቶችን ለዓለም

መጀመሪያ ወደ ምርምር የመራውን መሳሪያን (Telegraph) በጣም ይወደው ነበር። ይህ መሳሪያ መልዕክቶችን የሚያስተላልፈው ነጠብጣቦች (Dots) እና መስመሮች (Dashs) በመጣመር በሚወዱት መልዕክት ሲወዱ መመልከቱ የፊጠራ አይኑን ከፍቶለታል። Dot ና Dash የሚባሉትን ይወዳቸው ነበር። ለዚያ ነው የልጆቹን ቅፅል ስም Dot & Dash ሲል የሚጠራቸው። ልጆቹን ሲጠራ እነዚያ ወደፊጠራ የመሩትንና ከተሰጥኦው ጋር ያስተዋወቁትን መሳሪያዎች ማስታወስ ይፈልግ ነበር።[108]

አስቡት አላህ ቶማስ ኤድሰንን የኤሌክትሪክ ሀይል እንዲፈጥር ባይመራው ኖሮ ምድር ምን ልትመስል እንደምትችል መገመት አይከብድም።

የልጆቻችን የህፃንነት ስንፍና ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም። ተሰጥኦዎቻቸውን ፈልገን በዚያው እንዲገፉ ማገዝ ይኖርብናል። የሚፈልጉትን መስክ እንዲመርጡ ነፃነቱን ልንሰጣቸው ይገባል። በልጅነት የህይወት አላማ እንዲያሰምሩ መርዳት ይጠበቅብናል።

[108] DO YOU HAVE A BIG IDEA? A Book about - Adson

8.2 የህይወት ግብ ለጡረተኞች[109]

ጡረተኞችን ማነው ተጣሪ ያደረጋቸው? ገና አካላቸው ሳይደክም፣ለአመታት ያካበቱት የስራ ልምድ እያላቸው፣በረጅሙ እድሜያቸው ያንለበቱት ሰፊ ተሞክሮ ይዘው፣ አዕምሮአቸው ማሰቡን ሳያቆም! የመስራት ወኔያቸው ሳይደክም፣ ለዓመታት ያጠናከሩት ሰፊ የግንኙነት መረብ እያላቸው... እኮ ማነው ባክህ ተጣሪና ጥገኛ ያደረጋቸው?

"የህይወት ግብ ለሁሉም"! ብለን ይህን ምዕራፍ ጀምረናል። ሁሉም የዚህች ምድር የቤተሰብ አካል ስለሆነ ለቤተሰቡ እድገት መስራት ይጠበቅበታል ስንል ተወያይተናል። ከምድር ነዋሪዎች ውስጥ ደግሞ የሰፊ ህይወት ተሞክሮ ባለቤት የሆኑት አረጋዊያን ናቸው። እነዚህ አባቶቻችን ያን ሁሉ የህይወት ተሞክሮ ይዘው እያለ ተጣሪና ጥገኛ አድርገን፣ ቀኑ አልገፋ ብሏቸው ፀሀይ ሲሞቁ የሚውሉ አድርገን መተው ለአንድ ሀገር ትልቅ ኪሳራ ነው።

የቻይና አንዱ የእድገት ምንጭም ይህ ነው። የቻይና ጡረተኞች በጡረታ ከስራ ሲሰናበቱ ጥቂት የማይባሉት የግል ቢዝነስ ጀምረው ገቢ ለመፍጠር በአዲስ ትጋት ይነሳሉ። ጥቂት የማይባሉ የኛ ሀገር አባቶች ደግሞ በ65 ዓመት ጡረታ ይወጡና ቀሪውን እድሜያቸውን የቡና ወሬ በማውራት ያሳልፉታል። ከቤተሰቦቻቸው (በተለይ ከሚስቶቻቸው ጋ) አለመግባባት የሚጀምሩት ገና ጡረታ በወጡ ማግስት ነው።

አባቶቻችን ሰፊ የህይወት ልምድ አዳብረዋል፣ አዕምሯቸውም በተሞክሮ የንለበተ ነው። ታዲያ ይህን ሁሉ ጥሬ ሀብት በ65 ዓመታቸው በጡረታ ስም ከአገልግሎት መስጫ ክልል ውጭ ማድረግ ተገቢ ነውን? ገና የመስራት ወኔያቸው ሳይነጥፍ፣ ጡረተኛ ብሎ ከማስቀመጥ በላይ አባቶችን መበደል ያለ አይመስለኝም። እኔ እንዲያውም ይህ ጡረተኛ የሚባለው ስም መለወጥ አለበት ነው የምለው። የአባቶችን የስራ ሞራል የሚያሽመደምድ መጠሪያ ነው። ከጡረታ በኋላ በቀራቸው እድሜ ጥገኛ ነኝ ብለው እንዲያስቡ የሚያደርግ መጠሪያ ነው። ገና በጠዋቱ አርጅተናል

[109] በአሁኑ ሰዓት ከዓለም ህዝብ መሀል 10%ቱ አረጋውያን ናቸዉ። ይህ የአረጋውያን ሲሆን የጡረተኞች ቁጥር ደግሞ ከዚህ በላይ መሆኑን ልብ በሉ። ይህ ማለት ደግሞ በዓለም ላይ ከ 700 ሚሊዩን በላይ አረጋውያን አሉ ማለት ነው።

ብለው እንዲያስቡ ነው የምናደርጋቸው። ጡረተኞች እየሰሩ ቢኖሩ እኮ እርጅና አይጠጋቸውም። የልጅ እጅ እያዩ ከመኖር፣ በዘመድ አርዳታ ከመደገፍ ይድናሉ። ራሳቸውን እንዳስከበሩ ህይወትን ይዘልቃሉ። "እንተም የቤት እመቤት፣ እኔም የቤት እመቤት" ብላ የምትንቃቸው ባለቤት አትኖራቸውም ነበር።

እም! ጡረተኞች ገና አላረጁም። እርጅና የሚጀምረው ከአዕምሮ ነው። አንድ ለው እርጅቻለሁ ብሎ ካሰበ ያረጃል። እኛ እንዲህ እንዲያስቡ መፍቀድ የለብንም። እንዲህም እንዲያስቡ ማድረግ የለብንም።

ለእኔ ነጩ ሽበታቸው ውበታቸው፣ የተሸበሸበው ግንባራቸው ግርማቸው፣ የተጨማደደው ቆዳቸው ክብራቸው፣ እርጋታቸው ብስለታቸውን... ጠቋሚ ነው። መቼም ቢሆን የጥንካኝነታቸው መገለጫ አይሆንም።

Experience is Stronger than Strength – "የህይወት ተሞክሮ ከጥንካሬ በላይ ጠንካራ ነው" ያለው ማን ነበር?

እኔ አላረጀሁም

ታላቁ ሊቅ ኢብኑ ዐቂል በ80 ዓመታቸው ትልቅ ወኔን ያነገቡ የዐረብኛ ሰዋሰው አባት ነበሩ። እንዲህ ይሉ ነበር፡- "እኔ አላረጀሁም፣ ወኔዬ፣ ሞራሌ፣ ቸርነቴ፣ እምነቴ... አላረጀም። ጥቁሩ ፀጉሬ ወደ ነጭ ቢለወጥም፣ የፀጉር ሽበትና የሞራል ሽበት አንድ አይደለም። እኔ ከነሙሉ ወኔዬ ነኝ"።[110]

እም! ስሜት ሲተኛ፣ ሞራል ሲወድቅ፣ አዕምሮ ሲያረጅ ነው የሰው ልጅ የሚያረጀው። እስኪ የስልሳ አምስት አመት አባት የሰሩትን ስራ ላጫውትህ፡-

ኪንታኪ

ለአብዛኞቻችን ቆንጆ የዶሮ ጥበስ ስም ጥቂት ብንባል "ኪንታኪ ፍራይድ ችክን"ን በተቀዳሚነት እናወሳ ይሆናል። በአሁኑ ሰዓት አሜሪካ ከምትታወቅባቸው አለም አቀፍ ምርቶች (እንደ ኮካ ኮላ ከመሳሰሉ

[110] ኢብኑ ዐቂል - ታላቅ የኢስላም ምሁር

ምርቶች) ተርታ የሚሰለፍ ተወዳጅ ምግብ ሆኗል - ኪንታኪ።

ግለሰቡ ይህን የተጠበሰ ዶሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በምድረ አሜሪካ ሲያስተዋውቁ ተቀባይነት አጥተው ነበር። በጣም የሚገርመው ይህ አዲስ የምግብ አዘገጃጀት (recipe) ከአንድ ሺህ (1000) ጊዜ በላይ እደረሰ ተብሎ ተመልሰባቸዋል። ሽማግሌው ግን ተስፋ ሳይቆርጡ ጉዟቸውን ቀጠሉበት፣ ታዲያ አሁን አለም ላይ እጅ የሚያስቆረጥም ከተባለላቸው ምግቦች ግንባር ቀደሙ ለመሆን በቃ።

በጣም የሚደንቀው ሀርላንድ ዴቪድ ሳንደርስ ይህን የተጠበሰ ዶሮ አዲስ አዘገጃጀት (recipe) ለገበያ ለማቅረብ ሲያስቡ 65ተኛ ዓመታቸውን እያገባደዱ ነበር። አስቡት ኢትዮጵያዊ ቢሆኑ ኖሮ በጡረተኛ ስም የመስራት ጥረታቸውን ገድለን ጠዋት ጠዋት ጋቢ ደርበው ፀሀይ የሚሞቁ ሽማግሌ እናደርጋቸው ነበር።

ለዓለም ማሳየት አፈልጋለሁ

ከዘጠኝ ዓመት በፊት ጋዜጦች አንድ ድንቅ ታሪክ አስነብበውን ነበር። ነገሩ ወዲህ ነው፡- አንዲት በእድሜ የገፉ እናት ትምህርት ለመማር ይወስናሉ። ምንም እንኳን በልጅነታቸው መማር ፈልገው ባይሳካላቸውም፣ ምድርን ከመልቀታቸው በፊት ይህን ህልማቸውን እውን ለማድረግ ወስነዋል። የአርጅናውን ሜና ተቋቁመው ትምህርታቸውን በዕናት ቀጠሉበት። ከተወሰኑ አመት በኋላ (በ92 ዓመታቸው) በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሳይንስ በከፍተኛ ማዕረግ ዲፕሎማቸውን ተቀበሉ።

በ92 ዓመታቸው ተምረው ምን ያደርግላቸዋል? ምንስ ይሰሩበታል? አጉል ጊዜያቸውን ነው ያጠፉት... ልትል እንደምትችል እገምታለሁ። እኚህ ሴት የአንተ ዓይነት ስሜት ለተፈጠረባቸው ሰዎች እንዲህ ሲሉ ነበር መልስ የሰጡት፡-

"ከልጅነቴ ጀምሮ መማር የምፈልግ ቢሆንም ለመማር እድሉን ባለማግኘቴ ሳልማር ቀርቻለሁ። አሁን ግን እድሉን ስላገኘሁት ተጠቅሜበታለሁ። አርግጥ ነው በተማርኩበት መስክ ሰራ ላልሰራበት አችላለሁ፣ ነገር ግን ትምህርት አስኪሞቱ ድረስ ሊማሩት የሚገባ እንደሆነ ለዓለም ማሳየት አፈልጋለሁ።"

ይህን ድንቅ ታሪክ በ22 ዓመታቸው ትምህርትን ለሚያቋርጡ ወጣቶች ማን በነገረልኝ?!

ህልሜ እውን ይሆናል

በልጅነታቸው ቁርዓንን ማንበብ ቢማሩም፣ እንደ አንዳንድ ጓደኞቻቸው ቁርዓንን በቃል (በልቦና) መሸምደድ (መሀፈዝ) ባለመቻላቸው የሸመደዱ ሰዎች ቀብር ውስጥ ሲኖሩ አካላቸው አይበሰብስም[111] ተብሎ መስጅድ ውስጥ ሲነገር ሰምተዋል። "ቁርዓንን የሀፈዙ ሰዎች በቀሩት (ባንበቡት)ና በሀፈዙት መጠን የጀነት ደረጃዎችን ይወጣሉ"[112] ሲባል አድምጠዋል። "እውቀትን ከአንቀልባ እስከ ቀብር ድረስ ፈልጉ" የሚለው የነብዩ መሐመድ ﷺ ንግግር ውስጣቸው ሁሌም ይመላለስ ነበር።

ታዲያ አንዴ ራሳቸውን ሰባዎቹን ያጋመሱ አሳውንት ሆነው አገኙት። በዚህ እድሜዬ ቁርዓንን መማር እችላለሁን? ሲሉ ራሳቸውን ጠየቁ። ውስጣቸውም በትክክል እንደሚሳካላቸው ነገራቸው። እኚህ ሴት ሰባዎቹን ቢያጋምሱም በትጋት ቁርዓንን መሀፈዙን (መሸምደዱን) ተያያዙት። ለዓመታት በፅናት ቀጠሉበት። ሲነሱም ሲቀመጡም ከቁርዓን ጋር ነበር። የሚያዳምጡትም የቁርዓን ካሴቶችን ሆነ... ከዓመታት ጥረት በኋላ በ82 ዓመታቸው ቁርዓንን ለመሀፈዝ በቁ።

እርጅና የአመለካከት እንጂ የፀጉር ከለር ለውጥ አይደለም። ታላላቅ ሰዎች እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ አላማቸውን ለማሳካት እንደጣሩ ታሪክ ያስተምረናል።

የህይወት ግብ ለሁሉም ያስፈልጋል። ህፃናት፣ ወጣቶች፣ ጎልማሶች፣ አረጋዊያን... ሁሉም እንደአቅማቸው የህይወት ዓላማቸውን ሊያስምሩ ይገባል። ያኔ አለም በሁሉም የቤተሰብ አባሎቿ ጥረት ያማረች መኖሪያ ትሆናለች።

[111] የነብዩ ﷺ አስተምህሮዎች
[112] የነብዩ ﷺ አስተምህሮዎች

9

ምዕራፍ ዘጠኝ



ወደ ስኬት ስታቀና

- ሚዛናዊ ህይወትን ምራ
- ሀብት ስኬት አይደለም
- ግብህ ሁሌም አብሮህ ይሁን
- ትችላለህ
- ለህይወትህ ራስህ ሀላፊነትን ውሰድ

9.1 ሚዛናዊ ህይወትን ምራ

"... ጌታችን ሆይ! በዚህች ምድር መልካምን ነገር ስጠን፡ በቀጣዩም ዓለም መልካም ነገርን ለግሰን.." [113]

ለሚዛናዊ ህይወት የቀረበ ታላቅ መርህ ነው። እንደ አንድ አላማውን ለማሳካት እንደሚንቀሳቀስ ግለሰብ፣ ለህይወትህ ሁሉም ክፍል ተገቢውን ትኩረት (መብቶችን) እየሰጠህ መንገዝ ይኖርብሃል። "...ለሁሉም ነገር ሀት ሀቁን (ድርሻውን) ስጡ" ይሉናል ታላቁ መልዕክተኛ ነብዩ ሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ.። ለግብህ የምትሰጠው ትኩረትና ጊዜ የአንበሳውን ድርሻ ቢይዝም፣ ሌላው የህይወት ክፍልህንም መዘንጋት የለብህም። "ህይወት ልክ ብስክሌት እንደመንዳት ናት፣ ሚዛንህን ለመጠበቅ ካለማቋረጥ መንቀሳቀስ የግድ ነው።" ይለናል አውቁ ሳይንቲስት አንስታይን።

አውቁ ፀሀፊ ፓውሎ ኮልዮ "The Alchemist"[114] በተሰኘው ተወዳጅ መፅሐፉ ውስጥ ያነበብኳትን ታሪክ ከራሴው የብዕር አጣጣል ጋር እነሆ፡-

ታላቁ ውርስ

አንድ ባለፀጋ አባት ከራሳቸው በላይ የሚሳሱለት ልጅ ነበራቸው። ብዙ ሊያወርሱት የሚችሉ ንብረቶች እንዳላቸው ቢያውቁም፣ እነዚህ ንብረቶች ሊጠበቁና ቀጣይ ሊሆኑ የሚችሉት አመለካከት ሲስተካከል መሆኑንም ረዥሙ እድሜያቸው አስተምሯቸዋል። የራሳቸውን የስኬት ጎዳና እንዲከተል ያደረጉት የእስከዛሬው ጥረት ባለመሳካቱ ተስፋ አልቆረጡም። ሌላ የማስተማሪያ መንገድን መረጡ። ከሌላ ሰው ጋ ሄዶ ትምህርት ቀስሞ እንዲመጣ ላኩት።... ወደ ጠቢቡ ሰው።

---

[113] ቁርአን 1፣ 201

[114] The Alchemist - የዘመናችን ተወዳጅ መፅሀፍ ነው። መፅሀፉ ስለ አንድ የህይወት ግቡን ለማሳካት ስለማሰን ግለሰብ በጣፋጭ ብዕሩ ይተርክልናል። ከአላማው ለመድረስ ያሳለፋቸውን ውጣ ውረዶች በአይነ ህሊናችን ያስቃኘናል። መፅሐፉን ሁላችሁም ብታነቡት መልካም ነው። አለም ላይ በስፋት የተሰራጨና ከ43 ሚሊየን ኮፒ በላይ የተሸጠ መፅሀፍ ነው። በአስር ቶይታዩ ከቀዘምኳቸው መፅሀፎች ውስጥ አንዱ ነበር- አልኬሚስቱ።

አንድ ሩቅ ቦታ የሚኖር በጥበቡ የታወቀ ግለሰብ ነበር። ይህ ጠቢብ ሰው ከሰው ራቅ ብሎ ጫካ ውስጥ በሚገኝ አንድ ጥንታዊ ቤተ-መንግስት ውስጥ ይኖር ነበር። የሚኖርበት ታሪካዊ ህንፃ እጅግ በጣም ትልቅ፤ እጅግ ብዙና እንዲሁም ድንቅ የሆኑ ቅርሶችን የያዘ፤ በብዙ ጎብኚዎች የተጨናነቀ ነበር። በጣም ደክሞና ዝሎ ከቦታው ሲደርስ፤ ከብዙ ጎብኝዎች አንዱ እንደሆነ ተመለከተ። ወደ ጠቢቡ የሚወጣውና የሚገባው ምክር ፈላጊ ሰው ብዛትና ዓይነት ለቁጥር ይታክታል።

ከእንግዳ መቀበያው ሰፊ አዳራሽ ውስጥ እንደገባ ሰፊ ጠረጴዛ ላይ የተደረደሩ ምግቦችን እንግዶቹ ሲመገቡ ተመለከተ። እርሱም ተጋራቸው። ተራውን የሚጠብቅ ሰው እንዳይሰለች ለማዝናናት አንድ ግለሰብ በአዳራሹ አንድ ጥግ ላይ ለስለስ ያለና ጣፋጭ ሙዚቃን ያነበንባል። ወጣቱም ለሁለት ሰዓት ያህል ሙዚቃን በአንክሮ እያለሳለሰ ተራውን ሲጠብቅ ከቆየ በኋላ ወደ ጠቢቡ ገባ። "የመጣህበት ጉዳይ ምንድን ነው?" ሲል ጠቢቡ ጥያቄ አቀረበለት። "ህይወቴን ስልት በተሞላበት መንገድ ለመምራት የሚያስችለኝን ጥበብ ለመማር ነው"። ሲል መለሰ።

"ሀሳብህ ጥሩ ነው። ነገር ግን አሁን ትንሽ ስራ አለብኝ ከሁለት ሰዓት በኋላ ተመልሼ አገኝሀለሁ። እስከዚያው ግን አንድ ነገር እያደረክ ቆየኝ አለና ዘይት የተሞላ ማንኪያ አቀበለው። ከዚያም እንዲህ አለው "በህንፃው ውስጥ እየተዘዋወርክ ያሉትን ድንቅ ቅርሶች በመመልከት መጠበቅ ያለብህን ሁለት ሰዓታት አሳልፍ። ነገር ግን አንድ ነገር እንዳትረሳ በማንኪያው ላይ ያለው ዘይት መፍሰስ የለበትም" ሲል ተሰናበተው።

ወጣቱም ሰዓቱን ከተመለከተ በኋላ ቅድም ሙዚቃቹን በተመስጦ እያሰላሰለ ያሳለፈውን ሁለት ሰዓታት አሁን ደግሞ የህንፃውን ውበት በመመልከት ለማሳለፍ ተንቀሳቀሰ።

ፈታኝ የሆኑ ሁለት ሰዓታትን ጨርሶ ተመለሰ። እጅግ አድካሚ የሆኑትን የቤተ-መንግስቱን ደረጃዎች ሲወጣና ሲወርድ ትልቅ ትኩረት የሰጠው በእጁ የያዘው ዘይት የተሞላ ማንኪያ እንዳይደፋበት ነበር።

እጁ ላይ የያዘውን ዘይት የተሞላ ማንኪያ ጠብቆ በማቆየቱ ልበ-ሙሉነት እየተሰማው ወደ ጠቢቡ ገባ። ጠቢቡም የህንፃውን ጉብኝት ውሉ ጠየቀው። "የዓለምን ዕውቀት በሙሉ የያዘውን ቤተ-መፅሐፍ

አየኸው? በምግብ አዳራሽ ውስጥ በግድግዳው ላይ የተሰቀለውን የጥንት አበቦችና የዛፎች ስዕል እንዴት ማራኪ እንደሆነ ተመለከትከው? ያንንስ የታወቁ አትክልተኞች አስር ዓመት የፈጀባቸውን የአትክልት ስፍራ አስተዋልከው?" ሲል አከታትሎ ጠየቀው። ወጣቱ ሀፍረት ተሰማው። አንገቱንም አቀረቀረ። ለሁለት ሰዓታት ባደረገው ቆይታ ትኩረቱ ሁሉ የነበረው ማንኪያው ላይ ያለው ዘይት እንዳይፈስበት መጠንቀቅ ላይ መሆኑን ተገነዘበ።

ወጣቱ ቢያዝንም ጠቢቡ ግን ደስተኛ ነበር። ምክንያቱም ሊያስተምረው የፈለገውን የህይወት ጥበብ ግማሽ መንገድ ስለመጣለት። ከዚያም እንደገና በማንኪያ ያለውን ዘይት ይዘህ ሂድና እነዚህ የነገርኩህንና እንዲሁም ሌሎችን አስገራሚ ቅርሶች እንደገና ተመልከተህ ተመለስ አለው። ይህ ወጣት እንደ አዲስ ሁለት ሰዓት ሙሉ በእጁ ዘይት የተሞላውን ማንኪያ ይዞ ሲወጣና ሲወርድ እንዳይሰለቸው በማሰብ ጠቢቡ ለወጣቱ እንዲህ የሚል ምክንያት ሰጠው "አየህ የአንድን ሰው ቤት በሚገባ ካላወቅክ ያንን ሰው ማመን ያስቸግርሀል። ለእኔ ምክር ዋጋ የምትሰጠው ቤቴ ውስጥ ያለውን እፁብ ድንቅ ጥበብ ስታስተውል ነው።"

ሀላፊነቱ ፈታኝ ቢሆንም የተሰጠውን ፈተና ለመወጣት ተንቀሳቀሰ። ጉብኝቱን ቀጠለ። ባየው ነገር በጣም ተደመመ። በእርግጥም ጥበብ የተሞሉ ስዕሎችን የያዘ ቤተ-መንግስት መሆኑን ተመለከተ። ለማመን የሚያዳግቱ ቅርፃ ቅርፆችን አስተዋለ። "በዚህ ጥበብ የተሞላበት ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው በእርግጥም ጥበበኛ መሆን አለበት" ሲል አሰበ።

ለሁለት ሰዓት ሙሉ ቤተ-መንግስቱን ያስዋበውን ድንቅ ጥበብ ሲመለከት ከቆየ በኋላ ከጠቢቡ ጋር ተገናኘ። ለጠቢቡ ዕድል ሳይሰጥ ያየውን ሁሉ በግርምት መተንተን ይዟል። ጠቢቡም ብዙ ካዳመጠው በኋላ "እንዳይደፋ ያልኩህ ዘይት የታለ?" አለው። ወጣቱም በፍጥነት በእጁ ወደ ያዘው ማንኪያ ሲመለከት ዘይቱ ሙሉ በሙሉ ተደፍቷል። በጣም ደነገጠ። የቤቱን አሰራር ውበትና የግቢውን ድንቅ ጥበብ ሲመለከት ያገኘው ደስታ ሁሉ ጠፋበት። በተቃራኒው ግን ዳግመኛ ጠቢቡ በጣም ደስ አለው። ምክንያቱም ሊያስተምረው የፈለገው ነገር ስለተፈፀመለት። አያይዞም መጀመሪያ ሊጠይቀው ለመጣው ጥያቄ እንዲህ ሲል መልስ ሰጠው።

"ስኬታማ ህይወት ማለት ሚዛናዊነት የተላበሰ ህይወት መምራት መቻል ነው። ሚዛናዊነት ማለት ደግሞ ዙሪያህን አያየህ በማድነቅ ስትኖር በእጅህ ላይ ያለውን አደራ አለመዘንጋት ነው።"

ይህ ታሪክ ለሚዛናዊነት ህይወት አስፈላጊነትና ወሳኝነት ምሳሌ ይመስለኛል። ሁሌም ቢሆን ከሚዛናዊነት ጎራ መውጣት የለብህም። በዙሪያህ ላሉት ሁሉ ድርሻቸውን (መብታቸውን) ስጥ። ለአካልህ፣ ለጤናህ፣ ለትዳርህ፣ ለራስህ፣ ለትምህርትህ... ሁሉም በአንተ ላይ ሀቅ (መብት) ላላቸው ሁሉ የሚገባቸውን ድርሻ ስጥ።

ስለዚህ ወደ ስኬት ስታቀና ሰማይን ከምድር፣ ሲጋን ከመንፈስ፣ ዱንያን ከአኼራ (ከመጪው ዓለም) አትለይ ለሁሉም ድርሻቸውን ስጥ። ሚዛናዊነት የስኬትን በር ይከፍታልና ህይወትህን ከዚህ አንፃር ቃኘው። ወደ ስኬት የምናደርገው ግስጋሴ አሰልቺ እንዳይሆን ለሁሉም እኛነታችን ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይጠበቅብናል።

ራስን በተመለከተ

የሰው ልጅ አራት መሰረታዊ ክፍሎች እንዳሉት ይታመናል። **የመጀመሪያው አካሉ** (Physical intelligence) ነው። ይህን አካሉን ሁሌም ሊጠብቀው ይገባል። አመጋገብን በማስተካከል፣ ቋሚና ተመጣጣኝ የአካል እንቅስቃሴ በማድረግ፣ ጭንቀትና ውጥረትን በአግባቡ የማስተናገድን ጥበብ በመጠቀም... አካላችንን መጠበቅ ይኖርብናል።

ሁለተኛ፦ አዕምሮአችን (Mental intelligence) ነው። አዕምሮን ደግሞ ሁሌ መመገብና ማሳደግ ይኖርብናል። ትምህርቶችን በመማር፣ቋሚ የንባብ ፕሮግራሞችን በመከታተል እና ጥልቅ ጥናቶችን በማድረግ... ሁሌም ግንዛቤያችንን ማጎልበት ይጠበቅብናል።

ሶስተኛው፦ መንፈላችን (Spiritual Intelligence) ነው። የሰው ልጅ ማንነት መገለጫ ነው። የሰው ልጅ ህልውና የሚለካው በመንፈሱ ምጥቀት ወይም ዝቅጠት መጠን ነው። መንፈሳዊነታችንን (ኢማናችንን) ሁሌም መጠበቅ ይገባናል። መንፈሳዊ ክንዋኔዎችን በመፈፀም፣ መለኮታዊ መፅሀፍትን በማንበብ እንዲሁም ፈጣሪን ጠዋትና ማታ በማወደስ... ሁሌም ውስጣችንን ህያው ልናደርግ ይገባናል። አራተኛው ክፍል ደግሞ፦ ስሜታችን (Emotional Intelligence) ነው።

ለእነዚህ ለአራቱም የሰው ልጅ ክፍሎች ተገቢውን ድርሻ ልንሰጥ ይገባል። እነዚህን ክፍሎች ማሟላት የተሟላ ስብዕናን ይሰጠናል። የአራቱን ሚዛን መጠበቅ የስኬት ጉዟችንን ያፋጥንልናል።

በተጨማሪም ማህበራዊ ህይወታችን፣ ቤተሰብን፣ ልጆችን፣ ቤተ-ዘመድ፣ የጓደኛ ግንኙነት፣ ስራችን... ሁሉንም በሚዛናዊነት ልንመራ ይገባናል።ለሁሉም የህይወት ክፍላችን ተገቢውን ጊዜ መስጠት ይጠበቅብናል። ሚዛናዊ ህይወት ሁሌም ለስኬት ግብዓት ነውና።

"እርጥብ እትሁን ትጨቀያለህ፣ ደረቅ እትሁን ትሰበራለህ"
(ሉቅማን - እውቁ ኢትዮጵያዊ ጠቢብ)

9.2 ሀብት ስኬት አይደለም

ሀብት በየትኛውም መስፈርት ስኬት ሊሆን አይችልም። አንተ በሀብትህ መጠን ከመለካት ከፍ ያልክ ነህ። የአንተ መገለጫ ያለህ ነገር ከሆነ፣ ያ ነገር በተለየህ ጊዜ አንተ ማን ትሆናለህ? Sean እንዲህ ሲል ይጠይቃል፦

"If who I am is what I have, and what I have is lost, then who am I?"[115]
"የአኔ ማንነት የያዝኩት ንብረት ከሆነ፣ የያዝኩት ንብረት ደግሞ ድንገት ከጠፋ፣ አኔ ማን ነኝ?"... አዎ! ሀብት የማንነትህ መገለጫ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ወይ አንተ ጥለኸው ትሄዳለህ፣ አልያም እርሱ ጥሎህ ይዳል።

9.2.1 ጥሎህ ይሄዳል

ከአሁን በፊት እንደተመለከትነው ሀብት ብቻውን ስኬት አይደለም። ሀብት መዳረሻ (Means) እንጂ በራሱ መድረሻ (የመጨረሻ ግብ) አይደለም። የሰው ልጅ በህይወቱ ድንገት በተከሰቱ ችግሮችና አጋጣሚዎች ከቢልዮኖች የሀብት ምጥቀት ወደ ድህነት ዝቅጠት ሊምዘገዘግ ይችላል። በተፈጥሮ አደጋዎች አልያም በድንገተኛ የዋጋ ማሽቆልቆል የድህነት ወለል ላይ ራሱን ሊያገኘው ይችላል። ሺቭ ኬራ "You can win" ብለው በሰየሙት መፅሀፋቸው ያሰፈሩት አስገራሚ ታሪክ፣ ሀብት ብቻውን ስኬት

[115] Sean — The Seven Habits of Highly effective Teens (P. 20)

እንዳልሆነ ማሳያ አማኝ ይመስለኛል። ታሪኩን እነሆ፦

በ1923 ዓ.ል በዓለማችን አሉ የሚባሉ ስምንት ቱጃሮች ቺካጎ በምትባለው የአሜሪካ ከተማ ስለ ስኬትና ስለሀብት ለመነጋገር ተሰብስበው ነበር ይባላል። አጠቃላይ የሀብታቸው ድምር በዚያን ዘመን ከነበረው የዩናይትድ ስቴት መንግስት ጠቅላላ ሀብት ይበልጥ እንደነበር ይገመታል። እነዚህ ሰዎች በአርግጥም እንዴት መኖርና ገንዘብ ማከማቸት እንደሚቻል በሚገባ ያውቁ ነበር። ነገር ግን ከ25 ዓመታት በኋላ ምን እንደገጠማቸው እንመርምር፦

1. የግዙፍ ብረት አምራች ኩባንያ ፕሬዝዳንት የነበረው ቻርልስ ሽዋብ ለአምስት ዓመታት በብድር ካፒታል ሲንቀሳቀስ ከቆየ በኋላ ለኪሳራ ተዳርጎ ሞተ።

2. የግዙፍ ጋዝ አምራች ኩባንያ ፕሬዝዳንት የነበረው ሀዋርድ ሀብሰን በመጨረሻ ቀወሰ።

3. ከአለማችን ትላልቅ የሸቀጥ ነጋዴዎች አንዱ የነበረው አርተር ከተን (Arthur Cutten) ቤሳቤስቲ ሳይኖረው በእዳ ተዘፍቆ ሞተ።

4. የኒውዮርኩ ስቶክ ገበያ ፕሬዝዳንት (The president of the new York stock Exchange) የነበረው ሪቻርድ ዊትኒ እስር ቤት ለዓመታት ማቅቆ ልክ ሲፈታ ሞተ።

5. የፕሬዝዳንቱ ካቢኔ አባል የነበረው አልበርት ፎል በሰላም ቤቱ ውስጥ ህይወቱ እንዲያልፍ በሚል በምህረት ከእስር እንደተፈታ ብዙም ሳይቆይ ሞተ።

6. የምልስትሪቱ ትልቁ ስርዓት-አልበኛ ጆሲ ሊቨርሞር ራሱን አጥፍቶ ምድርን ተሰናበተ።

7. የአለማችን ታላቁ ሞኖፖሊ ፕሬዝዳንት ኢቫን ክሩገር ራሱን አጠፋ።

8. የኢንተርናሽናል ሴትልመንት ባንክ ፕሬዝዳንት ሊኑን ፍሬሰር ራሱን አጥፍቶ ዓለምን ጉድ አሰኘ።[116]

[116] Shive Khera — You can win P. 247 , Maxwell — Your Road Map for Success. ለአሸናፊነት መንዛት- ማህሌት ጥላሁንና ዳኜ መላኩ

እነዚህ የሀብት ማማ ላይ የወጡ ባለፀጋዎች ፍፃሜ ስኬት ሀብት እንዳልሆነ በቂ ማሳያዎች ሆነው አልፈዋል። ስኬት ከሀብት በላይ ነው። ገንዘብ አንድ ቀን ጥሎህ ይሄዳል፤ አልያም አንተ ጥለኸው ትሄዳለህ።

9.2.2 አንተ ጥለኸው ትሄዳለህ

በሞት የምትለየው ስኬት ሙሉ ስኬት አይደለም። ሀብትም ከነዚህ በሞት ትተኻቸው ከምትሄዳቸው ፀጋዎች ውስጥ አንዱ ነው። አለም በርካታ ሚሊየነሮችን አውቃለች። ሁሉም ግን ወደ ቀብር ተጠቅልለው ከገቡበት ልብስና ሳጥን ውጭ ሌላ ይዘው አልሄዱም። የአለምን ሁለት አቅጣጫ (East &West) ስለገዛ ታላቅ ንጉስ የምድር ስንብት ትንሽ እናውሳ፦

ታላቁ አሌክሳንደር (Alexander The Great)

ታላቁ መሪ አሌክሳንደር ከእየሱስ (ዓ.ሳ) ልደት በፊት በ ጁላይ 17/356 ነበር የተወለደው። የትውልድ ቦታውም በጥንት ዘመን መቄዶኒያ፤ ዛሬ ደግሞ ግሪክ ተብላ በምትታወቀው የአውሮፓ ሀገር ውስጥ ነበር። በወታደራዊ ጥበቡ የሚታወቀው ታላቁ አሌክሳንደር አለምን ለተወሰኑ ጊዜያት ተቆጣጥሮ እንደነበር ይነገራል። ዕድሜው ገና 30 ዓመት ሳይሞላው ከህንድ ጀምሮ እስከ ግሪክ ያለውን 3 ሺህ ማይልስ የዓለማችንን መሬት በግዛቱ ስር አድርጎ ነበር።

የንጉስ ፊሊፕ ልጅ እንደመሆኑ ከአባቱ ፓለቲካዊና ወታደራዊ ጥበብን የመማር እድል በልጅነቱ አግኝቷል። አርስቶትልን ጨምሮ በበርካታ ልሂቃን ትምህርት ተከታትሏል። Botany, Science, Anatomy, History, Literature, Political Science... እና ሌሎችንም በስፋት ተምሯል። ሰፊ ግንዛቤና የንባብ ልምድ እንደነበረው ይነገራል።

ይህ በሳል መሪ ገና በ32 ዓመቱ አለምን መምራት የቻለ ታሪካዊ ሰው ነበር። አሌክሳንደር ገና በጠዋቱ ምድርን በመዳፉ ማስገባት የቻለ ብቻ ሳይሆን፤ገና በለጋ እድሜው ምድርን የተሰናበተ መሪ በመሆኑም ይታወቃል።

አሌክሳንደር በጣም ታሞ ሞቱን እየጠበቀ በነበረበት ወቅት እንግዳ የሆነ ኑዛዜን በዙሪያው ላሉ ሰዎች ተናገረ። ጀኔራሎችን በማስጠራት እንዲህ ሲል ኑዛዜውን አስተላለፈ፦

"ስሞት አስክሬን ሳጥን ውስጥ ስታስገቡኝ እጆቼን እንደተለመደው አታጣምሯቸው። ከአስክሬን ሳጥኑ ጫፍና ጫፍ ላይ አድርጓቸው። የእጆቼ መዳፎችም በግልፅ ተዘርግተው ይታዩ። እጆቼ ላይ ምንም ነገር እንደሌለ በግልፅ ይታይ"።

ይህ እንግዳ (Odd) የሆነ ኑዛዜ አብዛኛውን ሰሚ ግራ ያጋባ ነበር። ከኑዛዜው በኋላ ብዙም በህይወት አልቆየም። በ32 ዓመቱ ምድርን ተሰናበተ። የቀብር ሥነ-ስርዓቱም በንጉስ ደንብ መሰረት በደማቁና ባማረ መልኩ እየተከናወነ ነው። በቀብሩ ስነ-ስርዓት ላይ ብዙ የዓለማችን ታላላቅና የተከበሩ ሹማምንት ተገኙ። እንግዶቹ ግን አስክሬኑን ሲመለከቱ በጣም ተገረሙ። የአሌክሳንደር እጆች በራሳ ሳጥኑ ጫፍና ጫፍ ሆነው የእጆቹ መዳፍም ተዘርግቶ ተመለከቱ። ይህን እንግዳ ድርጊት ለማጣራት ሹማምንቶች ለጀኔራሎቹ ጥያቄ አቀረቡ።

አንድ የሀገሬው ልሂቅም "እናንተ ሰዎች ሆይ! ታላቁ አሌክሳንደር በተናዘዘው መሰረት ነው አስክሬኑን በዚህ መልኩ ያዘጋጀነው። አሌክሳንደር ይህችን ዓለም ሲገዛ አለ የሚባል ወርቅ፣ ነሐስና በርካታ ሀብት በእጁ ነበር። አሁን ግን ወደ ማይቀረው ዓለም ሄዷል። ይህችን በመዳፉ ስር የነበረችውን ዓለምና ፀጋዎቿን ሁሉ ትቶ ባዶ እጁን ምድርን ተሰናብቷል።" በማለት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተናገሩ።[117]

የምድርን አንጡራ ሀብት በእጁ ያስገባው ታላቅ መሪ ባዶ እጁን ወጣ። ምድርን በጠባብ ሳጥን ውስጥ ሆኖ ተሰናበታት። አዎ! ሀብት ለዋናው ስኬት (The Goal of Goals) ግብዓት (InPut) እንጂ የስኬታችን ጉዞ ሚቋጭበት የመጨረሻ ውጤት አይደለም። ይህንን በውል የተረዱት ግሪካዊው ሚሊየነር (አሪስቶት) የሚሉትን ስሟቸው፦ "የተወሰነ ደረጃ ከደረስኩ በኋላ የገባኝ ነገር ይህ ነው፤ ገንዘብ ዋጋ ቢስ ነው። ስኬት ከገንዘብ ይበልጣል"

---

[117] Roopa Gosai — World Famous Personalities. P. 9-14, ምርጥ አስላማዊ ታሪኮች - ፀ አወድ አብዱልሰቡር ገፅ 27-28

ከሰላሳ ሚሊየን ቅጅ በላይ በተሸጠላት "Be Your Self" በተሰኘው ውድ መፅሀፏ ውስጥ ሊንዳ እንዲህ ትመክረናለች፡-

"ገንዘብ ውስጣዊ ሰላምንና ሁለንተናዊ እርካታን ሊገዛ አይችልም። ሁሉን አይነት ፍላጎቶቻችንን ከቁሳዊው ዓለም ብቻ ለማሟላት የምንፈልግ ከሆነ መቼም እውነተኛ ደስታ አንጎናፀፍም። በቂ ምግብ፣ አልባሳትና መኖሪያ መጠለያ ካገኘን በኋላ ከቁሳዊው ዓለም በላይ ማሰብ ካልቻልን እውነተኛ ደስታንና በራስ መብቃቃትን ልንጎናፀፍ አንችልም። ቁሳዊ ነገሮችን ብቻ እያሳደዱ ብልጭልጭ ነገሮች ውስጥ መጥፋቱ ቀላል ቢሆንም ደስታው ለረጅም ጊዜ አይቆይም።"[118]

ወደ ስኬት ስታቀና ልትረሳው ከማይገቡ እውነታዎች ውስጥ አንዱ ይህ ነው- ስኬት ከሀብት በላይ ነው። ሀብት ለመሰረታዊውና ለዋናው ግባችን መዳረሻ እንጂ ሌላ አይደለም። ስለዚህ ራስህን ቀና አድርግና ከሀብት ባሻገር ወዳለው እውነተኛ ስኬት አማትር፣ ቀበቶህን ዳግም ጠበቅ አድርግና ወደ ዋናው ስኬት አቅና።

[118] Lynda Field- Be Your Self P.57-58, ራስን መሆን -በረከት ብርሀኑ 2001

9.3 ግብህ ሁሌም አብሮህ ይሁን

የቀረፅከው ግብ፣ ያሰመርከው የህይወት አላማ ሁሌም ከአይንህ አይጥፋ። በዙሪያህ ያሉ ነገሮች ሁሉ ይህን ግብህን የሚያስታውሱህ ይሁኑ። መኪናህ ላይ፣ የሞባይል መጥሪያህ ላይ፣ የላፕቶፕ እስክሪን ሴቨርህ ላይ፣ መኝታ ቤትህ ላይ፣ የቢሮ ጠረጴዛህ ላይ.... የህይወት ግብህን አስቀምጠው። ይህ ድርጊትህ አላማህን ሁሌም እንዳትዘነጋ ያደርግሀል። ከአላማህ ጋር ዘወትር እንድትኖር ያግዝሀል።

ፊሊፕስ ካምፓኒ

የፊሊፕስ ካምፓኒ ምርቶች በአሁኑ ሰዓት ዓለም ላይ ሁሉም ቦታ ይገኛሉ። በኤሌክትሮኒክስ አቅርቦት ዓለምን ከሚመሩ ጥቂት ድርጅቶች ውስጥ ፊሊፕስ አንዱና ዋነኛው ነው። ይህ ግን ዝም ብሎ የተገኘ ውጤት አይደለም። ግልፅ ራዕይን አንግቦ፣ ሁሌም ከአላማ ጋር በመኖር የተገኘ እንጅ።

የዚህ ግዙፍ ካምፓኒ ማኔጀር በበላል አመራራቸው ይታወቃሉ። ከቢሯቸው ጣራ (ኮርኒስ) ላይ የድርጅታቸውን ራዕይ በግልፅ ፅፈው ለጥፈዋታል።

"ፊሊፕስን ለዓለም ማድረስ" የሚል ራዕይ ኮርኒሱ ላይ ተሰቅሏል። ታዲያ ሁሌም ግለሰቡ ጠረጴዛቸው ላይ ተደፍተው ሲሰሩ ይቆዩና ደክሟቸው ወደ ወንበራቸው ደገፍ ብለው ዘና ሲሉ ይህን ፅሁፍ ይመለከቱታል። ፅሁፉም ራዕያቸውን ያስታውሳቸዋል። ፊሊፕስን የአለም ጥግ ለማድረስ ትልቅ ፅናት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማቸዋል። ታዲያ ወዲያውኑ ትጋትን ተላብሰው ያለመትን ራዕይ ለማሳካት በአዲስ ሞራል ዳግም ወደስራቸው ያቀረቅራሉ። በቃ ይህ ነበር ኮርኒሱ ላይ የድርጅቱን ራዕይ የለጠፉበት አብይ ምክንያት።[119] ሁሌም አላማቸውን በማሳካት ላይ እንዲጥሩ፣ ከአላማቸው አንዳር እርምጃቸውን ሁሌም እንዲቃኙ።

በየቀኑ ወደ ግብህ የሚያደርስህን አንድ ነገር አድርግ- የራዕይና የግብ ጉዳይ በወር አንድ ጊዜ ወይም ደግሞ ሲመችህ እያሰብክው የሚደረስበት

[119] ዶ/ር ዐምር ካሊድ - ሀታ ዩገይሩ ማቢአንፉሲሃም

ጉዳይ አይደለም። አምስቱም የስሜት ህዋሳቶችህ ካለማቋረጥ መሳተፍ አለባቸው። ግብህን ውስጥህ ካለማቋረጥ ማየት አለበት። በእጆችህ በመተግበር መዳሰስ አለብህ፣ ስለግብህ ለማንነትህ በመንገር ራስህን ማስታወስ አለብህ።

የግብህን ጣፋጭነት ማጣጣም አለብህ፣ የግብህን መልካም ጠረን ማሽተት አለብህ። ይህ ደግሞ ሊሆን የሚገባው በየቀኑ ነው። ወደ መኝታህ ከመሄድህ በፊት ግብህን አስበህ ተኛ። ይህንን ማድረግህ ውስጠ-ህሊናህ (Subconscious mind) ግቡን አብስሎት እንዲያድር ያደርገዋል። ጠዋት ወደ ተግባርህ ስትሰማራ ግብህን በቅርብ በምታይበት ስፍራ ለጥፈው፣ ውሎህን ከግብህ ጋር አድርግ። ይህንን ስታደርግ ግብህ ከመድረስ ውጪ ምንም ምርጫ አይኖርህም።[120]

"በህይወት ጎዳና ላይ ስትጓዙ አይናቻችሁን ከግባችሁ ላይ አትንቀሉ። ትኩረታችሁ በቦምቦሊኖው ላይ እንጂ በቀዳዳው ላይ አይሁን።"

ስቲቭ ጆብስ

አይፎንንና አይፓድን በዚህ ዘመን የማያውቅ አለ እንዴ? በዚህ ዘመን እነዚህ የኤሌክተሮኒክስ መሳሪያዎች የዘመናዊነት መገለጫዎች ሆነዋል። የአፕል ካምፓኒ አንዱ መስራች የሆነው ስቲቭ ጆብስ ነው ለድርጅቱ ስኬት የማይተካ ሚና የተጫወተው።

ስቲቭ ከአፍላ ወጣትነቱ ጀምሮ ከአላማው ጋር ተሰፍቶ የኖረ ሰው ነበር። ስለራሱ ሲናገር እንዲህ ይላል፦

"የአስራ ሰባት ዓመት ወጣት ሳለሁ እንዲህ የሚል አባባል አነበብኩ። "እያንዳንዷን ቀን ልክ የመጨረሻህ እንደሆነች አድርገህ ከኖርክ አንድ ቀን ትክክል (ስኬታማ) ትሆናለህ" ይላል። ይህ አባባል አእምሮዬ ውስጥ ከፍተኛ ስሜት ነው ያሳደረው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ላሉት 33 ዓመታት በእያንዳንዱ ቀን ማለዳ በመስታወት ፊት እየቆምኩ ራሴን እንዲህ ብዬ እጠይቃለሁ፦ "ዛሬ የህይወቴ የመጨረሻ ቀኔ ቢሆን ዛሬ ልሰራው

[120] አዮብ ማሞ (ዶ/ር) -25 የስኬት ቁልፎች

ያቀድኩትን ነገር መስራት አፈልጋለሁ? መልሱ ለተከታታይ ቀናት "መስራት አልፈልግም" የሚል ከሆነ፣ የሆነ ነገር መለወጥ እንዳለብኝ እገነዘባለሁ።"... አዎ! ይህ ነበር የስኬታማነት ምስጥሩ

ታዲያ አንተም ወደ አላማህ ስታቀና ከግብህ ጋር ተጋባ፣ ከአላማህ ጋር ተዋሀድ፣ ከተልዕኮህ ጋር ተዛመድ፣ ከእቅድህ ጋር ተጣመር። ግብህን ዳብሰው፣ ቅመሰው፣ አሽተው፣ አዳምጠው፣ ተናገረው..." ግብህ አብሮህ ይተኛ፣ አብሮህ ይዋል... ያኔ ስኬት ራሱ ይከተልሀል። ... Stick with your goal!

9.4 ትችላለህ

ስኬት የአደም ልጆች ሁሉ ተፈጥሯዊ መብታቸው ነው። ወደ ስኬት ስታቀና እንደሚሳካልህ አስብ፣ ግብህ ላይ እንደምትደርስ እርግጠኛ ሁን። አንተ ያወጣኸውን ግብ በጊዜ ከፋፍለህ በየቀኑ እየተገበርከው ከሆነ አላማህን ከማሳካት፣ ኢላማህን ከመምታት አትወገድም።

አትሌት ሀይሌ "ይቻላል" ብሎ ማሸነፍን በተግባር አሳይቶናል። "Nothing is imposible Except the word impossible" "በዚህች ምድር ላይ "አይቻልም" ከሚለው ቃል በስተቀር የማይቻል ነገር የለም" ይለሉ በትጋታቸው የቁሳዊ ስልጣኔ ማማ ላይ የደረሱት ነጮቹ። አዎ! በአላማ ከኖርን፣ እቅዳችንን በጊዜ ከፋፍለን ከተገበርን፣ በፅናት ከቀጠልን ውጤታማ እንሆናለን። የማይቻለው መዝገበ ቃላት ውስጥ ያለው "አይቻልም" የሚለው ቃል ብቻ ነው።

ጥምጣሜ ነጭ ነው

ኢብኑ ሐዝም የተባሉ ታላቅ ሊቅ "ጡቁል ሀማመህ" በተሰኘው ድርሳናቸው አንድን አስደናቂ ታሪክ ያስነብቡናል። እስኪ አብረን እንከታተላቸው።.

በአንደሉስ (በአሁኗ Spain) ምድር የሚኖር አንድ የታወቀ ቱጃር ነበር። ንግዱ የሰመረለት፣ ትርፉ የተነባበረለት ባለፀጋ በመሆኑ ሀገር ያውቀዋል። ይህ ስኬቱ ግን በአራት ታዋቂ ነጋዴዎች ዘንድ ጥርስ ውስጥ ከቶት ነበር። እነዚህ ነጋዴዎች እጅጉን ጠሉት። እሱን እንዳበሳጩ ለመኖር የወሰኑ ይመስላሉ።

ይህ ባለፀጋ አንዴ በጠዋት ተነስቶ ነጭ ጀለብያ (ቀሚስ) ና ነጭ ጥምጣም ለብሶ ወደ ስራው ማቅናት ይሄዳል። በጣም ከሚጠሉትና ውድቀቱን ከሚመኙለት አራት ነጋዴዎች አንደኛው መንገድ ላይ አገኘው። ሞቅ ያለ ሰላምታ ከሰጠው በኋላ አለባበሱን ማድነቅ ጀመረ። "ዛሬ አለባበስህ ያምራል፣በተለይ ይህ ቢጫ ጥምጣም ደግሞ አይን ውስጥ ይገባል" አለው።

ባለፀጋውም "አይንህ ታውሯል እንዴ? ጥምጣሜ ነጭ ነው" ሲል መለሰ። ግለሰቡም "እንዴ ምን ነካህ ቢጫ ነው እንጂ። ነገር ግን በጣም ያምራል" ብሎት ተሰናበተው።

ከዚህ ግለሰብ ጋር ተሰነባብቶ ትንሽ እንደተራመደ ከሁለተኛው ግለሰብ ጋር ተገናኙ። እርሱም እንደመጀሪያው ጥሩ ሰላምታ ሰጠውና አለባበሱን ማድነቅ ጀመረ። "ዛሬ እንዴት አምሮብሀል መሰለህ፣ አለባበስህም ከወትሮው የተለየ ነው፣ በተለይ አረንጓዴው ጥምጣም!!!" አለው። ባለፀጋውም "እንዴ ምን ነካህ ጥምጣሜ ነጭ ነው። አታይም እንዴ?... በል ከፊቴ ዞር በል" ብሎት ወደ ስራ ቦታው መንገዱን ቀጠለ። ነገር ግን ሁለት ሰው ስለጥምጣሙ የተለያየ አስተያየት ስለሰጡት፣ የጥምጣሙን ክለር እርግጠኛ ለመሆን ከራሱ ወደ ትከሻው የተንሸራተገውን ጥምጣም መመልከት ቀጥሏል።

በዚህ ስሜት ውስጥ እንደሆነ ወደ ስራቦታው ደረሰ። ድርጅቱንም ከፍቶ ትንሽ እንደተቀመጠ ከነዛ ከአራት ምቀኞቹ ውስጥ ሶስተኛው መጣና ሰላምታ አቀረበለት። አስከትሎም እንደ ጓደኞቹ አለባበሱን ማድነቅ ያዘ። "ዛሬ በጣም አምሮብሀል ባክህ። በተለይ ይህ ሰማያዊ ጥምጣምህ ደግሞ የበለጠ ግርማ አላብሶሀል" አለው።

ባለፀጋው ግራ በመጋባት ወደ ጥምጣሙ እየተመለከተ "ጥምጣሜ ነጭ ነው" ሲል ጮኸ።

"አይ ጥምጣምህ እንኳ ሰማያዊ ነው ነገር ግን በጣም ያምራል" ብሎት ተሰናብቶት ሄደ። ይህ ባለፀጋ ግራ በመጋባት ጥምጣሙን እያገላበጠ መመልከት ያዘ። ይህ ነጭ አይደለም እንዴ?... ለደቂቃዎች አይኖቹን በጥምጣሙ ላይ እንደተከለ ቆየ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አራተኛው ግለሰብ መጣና እንደጓደኞቹ ሰላምታ አቀረበለት። ከዚያም "እንዴ ይህን የሚያምር ቀይ ጥምጣም የት ገዛኸው?" ሲል ጠየቀው። ባለፀጋውም ሳያውቀው በጣም በመጮህ "ጥምጣሜ አረንጓዴ ነው"... አለ ተሳስቶ። ግለሰቡም "አይ ቀይ ነው እንጂ" ሲል መለሰ።

ባለፀጋው የሚያወራውን ሳያውቅ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሰማያዊ ነው... አይ ነጭ ነው.... አይ ቀይ ነው እያለ መዘባረቅ ያዘ። ከዛም ብቻውን ነጭ፣አረንጓዴ፣ቀይ፣ቢጫ... እያለ ለራሱ መመላለስ ጀመረ። ብቻውን መሳቅ ቀጠለ። ትንሽ ቆይቶም አለቀሰ... ግራ ተጋባ... ተነስቶ መዝለል ጀመረ... መጮሁን ቀጠለበት... ለካስ አሳብደውት ነበር።

አም! ግለሰቡ አዕምሮውን ሳተ። ወደ እብድነትም ተቀየረ። ታላቁ ሊቅ ኢብኑ ሐዝም እንዲህ ሲሉ ታሪኩን ይቋጨታል፦ "ያን ባለፀጋ በአንደሉስ (Spain) ጎዳና ላይ እብድ ሆኖ ህፃናት በድንጋይ እየመቱት አመለከት ነበር"።[121]

እነዚህ አራት ምቀኞች እንዴት እርኩስ አላማቸውን እንዳሳኩ ተመልከት። እነሱ የሰውን ጭንቅላት በተራ ጥረት መቀየር ከቻሉ፣ አንተስ ለምንድን ነው ራስህን የማትቀይረው? ከትናንት ማንነትህ የተሻልክ ሰው ለመሆን የማትተጋው ለምንድን ነው? አም! ተግተህ ከተነሳህ የአላማህ ጥግ ላይ ትደርሳለህ። የቀረፅከውን አላማ ከማሳካት የሚያግድህ ነገር አይኖርም። ... ጠንክር በል ትችላለህ።

አውቃለሁ - በዙሪያችን ያሉ ነገሮች ሁሉ እንድንሳነፍና ተስፋ እንድንቆርጥ ገፊ ሊሆኑ ይችላሉ። አንተ ግን ለእነዚህ አስተያየቶች ቦታ ሳትሰጥ በጀመርከው የስኬት ጎዳና ላይ በትጋት አቅና... ምንም ይሁን መድረስህ አይቀርም!።

እንዲህ ተብሎ ነበር

በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የተነገሩ ተስፋ አስቆራጭና አስገራሚ አባባሎችን (Quotes) ከዚህ በታች እዘረዝርልሀለሁ። እነዚህ አባባሎች በዘመናቸው የተጨበጨበላቸው ነበሩ። አሁን ግን ከእውነታዎች ጋር

[121] ኢብኑ-ሐዝም- ጡቂል ሀማመህ - Enjoy Your Life ዶ/ር መሀመድ ዐረፋ ገፅ - 17-18

የሚጣረሱ ታሪካዊ አስቂኝ ንግግር ሆነዋል። እስኪ ከታች ወደ ላይ (ከአስር ወደ አንድ) እናስፍራቸው፡-

10) ስለ ኮምፒዩተር፡- የ "digital equipment" መስራችና የካምፓኒው ፕሬዝዳንት ኬኔዝ ኦልሰን በ1977 እንዲህ ብሎ ነበር፡- "ሰዎች በየቤታቸው ኮምፒዩተር እንዲኖራቸው የሚያስገድድ ምንም ዓይነት ምክንያት ሊኖር አይችልም።"

አዎ! እንዲህ ተብሎ ነበር።ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት ኮምፒዩተር በሰው ልጆች የእለት ተዕለት ህይወት ያለውን ሚና ለመመስከር እማኝ የሚያስፈልግ አይመስለኝም።

9) ስለ አውሮፕላኖች ደግሞ ማርሻል ፈርዲናንድ ፎች የ "French Military Strategist" የነበረው በ1911 እንዲህ ማለቱ ተዘግቧል፡- "አውሮፕላኖች ደስ የሚሉ የልጆች መጫወቻዎች ናቸው። በፍፁም ወታደራዊ ጠቀሜታ ሊኖራቸው አይችልም።" - አዎ! እንዲህ ተብሎ ነበር። ነገር ግን በአሁን ዘመን የጦር ጀቶች ያላቸውን ሚና ሁላችሁም ታውቃላችሁ።

8) አውቁ ሳይንቲስት፣ የ "Audion Tube" ፈጣሪ (ፈልሳፊ)፣ የራዲዮ ፈልሳፊ አባት የሚባሉት ግለሰብ በ 1967 እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡- "የሰው ልጅ በፍፁም ጨረቃ ላይ ሊደርስ አይችልም - ወደፊት የትኛውም ዓይነት ሳይንሳዊ ዕድገት ቢያስመዘግብ እንኳ"።...
ስለዚህ ተስፋ አስቆራጭ ንግግራቸው ምን አላችሁ?

7) ስለቴሌቪዥን - የ "20th Century fox" የፊልም ኢንዱስትሪ የበላይ ሀላፊ የሆነው ዳሪል ኤፍ ዛኑክ በ1946 እንዲህ ብሎ ነበር። "ቴሌቪዥን ከስድስት ወራት በኋላ አሁን ያለውን የገበያ ድርሻ እንደያዘ የመቀጠል አቅም የለውም። ሰዎች በዕንጨት በተሰራ ሳጥን ላይ አፍጥጠው ማምሸቱ በቅርብ ይሰለቻቸዋል።"

6) 1962 "Decca Records" የተባለ የሙዚቃ ሕትመት ድርጅት የ "Beatles" ስራዎችን ላለማሳተም ምክንያት እንዲህ ብለው ነበር፡- "ድምፃቸውን አልወደድነውም። ስለዚህ ጊታሮችን ከገበያ እያሰናበትናቸው ነው።"

5) NewsWeek የተሰኘው እውቅ መፅሄት በ1969 የዶ/ር ኢያን ማክዶናልድን አንድ አስገራሚ ንግግር አስነብቦናል። እንዲህ ይላል፡- "ለአብዛኛው የሰው ልጅ ትንባሆን ማጨስ ጠቃሚ ጎን አለው።"

4) "Western Union International" የተባለ ድርጅት በ1876 እንዲህ ማለቱ ተዘግቧል፡- "ይህንን ስልክ እንደ ሁነኛ የመገናኛ መሳሪያ እንዳንቆጥረው የሚያስገድዱን እጅግ በርካታ ችግሮች አሉበት። መሳሪያው ከስረ-መሰረቱ የሚረባ ነገር የለውም።"...

በአሁኑ ዘመን ስልክ በሰው ልጅ የእለት-ተዕለት ኑሮ ላይ ያለውን አገልግሎት ለአንባቢያን ዳኝነቱን እተዋለሁ።

3) የእንግሊዙ ንጉስ በ July 1976 እንዲህ ብሎ ነበር፡- "በአሁኑ ዘመን ምንም ጠቀሜታ ያለው ነገር አልተፈጠረም።"

2) በ1899 የአሜሪካው ፓተንት (የፈጠራ ውጤቶች እውቅና ሰጭ) ኮሚሽነር እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡- "ሊፈጠር የሚችለው ፈጠራ ሁሉ ተፈጥሮ አልቋል።"...

ከ 1899 በኋላ አለም በርካታ ፈጠራዎች እንዳየች ልብ በሉ።

1) የራይት ወንድማማቾች የመጀመሪያውን የበረራ ሙከራ ለማድረግ በተዘጋጁበት ሰዓት በርካታ ተስፋ አስቆራጭ አስተያየቶችን አስተናግደዋል። በ1903 እውቁ የ "New York Times" መፅሄት በርዕሰ አንቀፁ ላይ እንዲህ ብሎ ነበር፡- "ፍፁም የማይሳካ የበረራ ሙከራ"

ይህን "የአይቻልም" ስሜት ሰብረው የራይት ወንድማማቾች አስገራሚ ታሪክ ሰሩ። በኪቲ ሀውክ ያንን ዓለምን ያስደመመ የተሳካ በረራቸውን አደረጉ።

ከላይ የተመለከትካቸው አስሩ ነጥቦች ከበርካቶች ጥቂቶቹ ናቸው። በዙሪያህ ያለ፣ ጓደኛ፣ ቤተሰብ... የመጀመሪያው ጉዞ ከባድና የማይሳካ እንደሆነ ደጋግመው ሊነግሩህ ይችላሉ። ከዚህም አልፈው ሲያወግዙህ ታገኛቸዋለህ።

የ "friode tube" ፊልሳፊ ሊ ዲ ፎረስት (Lee de Forest) የተባለው ግለሰብ በ 1913 በወረዳው ጠበቃ ክስ ተመስርቶበት ነበር። የክሱ ጭብጥም እንዲህ የሚል ነበር። "የኦትላንቲክ ውቅያኖስን አቆራርጦ ድምፅ ሊያስተላልፍ የሚችል መሣሪያ እሰራለሁ በማለት ሰዎችን በማጭበርበር አክሲዮኖችን እንዲገዙ ለማድረግ ሞክሯል።" ...ይህ ግለሰብ በወቅቱ ትልቅ የሆነ ውግዘት ገጥሞት ነበር።

እስቲ አሁን ይህ ቴክኖሎጂ ባይኖር ምን ይውጠን እንደነበር አስቡት። አዎ! ፊርቀዳጅ የለውጥ ቀንዲሎች ይህን "የአይቻልም" ድባብ ገልጠው የሚወጡት ናቸው። በዙሪያቸው ለሚሰሙት አሳናፊ ንግግሮች ጆሮ የማይሰጡ ናቸው። የውድድሩ ሻምፒዮንም የስኬቷ ሚስጢር ይኸው ነው። ውድድሩን አብረን እንከታተል፦

የውድድሩ ሻምፒዮን

ከተወሰነ ክ/ዘመን በፊት በጦጣዎች መካከል የተደረገ ረዥም አለታማ ተራራን የመውጣት እሽቅድድም ነበር። ይህን ተራራ በታሪክ ወጥቶ የሚያውቅ ጦጣ አልተገኘም። የውድድሩ ዝግጅት በየዓመቱ የሚደረግ ስለሆነ በርካታ የጦጣ ቤተሰቦች ከየበረሀው ወጥተው ውድድሩን ይታደሙ ነበር። ሞፊራውና ጩኸቱ ለጉድ ነው። ከየጎሳው ለውድድር የመጡ ጦጣዎች አሸናፊ ለመሆን ተዘጋጅተዋል። ቢሆንም ሁሉም መውጣት እንደማይችሉ ያምናሉ። ይህንኑም ነው ሲሰሙ የከረሙት። ምክንያቱም ይህን አለታማ ረዥም ተራራ በጦጣዎች ታሪክ ወጥቶት የሚያውቅ ከአሁን በፊት ስላልታየ። የጦጣዎች አሰልጣኞችም የሚሏቸው ይህንኑ ነው። "እስክጫፍ እንኳን አትደርሱም፤ ባይሆን የተሻለ ርቀት መሄድ ከቻላችሁ በርቱ።" የጦጣዎች ማህበረሰብም ይህን ነው የሚያምኑት።

ውድድሩ ቀጥሏል። ጦጣዎቹ ወደ ተራራው አናት የሚያደርጉትን እሽቅድድም ተያይዘውታል። የደጋፊ ድምፆችም በድምቀት ይሰማሉ። በተመሳሳይም "ጫፍ መድረስ ባትችሉም እንኳን የተቻላችሁን ያህል ግፉ" የሚለው አስተያየት ይደመጥ ነበር። ይህን ተስፋ አስቆራጭ አስተያየት እየሰሙ በሰባራ ሞራል ጦጣዎቹ ወደላይ አቀኑ። ቀድሞውንም ወደላይ መድረስ አትችሉም የሚለው አስተያየት ወኔያቸውን ስለሰለበው በትጋት መቀጠል አልቻሉበትም።

አንዲት ጦጣ ግን ከሌላው በተለየ ትጋት ወደላይ ግስጋሴዋን ቀጥላለች። ፍጥነቷም ለጉድ ነው። ተራራው ጫፍ ላይ ሳይሆን ሰማዩ ላይ ለመውጣት የቆረጠች ትመስላለች። ከታች ካሉት ደጋፊዎች "እረ ረጋ በይ ጫፍ እንደሆነ መድረስ አይሳክልሽም" የሚሉ ድምጾች በርክተዋል። አሁንም ግስጋሴዋን ከአንዱ ድንጋይ ወደ ሌላው እየነጠረች ተያያዘችው። ሌሎች ተወዳዳሪዎች እየተንጠባጠቡ ከጨዋታው ውጭ ሆኑ። እርሷ ብቻ

ሆነ የምትታየው። ከስሯ የተሰበሰበው ታዳሚ አሁንም ጩኸቱን አላቆመም "ይበቃሻል። ከጫፍ እንኳን መድረስ አትችይም። ይህ ሆኖ አያቅም" የሚሉ አስተያየቶች በስፋት ይሰፈሩ ነበር። ጦጢት ውድድሯን በትጋት ቀጥላ በጦጣዎች ታሪክ ተሰርቶ የማያውቀውን አንፀባራቂ ድል አገኘች። ተራራው ጫፍ ላይ ወጣች።

የታዳሚውን አግራሞት የሳበ፣ የብዙሀኑን ስሜት የገዛ ታሪካዊ ክስተት ነበር። የጦጣው ማህበረሰብም የአበባ ጉንጉን እየያዘ አድናቆቱን ቸራት። ስሟን ከፍ አድርገውም አወደሷት። እንኮኮ አድርገው በርሀውን አዞሯት።

ከዚህ ታሪካዊ ስኬት ላይ እንዴት እንደደረሰች ሲጠይቃት አንድ ጋዜጠኛ (የጦጣ ጋዜጠኛ) ተጠጋት። "እንዴት ነው ማንም ሰርቶት የማያውቀውን አስደናቂ ታሪክ ልትሰሪ የቻልሽው?" ሲል ማይኩን ወደ አፏ አስጠጋ። እርሷ ግን መልስ አልሰጠችም። ጥያቄውን ደገመላት። አሁንም መልስ የለም። ጋዜጠኛው ጥያቄውን በሌላ ይዘት ቀይሮ ለሶስተኛ ጊዜ አቀረበላት። አሁንም መልስ የለም።... ለካስ ጦጢት መስማት ከተሳናቸው ውስጥ ነበረች። አሥ! የስኬቷ ምንጭም ይህ ነበር። የማህበረሰቡን አሳናፊ አስተያየት ስላልሰማች ነበር ማሸነፍ የቻለችው። "ይህን ተራራ መውጣት የሚችል የለም" የሚለውን ስንፈት ወለድ አባባል ሳትሰማ ነበር ያደገችው።

በቃ በዙሪያህ ያሉ ሰዎች የሚሉህን አሳናፊ ምክር ቦታ አትስጠው። እችላለሁ የሚለውን መፈክር ዘውትር አንግብ። ችግሮችን በድፍረትና በወኔ ተጋፈጣቸው። ያኔ ግብህ ላይ መድረስህ አይቀርም።

Dr.David Schwartz - ከስድስት ሚሊዮን ኮፒ በላይ በተሸጠላቸው "The Magic of thinking Big" "በትልቁ የማሰብ ኃይል" በተሰኘው መፅሀፍ ውስጥ እንዲህ ሲሉ ይመክሩናል:-

"ማንኛውም ነገር እንደማይቻል የሚነግሩህ ያልተሳካላቸው ሰዎች መሆናቸውን አስታውስ። እንዲህ ያሉ ሰዎች አስተያየት መርዝ ነው። ስለዚህ አስተሳሰባቸው ትንሽ ከሆነና የአንተን ትልቅ ሃሳብ ለማቀጨጭ ከሚቃጡ ሰዎች ራስህን አርቅ። ሰዎችን ማመስገን ልመድ:- ሰዎች ላደረጉልህ ነገር ምስጋና ማድረግን ህግህ አድርገው። ማንኛውም ሰው

ቢሆን የተጠቀምክበት መስሎ እንዳይሰማው ተጠንቀቅ። ምስጋናህንም በልባዊ ፈገግታ አጅበው። ፈገግታ ለሌሎች ያለህን መልካም አመለካከት ይገልፃል። "አንተ ባትኖር ምን ልንሰራ እንችል እንደነበር ግን ይገባኛል" የሚል መገሳንም ተጠቀም። ይህ የበለጠ እንዲሰሩ ያበረታታቸዋል።[123]

[123] Dr. David Schwartz – The Magic of Thinking Big (በትልቁ የማሰብ ኃይል - ሱራፌል ግርማ)

YOU CAN

Figure it out for yourself, my lad,
You've all that the greatest of men have had;
Two arms, two hands, two legs, two eyes,
And a brain to use if you would be wise.
With this equipment, they all began
Do start from the top and say: ``I can``.
Look them Over,the wise and the great;
They take their food from a common plate,
And similar knives and forks they use,
With similar laces, they tie their shoes.
The world considers them brave and Smart,
But You've all they had when they made their smart.
You can triumph and come to skill,
You can be great if you only will.
You've all equipped for what fight you choose;
You have arms and legs and a brain to use;
And the man who has risen, great deeds to do,
Began his life with no more than you.
You are the handicap you must face;
You are the one who must choose his place;
You must say what you want to do,
How much you will study, the truth to know;
Allah (God) has equipped you for life, but he
Lets you decide what you want to be.
Courage must come from the soul within,
The man must furnish the will to win.
So figure it out for yourself, my lad;
You were born with all that the greatest have had;
With your equipment, they all began...
Get hold of yourself and say : ``I can.``

George Washington. C

ትችላለህ

9.5 ለህይወትህ ራስህ ሀላፊነትን ውሰድ

"(ለተፈጠሩ ችግሮች ሁሉ) ሰበብ በመፍጠር ሁሌ የሚሳካለት ሰው፣ በሌላ በምንም ነገር ሊሳካለት አይችልም።" ቤንጃሚን ፍራንክሊን[124]

አብዛኛው ሰው ስኬታማ ላለመሆኑ ተጠያቂ የሚያደርገው አካል አለው። ሁሌም እጆቹን ወደሌላው ይቀስራል። አንድ ጣቱን ወደ ሌላ ሲቀስር፣ ሶስቱ ጣቶቹ ወደእርሱ እንደሚያመላክቱ የዘነጋ ይመስላል። አንተ ግን ለህይወትህ ሙሉ ሃላፊነትን ውሰድ። ስኬታማ ላለመሆንህ ተጠያቂው አንተና አንተ ብቻ እንደሆንክ እመን። ህይወትህን በአላማ ላለመምራትህ ተጠያቂው ራስህን ብቻ አድርግ። ያኔ ነው በህይወትህ ላይ ለውጥን ለማምጣት ተነሳሽ (Proactive) የምትሆነው።

ብዙዎቹ ህይወትን በአላማ ላለመምራታቸው የሚያቀርቡት ምክንያት አያጡም። በዚህ ላይ ተክነውበታል። እድሌ ጠማማ ባይሆን ኖሮ፣ ወላጆቼ በደምብ ተንከባክበው ቢያሳድጉኝ ኖሮ፣ጥሩ ትምህርት ቤት ብማር ኖሮ፣ጥሩ ጓደኞች ቢኖሩኝ ኖሮ፣ የቤት አስጠኚ ቢቀጠርልኝ ኖሮ፣ ጥሩ ሚስት/ባል ቢኖረኝ ኖሮ፣ እዚህ ሀገር ባልወለድ ኖሮ፣ ጊዜው ጥሩ ቢሆን ኖሮ... የሚሉ መፈክሮችን ይዘው ታገኛቸዋለህ።

Dr. David Schwartz እንዲህ የሚል አስተያየት አላቸው፡-

"ስኬታማ የማይሆኑ ሰዎች እርምጃ ላለመውሰዳቸው ምክንያት ፍፁም የሚያመች ጊዜን መጠበቃቸው ነው። እውነቱን ልንገራችሁ - በዚህ ዓለም ላይ ፍፁም የሚያመች ጊዜን መጠበቅ ማለት ደግሞ የለማይዋን ወተት መጠበቅ ማለት ነው። ምቹ ሁኔታ የሚባል ነገር የለም። ሁኔታዎችን ምቹም ሆነ የማይመቹ የምናደርጋቸው እኛው ነን።"[125]

እራስህን ለመለወጥ ለራስህ እድል ስጠው። ያልተሳካልኝ በራሴው ችግር እንጂ በዙሪያዬ ባሉ ነገሮች ተፅዕኖ አይደለም ብለህ አስብ። ያኔ ነው ለችግሮች መፍትሄ ለማግኘት የምትጣጣረው። ያኔ ነው ከወደቅክበት ለመነሳት ተነሳሽ የምትሆነው።

---

[124] ቤንጃሚን ፍራንክሊን - (1706-1790) - የአሁኒቷን አሜሪካ በመመስረት ላይ ትልቅ ሚና የነበረው ልሂቅ።

[125] The magic of thinking Big

10

ምዕራፍ አስር



በመንገድህ ላይ

- ሰራህን ለዓለማት ጌታ ብቻ አድርግ
- በጌታህ ተደገፍ
- ጠንካራ ወኔ ይኑርህ
- አላማህ እስኪሳካ ታጋሽ ሁን

ወደ ስኬት ስናቀና በመንገዳችን ላይ ልንረሳቸው የማይገቡ መሰረታዊ ነጥቦች አሉ። ለሙሉ ስኬትና ለአመርቂ ውጤት የማይተካ ሚና አላቸው። እነሱን በገዘርዝር እናያለን፦

10.1 ስራህን ለአለማት ጌታ ብቻ አድርግ

"ራስን ማሻሻል መቻል የሰው ልጅ በተፈጥሮ የተቸረው ሰጣታ ነው። እራሱን መለወጥ ከተሳካለት፣ ያኔ ዓለምን መለወጥ ይችላል"

በስኬት መንገድህ ላይ እንቅስቃሴዎችህ ሁሉ የሀያሉን ጌታ ውዴታ ከማግኘት አንፃር ብቻ የተቃኙ መሆን እንዳለባቸው አትርሳ። ምድራዊ ንዋይን፣ ዝናን፣ ክብርን፣ አድናቆትን... በመሻት የምታከናውናቸው ስራዎች ሁሉ ፈጣሪ ዘንድ ዋጋ የላቸውም።

ስራዎች ሁሉ ፈጣሪ ዘንድ ዋጋ የሚኖራቸው በአሳቦት ዕዳታቸው (በኢኽላሳቸው) መጠን ነው። ወደ አላህ ሰማየ ሰማያትን አቋርጠው የሚወጡትና ተቀባይነት የሚቸራቸው ይህ ሲሚላ ብቻ ነው። ይህን በምሳሌ እንመልከት፦

ባሎን ሻጩ

እነሆ ባሎኖችን (ፊኛዎችን) በመሸጥ የሚተዳደር አንድ ግለሰብ ነበር። ቀይ፣ ቢጫ፣ ነጭ፣ ጥቁር... ከለር ያላቸው ፊኛዎችን በእጁ ይዞ ለሰፈሩ ሰዎችና ለአልፎ ሄያጁ ይሸጥ ነበር።

አልፎ አልፎ ገበያ ሲጠፋ አንዱን ፊኛ ወደ ሰማይ ይለቀዋል። ማስታወቂያ (አድቨርት) መሆኑ ነው። ይህን የተመለከቱ ህፃናት ለመግዛት ይሽቀዳደማሉ። በታ ይህ የዘወትር ስራው ነው። ገበያውን የሚያደራው ፊኛዎችን ወደ ላይ በመልቀቅ ነበር።

ታዲያ አንዴ በቆመበት ልብሱ ከኋላ ሲጎተት ተሰማው። ልብሱ ወደ ተሳተተበት አቅጣጫ ሲዞር አንድ ትንሽ ልጅ ቆሟል። አይኖቹን አያቁለጨለጨ እንዲህ የሚል ጥያቄ አቀረበለት፦ "ጥቁሩን ፊኛ ወደላይ ብትለቀው እንደሌሎቹ አየር ላይ ይንሳፈፋል?"

ሰውየውም በመገረም "Son it is not the color of the ballon. It is what's inside that makes it go up." "ልጄ ወሳኙ የፊኛው ቀለም አይደለም፣ ወደላይ አንዲንሳፈፍ የሚያደርገው ውስጡ የተሞላው አየር ነው።" ሲል መለሰለት።[126]

ልክ እንደዚሁ ሁሉ የሰው ልጅ ለስራው ዋጋ የሚሰጠው፣ስራው ወደ ፈጣሪ የሚወጣው፣ ከጌታ ዘንድ ስራው ተቀባይነት የሚያገኘው... በተክለ ቁመናው፣ በቆዳ ቀለሙ፣ በሀብትና ንብረቱ፣ በዘር ግንዱ... አይደለም። ወደ አለማቱ አስገኚ የሚያቃርበው ውስጡ ያበበው የፈጣሪ ፍራቻና ጥንቃቄ ነው። ፊኛው ውስጡ በተሞላው አየር ወደላይ እንደወጣ ሁሉ፣ የሰው ልጅ ስራውም በክብር ወደላይ የሚወጣው ውስጡ ንፁህ አሳቡት (ኢኽላስ) ሲኖር ነው።

የሐጅ ስነ-ሰርዓት ላይ ለሚደረገው ክንውን የቤት እንሰሳዎችን ለእርድ ያቀረቡትን ምዕመናን አላህ እንዲያ ሲል ያስታውሳቸዋል፡-

"አላህ ሥጋዎቿም ደሞቿም አይደርሰውም፣ ግን ከእናንተ የሆነው ፍራቻ ይደርሰዋል። ..."[127]

አዎ! ቁም ነገሩ የተሰውት እንስሳት ብዛትና አይነት ሳይሆን የተሰውበት አሳቡት (አላማ) ነው። በኢኽላሳችን (በአሳቡት ዕዳታችን) መጠን ስራችን ወደ አላህ በክብር ይወጣል።

ታዲያ አንተም በመንገድህ ላይ ልታሳካው በምትሮጥለት አላማ የፈጣሪን ፊት ብቻ መፈለግህን እንዳትረሳ። ኢኽላስ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። የምታሳካቸው ግቦች (ሀብት፣ ክብር...) ቢያመጣልህም በቀጣዩ ዓለም ጌታህ ዘንድ ግን ዋጋ አይሰጠውም። ለዋናውና ለተፈጠርክለት አላማ (The Goal of Goals) ግብዓት መሆን አይችሉም። ውጤቱ መቃብር በመግባት የሚጠናቀቅ ከሆነ ምኑን ስኬት ይባላል?

---

[126] የአሸናፊነት ዳንዲ - ለአሸናፊነት መገዛት
[127] ቁርአን 22 : 37

ስለዚህ እራስህን ግራው። ውስጥህን ለመለወጥ ቆርጠህ ከተነሳህ ደግሞ የማይሳካ ነገር አይኖርም።

"በዚህች አለም ውስጥ ልታሸንፈው እንደምትችል እርግጠኛ የሆንክበት አንድ ነገር አለ፡አርሱም እራስህን ነው።" Aldous Huxler

አሳቦትህን ማፅዳት የዘወትር ስራህ ይሁን። ምንም ነገር ከማድረግህ በፊት፣ አላማህን ከማስፈርህና ለማሳካት ከመራመድህ በፊት ራስህን ጠይቅ። "ይህን አላማ ለማሳካት የምማስነው ምንን ፈልጌ ነው?" ስትል ከራስህ ጋር አውራ። በጉሏችን ላይ ኢኽላስን መላበስና ውስጥን ለፈጣሪ ማፅዳት በእርግጥ ትልቅ ተግባር ነው። አላህ በተከበረው ቃሉ እንዲህ ይለናል፦

"በነፍስም ባስተካከላትም፤ አመፅዋንም ፍርሃትዋንም ባሳወቃት (አምላክ አምላለሁ)። (ከኃጢአት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ። (በኃጢአት) የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ።"[128]

10.2 <u>በጌታህ ተደገፍ</u>

የስኬት ምንጩ በፈጣሪ መደገፍ ነው። የስኬትን ረዥም ጉዞ ብቻህን አትችለውም። በራስ ላይ ተብቃቅቶ መንዝ ወንዝ አያሻግርም። በግል ጥረት ዳር ለመድረስ የሚጥሩ ሁሉ ለግል ጥረታቸው ይተዋሉ። ረዥሙን ርቀት ብቻቸውን ይጓዛሉ። ትልቁን ከፍታ ብቻቸውን ለመውጣት ይገደዳሉ። ያ በጌታ የተመካው ግን በስንዝር ጥረት የክንድ ያህል ይራመዳል። ከጥረቱ በላይ ውጤት ያገኛል።

<u>ሽልማት ይገባኛል</u>

አስካሪ መጠጥን ከውሃ በላይ ሁሌም የሚጎነጭ ግለሰብ እንደነበር ይነገራል። ይህ ግለሰብ ህይወቱ የተዛባ፣ ማህበራዊ ትስስሩ የተመሰቃቀለ ነበር። ሁሌም ከብድር አይወጣም። ወሩ በተጀመረ በአስረኛው ቀን እራሱን

[128] አሽ-ሸምስ ም. 91 ቁ.7-10

እዳ ውስጥ ያገኘዋል። ማታ ከስራ ሲመለስ ከቤቱ ከመድረሱ በፊት ካሉት 15 መጠጥ ቤቶች የቻለውን ኮምኩሞ ተደግፎ ቤቱ ይገባል። ጠዋት ወደ ስራ ሲያቀና አንጎበሩን ለማጥፋት በመንገዱ ላይ ከተኮለኮሉት ቤቶች እየገባ ትንሽ ይቀማምሳል።

የእርሱ ህይወት ሁሌም ከመጠጥ ጋር ነው። ማታ ለመስከር ይጠጣል። ጠዋት የስካር ድብርት (ሀንጎቨር) ለማጥፋት ይጠጣል።

ሁሌም ቢሆን ታዲያ ከዚህ የመጠጥ እሽክርክሪት ለመውጣት ያስባል። ቢሮው ውስጥ ቁጭ ባለበት "ዛሬ መጠጥ ሳልጠጣ ቤቴ እገባለሁ" ሲል ይፎክራል። ከስራ ወጥቶ ሲመለስ ወኔው ይከዳውና መጠጣቱን ይያያዘዋል። ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነቃ ፍራሹ ላይ ጋደም እንዳለ ማሰላሰል ይጀምራል። "የኔ ህይወት እስከመቼ ነው በዚህ ሁኔታ የሚቀጥለው?" ሲል ራሱን መላልሶ ይጠይቃል። በዚህ ስሜት ተነስቶ መስታወቱ ላይ ልብሱን እየለባበስ ከራሱ ጋር ይጫወታል። "ዛሬ ወደ መጠጥ ቤቶች ሳላማትር ቀጥ ብዬ ስራዬ እገባለሁ" እያለ ፀጉሩን እያበጠረ ይፎክራል። በወኔው ላይ እንዲያፀናው ፈጣሪውን ሳይማፀን ከቤቱ ይወጣል። ከቤቱ ወጥቶ ትንሽ እንደተራመደ ያ የመጠጥ ፍቅሩ ይጠራዋል፣ የመጠጥ ሽታ ያውደዋል... ከተወሰኑት ቤቶች ገብቶ የወጉን አደራርሶ ወደስራው ያቀናል።

ከአለታት አንድ ቀን ከእንቅልፉ በጠዋት ነቃ። ከነሙሉ የቢሮ ልብሱና ከነጫማው ራሱን ብርድልብስ ውስጥ አገኘው። እርሱ ትናንትና ከስራ ወጥቶ ወደቤቱ እያቀና እንደነበር ነው የሚያስታውሰው። አሁን ግን ከነ ልብሱ ፍራሹ ላይ ተኝቷል። በሁኔታው በጣም ተበሳጨ። ራሱን ጠላ። ከዛሬ በኋላ ህይወትን "ሀ" ብዬ መጀመር አለብኝ ብሎ በሙሉ ወኔ ተነሳ። ልብሶቹን ቀይሮ ከቤቱ ወጣ።

ትንሽ እንደተራመደ "አስካለች መጠጥ ቤት" ከፊት ተቀበለው።ጥርሱን ነክሶ አለፈው። ጥቂት እንደተራመደ ደግሞ "የሺ መጠጥ ቤት" ጎን ደረሰ፣ አሁንም በውሳኔው ፀና። ዳገቱን እየወጣ እያለ "ሳሙኤል ግሮሰሪ(መጠጥ ቤት)" ጥግ ደረሰ አሁንም ወኔው አልካደውም። በአቋሙ ፀና።... በዚህ መልኩ 14 መጠጥ ቤቶችን አለፈ። ደስታው ለጉድ ነበር። በራሱ ኮራ፣ስኬታማ እንደሆነ ተሰማው። ነገር ግን ከፊት ለፊቱ አማላይ አስተናጋጆች ያሉበት አንድ ትልቅ ሆቴል ይጠብቀዋል፣ ይህንም ቢሆን

በሙሉ ራስ መተማመን ማለፍ አንዳለበት ወሰነ። በጥሩ ወኔም ተሻገረው። አሁን ግን ስሜቱን መቆጣጠር አልቻለም። ላለፉት 8 ዓመታት ለማድረግ ወስኖ ያልተሳካለትን ጥረት ዛሬ እውን ሆኖ አየው። በራሱ ኮራ፣ ጀግና እንደሆነ ተሰማው። ትንሽም ሆቴሉን አለፍ ብሎ እንደሄደ ድንገት መለስ አለና "ለዛሬው ስኬቴ አንድ ጠርሙስ ውስኪ ራሴን መሸለም አለብኝ" አለና ሙሉ ውስኪ አስወርዶ በስካር አመሸ።

በቃ! በራስ ላይ ብቻ መተማመን፣ በራስ ብቻ መኮፈስ ወንዝ አያሻግርም። የሰው ልጅ የጌታው እርዳታ ያስፈልገዋል። ሰዋዊ ምክንያቶችን (ሰበቦችን) ካሟላን በኋላ ጌታችንን እርዳን፣ በአቋማችን አፅናን ብለን መማፀን ይኖርብናል። ያኔ በትንሽ ጥረት ብዙ ውጤት እናያለን። ያኔ ለስኬት የቀረብን እንሆናለን።

10.2.1 በጌታ የመመካት (የተወኩል) ትክክለኛ ገፅታ

አብዛኛው ሰው በጌታ መመካት (ተወኩል) ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ግንዛቤ የላቸውም። ከፊሎቹ ምክንያቱን (ሰበቡን) በማድረስ፣ ሀላፊነትን በመወጣት ብቻ ይብቃቃሉ። እነዚህ ረዥሙን መንገድ ብቻቸውን ለመጓዝ ይገደዳሉ። ሌሎቹ ደግሞ እጃቸውን አጣጥፈው ይቀመጡና የጌታቸውን እርዳታ ይጠብቃሉ። ሳያርሱ አዝመራውን፣ ሳይጋግሩ መብላትን፣ ሳይታጠቡ መዕዳትን... ይፈልጋሉ። እነዚህ አጉል ተስፈኞች ናቸው።

እርግጥ ነው ለፈጣሪ የሚሳነው የለም። ያለእኛ ተሳትፎ የምንፈልገውን ነገር ሁሉ ሊያሟላልን ይችላል። ነገር ግን የምድርን ስርዓት እንዲህ አይደለም ያስቀመጠው። የአደም ልጆች በሁለት ክንፍ እንዲበሩ ይፈልጋል። አንደኛው ክንፍ በእርሱ ላይ መመካት ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ሰበቦችን ማድረስ።

አንድ ገጠሬ ወደ ታላቁ መልዕክተኛ ነብዩ ሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ. መጣና "የአላህ መልዕክተኛ ግመሌን እንዲሁ ልተዋትና አላህ ይጠብቃታል ብዬ በእርሱ ልደገፍ (ልወክል) ወይስ ልሰራት?" አላቸው። መልዕክተኛውም "ግመልህን አስር፣ በጌታህም ተደገፍ/ተመካ" አሉት።

ይህ የዩንቨርሱ መርህ ነው። ይህን መርህ መልእክተኛው በተግባር ኖረውት አልፈዋል። በህይወታቸው የትኛውም እርምጃ ላይ ይህን ህግ ተግብረው የሁለት ዓለምን ስኬት ተቀናጠዋል። የሰው ልጅችን ከጥፋት ለመታደግ ባሳለፉት ጉዞ ይህ መርህ ከአይናቸው አልጠፋም ነበር። እንደማሳያ ከትውልድ ሀገራቸው መካ ወደ መዲና ያደረጉትን የስደት (ሂጅራ) እስትራቴጂ እንመልከት፡-

ሂጅራ

ሂጅራ በእስልምና ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ክስተት ነው። የአላህ መልዕክተኛ ሰ.ዐ.ወ. የትውልድ ሀገራቸውን መካን ለቀው ከመካ 500ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደምትገኘው መዲና ያደረጉት ታሪካዊ ጉዞ ነው። ይህን የስደት ጉዞ ስኬታማ ለማድረግ የወሰዱት ጥንቃቄ ታላቅ አስተምህሮ ስላለው የተወሰኑትን አብረን እንያቸው፡-

1ኛ) ከመዲና የተወሰኑ ነዋሪዎች ጋር ወደ መካ ለሀጅ ስነ-ስርዓት ሲመጡ፤ ከመካዊያን መሳፍንቶች እይታ ርቀው በሌሊት የመጀመሪያውን የመደጋገፍና የመረዳዳት ስምምነት ፈፀሙ። (የመጀመሪያው የአቀባ ቃልኪዳን ይባላል።)

2ኛ) መስዐብ የተባለውን ተማሪያቸውን መዲና በመሄድ አስልምና እንዲሰብክ፤ ቁርዓንን እንዲያስተምር ላኩት። ሙስዓብም በርካታ የመዲና ባለአባቶችን ወደ ኢስላም እንዲቀላቀሉ አደረጋቸው። አየሩም ሀገሩም የአላህን መልዕክተኛ ለመቀበል የተመቻቸ ሆነ።

3ኛ) በሙስዓብ አማካኝነት እስልምናን የተቀበሉ የመዲና ነዋሪዎች ለሀጅ ስነ-ስርዓት ለመተግበር ወደ መካ ሲመጡ ከሰው አይን ተሰውረው በሌሊት ዳግመኛ ቃል ተጋቡ። እነሱም የአላህን መልዕክተኛ ሁሌም ሲረዱ፤በደስታም በሀዘናቸው አብረዋቸው ሲቆሙ ቃል ገቡ። ይህ በእስልምና ታሪክ "በይዐቱል ዐቀበቱ ሳኒያህ" (ሁለተኛው የአቀባ ቃልኪዳን) ይባላል።

4ኛ) የእምነት ነፃነት የተነፈጉት ምዕመናን በአጠቃላይ ቀድመው መካን

ለቀው ወደ መዲና እንዲሄዱ አደረጉ::[129]

5ኛ) አቡበክርን የስደት አጋዥ ጓደኛ አድርገው አዘጋጁ:: ጓደኛ ብርታት ነው:: ወንድም ጥንካሬ ነው... ያለ ጓደኛ ጉዞ ምን ይዞ::[130]

6ኛ) ከሶስት ሌሊቶች በኋላ ለጊዜው ሊደበቁበት ካሰቡት ዋሻ አካባቢ እንዲገናኙ ቀጠሮ በመያዝ መጓጓዣዎችን ቀድመው አዘጋጅተው ለባለሙያ አስተላለፉ::

7ኛ) ስደት እንዲሄዱ ከጌታቸው በተፈቀደላቸው ጊዜ፤ ይህን ትዕዛዝ ለመንገር ወደ ባልደረባቸው አቡበክር ቤት በቀትር ሰዓት[131] ሄዱ::

8ኛ) የአጎታቸውን ልጅ ዓሊይን በአርሳቸው ፍራሽ ላይ እንዲተኛ አደረጉ:: ይህም ጠላቶቻቸውን ለማዘናጋት ረድቷቸዋል:: ቤታቸውን በመክበብ ደመ-ከልብ ለማድረግ ተዘጋጅተው እየተጠባበቁ እያሉ ነብዩ ﷺ ዓሊይን ከፍራሻቸው አስተኝተው ቁርዓን እየቀሩ ወጥተው ሄዱ:: ከሀድያን በቀዳዳ እያጮለቁ (እያዩ) መሐመድ እንደተኛ ነው ብለው እንዲያስቡ አድርገቸዋል ::

---

[129] ይህ ታላቅ የመሪነት መስፈርት ነው:: ከፊት ሆኖ ይመራል፤ ችግሮችን ሁሉ ለመጋፈጥ ራሱን ያስቀድማል:: ጥቁር አሜሪካውያን ለምን ማልኮም ኤክስን እንደሚከተሉ ሲጠየቁ፤ "ማልኮም ኤክስ ጥሉን ስለማይሄድ ነው" ነበር ያሉት:: ታላቁ መልዕክተኛም ይህንኑ ነው ያደረጉት::

[130] "በህብረት ወደ ዓላማህ ተጓዝ" የሚለውን ይመልከቱ - ምዕራፍ - 11

[131] በቀትር ሰዓት- በአረቢያን ምድር ፀሀይ ስለሚበረታ ወፍ እንኳ ዝር አይልም:: ሰው ሁሉ ቤቱ ረፍት የሚያደርግበት ወቅት ነው:: ስለዚህ ነብዩ መሐመድ ﷺ እንቅስቃሴያቸውን ከአይታ ለመደበቅ ጥሩ ጊዜ ነዉ::

መካዊያን የነብዩ መሐመድን ﷺ ጥሪ ከመቀበል እሻፈረን ቢሉም፤ የነብዩን ታማኝነት ግን በተገቢዉ ያውቃሉ:: ለዚህም ሲባል ንብረቶቻቸዉን በአደራ መልክ የሚያስቀምጡት ከጣኦታዊያን ስርዓተ-ፀሎት መሪዎች ሳይሆን ከነብዩ ጋር ነበር:: ወደ ስደት ሲሄዱ ንብረቶቻቸውን የሚያስረክቡበት እድል ስላላገኙ የአጎታቸዉን ልጅ ዓሊይን እንዲያስረክብ አዘዙት:: የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ወደ መዲና ስደት ባደረጉበት ሌሊት የመካ መሳፍንቶች ሁሉንም ጎሳ ባማከለ ሴራቸዉ ቤታቸውን በመክበብ ለመግደል ተዘጋጅተዉ ነበር:: ያኔ እርሳቸውን መስሎ የአጎታቸዉን ልጅ ከራሳቸዉ መኝታ ላይ አስተኙት:: ከሀዲያን ቤቱን ሰብረዉ ገብተው ብርድ ልብሱን ሲገልጡ የተኛው ዐሊይ ሆኖ ተገኘ::... ይህ የመሪ ትልቅ መገለጫ ነዉ:: በመስዋዕትነት ቀድመዉ የሚገኙት እነሱም ናቸው:: ነብዩም ﷺ በቦታቸው ላይ እንዲተኛ ያደረጉት የእነዚህ አይነቶችን ድሃ ተከታዮቻቸውን አልነበረም:: እንደ ልጃቸው ያሳደጉትን የአጎታቸውን ልጅ ነበረ ሀላፊነቱን እንዲወስድ ያደረጉት:: ትክክለኛ መሪ በችግር ጊዜ ቀድሞ የሚገኝ፤ በድሉት ጊዜ ሌሎችን የሚያስቀድም ነው:: ይህን ዕሁፍ በፃፍኩበት ጊዜ ታናሽ ወንድሜ ፋኢዝ ኑሩ ሀምሌ 11/2006 እንዋር በተደረገው የጁመዓ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በደህንነት ኃይሎች ጥይት ተመቶ ሆስፒታል እየታከመ ነበር:: ብዙም ሳይቆይ ወደ ጣቢያ በመውሰድ ቁስሉ ሳይድን ፓሊስ በማያል ሙከራ ተከሶ ፍርድ ቤት ቆሞ ነበር::... ይህ በመሆኑ ተደስቼ ነበር:: የሰላማዊው ትግሉ የሚያመጣውን መከራና ችግር ከህዝብ ጋር አብሮ የቤተሰቡ ክፍል ማስተናገዳቸው በእርግጥም መታደል ነው::

9ኛ) የሚሄዱባት ሀገር መዲና በስተሰሜን አቅጣጫ ብትሆንም ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ግን ወደ ደቡብ ነበር ያቀኑት። በዚህም የሚያሳድዷቸውን ማሳሳት ችለዋል።

10ኛ) በመንገዳቸው ላይ ከሚገኝ በአባብ ከተሞላ ዋሻ ውስጥ ተደብቀው ለሶስት ቀናት ቆይተዋል።

11ኛ) የስደት ባልደረባቸው የሆኑት የአቡበክር ልጅ አስማእ ወደ ዋሻው ምግብ ለነብዩና ለአባቷ እንድታመላልስ መደረጓ ከሂጅራ እስትራቴጂዎች አንዱ ነበር።

12ኛ) መካዊያን የሚያወሩትንና የሚወያዩትን ጉዳዮች ወደ ነብዩና ወደ አባቱ እንዲያደርስ የአቡበክር ልጅ ዐብዱላህን መድበዋል። እርሱም ሀገሪቱ ላይ ያሉ መረጃዎችን (ኢንፎርሜሽኖችን) አንድ በአንድ ያደርስ ነበር።

13ኛ) ዓሚር ኢብኑ ፉሀይራህ (የአቡበክር አገልጋይ) ወደዋሻው ፍየሎችን እየነዳ በመምጣት እንሰሳዎችን አልቦ ለነብዩና ሰ.ዐ.ወ ለአቡበክር ወተት እንዲያጠጣ መመደቡ። በተጨማሪም አስማእ ምግብ ስታመላልስ፣ ወንድሟ አብዱላህ ኢንፎርሜሽን ሲያመላልስ የተፈጠረውን የእግር ኮቴ ፋና እንዲያጠፋ ፍየሎችን በጎዳናው ላይ እንዲነዳ አድርገዋል።

14ኛ) ዐብዱላህ ዑረይቲጥ የተባለን ግለሰብ (መንገድ አዋቂ) ወደ መዲና ሚደረገውን የስደት ጉዞ የሚመራ እውቅ ግለሰብ መድበዋል።

ይህ እንግዲህ ታላቁ የአላህ መልዕክተኛ ሰ.ዐ.ወ. መካን ለቀው ሲወጡ የተከተሉት ስትራቴጂ ነው። ምናልባት ለአብዛኛዎቻችን እንግዳ ነገር ሊሆን ይችላል። ነብዩ ሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ የአለማት ፈጣሪ መልዕክተኛ ናቸው። መልአኩ ጅብሪል ጠዋትና ማታ ከጌታው መልዕክት በማመላለስ አብሯቸው ነው። ታዲያ ይህን ሁሉ ሰበብ ማሟላት ለምን አስፈለገ? አላህ በሌሊቱ ጉዟቸው ላይ የሰባቱን ሰማይ አስጎብኝቶ በዚያው ሌሊት እንደመለሳቸው ሁሉ ለምን አውንስ ከመካ ወደ መዲና በመላዕክት አክናፍ አልወሰዳቸውም?

አዎ! እርሳቸው የሰው ልጆች ሁሉ አስተማሪ ናቸው። ምዕመናን እንደ አርአያ (ሞዴል) እንዲከተሏቸው ታዘዋል። ለአደም ልጆች እንዴት

ለበቦችን እንደሚያደርሱ እንዲያስተምሩ ይፈለግ ነበርና ይህን የስደት ጉዞ በዚህ መልኩ እንዲያከናውኑ ተደረገ። መልዕክተኛውም ሰ.ዐ.ወ "ገመልህን አለር በአላህም ተደገፍ (ተመካ)" ብለው ላስተማሩት ትምህርታቸው ተምሳሌት ሆነው ታዩ።

በጣም የሚገርመው ይህን ሁሉ ሰበብ ቢያደርሱም ከጠላቶቻቸው ሙሉ ለሙሉ መሸሸ አልቻሉም። የመካ መሳፍንቶች ፋናቸውን አስለው ዋሻው ጋ ደረሱ። ዋሻው በእባብ የተሞላ መሆኑ ስለሚታወቅ ከዚህ ውስጥ አይኖሩም ብለው ተመለሱ። ያኔ ታዲያ የጉዞ ባልደረባቸው አቡበክር ደንግጠው፡- "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አንዳቸው እኮ ወደ እግሩ ቢመለከት ያየን ነበር" ሲል ተናገሩ። ነብዩም ሰ.ዐ.ወ ታሪካዊ መልስ ሰጡት፡- "አንተ አቡበክር ሁለት ሆነው ሶስተኛቸው አላህ የሆነን ስብስቦች ምን ይነካቸዋል ብለህ ነው?!።"

አዎ! ምክንያቱን (ሰበቡን) በተገቢ መልኩ ካደረስንና ሀላፊነትንን ከተወጣን ከዚያ በኋላ ለሚያጋጥመን ችግር ፈጣሪያችን ይረዳናል። የተወኩል ትክክለኛ ትርጉምም ይህ ነው። ሰበቡን በተገቢው መልኩ እናደርሳለን። ከዛም ሰበቡ ብቻውን ምንም እንደማይጠቅመን በማሰብ ፈጣሪ ላይ እንደገፋለን።

አንተም በስኬት መንገድህ ላይ በፈጣሪ መመካትህን አትርሳ። ለስኬት የሚጠበቅብህን ሙሉ እርምጃ ውሰድ፤ በደምብ አንብብ፤ ተንቀሳቀስ፤ ሌሎችን አማክር፤ ከአላማህ ጋር አብረህ ኑር (Stick with your goal)፤ ፤የሚጠበቅብህን ሙሉ ክፍያ አድርግ... ከዛም እነዚህ ሁሉ ጥረቶችህ የማይጠቅሙህ ያህል በሙሉ ልብህ ጌታ ላይ ተደገፍ። ያኔ በስኬት ትንበሸበሻለህ።

10.3 ጠንካራ ወኔ ይኑርህ

"አንጋጥጬ ቆሜ	-	ደመናው ሰፎ ባይ
መሬት ላይ ቁጭ ብዬ	-	ከታች ወደ ሰማይ
ቆርጬ ተነሳሁ	-	ሳያሻኝ አይዘሀ ባይ
ከፀሐዩ ቢታች	-	ከደመናው በላይ
ደመናውን ቁልቁል	-	አየር ላይ ሆኜ ላይ"[133] ሃN

[133] የኡስታዙ ማስታወሻ - ግጥም በያሲን ኑሩ ኢሳ (ያልታተመ)

በመንገድህ ላይ የማይበርድ ወኔ ይኑርህ። ጠንካራ ስሜት ይጋባሃል። ግቦችህ ዋነኛ እንጅ መናኛ አይሁኑ። ከተረፅከው ግብህ ትደርስ ዘንድ ውስጥህ ሁሌም በለውጥ ስሜት የሚቀጣጠል መሆን አለበት። ከአንዱ ስኬት ወደ ሌላው ስኬት የሚያሻግርህ ጠንካራ ወኔ ሁሌም አይለይህ።

ስኬታማ ለመሆን ያለን ጉጉት፣ አንድን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ካለን ጠንካራ ፍላጎት ይመነጫል። ናፖሊዮን ሂል እንዲህ የሚል አምነት አለው፡- "የሰው ልጅ አዕምሮ አገኛለሁ ብሎ ያመነበትን ማንኛውም ነገር ያገኘዋል።"

በቁርጥ ፈልገው

በአንድ ወቅት አንድ ወጣት ሶቅራጥስን የስኬት ምስጢር ምን እንደሆነ እንዲነግረው ጠየቀው። ሶቅራጥስ ከወጣቱ ጋር በነጋታው ጠዋት ከወንዙ ዳርቻ ለመገናኘት ቀጠሮ ያዘ። በነጋታው ሁለቱም እየተራመዱ ወደ ወንዙ ገቡ። ውሃው አንገታቸው ላይ ሲደርስ በድንገት ሶቅራጥስ ልጁን ጎትቶ ውሀው ውስጥ ደፈቀው። ልጁ ለመውጣት ቢታገልም፣ ጉልበቱ ከሶቅራጥስ ጋር ሊመጣጠን ስላልቻለ ጥረቱ አልተሳካለትም። በመጨረሻ ወጣቱ ከጭንቀት የተነሳ ፊቱ መቀያየር ሲጀምር ሶቅራጥስ ለቀቀው። ልጁ አየር ስቦ ከተረጋጋ በኃላ ሶቅራጥስ እንዲህ ሲል ጥያቄ አቀረበለት። "ለመሆኑ ውሃ ውስጥ ሳለህ ከምንም ነገር በላይ አስፈልጎህ የነበረው ነገር ምንድን ነው?" ልጁ ሳያመነታ በፍጥነት "አየር!" ሲል መለሰ። "የስኬት ሚስጥር ይህ ነው። ውሃ ውስጥ ሆነህ ልክ አየር የፈለከውን ያህል ስኬትንም በቁርጥ ፈልገውና ታገኘዋለህ። ይህ ብቻ ነው ሌላ ሚስጥር የለውም" አለው ሶቅራጥስ[134]።

"ከልብ መሻት የውጤታማ ጉዞ ዋነኛ መነሻ ነጥብ ነው። በቂ ሙቀት ማግኘት እንደማይቻል ሁሉ ደካማ ፍላጎትም ታላቅ ውጤትን ሊያስገኝ አይችልም።" ይሉናል ሺቭ ኬራ።

---

[134] ሶቅራጥስ - አዉቅ ፈላስፋ (ከ469 - 399BC) አካባቢ የነበረ። — "በህይወት ከሚገኙ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ጠቢቡ እኔ ነኝ፣ ምክንያቱም እንድ ነገር አውቃለሁና ነው። ይህም ምንም ነገር የማላውቅ መሆኔን ነው" በሚለው ጠቢባዊ ንግግሩ ይታወቃል።

ሶስቱ አሳ አጥማጆች

ስፔን ውስጥ የሚኖሩ ሶስት ወጣት አሳ አጥማጆች እንደነበሩ ይነገራል። ለአካባቢው ማህበረሰብ አሳዎችን በማቅረብ ይታወቃሉ። ታዲያ አንዱ ከመካከላቸው እንደኛው የአሳ ማጥመድ ህይወቱ አስጠላው። ከአሳ አጥማጅነት ሙያ በላይ ያስፈልገኛል። "እንዲያውም የዚህች ሀገር መሪ ነው መሆን ያለብኝ" ብሎ አለመ።

በማግስቱ ጠዋት ከሁለት ጓደኞቹ ጋር ወንዙ ዳርቻ እንደተቀመጡ ይህን ምኞቱን ነገራቸው። ጓደኞቹም ብዙም ቦታ ሳይሰጡት ወደ ሌላ ወሬ ገቡ። እርሱ ግን ወሬውን ቀጠለ። "ወደፊት የዚህች ሀገር ፕሬዝዳንት እሆናለሁ" አለ የጓደኞቹን ዓይን በአትኩሮት እየተመለከተ። እነሱ "ይህ የማይሞከር ነው። ይህ አጉል ህልም (ቅዠት) እንጂ አላማ አይደለም" አሉት። በመልሳቸው በጣም ተበሳጨ። አስከትሎም "ለወደፊት የዚህች ሀገር ፕሬዝዳንት (ንጉስ) እንደምሆን አትጠራጠሩ" አላቸው። እነሱም "ዛሬ ምን ነክቶሀል። አንተ እኮ ተራ አሳ አጥማጅ ነህ እንዴት ፕሬዝዳንት ለመሆን ታስባለህ? ይህ አይታሰብም አርፈህ ቁጭ በልና ስራህን ስራ" አሉት።

አሁን ግን በጣም ተበሳጨ። የተናገረውን ነገር ለመተግበር ያለውን ጠንካራ ወኔና ቁርጥ ውሳኔ ሊያሳያቸው ፈልጎ "ለወደፊት የዚህች ሀገር ፕሬዝዳንት ስሆን ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ?" ሲል እንደኛውን አፈጠጠበት። ጓደኛው በጣም ተገርሞ ሳቀ። "አንተ የዚህች ሀገር ፕሬዝዳንት ልትሆን? ይህማ አይታሰብም" አለው። "በለስ ቀንቶህ የሀገሪቱ መሪ ከሆንክ፣ እኔን ራቁቴን አህያ ላይ አስተኝተህ በከተማይቱ አዙረኝ" አለው እያሾፈ። እርሱ ግን አልሳቀም። ወደ ሁለተኛው ጓደኛው በመዞር "አንተስ ለወደፊት ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?" ሲል ጠየቀው። ይህ ጓደኛውም አንደ መጀመሪያው ሊያናድደው አልፈለገም። "አላህ ካሰብከው ያድርስህ። ያኔ ንጉስ ስትሆን ሰማይ ጠቀስ ፎቅ፣ መርቅ፣ ብር፣ ሰፊ ለም መሬት፣... እንድትሰጠኝ እመኛለሁ" አለው ማስገሪያ መረቡን ወደ ወንዙ እየወረወረ። በእርግጥ ይህን ሲል ንዴቱን ለማብረድ እንጂ የማይታሰብ አላማ እንደ ነበር ያምናል።

ዳሩ ግን ይህ ወጣት በአላማው ፀና። የአላ ማጥመጃ መረቡን ጥሎ ወደ አላመው ግብ የሚያደርሰውን መንገድ ተከተለ። ያኔ በነበረው ስርዓት አንድ ሰው ወደ ስልጣን ለመምጣት ከፈለገ የወታደራዊ ብቃት ያስፈልግ ነበር። ወጣቱም በወታደራዊ ስልጠና ውስጥ ገባ። ሁሌም ታታሪና ትጉህ ነበር። በተመደበበት ማንባር ግዳጁን በተገቢው ሁኔታ አጠናቆ ይመለስ ያዘ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያሳየው ትጋትና ብቃት ማዕረጎችን እያገኘ ይሄድ ጀመር። ይህ የማዕረግ እድገቱ እየጨመረ መጥቶ ከ33 ዓመት የውትድርና አገልግሎት በኋላ የሀገሪቱ ኢታማዦር ሹም ለመሆን በቃ። በዚህ የተነሳ የፕሬዝዳንቱ የቅርብ አማካሪ ተደረገ። ፕሬዝዳንቱ ለቁልፍ ውሳኔዎች የሚያወያየው ብቸኛ ሰው ሆነ።

ድንገት በዚያው ዓመት ፕሬዝዳንቱ ሞተ። የሀገሩ ህዝብ የፕሬዝዳንቱን ህፃን ልጅ የሀገሪቱ አልጋ ወራሽ አድርጎ ሾመ። ነገር ግን ልጁ በጣም ሊጋ ስለሆነና ሀገር የማስተዳደር ብቃት ስለሌለው የጦር ሀይሉን ጠቅላይ አዛዥ አጋዥ የሀገሪቱ መሪ አድርገው በበዓለ-ሲመቱ ላይ አወደቁ። ህፃኑ እንደ ደንቡ ዙፋኑን ቢይዝም፤የሀገሪቱ አስተዳዳሪ ግን የጦርሀይሉ አዛዥ (አላ አጥማጁ ወጣት) ሆነ።

ታዲያ እንዴ ከተንጣለለው ቤተ-መንግስቱ ውስጥ እንደተቀመጠ ረዥም የስኬት ጉዞውን መመርመር ጀመረ። በወታደራዊ አለም ያሳለፋቸው ውጣ ውረዶች አዕምሮው ውስጥ ተከሰቱ። እንዴት ወደ ወታደራዊ ህይወት እንደገባ በህሊናው ቃኘው። ድንገት እነዛ አላ አጥማጅ ጓደኞቹ ትዝ አሉት። ቦታውን በመጠቀም እነዚህ አላ አጥማጆች በህይወት ካሉ ፈልገው እንዲያመጡለት አዘዘ። ወታደሮችም ወደ ተላኩበት ቦታ ሲያቀኑ ሁለት በእድሜ ገፋ ያሉ አላ አጥማጆችን ተመለከቱ። ስማቸውን ጠየቁና ማንነታቸውን አረጋገጡ። ቤተ-መንግስት ውስጥ እንደሚፈለጉ ሲነግሯቸው ግን ማመን አልቻሉም። "የሰም ስህተት ይሆናል እንጂ እኛን ማን ይፈልገናል" ሲሉ ሞገቱ። በመጨረሻም አማራጭ ስላልነበራቸው ከወታደሮቹ ጋር ወደ ቤተ-መንግስቱ አቀኑ።

ወደ እልፍኙ ውስጥ እንደገቡም ሁሌም ዝናውን የሚሰሙለትንና አይተውት የማያውቁትን የሀገሪቱ የጦር ሀይል ኢታማዦርሹም ጋር ተገናኙ። እርሱም እንኳን ደህና መጣችሁ ካለ በኋላ ስለ ህይወታቸው

ጠየቃቸው። አስከትሎም እርሱን ያውቁት እንደሆነ ጠየቃቸው። እነሱም "ንጉስ ሆይ! እኛ ከአሁን በፊት አይተነዎት አናውቅም" ሲሉ መለሱ። በእርግጥ ከ33 ዓመት በኋላ ሊያውቁት ይከብዳል። እርሱም አሁን አለባበሱ የነገስታቶች አይነት ነው። እንዴት ሊያስታውሱት ይችላሉ?!

ንጉሱም በማስከተል የድሮ ጓደኛቸው እንደነበር አስታወሳቸው። ከ 33 ዓመት በፊት አብሯቸው አሳ ያጠምድ እንደነበር ነገራቸው። በጣም ተደናገጡ። በአትኩሮትም ሲመለከቱት የወጣትነት ፊቱ ትዝ አላቸው። አዎን! ይህ ንጉስ ከዓመታት በፊት አብሯቸው አሳ ያጠምድ ነበር። በአንድ የህይወት አጋጣሚ ወንዙ ዳር ላይ ሆነው ብዙ ተወያይተዋል። አሁን ደግሞ ግቡን አሳክቶ የሀገሪቱ ፕሬዝዳነት ሆኗል። በጣም ተገረሙ።

ንጉሱም ወደ አንደኛው በመዞር "አንተ ለወደፊት የዚህች ሀገር መሪ ስሆን ምን ትፈልጋለህ? ብዬ ስጠይቅህ ምን ነበር ያልከኝ?" አለው። እርሱም "ንጉስ ሆይ! እንኳን አላህ እዚህ አደረሰልኝ እንጂ፣ እኔማ ሰማይ ጠቀስ ፎቅ፣ ወርቅ፣ ብር፣ ሰፊ ሰም መሬት፣ መናፈሻ፣ በወርቅ ኮርቻ ያሸበረቁ ሰረገላዎች... እንዲሰጠኝ ነበር የተመኘሁት" አለ። ንጉስ ወዲያውኑ እንዲሰጠው አዘዘ።

ወደ ሌላኛው በመዞር "አንተስ ምን ነበር ያልከው?" አለው ቁጣ አዘል ፈገግታ እያሳየው። ይህ አሳ አጥማጅ የሚናገረው ግራ ገባው። ያኔ ቀልድ መስሎት የማይሆን ነገር ተናግሯልና።

አሳ አጥማጁ፡- "ንጉስ ሆይ! ያልኩትን ነገር አላስታውስም። ረስቸዋለሁ።" ሲል መለሰ። ንጉሱም "በፍፁም" በሚል ቃና በተደጋጋሚ ጠየቀው። መመለሱ ግድ እንደሆነ ሲያቅ፡- "ንጉስ ሆይ! ያኔ ጨዋታ መስሎኝ ብዙ ዘባርቄያለሁ። ለወደፊት የዚህች ሀገር መሪ ከሆንክ አህያ ላይ ራቁቴን አስረህ ከተማይቱን አዙረኝ ነበር ያልኩት" አለና ራሱን አቀረቀረ።

ንጉሱ ግን አላዘነለትም። እንዲህ የሚል ትዕዛዝ አስተላለፈ፡- "ይህን ሰው ራቁቱን አህያ ላይ አስተኝታችሁ ከተማይቱን አዙሩት። ማህበረሰቡም ሲጠይቃችሁ የሶስታችንን ታሪክ ተርኩለት። አላህ የተመኙትን የሚሰጥና እርሱም በሁሉ ነገር ላይ ቻይ መሆኑን ህዝቤ እንዲያውቅ እፈልጋለሁ።"

ግለሰቡ አህያው ላይ በሆዱ ተኝቶ ከተማይቱን ዞራት። ይህም ክስተት በስፔን (Spain) ታሪክ ውስጥ አስገራሚ ክስተት ተብሎ ተመዘገበ።[135]

አንተስ ግብህ መናኛ ነው ሁነኛ? ተራ አላ አስጋሪ ወይስ ፍትሃዊ ሀገር መሪ?... ትልቅ አላማ ይኑርህ። ይህንንም ለማሳካት ጠንካራ ወኔን ተላበስ፣ እርምጃህን በፅናት ቀጥል፣ ያኔ ወደ ስኬት ከመድረስ ውጭ ምንም አማራጭ አይኖርህም።

ነፍሴ ወኔ የተሞላች ናት

ከነብዩ ስ.ዐ.ወ በኋላ ከመጡ አምስት ቅንና ብቁ መሪዎች ውስጥ አምስተኛው - ዑመር ኢብኑ ዐብዱል ዐዚዝ[136] ይባላሉ። የታላቁ መሪ ዑመር ኢብኑል ኸጣብ[137] የልጃቸው ልጅ ነው። ዑመር ኢብኑ ዐብዱልዐዚዝ የስኬት ምንጫቸውን እንዲህ ሲል ይተርክልናል፦

"እኔ ወኔዋ የማይበርድ፣ በጠንካራ ስሜት የታጨቀች ነፍስ አለችኝ። ከአንድ ስኬት ላይ ስትደርስ ከፍ ወዳለ ስኬት ለመድረስ ትቃጣለች። ገና በወጣትነቴ የአጎቴን ልጅ ፋጢማን ለማግባት ነፍሴ ፈለገች። ምክንያቱም ፋጢማ በጣም ቆንጆ፣ አላህን ፈሪ፣ ገጣሚ፣ ቁርዓንን በቃሏ የሸመደደች፣ ሊቅ ናትና። በዚህ ላይ ሰባቱም የቤተሰብ ክፍሎቿ የሙስሊሙ ዓለም መሪዎች (ኸሊፋ) ናቸው። አያቷ፣ አባቷና አራቱ ወንድሞቿ የዓለምን አንድ ሶስተኛ የሚሸፍነውን የሙስሊሙን ዓለም ያስተዳድሩ ነበር። እርሷን ማግባት ምንኛ ስኬት ነው?! በአላህ ፈቃድ አገባኋት።

"ከዚያም ነፍሴ የሀገር አስተዳዳሪ መሆንን ተመኘች። ከጥረት በኋላ የመዲና (የሳዑዲ ዐረቢያ አንዷ ግዛት) መሪ ሆንኩኝ። በዚህም ስኬት ነፍሴ ፍላጎቷ አልተገታም። የሙስሊሙ ዓለም መሪ (ኸሊፋ) መሆን አለብኝ ብዬ ተነሳሁ። በአላህ እገዛ የዓለምን አንድ ሶስተኛ ለማስተዳደር

---

[135] ዶ/ር ጣሪቅ አስ-ሱወይዳን - ተግይሩ ነፍሲ (ከከፊል ማሻሻያና አተራረክ ጋር)

[136] ዑመር ኢብኑ ዐብዱልዐዚዝ - በሂጅርያ አቆጣጠር 99-101 ድረስ የሙስሊሙን ዓለም (የዓለምን አንድ ሶስተኛ) የመሩ ታላቅ ሰው።

[137] ዑመር ኢብኑል ኸጣብ - ታላቅ መሪ፣ የነብዩ ሙሐመድ ﷺ ባልደረባ፣ ከእርሳቸው በኋላ አብዛኞቹን ተክቶ የሙስሊሙን አለም ከ10 ዓመት በላይ ያስተዳደሩ። እውቁ ምሁር Micheal Hart – "The 100 Ranking of the most Influential persons in History" በተሰኘዉ ድንቅ ስራቸዉ ዑመር ኢብኑል ኸጣብን ዓለም ላይ ተፅዕኖ ፈጥረው ካለፉ ታላላቅ ሰብዕናዎች ጋር

በታሁ። አሁንም ከፍ ወዳለ ስሜት እየጠራኝ ነው። አሁን ነፍሴ ወደ ጀነት ቋምጣለች።"

ታላቁ መሪ ዑመር ኢብኑ ዐብዱል-ዐዚዝ ጠንካራ ወኔ ነበራቸው። ከስኬት ወደ ስኬት ያሸጋገራቸውን የማይበርድ ስሜት ውስጣቸው ለንቀዋል። ቆንጆ ሚስት አግብቷል፣ የዓለምን አንድ ሶስተኛ የማስተዳደር የመሪነት ወንበር ላይ ተቀምጠዋል። ነገር ግን ይህ ሁሉ ብቻውን ስኬት አይደለም። ይህ መዳረሻ (Means) እንጅ መድረሻ (Final Goal) አይደለም። የምድራዊ ስኬቶችን ሁሉ የምናሰልፍበት ሌላ መሰረታዊ ግብ (The Goal of Goals) አላቸው። ይህን የመጭው ዓለም ሙሉና ዘልዓለማዊ ስኬት ነማግኘት የምድራዊ ስኬታቸውን እንደ ጥሬ እቃ (Input) ተጠቀሙበት።

ይህ ታላቅ ሰው በስልጣን ላይ የቆዩት ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር (ለሰላሳ ወራት) ብቻ ነበር። በዚህች አጭር ጊዜ ውስጥ ግን ምድርን በፍትህ ሞልተዋት አልፈዋል። ከእርሱ በፊት ቦታው ላይ የነበሩ አመራሮች የፈጠሩትን ክፍተቶች ሁሉ ሸፍነዋል። ማህበረሰቡን ከችግር አላቀዋል። ህዝቡ ኢኮኖሚያዊ ድሎት (financial freedom) ላይ ከመድረሱ የተነሳ የዘካ[138] ብር የሚቀበል ጠፍቶ ነበር። ከሚያስተዳድሩት ሰፊ ግዛት ዘካ የሚቀበል በመጥፋቱ ምክንያት፣ ገንዘቡ ተሰብስቦ ደቡብ አፍሪካ (ኬፕ-ውን ከተማ) ለሚገኙ ድሆች እንዲከፋፈል ተደርጓል።

በፍትህ ያስተዳደሯትን መሬት አላህ ባርኮላቸው ነበር። እንደሚታወቀው ሁሌም ፍትህ ሲንሰራፋ፣ ብክለት ሲወገድ የአላህ ረድኤት ምድር ላይ ይሰፍናል። በዑመር ዘመንም የሆነው ይኸው ነው። የተዘሩ አዝመራዎች ውርጭ ሳይመታቸው ፍሬያቸውን ይለግሳሉ። በእርሳቸው የግዛት ዘመን የበቀለ የስንዴ ፍሬ ቱርክ (ኢስታንቡል) የሚገኝ አንድ ሙዚዬም ውስጥ ለታሪክ ተቀምጧል። ይህ የስንዴ ፍሬ የቴምር ፍሬ ያህላል።... ምን አይነት በረከት ነበር በዑመር የግዛት ዘመን ፊጣሪ ወደ ምድር ያወረደው?!!

[138] ዘካ - ከእስልምና እምነት 5 መሰረታዊ ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ ነው። አንድ ሙስሊም 85 ግራም ወርቅ መግዛት የሚችል አቅም ካለዉ በአመት 2.5 ፐርሰንት ዘካ የማውጣት ግዴታ አለበት።

ውድ የሀገሬ ልጆች- ምድር በሁለት ህጎች ትመራለች። አላህ ሁለት መሰረታዊ ህጎችን አስቀምጧል። አንደኛው በሰዋዊ ጥረቶች የሚፈፀም ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በፈጣሪ ቀጥተኛ እርዳታ የሚከናወን ነው። የሰው ልጅ ዘርቶ፤አርሞ፤ ኮትኩቶ... ጥሩ ምርት ያገኛል። ይህ የሰዋዊ ህግ ነው። ነገር ግን ፈጣሪውን ከታዘዘ፤ለእርሱ ታማኝና ጥንቁቅ ከሆነ፤ ከዘራው በላይ ውጤት ያገኛል። በቃ! ህጎቹ እነዚህ ናቸው። የሰዋዊ ህግ (የጥረት ህግ) እና የኢማን ህግ ይባላሉ። ሁለቱን ያከበረና የተገበረ ሰው የስኬት ማማ ላይ ይወጣል። አላህ (ሰ.ወ) ይህን የኢማን ህግ ቁርዓን ላይ እንዲህ ሲል ያስቀምጠዋል፦

"የከተማዋም ሰዎች ባመኑና በተጠነቀቁ ኖሮ፤ በእነሱ ላይ ከሰማይም ከምድርም በረከቶችን በከፈትንላቸው ነበር..."[139]

አዎ! አንተም ጠንካራ ወኔ ይኑርህ። ከፍ አድርገህ አስብ። ይህንንም ለመተግበር ውስጥህ በከፍተኛ ስሜት ይናጥ። ይህ ጠንካራ ወኔ የአላማህ ጥግ እንድትደርስ የሚያደርግህ ወሳኝ ንጥረ-ነገር ነው።

መናኛ ግቦች

አንድ ገበሬ - መንገድ ዳር ተቀምጦ በአካባቢው የሚያልፉትን መኪኖች በዓይነ ቁራኛ የሚጠብቅ ውሻ ነበረው። አንድ መኪና ሲመጣ ካየ ወዲያውኑ ወደ መንገዱ እየሄደ በመጮህ ሊደርስበት ይሞክራል። አንድ ቀን ጎረቤቱ "ውሻህ መኪና የሚይዝ ይመስላል?" ብሎ ቢጠይቀው፤ "እኔን የሚያስጨንቀኝ እሱ ሳይሆን፤ መኪና መያዝ ቢችል ምን ሊያደርገው እንደሚችል ነው" በማለት ገበሬው መለሰለት።[140]

ታዲያ አንተ በመንገድህ ላይ ዋነኛ እንጂ መናኛ ግቦች አይኑርህ። የዳንኤል ኤች በርንሀም ምክር ተመችታኛለች። አንተም እስኪ ልብ ብለህ አንብባት፦ "ትናንሽ ግቦችን አታውጡ። ትናንሽ አቅዶች የሰዎችን የልብ

[139] ቁርአን 9 : 96
[140] Shive Kehera- You can win

ምት የሚያጣድፍ ሀይል የላቸውም። ትላልቅ እቅዶችን በመንደፍ በተስፋና በስራ ተንጠራርታችሁ አልመ።"

10.4 አላማህ እስኪሳካ ታጋሽ ሁን

"ድል (Success) ከትዕግስት ጋር ነው" ነብዩ መሐመድ ﷺ

የቀረፅከው አላማህ ጥግ እስኪደርስ ድረስ መታገስ ታላቅ ቁም ነገር ነው። በመንገድህ ላይ ትዕግስት ዘመድህ፣ ዕናት ወዳጅህ ይሁን።

ከታላቁ መለኮታዊ መፅሀፍ (ቁርዓን) ውስጥ "ትዕግስት" የሚለው ቃል ከዘጠና ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። "ቁርዓን ውስጥ እንደ ትዕግስት (ሰብር) በብዛት የተጠቀሰ ቃል የለም። ይህም ፈጣሪ ለትዕግስት የሰጠውን ትልቅ ቦታ ያመላክተናል" ይላሉ ታላቁ ሊቅ ኢማሙ አህመድ[141]። ፈጣሪ ኩን (ሁን!) በሚለው ትዕዛዙ ሰማይና ምድርን መፍጠር እየቻለ ስድስት ቀን መውሰዱ ለእኛ በሂደት መለወጥን ለማስተማር መሆኑን ልብ ልትለው ይገባል።

እንደ አብዛኛው ሰው ግንዛቤ ትዕግስት ማለት የመጣብንን ችግር መቋቋም፣ የወረደብንን መከራ በዕናት ማሳለፍ ነው። ነገር ግን ትዕግስት ይህ ብቻ አይደለም። "ትዕግስት የያዝከውን ዓላማ፣ የጀመርከውን ስራ፣ የቀረፅከውን የህይወት ጉዞ ጥግ እስኪደርስ መፅናትም ነው"።[142]

ግልፅ አላማ ያነገቡ ሰዎች ጉዟቸው አልሰምር ሲል አላማውን ሳይሆን ዘዴያቸውን (አተገባበራቸውን) ይቀይራሉ። የተለያዩ አማራጮችን ይጠቀማሉ። 2 የ (1+1) ውጤት ብቻ ነው ብለው አያምኑም። 4÷2=2 ፣ 6 4=2 ፣ 2×1=2... መሆኑን ያውቃሉ።

ወደ ስኬት በምታደርገው ጉዞህ ላይ ሁሌም በለስ አይቀናህም። ሁሉም ነገር ባቀድከው መልኩ ላይተገበር ይችላል። ዋናው ቁም ነገሩ የትግሉን ጉዞ ድምር ውጤት ማሸነፍ እንጂ እያንዳንዱን ፍልሚያ በበላይነት ማጠናቀቅ አይደለም። ለዚህም ነው "Success Means Winning the war, not every battle" -"ስኬት እያንዳንዱን ግጥሚያ (ፍልሚያ) ማሸነፍ ሳይሆን

[141] ኢማሙ አሕመድ ኢብኑ ሐንበል - ከአስልምና ታዋቂ አራት መዝሀቦች (School of thought) ውስጥ የአንዱ መስራች የሆኑና በ800 ዓ.ል አካባቢ የነበሩ ታላቅ ሊቅ።
[142] ዶ/ር ጃሲም ሱልጣን - ሚነስህዉቲ ኢለልየቀዛ

ጥቅል ጦርነቱን ማሸነፍ ነው" የሚባለው።

"ብዙ አሸናፊ (ስኬታማ) ግለሰቦች ለውጤት ከመብቃታቸው በፊት እልህ አስጨራሽ ትግሎችን ማለፍ እንደነበረባቸው ታሪክ ዘግቦታል። ለአሸናፊነት የበቁት ሽንፈትንና ተስፋ መቁረጥን በፀጋ መቀበል ባለመፈለጋቸው ነው።" ቢ.ሲ ፎርብስ

ግብህ እስኪሳካ ከፊት ለፊትህ የሚገጥሙህን ችግሮች በፅናት አለፋቸው። የጀመርካቸው ስራዎች ጥሜ እስኪደርሱ ድረስ ታገስ።

ቶማስ ኤድሰን

ኤድሰን ሰነፍ ነው ተብሎ ከትምህርት ቤት ከተባረረ ጀምሮ የእናቱ እንክብካቤ አልተለየውም ነበር። ቤት ውስጥ የሚያስፈልገውን ትምህርት ሁሉ ተከታተለ። ኤድሰን ሌት-ተቀን ስራው ላይ ይውል ነበር። በቀን ውስጥ ከ18-20 ሰዓታትን በስራ ላይ ያሳልፍ ነበር። የኤሌክትሪክ መብራትን ለመፍጠር አንድ ሺህ ያህል ሙከራዎችን እንዳደረገ ይናገራል፡

"አንድ ስኬት ወደ ሌላ ስኬት ይመራል" እንደሚባለው ሁሉ ኤድሰን ምርምሩን በትጋት ቀጠለ። ሶስት ሚሊየን ዶላር ወጪ ተደርጎ ከ 50 ሺህ ሙከራ በኋላ፣ የመኪና ባትሪን፣ ባቡር ሀዲድ ላይ የሚገጠም አመላካች መሳሪያን እንዲሁም የሰርጓጅ መርከብ መብራቶችን ፈጠረ። ሁሌም የምርምር ላብራቶሪው ውስጥ የሚያዩት ወዳጆቹ "እረፍት መቼ ነው የምትወስደው?" ብለው ሲጠይቁት እርሱም "ሬሳዬ ወደ መቃብር ሲገዝ ነዋ" ሲል መለሰላቸው።[143]

አንተም በመንገድህ ላይ ፅናት ያስፈልግሀል። ጥሩ ውጤት ትጋትን ይፈልጋል። ስኬት በአበባ ላይ ተራምደን የምንደርስበት መስክ አይደለም። እወቅ "ትላልቅ ስራዎች የሚከናወኑት በታላቅ ጉልበት ሳይሆን ሳያቋርጡ በመስራት ነው" Samuel Johnson

ችግሮችን በፅናት ተጋፍጠህ አለፋቸው። ነገሮቹ የተወሳሰቡ ሲመስሉህ ስኬታቸው እንደቀረበ ተረዳ። የነገሮቹ መወሳሰብ የስኬት ደውሎች መሆናቸውን አትርሳ። ያኔ ነው የበለጠ መጠንከር ያለብህ... ያኔ ነው ግስጋሴህን መቀጠል የሚጠበቅብህ።

[143] ዶ/ር ዐሊይ አልቀርኒ - ኢሻራቱን ዐለ ጦሪቅ ገፅ. 37

የቡኻሪ ፅናት

ቡኻሪ አባታቸው በርካታ ንብረት ትተውላቸው ቢያልፉም ሀዲስን ለመሰብሰብ አላማቸው ሙሉ ለሙሉ አውለውት ነበር።

አንዴ ምን ተከሰተ መሰላችሁ፡- ቡኻሪ ባልተለመደ መልኩ ከሐዲስ ትምህርት ገበታቸው ቀሩ። አስተማሪያቸውና ተማሪዎቹ በዚህ እንግዳ ነገር ተደናገጡ። በአጋጣሚ የተፈጠረ ጉዳይ ሊሆን ይችላል ብለው አለፉት። ሆኖም በተከታታይ ቀናት ተደገመ። ሁኔታውን ለማጣራት ጓደኞቻቸው ወደ ቡኻሪ ቤት አቀኑ። ከቤትም ሲደርሱ ቡኻሪን በመኝታ ልብሳቸው አገኟቸው። አስከትለውም ለምን እንደጠፉ ጠየቋቸው። የቡኻሪ መልስ ግን በጓደኞቻቸው ልብ ውስጥ ትልቅን ቦታ የፈጠረ ሆኖ አለፈ። አዎ! ቡኻሪ ሐዲስን ለመሰብሰብ የአመታት ጉዞ ሙሉ ንብረታቸውን ወጪ ከማድረግ አልፈው የቀን ልብሳቸውን እስከመሸጥ በመድረሳቸው ለብሰውት ወደ ትምህርት ገበታ የሚሄዱበት ልብስ ማጣታቸውን ነገሯቸው።

ጓደኞቻቸውም ለዓላማ የሚከፈልን ዋጋ ልብ እንዲሉ እድል ሰጣቸው። ስኬት ፅናትን እንደሚፈልግ አስተማሩዋቸው። በቡኻሪም ከፍተኛ የሐዲስ ጥናት ጥማት በጣም ተማረኩ። ገንዘብ አሰባስበው ልብስ ገዙላቸው። አሁን ቡኻሪ ወደ ትምህርት ገበታቸው መመለስ ይችላሉ።[144]

ሌላ ጊዜ ምን ተከሰተ መሰላችሁ፡- ከላይ እንደተመለከትነው ቡኻሪ ወደ በርካታ ሀገራት እየተንዘዙ የሀዲስን እውቀት ከ1000 በላይ ከሆኑ ምሁራኖች ቃርመዋል።

ታዲያ ሁሌም ጉዞዎቹ የሰመሩ አይሆኑም። ለችግርና ለአደጋ የሚጋለጡበት ጊዜም ነበር። በአንድ ጉዞ ላይ የገጠማቸውን ችግር እንዲህ ያስነብቡናል፡- "ከጉዞዎቼ መሀል በአንዱ... መንገድ ላይ ገንዘብ አለቀብኝ ቅጠላቅጠሎችን መብላት ግድ ሆነብኝ። ለተከታታይ ሶስት ቀናትም ቅጠል እየበላሁ ቆየሁ። ከዚያ ግን የማላውቀው ሰው በቦርሳ ሙሉ ገንዘብ ይዞልኝ መጣና ለራስህ ብቻ ተጠቀምበት ብሎ ሰጠኝ።"[145]

---

[144] Maulana Ahmed Ali, imam bukhari, his life and works

[145] ጦቢቃቱ ሱብቂ, 6ቱ የሀዲስ ሊቃውንት - ዝግጅት መሐመድ ዓሊ

እኒህ በቅንጦት ያደጉ የባለፀጋ ቤተሰብ ተወላጅ ለዓላማቸው ሲሉ ይህን ያህል መስዋዕትነት ከፍለዋል። በተለያዩ ጉዞዎች ቅጠል ከመብላታቸው የተነሳም በክባድ የሆድ ድርቀት ህመም ይሰቃዩ ነበር። ታዲያ ሁሌም ህክምናን ሊወስዱ የሚሄዱባቸው ቅጠል መብላታቸውን እንዲያቆሙ ያስጠነቅቃቸዋል። አሥ! ስኬት ሙሉ ለሙሉ ራስን ለዓላማ መስጠትን ይጠይቃል።

ልብ ብለህ ከሆነ ከዚህ ታሪክ ውስጥ አትኩሮትን የሚስብ ሌላ ጉዳይ አለ። ያ በቦርሳ ሙሉ ገንዘብ ሰጧቸው የተሰወረው ግለሰብ ነው። ማን ይሆን በዚያ በረሃ በብር ያንበሸበሻቸው? ለዓላማቸው የከፈሉት መስዋዕትነት የተመለከተው የዓለማቱ ጌታ የላከው መልዕክተኛ ይሆን?... ለዚህም ነው እኮ የስኬትን ረሻቦም ጉዞ ብቻህን አትችለውም ያልኩህ። በስኬት ምንገድህ ላይ በጌታህ ተደፈግ ስል ያስታወስኩህ። ሰዋዊ ጥረቶች ሁሉ ሲነጥፉ የእርሱን እርዳታ ፊት ለፊት ታገኘዋለህ።

ቡኻሪ ዓለም ላይ የተሰራጩ የነብዩን ﷺ ሀዲሶች (የነብዩ ንግግሮች፣ አስተምህሮዎች፣ ትዛዞች፣ ክልከላዎች፣ ድርጊቶች) በመሰብሰብ ዓመታትን ማስነዋል። ይህ ግብ የሚጠይቃቸው ክፍያ ሁሉ ከፍለዋል። በተለይ ደግሞ ተቀባይነት ያለው የሀዲስ ዘጋቢ ለመሆን ተአማኝና እውነተኛ መሆን ግዴታ ነው። አንድ ሰው በማህበራዊ ህይወቱ ውሸታምና ከሀዲ ከሆነ እንዴት ብሎ የነብዩን ሰ.ዐ.ወ ሀዲሶች፣ መለኮታዊ መመሪያዎች ሲያስተላልፉ ተቀባይነት ይቸረዋል? ቡኻሪም እጅግ ታማኝና እውነተኛ ነበሩ። "ለአቅመ-አዳም ከደረስኩበት ጊዜ ጀምሮ ውሸት ወቦኝ አያውቅም ይላሉ ታላቁ የሀዲስ ዘጋቢ። መልካም ስራቸውንና ታማኝነታቸውን ለመጠበቅ ያደረጉትን ጥንቃቄ ላውሳልህ።

ነገሩ ወዲህ ነው። ቡኻሪ የሀዲስን እውቀት ፍለጋ ያልረገጡት ቦታ የለም። በእግር፣ በፈረስ... ሁሉን ቦታ ጎብኝተዋል። አሁን ደግሞ በመርከብ ተሳፍረው እየተጓዙ ነው። ቡኻሪ መርከቧን እንደተሳፈሩ ብዙም ሳይቆዩ ከተሳፋሪዎች ጋር ተቀራርበው መጨዋወት ጀመሩ። ከተሳፋሪዎች መሃል አንዱ ቀረባቸውና ሰላምታ ሰጣቸው። በሂደት በጣም ተቀራርበው ማውራት ጀመሩ። ከርቀት ላያቸው ሰው የጥንት አብሮ አደግ ጓደኛ ይመስሉ ነበር። ቡኻሪም ሰውየውን በጥሩ ተመልክተው የልባቸውን ንጫወታቸውን ቀጠሉ። በወሬያቸው መሃል ስለያዙት አንድ ሺህ ዲናር

ነገሩት። (አንድ ሺ ዲናር በአሁን ዘመን ከሚሊየኖች ብር እንደሚበልጥ ልብ ይሏል።)

በያዙት ገንዘብ እጅግ የቋመጠው ግለሰብ ታዲያ አንዳች እኩይ ነገር አሰበ። ይህን የወርቅ ሳንቲም እጁ የሚያስገባበትን መንገድ አሰላሰለ። የተሻለው አማራጭ አንድ ብቻ እንደሆን ተረዳ። ገንዘብ እንደጠፋው አድርጎ መጮህ እንዳለበት ወሰነ።

በማግስቱ ማልዶ በመነሳት "ገንዘቤን ተሰረኩ" ሲል አለቀሰ። "አንድ ሺህ ዲናር የወሰደብኝ ማን ነው" ሲል ጮኸ።

እንዲህ አይነት ከንቱ ምግባር በማየታቸው ያዘኑት ቡኻሪ ገንዘቡን ከባህሩ ይጥሉታል። ጨኸትና ለቅሶው ረፍት የነሳቸው የመርከቡ ሠራተኞችም ተሳፋሪዎች በአጠቃላይ እንዲፈተሹ አደረጉ። ፍተሻው ቡኻሪንም የጨመረ ነበር። ነገር ግን ገንዘቡን ከየትኛውም ተሳፋሪ ሊያገኙ አልቻሉም። የመርከቡ ሰራተኞች ሰውየውን በአጭበርባሪነት ፈርጀው ያልፋታል።

ነገሩ ያስደነገጠውና ያሰበው ያልተሳካለት አጭበርባሪም ታዲያ ሀፍረቱን በጨው አጥቦ ወደ ቡኻሪ ጠጋ በማለት ስለገንዘቡ ይጠይቃቸዋል። እርሳቸውም ተንኮሉን ተከትለው ከባህሩ መጣላቸውን ይነግሩታል። "እንዴት ታዲያ ያን ያል ገንዘብ ከባህር ጥለው ምንም እንዳልተፈጠረበት ሰው ሊረጋጉ ቻሉ?" ሲልም አይኑን አፍጥጦ ጥያቄ አቀረበላቸው። ቡኻሪም እንዲህ በማለት መለሱ። "ህይወቱን ሙሉ የነብዩን ሰ.ዐ.ወ. ሀዲስ እየዘገብኩ የኖርኩና ዓለም ሁሉ በታማኝነት የሚያውቀኝ ሰው ስለመሆኔ የማታውቅ ምን ዓይነት ሰው ነህ? እንዲህ ሆኜ ሳለ ለተነሳብኝ የሀሰት ክስ ራሴን አጋልጬ የምሰጥ ይመስልሃል?"

ይህን መሰሉን ገድል ነው "The Price of success" የምንለው። ቡኻሪ በዚህ መልኩ ደክመውና ስማቸውን ጠብቀው የሰበሰቡትን ሐዲሶች በአንድ ድንቅ ድርሳን ውስጥ አሰፈሩት። "ጃሚዑ አስ-ሶሂህ" የሚባልና ከነብዩ ሰ.ዐ.ወ. የተላለፉ ትክክለኛ ዘገባዎችን ብቻ መዕሐፋቸውን ለዓለም አበረከቱ። ይህ ውብ ድርሳን 97 አብይ ምዕራፎችንና በስራቸውም በርካታ ንዑስ ክፍሎችን የያዘ ሲሆን፤ እንዲሁም ከ 7397 ትክክለኛ ሐዲሶችን የያዘ ነው።

ይህን የስኬት ረሻዮም ጉዞ በትዕግስት ተጉዘዋል። ድርሳኑንም ትውልድ በክብር ተቀብሏ.ል። ከ 82 በላይ የሆኑ በየክፍለ ዘመናት የመጡ ሊቆችም በቡኻሪ መፅሐፍ ዙሪያ ሰፊ ትንታኔ የሰጡ መፅሐፍትን ለህትመት አብቅተዋል። እያንዳንዷ ትንታኔን የያዙ መፅሐፎች በርካታ ቅያች አንዳላቸው ልብ ይሏ.ል።[146]

ስኬት በእርግጥ ፅናትንና ልፋትን ይጠይቃል።

ጉንዳን ካሰበችው ለመድረስ ሺህ ጊዜ ከምሰሶው ላይ ትወድቃለች፤ትነሳለች። ንብ ጣፋጩን ማር ለመጋገር ሚሊዮን ጊዜ አበቦች አካባቢ ትመላለሳለች። አዎ! ስኬት ትዕግስትንና ትኩረትን ይጠይቃል... ተኩላ ያለመውን ለማደን ቦታና አቅጣጫ ቀያይሮ ያደባል። ድመት የተመኘችውን ለማግኘት በትእግስት ትጠባበቃች፤ አንበሳ ያቀደውን ለመያዝ በአንክሮ ይከታተላል።

ስለዚህ አንተም ተንቀሳቀስ አትተኛ... ለረሻዮም ጊዜ የተኛ ውሃ ይሸታል። በቦታው ለዘመናት የቆየ ድንጋይ አንድ ቀን ይፈለጣል። ሽቶ ጫን ጫን ሲሉት ጥሩ ሽተተ። ሰንደል ሲያቃጥሉት አካባቢውን አወደ። የሰው ልጅም በችግሮች ሲደበደብ ካልሆነ ጥሩ ጠረን አይወጣውም። ያለ ጥረትና ፅናት ከስኬት ጫፍ አይደረስም።

አትርሳ! ዱንያን የታገለት ነው የሚጥለት። ዓለምን አልሀ የተጋባ ነው የሚያሸንፋት።[147]

አናት ላይ ቁጭ ሲል	-	ቅቤን ብንጠይቀው
"ገፍተውኝ ነው" ይላል	-	አናት ላይ የወጣው
ይሀማ ደንብ ነው	-	ይሀማ በጎ ነው
ያልተገፋ ወተት	-	ቅቤ እንደማይወጣው
የወተት ልጅ አርጎ	-	የእርጎ ልጅ ቅቤ ነው።

[146] 6ቱ የሀዲስ ሊቃውንት - ሙሐመድ ዓሊ
[147] በረካ - ሙሐመድ ሰዒድ (ABX/አቡ ጦልሃ)

እንዳታቆም

ጉዞህ የጨለመ ሲመስልህ ወደ ስኬት እንደተጠጋህ አስብ። የነገሮች መወጣጠር የድል ነጋሪ ደውሎች ናቸው። ሊነጋ ሲል ይጨልማል የሚባለውም ለዚህ ነው። ያኔ ለስኬት እንደቀረብክ እርግጠኛ ሁን። ተስፋን ስንቅ።

"ያ ተስፋን ያልሰነቀው፤ ነፋሱ መጥቶ የመርከቡን አቅጣጫ እንዳያስለውጠው ሲሰጋ፤ ያ ተስፈኛው ደግሞ ነፋሱ ይረጋል ብሎ ሲመኝ፤ ስኬታማዎች ግን የነፋሱን ግፊት የመርከቧን ጉዞ ለማፍጠን ይጠቀሙበታል።"[148]

[148] ዶ/ር ጣሪቅ አስ-ሰወይዳን - ሲናዐቱል ቃዳህ

Don't Quit

When things go wrong,
As they sometimes will,
When the road you are trudging seems all uphill,
When the funds are low and the debts are high,
And you want to smile, but you have to sigh,
When care is pressing you down a bit
Rest if you must, but don't you quit.

...

Life is queer with its twists and turns,
As every one of us sometimes learns,
And many a failure turns about
When he might have won had he stuck it out.
Don't give up though the pace seems slow
You may Succeed with another blow.

....

Success is failure turned inside out
The silver of the clouds of doubt,
And you never can tell how close you are,
It may be near when it seems so far;
So Stick to the fight when you are hardest hit
It's When things seem worst that you must not quit.

CamScanner

11

ምዕራፍ አሰራ አንድ



የስኬት መርሆዎች

- በአላማ ኑር
- የለውጥ ሀግ
- በሀብረት ወደ አላማህ ተጓዝ
- የስኬት ዋጋ
- ተግባራዊ እርምጃ
- ከፍተኛ ጉጉት ይኑርህ
- የግብህን ጉዞ ልመደው
- አሻራህን ትተህ እለፍ
- ከውድቀትህ ተማር
- በስኬትህ አትኩራ
- ሰጪ እንጂ ተቀባይ አትሁን
- የማይመለከትህ ነገር ውስጥ አትግባ
- እንዳትጠለፍ
- ሁሉም ነገር መፍትሄ አለው
- ሁሉንም ማስደሰት አትችልም
- ጥበብን ሁሉም ቦታ ፈልገው

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በጊዜ የማይገደቡ (Time less)፣ በቦታ የማይወሰኑ (Universal) የሰኬት መርሆዎችን እናያለን። እነዚህ መርሆዎች ቋሚ የለውጥ ህጎች ናቸው።

ልክ እንደ መሬት ስበት ህግ (Low of gravity) ሁሉ፣ ለውጥም ራሱ የሆኑ ቋሚ ህጎች አሉት። ህጎቹን የጠበቀ ያለመለትን ስኬት ያገኛል... ግቡ አመፅና በደል ቢሆን እንኳን። እነዚህን ህጎች የተዋቸውና ችላ ያላቸው ውድቀትን ይከናነባል... ግቡ መልካምና ሰብአዊ ቢሆን እንኳን። ህጎቹ ለሰው ልጆች ሁሉ ልክ እንደ ኦክስጅኑ እኩል የተበረከቱ ናቸው። እነዚህን ቋሚ የለውጥ መርሆዎችን እነሆ፡-

11.1 በአላማ ኑር

"በአላማ ከተመራ ህይወት የሚገኝ ስኬት እርካታን ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ አርምጃ በራስ ላይ መተማመንንና ሞራልን ወልዶ ያልፋል።"

እውነታው ይህ ነው። ያቀድነው እቅድ ሲሳካ፣ ባሰብነው መስረት ሲተገበር፣ በቀረፅነው መልኩ ስንራመድ... ያኔ ሌላ አላማዎችን ለማውጣት ሞራል እናገኛለን። ሌላም ጊዜ እቅድ አውጥቼ ይሳካልኛል የሚል ሞራል ውስጣችን ይጎለብታል። ፍሬውም ጣፋጭ ይሆናል።

ህግ 1 - "እቅድ የወለደው ስኬት፣ ለቀጣይ ስኬት መነሻ ነው"

11.2 **የለውጥ ህግ** - ለውጥ ቋሚ ህጎች እንዳሉት መግቢያ ላይ አትተናል። እስኪ ዘርዘር እናድርጋቸው፡-

11.2.1 ለውጥ- ከውስጥ ወደ ውጭ

"አላህ በሰዎች ያለን ሁኔታ አይቀይርም፣ በነፍሶቻቸው ያለን አስኪቀይሩ ድረስ ..."[149]

[149] ቁርአን 13 :11

ፈጣሪ ከእኛ የመጀመሪያ እርምጃ ይፈልጋል። ለለውጥ ያግዘን ዘንድ ቅድሚያ ውስጣችን ለመለወጥ መቁረጥና መዘጋጀት አለበት። ይህንም ማድረግ የለው ልጅ ይችላል። እውነተኛውም ድል እርሱ ነው።

"ፀፀት የሌለው ቋሚ ድል ራሳችንን የምናሸንፍበት ድል ነው።"
Napoleon Bonapart

"በዚህ አለም ልታሸንፈው እንደምትችል እርግጠኛ የሆንክለት አንድ ነገር አለ፣ እርሱም ራስህን ነው።" Aldous Huxler

ስለዚህ አንተም ለውጥን ከሁለት ትከሻህ መሀል ካለው ሰው (ከራስህ) ጀምር። በመስታወት ከምታየው ማንነትህ ተነሳ። ራስህን ቅድሚያ ለውጠው። ይህንንም ለማድረግ ትመጥናለህ።

"ራስን መለወጥ መቻል የለው ልጅ በተፈጥሮ የተቸረው ስጦታ ነው። ታዲያ ራስህን መለወጥ ከተሳካልህ ያኔ ዓለምን መለወጥ አይከብድህም።"

ይህ መሰረታዊ የለውጥ መርህ ነው። ሌሎች ላይ ተፅዕኖ ማሳደር ካሰብን፣ ሌሎችን ለመለወጥ ከፈለግን ቅድሚያ ራሳችንን መለወጥ ይጠበቅብናል። ከራስ በፊት ሌሎችን ለመለወጥ መነሳት አጉል ድካም ነው። አዎ! ልክ እንደ ጀርመናዊው ግለሰብ ሆንክ ማለት ነው። ጀርመናዊውን ምን አሳወቀህ? ትንሽ ላጫውትህ፦

አንድ ጀርመናዊ ግለሰብ ነበር አሉ። ይህ ግለሰብ ዓለምን ለመለወጥ ፅኑ እምነት ነበረው። ምድርን ተለውጣ፣ የተሻለች ሆና ማየት ይመኝ ነበር። ቀበቶውን ጠበቅ አድርጎ ዓለምን ለመለወጥ በፅኑ ተነሳ። ለዓመታት ደፋ ቀና አለ። ረፍት የለሽ ስራ ውስጥ ገባ። በአታካች እንቅስቃሴ ተወጠረ። ነገር ግን ጠብ ያለ ነገር የለም። "ምናልባትም ከዓለም በፊት አውሮፓን ለመለወጥ መነሳት ነበረብኝ" አለና አውሮፓን ለመለወጥ ተነሳ። አመታት ቢማስንም ድካሙ የውሃ ሽታ ሆነ። ተስፋ ሳይቆርጥ ቅድሚያ ሀገሩን ጀርመንን ለመለወጥ ወሰነ። በጣምም ደከመ። በሀገሪቱ ላይ ያመጣው ግን ምንም ለውጥ የለም። ግራ ተጋባ። ከአካባቢዬ መጀመር አለብኝ ብሎ ወሰነ። እንዳሰበው አልሆነለትም። አይደለም የአካባቢው ማህበረሰብ በደሞዙ የሚያስተዳድራቸው ቤተሰቦቹ እንኳን ለውጥ ማሳየት አልቻሉም። አንድ ችግር እንዳለ ተረዳ። ከራስ በፊት ሌሎችን ለመለወጥ

መሞከር ከንቱ ድካም መሆኑን ተገነዘበ። በመስታወት ከሚያየው የግል ምስሉ ለመጀመር ወሰነ።... ራሱን ለመለወጥ ራሱ ላይ መድከሙን (ኢንቨስት ማድረጉን) ተያያዘው።

11.2.2 በራስህ ላይ ድል ተቀዳጅ

ራሱን የተቆጣጠረ፣ የለወጠ፣ ራሱን በመዳፉ ስር ያስገባ፣ሌሎችንም መምራትና መለወጥ ይችላል። እውነተኛውም መሪነት እርሱ ነው። የራስ መሪ፣የራስ አዛዥ መሆን።

"እኔ በርግጥ ንጉስ ነኝ፣ ምክኒያቱም ራሴን መግዛት አውቅበታለሁና።"

Pietro Aretino

11.2.3 እውነተኛ ለውጥ

ብዙዎቻችን ለለውጥ ያለን እይታ የተስተካከለ አይደለም። ለውጥን የምንመዝነው በዙሪያችን ካሉ ነገሮች አንፃር ነው። በዙሪያችን ካሉ የስራ ባልደረቦቻችን፣ ጓደኞቻችን፣ ጎረቤቶቻችን... የተሻልን መስሎ ከተሰማን፣ ያኔ የተለወጥን ይመስለናል። ለውጥ ግን ይህ አይደለም። እውነተኛ ለውጥ ከትናንት ማንነታችን የተሻልን እየሆንን መሄድ ነው። በየቀኑ አዲስ የምናሳየው እድገት መኖር ነው።

"There is nothing noble in being superior to some other man. True nobility is being superior to former self" Hindu proverb

"ታላቅነት ከሌሎች በላይ መሆን አይደለም። እውነተኛ ታላቅነት ከትናንት ማንነታችን በላይ መሆን ነው።" የህንዶች አባባል።

በጭራሽ የዛሬው ማንነትህ ከትናንቱ ጋር አንድ አይሁን። በጭራሽ፣በጭራሽ የዛሬው ማንነትህ ከትናንቱ አንተነትህ የከፋ እንዳይሆን። ሁሌ ከሌሎች ጋ ሳይሆን ከስራህ ጋር ውድድሩን ተያያዘው። ሁሌም ከትናንት ዛሬ የጨመርከው ነገር ስለመኖሩ እርግጠኛ ሁን።

11.2.4 ዛሬን መለወጥ ትችላለህ

የሰው ልጅ የዛሬ ማንነት የትናንት ውጤት ነው። ትናንት ለዛሬ መነሻ ቢሆንም፣ የትናንት እስረኞች መሆን የለብንም። ትናንት ላይመለስ ሄዷል፣ ፀሐይዋ ጠልቃለች... ስለዚህ የአሉታዊ ተፅዕኖ ጥላው አንተ ላይ እንዲያጠላ አትፍቀድለት። ዛሬ አዲስ ቀን ነው። አዲስ ፀሐይ ፈንጥቋል። እድሜህም በአንድ ቀን ጨምሯል። የምድራዊ ቆይታህም በአንድ ቀን ቀንሷል። ስለዚህ ከዛሬ ጋር ኑር። ትላንትን መለወጥ ባትችልም ዛሬ ግን በእጅህ ነው። ዛሬን ለመለወጥ ተነሳ።

"ማናችንም ትላንታችንን መለወጥ አንችልም። ነገር ግን ሁላችንም ነገን መለወጥ እንችላለን።" Collin Powel

11.2.5 ለውጥንና ነውጥን አታምታታ

ብዙዎቻችን መናጋትና መቃናት ይምታቱብናል፣ ለውጥና ነውጥ ይቀላቀሉብናል፣ መታደስና መፋለስ ይዘበራረቁብናል። ህይወትህ ላይ የመጣው አዲስ ነገር ከአንተ ማንነት ላይ የጨመረው ነገር ስለመኖሩ እርግጠኛ ሁን። ምክኒያቱም "ሁሉም ለውጦች እድገት አይደሉምና።"

"Do not confuse motion and progress, A rocking horse keeps moving but does not make any progress" Alfred A. Montapert

"እንቅስቃሴንና መሻሻልን (ለውጥን) አታምታታቸው። ልጆች የሚጫወቱበት ተወዛዋዥ የእንጨት ፈረስ መንቃነቁን ባይተውም ምንም አይነት ለውጥ አያመጣም።" አልፈሬድ ኤ. ምንታፕርት

በስራ መጠመድህን (ቢዚ) መሆንህን ሳይሆን እቅድህን ማሳካትህን አስተውል። በስራ መወጠርህን ሳይሆን ወደ ግብህ ማቅናትህን ልብ በል። እርምጃዎችህ ለእድገትህ ግብዐት መሆናቸውን በደንብ መዝናቸው።

"በራሳችን ላይ ለውጥን ማወጅ የውድድሩ ዘመን በኛ ላይ ግዴታ ያደረገው ሀላፊነት ሆኗል።"

ህግ 2 - "የእውነተኛ ለውጥ መሰረት ከራስ መጀመር ነው"

11.3 በህብረት ወደ አላማህ ተጓዝ

የልብ ጓደኛና የቅርብ ወዳጅ የራዕይ ምጥ አዋላጅ መሆኑን አትርሳ። በጉዞህ ላይ ወንድም ያስፈልግሀል። ያላየኸውን እንድታይ፣ ያልገባህን እንድትረዳ፣ ስህተትህን በግልፅ እንድታስተውል ይረዳሃል።

"ከሌሎች ራቅ አድርጌ ማየት የቻልኩት በታላላቅ ሰዎች ትከሻ ላይ በመቆሜ ምክንያት ነው።" Issac Newton

11.3.1) በመሐላችሁ ያለ የህሳብ ልዩነት አብሮ ከመጓዝ እንቅፋት አይሁንህ። ነገሮችን እያጠበብክ ወደ አብሮነት ሜዳ አትና።

"ወደ አንድነት መምጣት ጅማሮ ነው። አብሮ መቆየት አድገት ነው። አብሮ መስራት ስኬት ነው"። Henry ford

11.3.2) አንድነት ማለት ልዩነት ጭራሽ የማይፈጠርበት መስክ አይደለም። የህሳብ፣ የግንዛቤ፣ የአካሄድ ልዩነቶች ሁሌም ይኖራሉ። ቁምነገሩ ግን በእነዚህ መሀል ተቻችሎና ተደጋግፎ መጓዙ ላይ ነው።

"ልዩነትና አለመግባባት የማይቀሩ ጉዳዮች ናቸው። ጦርነትና ፀብ ግን የምርጫ ጉዳይ ነው።" Max Lucado

11.3.3) "አንድ እጅ ብቻውን አያጨበጭብም።" ያለው ማን ነበር? "ምላስ ስህተቶቿ የበዛው አንድ ብቻ ስለሆነች ነው።" ያለውስ? ወደ ግብህ ስታቀና የሌሎች ድጋፍና ምክር ያስፈልግሃል። የቅርብ ወዳጅ፣ የልብ ጓደኛ፣ የስራ አጋር... ሀይልና ብርታት መሆኑን አትርሳ። አላህ ታላቁን መልዕክተኛ ሙሳን (ዐ.ሰ) የእስራኤል ልጆችን ከባርነት ቀንበር እንዲያወጡ ወደ ፈርዖን ሲልካቸው፣ አብሮ አጋዥ ወንድማቸውን አድርጎላቸው ነበር። እንዲህም ሲል አበሰራቸው፡-

"ጡንቻህን በወንድምህ እናበረታዋለን ..."[150]

[150] ቁርአን 28 : 35

የእስራኤል ልጆችን ከባርነት ቀንበር የማውጣቱ ጉዞ ቀላል አልነበረም። እልህ አስጨራሽ ትግልን አድርገዋል። ለዚህ ተልዕኮ አጋዥ ይሆን ዘንድ ወንድማቸውን አብሮ አደረገላቸው።

ሀግ- 3 "ያለ ወንድም ጉዞ ምን ይዞ"

11.4 የስኬት ዋጋ እንዳለው ልብ በል

"ዝየትኛውም የሙያ መስክ ላይ ቢሆን የሁሉም ሰው ህይወታዊ ስኬት የሚወሰነው ለላቀ ምርጥ ህይወት በሚከፍለው መስዋዕትነትና ባለው ቁርጠኝነት ላይ ተመስርቶ ነው።" Unknown

ስኬት ሙሉ መስዋዕትነትን ይጠይቃል። አንተነትህን ለአላማህ ማስገዛት ስትጀምር ስኬትን ለመቆናጠጥ ቀርበሃል ማለት ነው። ስኬት ሰነፎችን አትጠጋቸውም። እነሱም መቼም ቢሆን አያገኟትም። ሁሌም የተራራቁ ሁለት ዋልታዎች ናቸው።

የስኬት ጥግ ላይ የደረሱ ሰዎችን ታሪክ ብትፈትሽ፣ አንድ ሁነኛ ነገር ታገኝባቸዋለህ። ይህም ሁሉም ላመኑበት አላማ ሙሉ ማንነታቸውን እንደሰጡ ትመለከታለህ። እውቁ ሚካኤል አንጀሉ እንዲህ ማለቱ ይታወሳል፦

"እንዲህ የተዋጣለት ሰዓሊ ለመሆን ምን ያህል ጠንክሬ መስራት እንደነበረብኝ ሰዎች ቢያውቁ ናሮ ስራዎቼ ይሆን ያህል ባላስደነቋቸው ነበር።"[51]

ከምርጥ ምግብ በስተጀርባ ጎበዝ የምግብ ባለሙያና በርካታ ቀመማቅመሞች እንዳሉ አትዘንጋ። ከምርጥ መፅሐፍ ጀርባ በርካታ መፅሀፎችን ያገላበጠ፣ ሌት ተቀን የተጋ ደራሲ መኖሩን ልብ በል። ከምርጥ የእግር ኳስ ቡድን በስተጀርባ ታታሪ አሰልጣኝና በትጋት የሰለጠኑ ተጫዋቾች መኖራቸውን አስተውል።... በእጭሩ ከስኬታማ ሰዎች በስተጀርባ ሙሉ መስዋዕትነትና ራስን ለአላማ ማስገዛት መኖሩን አትርሳ።

---

[51] ሰዕል በእስልምና የተሰጠው ህይማኖታዊ ብይን ለሁሉም ግልፅ ነው። ከዚህ ላይ የተፈለገው የግለሰቡን ትጋትና የአላማ ፅናት እንደ ተምሳሌ ለመውሰድ ነዉ።
"ዕውቀት ከሙዕሚኖች ጠፍታ የጂደች ሀብት ናት፤ ከእምነት አልባ ሰው ብታኖት እንኳን ውሰዳት" የነቢይ ﷺ የአስት ልጅ በሊይ ኢብኑ አቢጣሊብ

በአንድ ወቅት ታላቁ ፍሪትዝ ክሪስለርን አንዱ አድናቂው ተጠጋውና "አንተ እንደምትጫወተው ቫዮሊን ለመጫወት ህይወቴን እሰጣለሁ" አለው። የፍሪትዝ አጭር መልስ "እኔም እኮ የሰጠሁት ህይወቴን ነው" የሚል ነበር።[152]

ስኬት ሙሉ ማንነትን ማስረከብ፣ ሙሉ አንተነትን ለአላማ ማስገዛትን ይጠይቃል። የኦሎምፒክ ወርቅ ሜዳሊያ ካጠለቀ ስፖርተኛ በስተጀርባ፣ ጠዋትና ማታ ልምምድ ያደረገ፣ በክረምት በበጋው በስልጠና የተጋ፣ በቅቤ ጠቃ ያለ ምግብን የተወ፣ ከሱስ የራቀ... ታታሪ አትሌት ታገኛለህ። ከቦርጭ የፀዱ እና በጥሩ ቅርፅ (Six pack) የተዋቡ የሆድ ቅርፆችን ለማግኘት፣ በጠዋት ተነስቶ የሆድ ቅርፅ ማስተካከያ ስፖርት (Sit up) መስራትና እራትን መስዋዕት ማድረግ ይጠይቃል።

ታዲያ አንተም ወደ ስኬት ስታቀና ሁሉም ለውጦች ዋጋ እንዳላቸው አትዘንጋ። ያለክፍያ ነፃ ምሳ እንደሌለ ተረዳ።

"Dr." የምትባለውን ሁለት ፊደል ከስምህ ፊት ለማስጨመር ከሀያ ዓመት በላይ በትምህርት ላይ ማሳለፍ እንደሚጠይቅ እመን ነው። ሁለተኛ ደረጃ እስክንጨርስ 12 ዓመት እንፈጃለን፣ የመጀመሪያ ድግሪ ስንሰራ 4 ዓመት እንወስዳለን፣ ሁለተኛ ድግሪ ስንጨምር ሌላ 3 ዓመት ያስፈልገናል፣ በመጨረሻም የዶክትሬት ድግሪያችንን ለመያዝ ተጨማሪ 4 እስከ 5 ዓመት እንወስዳለን። በድምሩ ከሀያ ዓመት በላይ ያስፈልገናል። በመጨረሻም "Dr." የሚሉት ሁለት ፊደላት ከስማችን ፊት ይጨመሩና "ዶክተር እገሌ" እየተባልን እንጠራለን።[153] አየህ ሁሉም ለውጦች ክፍያ አላቸው።

አንድ ታላቅ ንጉስ በግዛቱ ስር ያሉትን ጠቢባኖቹን ሰብስቦ ለመጪው ትውልድ ሊተላለፍ የሚችል ካለፉት ትውልዶች የቀሰሙትን የላቀ ጥበብ ፅፈው እንዲመያመጡ አዘዛቸው። ከጥልቅ ምክክርና ከብዙ ልፋት በኋላ ጠቢባኖቹ ባለ ብዙ ቅፅ መፅሐፍ አዘጋጅተው ለንጉሱ አቀረቡ።

---

[152] በተመሳሳይ እዚህም ጋ የተፈለገው፣ ሰዎች ለምድራዊ ስኬታቸው ምን ያህል ዋጋ እንደከፈሉ አስተምህሮ መውሰድ ነው።
"የተናጋሪውን ማንነት ሳይሆን፣ የሚናገረውን መልዕክት ልብ ብለህ አስተውል"
(ዐሊይ ኢብኑ አቢጣሊብ)

[153] ዶ/ር መሐመድ ራቲብ አናቡልሲ

ቅዖችን አገለብጦ ከተመለከተ በኋላ ንጉሱ መጪው ትልድ እነዚህን ሁሉ ቅዖች ሊያነባቸው ስለማይችል አሳጥረው ሌላ እንዲያዘጋጁ ደግሞ አዘዛቸው። ጠቢባኖቹም ከእልህ አስጨራሽ ምርምርና ጥናት በኋላ ባለ አንድ ቅፅ ምርጥ ዕውቀት ብቻ በመያዝ ንጉሱ ፊት ዳግም ቀረቡ። አሁንም ንጉሱ አልረካም። መጪው ትውልድ ይህን ወፍራም ጥራዝ የማንበብ ወኔ የለውም። ስለዚህ አጠር ብሎ እንዲዘጋጅ ተጨማሪ ትእዛዝ አዘዛቸው። ጠቢባኖቹም ጠዋት ማታ ተጠበው የአለምን ጥበብ በአንዲት ዐ.ነገር ብቻ አቀረቡለት። ንጉሱ እጅግ ደስ አለው። አረፍተ ነገሯም እንዲህ የምትል ነበረች፡- "ነፃ ምሳ የሚባል ነገር የለም!"[154]

አዎ! መልዕክቱ ግልፅ ነው። ያለ ክፍያ ለውጥ የለም። የምናገኘው የሰጠነውን ያህል ነው።

"አያንዳንዱ ሰው የአሸናፊነት ፍላጎት አለው። ሆኖም ለአሸናፊነት የሚዘጋጁትና ቅድመ-ዝግጅት የሚያደርጉት ጥቂቶች ብቻ ናቸው።"

ቪንስ ሎምባርዲ

ህግ - 4 "እውነተኛ ስኬቶች ሁሉ ዋጋ አላቸው"

11.5 ተግባራዊ እርምጃን ውሰድ

"ደርዘን ያህል ሀልሞችን (ዕቅዶችን) ማማኘት ይቻላል። የሀልሞች ዋጋ የሚለካው ግን ወደ ተግባር የተለወጠ እንደሆነ ነው።" ቴዎዶር ሩዝቬልት

እቅዶቻችንን ለመተግበር ተግባራዊ እርምጃ መጀመር አለብን። በህልምና በአላማ መካከል ያለውም መሰረታዊ ልዩነት እርሱ ነው። ግብህን በጊዜ ከፋፍለህ ወደ መሬት አውርደው።

11.5.1 ነገ እሰራዋለሁ አትበል

"እሰክ ጨረታ ውልደት ድረስ ይተኛል፣ ቀን በፀሐይዋ ሙቀት ሲዝናና ይውላል፣ ሀይወቱን በሙሉ ነገ እሰራዋለሁ ሲል ያሳልፈዋል፣ ምንም ነገር ሳይሰራም ይሞታል።" (ጀምስ አልበሪ)

---

[154] ለአሸናፊነት መገፋት ትርጉም፡- ማኑሌት ጥላሁን እና ዳኜ መላኩ- 2001

ዛሬ የምትችለውን ያህል ደፋቀና በል፣ የምትችለውን ያህል ወደ አላማህ አቅና፣ የቻልከውን ርቀት ያህል ተጓዝ። ነገ ሌላ ቀን ነው። የራሱ በሆኑ ውጣ ውረዶች የተሞላ ነው። እንኳን የዛሬውን ጨምረህበት ነገ ራሱ ይዞት የሚመጣውን ጣጣ (ስራ) በነገው ውሎህ ራሱ አትጨርሰውም። ስለዚህ "ዛሬ ልትሰራው የምትችለውን ነገር በፍጹም ለነገ አታሳድረው!" ቤንጃሚን ፍራንክሊን።... Don't Procrastinate.

11.5.2 ተግባራዊ እቅድ ይኑርህ

"መታጠቢያ ቤት (ሽንት ቤት) ውስጥ ሆኖ የማያስብ ሰው መቼም አይናርም። ነገር ግን ለውጥን የሚፈጥረው የራሰ ፀጉሩን አደራርቆና ልብሱን ለባብሶ ከዚያ ከወጣ በኋላ ሃሳቡን ለመተግበር በቁርጠኝነት የሚንቀሳቀስ ሰው ብቻ ነው።"

(ኖላን ቡሽኔል)

ማሰብ፣ ማስተንተን፣ ማለም... የሚያምር ነህስ ሲሆን፣ መተግበር ግን ውብ ወርቅ ነው። ደግሞም፡- "አንድ ወቄት ተግባር ከአንድ ቶን ንድፈ-ሀሳብ የበለጠ ዋጋ አለው።" የሚለውን የፍሬድሪክ ኤንግልስ አባባል አትርሳ።

11.5.3 ተግባር ወደ ስኬት ይመራሃል

"ስኬት ከተግባር ጋር የተያያዘ ነው። ስኬታማ ሰዎች ደግሞ የተግባር ሰዎች ናቸው፣ሁሌም ለተግባራዊነቱ እንደተጉ ናቸው። ስሀተት ይሰሩ ይሆናል ግን ጥለው አይሸሹም።" (ኮንራድ ሂልተን)

ተግባር የስኬት ክፍያ ነው። ያልተተገበረ እቅድ፣በተግባር ያልተፈተሸ አላማ፣ወደ መሬት ያልወረደ ህልም... ትልቅ ዋጋ አይሰጠውም። የግባችን ምጡቅነት የሚለካው፣በትግበራ መጠናችን ነው።

"አንድ ቀን መብረርን ለመማር የሚያስብ ሰው በቅድሚያ መቆምና መራመድን እንዲሁም መሮጥን መማር አለበት።" (ፍሬድሪክ ኒቼ)

ሀግ - 5 "ተግባር ያልከሰተው እቅድ ህልም ነው"

11.6 ከፍተኛ ጉጉት ይኑርህ

"የትኛውም ታላቅ ነገር ያለ ከፍተኛ ጉጉት ተገኝቶ አያውቅም።"
ኤመርሰን

ለአላህ መልዕክተኛ (ለነብዩ ሙሀመድ) ﷺ ከፍተኛ ፍቅር እንዳለው የሚናገር ሰው ነበር። ታዲያ ይህ ግለሰብ ነብዩን ﷺ በህይወት ማየትን ባይታደልም፤ በህልሙ ግን እርሳቸውን ማየት ይመኝ ነበር። በተኛ ቁጥር እርሳቸውን ማየትን ተመኝቶ ያድራል። ታዲያ ሁሌም ህልሙን (ምኞቱን) በህልሙ ሳያገኝ ጎህ ይቀዳል።

ነገሩ ግራ ቢገባው ወደ አንድ ሊቅ (ዐሊም) ሄዶ አማከራቸው። "እኔ ነብዩን ሰ.ዐ.ወ. በጣም እወዳቸዋለሁ፤ ሁሌም በህልሜ እንዳያቸው እመኛለሁ፤ ነገር ግን እስከ አሁን ይህ ምኞቴ አልተሳካልኝም።" አለና መልሳቸውን በጉጉት እየጠበቀ አይን አይናቸውን መመልከት ያዘ።

ሊቁም (ዐሊሙም) "ለዚህ መልስ የምሰጥህ ጠዋት ነው። ዛሬ ማታ የእኔ እንግዳ ነህ ቤቴ ታድራለህ" አሉት። እርሱም ሁሌም ሲያማስነው ለኖረ ፍላጎቱ መፍትሄ እንደሚያገኝ ስላሰበ በሀሴት ተሞላ። እራት ላይ በጣም ጥሩ ምግብ አቅርበው አስተናገዱት። ምግቡ ጥሩና ሚያሳሳ ቢሆንም፤ ጨው ግን በጣም በዝቶበታል። ግለሰቡ ምግቡን እንደቀመሰ በጣም ውሃ አስፈለገው። ሊቁ (ዐሊሙ) ግን ግብጎው ውሃ መጠጣትን እንደማያካትት ገለፁለት። "ለጠየከው ጥያቄ ጠዋት መልስ እንድታገኝ ውሃ ሳትጠጣ ማደር አለብህ" አሉት። ግለሰቡም በሀሳቡ ተስማማ። ውሃ የአየር ያህል እንዳስፈለገውና በጣም እንደጠማው ተኛ።

እንግዳው በጠዋት ተነስቶ የዐሊሙን መልስ በጉጉት ይጠብቃል። ሊቁም "አዳር እንዴት ነበር?" የሚል ጥያቄ አቀረቡለት። "ግለሰቡም በጣም ጥሩ ነው።"ሲል መለሰ። "በህልምህ ምን አየህ?" አሉት። እርሱም "ከሰማይ ዝናብ ሲዘንብ፤ ወንዞች ሲፈሱ፤ ውቅያኖስ ውስጥ ስዋኝ... ተመለከትኩ" አላቸው። የዐሊሙም መልስ እንዲህ የሚል ነበር "አየህ ማታ በጣም ውሃ አስፈልጎህ ስላደርክ ስለዝናብ፤ ስለወንዞች... ተመለከትክ። ልክ እንደዚሁም ነብዩን ﷺ ለማየት በጣም ከጓጓህና በቁርጥ ከተመኘህ ትመለከታቸዋለህ ::"[155]

[155] ሐቢቢ ያ ሩሁል ኢማን - ዶ/ር ኻሊድ አቡሻዲ ገፅ -151 (ከመጠነኛ ለውጥ ጋር)

እውነቱ ይህ ነው። ለነገሮች ፅኑ ፍላጎት ካለን፣ ሙሉ ጉጉት ከሰነቅን... እንደርስባቸዋለን። አንተም መሆን የምትፈልገውን ነገር፣ማሳካት የምትመኘውን ግብ፣መድረስ የምትፈልገውን አላማ በቁርጥ ፈልገው፣ በፅኑ ተመኘው፣በሙሉ ጉጉት አልመው... ያኔ ስኬት ራሱ ይከተልሃል።

"ሞተሩን የሚያንቀሳቅሰው ምንድነው? ፅኑ ፍላጎት፣ ፅኑ ፍላጎት ፅኑ ፍላጎት!" Kunitz

ሀማ - 6 "ከፍተኛ ጉጉት ታላቅን ስኬት ይወልዳል"

11.7 የግብህን ጉዞ ልመደው

"ወደ አላማህ፣ ወደ ቀረፅከው የህይወት ጥሪ የሚያደርሱህን መንገዶችን ሁሉ ልመዳቸው (ባህሪህ አድርጋቸው) ያኔ ወደ ግብህ መድረስ ቀላል ሆኖ ታገኘዋለህ።"

ወደ አላማህ የሚያደርሱህን መንገዶች ሁሉ ልመዳቸው። የተዋሀዱህ ባህሪህ አድርጋቸው። ባህሪህ የሆነ ነገር ሳታስብና ሳትጨነቅ እንዲሁም በማንኛውም ቦታ ያለማንም ማስታወስ የምታደርገው ተግባር ይሆናል። ለምሳሌ አንድ ሰው "እውቅ ደራሲ መሆን አለብኝ" ብሎ የህይወት ግብ አውጥቷል እንበል። እውቅ ደራሲ ለመሆን ጎበዝ አንባቢ መሆን እንዳለበት እሙን ነው።ታዲያ ይህ ሰው በሁሉም ቦታ ማንበብንና መፃፍን ልማዱ ማድረግ ይኖርበታል። ታክሲ ውስጥ፣ አውሮፕላን ውስጥ፣ ወረፋ እየጠበቀ፣ ሻይ እየጠጣ፣ ቤት ውስጥ፣ ቢሮ ውስጥ... ሁሉም ቦታ ማንበብና መፃፍን ቋሚ ባህሪው ካደረገ ወደ ስኬት በሮች እያቀና ነው ማለት ነው። አላማቸውን ለማሳካት ምቹ ጊዜና ቦታን የሚጠብቁ ሰዎች ከግባቸው ለመድረስ ረዥም ርቀት መጓዝ ይጠበቅባቸዋል።

ነብዩ መሐመድ ﷺ "አንድ ሰው ለ40 ቀናት በተከታታይ ተክቢራ (የስግደት መክፈቻ ውዳሴ) ከኢማሙ (ስግደት መሪው) ጋር ሳያመልጠው የሰገደ፣ ሁለት ፅዳቶችን (ነፃነቶችን) ይጎናፀፋል። አንደኛው ከንፍቅና ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከእሳት።" ይሉናል።

አንድ ሰው ለ40 ቀን በተከታታይ ትዕዛዙን መፈፀሙ፣ለእምነቱ ያለውን ታማኝነት ይጠቁማል። ለማስመሰል ነገሮችን ከሚያደርጉት መናፍቃን

ጎራ እንዳልሆነም መገለጫ ነው። በተጨማሪም ከስግደቱ ጋር ይዋሀድና ከአማኞች ጎራ ይቀላቀላል። ከዚህ በኋላ ስግደትን ልተወው ቢል እንኳን አይሳካለትም። ምክንያቱም ልማዱ ሆኗልና።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የማህበራዊ አጥኚዎች አንድ ነገር ያለማቋረጥ በተደጋጋሚ ከ21 እስከ 30 ጊዜ ከተደረገ/ከተሰራ ያ ጉዳይ ወደ ባህሪ ይቀየራል ይላሉ። ከዚህ ጥናት ይልቅ ትክክለኛው የነብዩ ሰ.ዐ.ወ. ትምህርት ነው። ምክንያቱም መመሪያው የወረደው የሰውን ልጆች ከፈጠረው፣ ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን አበጥሮ ከሚያቀው የዓለማት ጌታ ነው። መቼም ቢሆን መለኮታዊ ተዕዛዞችን ማስቀደም እምነት ብቻ ሳይሆን ብልህነትም ነው።

ስለዚህ ወደ ስኬት የሚያደርሱንን ተግባራቶች ሁሉ ልማዶቻችን እናድርጋቸው። እንደ ቋሚ ባህሪይ እንያዛቸው። ያኔ ጥራት ያለው ስኬትን እንቆናጠጣለን።

"ደጋግመን የምናደርገውን ነገር ወደ መሆን እንመጣለን፡ስለዚህ ጥራት የአንድ ጊዜ ክስተት ሳይሆን የልማድ ጉዳይ ነው።" Aristotle

ልማድ ጉዞህን ሳትቸገር አንድትቀጥል ያደርግሀል። *"አንድን ነገር አንድትጀምር የሚያደርግህ የሰሜት መነሳሳት ነው። በነገሩ አንድትቀጥልበት የሚያደርግህ ግን ልማድ ነው።"* Jim Rohn

መርህ - 7 "ልማድ ጉዞን ገር፣ ሰራን ቀላል ያደርጋል"

11.8 አሻራህን ትተህ እለፍ

"አንዳችሁ እጁ ላይ ችግኝ አያለ፣ትንሳኤ ሊከሰት ቢልና ከመከሰቱ በፊት መትከል ከቻለ ይትከለው።" ነብዩ ሙሀመድ ﷺ

ነብዩ ﷺ በዚህ ንግግራቸው የሰውን ልጅ ወደ መልካም ድርጊት ተጣርተዋል። መልካምን ነገር ተግብረው እንዲሄዱ መክረዋል። አስቡት! ትንሳኤ ከደቂቃዎች በኋላ የምትቆም ከሆነ፣ ከዓመታት በኋላ ፍሬ የሚሰጠውን ችግኝ መትከሉ ምን ዋጋ አለው? አያችሁ! የመልዕክቱም ጥልቀት ከዚህ ላይ ነው። አስከመጨረሻው ሰዓት መልካምን ነገር ለማበርከት እንድንተጋ ማስተማር ነው።

ታላቅነት ማለት አንተ ካለፍክ በኋላ ለሌሎች አልፎ የሚሄድና የሚዘልቅ ነገር አስቀምጦ ማለፍ እንደሆነ የስኬት ዘማሪዎች በአንድ ድምፅ ይስማማሉ። ስለዚህ አንተም በቻልከው መጠን ከምድር ያገኘኸውን አገልግሎት ከፍለኸው ሂድ። ምድር ላይ አንድን ነገር ካልጨመርክ አንተ በምድር ላይ ጭማሪ መሆንህን አትዘንጋ።

አንድ ሰው በዕድሜ የገፉ አዛውንትን "የህይወት ከባዱ ሽከም ምንድነው?" ብሎ ጠየቃቸው። አዛውንቱም በማዘን "ምንም ነገር አለመሸከም" ብለውት አረፉ።

ሀግ - 8 "በታሪክ አምድ የምትዘክረው ባሰቀደምከው መልካም ተግባርህ ነው"

11.9 ከውድቀትህ ተማር

"ስኬት ዘጠና ዘጠኝ በመቶ የተገነባው ከሽንፈት ነው"
(የሆንዳ ሞተር ኮርፖሬሽን መስራች- ሶይቺሮ ሆንዳ)

በሽንፈትና በውድቀት መሀል ሰፊ ልዩነት አለ። መውደቅ መሸነፍ አይደለም፣ ቶሎ ተነስተን እርምጃችን ለመቀጠል እስከወሰንን ድረስ።

ቶማስ ኤድሰን የኤሌክትሪክ መብራት ከመፍጠሩ (ከማግኘቱ) በፊት ከአንድ ሺህ የማያንሱ ሙከራዎችን አድርጎ እንዳልተሳካለት ይናገራል[158]። ይህን ሁኔታ ሲናገር እንዲህ ይላል፡- "እኔ አንድ ሺህ መብራት የማይሰራበትን መንገድ አውቃለሁ"።

አያችሁ! ሽንፈቱንና ድካሙን እንደ ስኬት ቆጠረው። እንዳለውም ከአንድ ሺህ ያልተሳኩ ሙከራዎች በኋላ ባደረገው አንድ ሙከራ ተሳካለት።

እውነታው ይህ ነው። ሁሌም ወደ ስኬት ስታቀና በለስ ላይቀናህ ይችላል። ግን አንድ ነገር ላይ እርግጠኛ ሁን በጉዞህ ላይ ችግሮችን ተቋቁመህ ከፀናህ አላማህ ላይ መድረስህ አይቀርም።

---

[158] ቶማስ በጣም ጨለማን እንደሚፈራ ይነገራል። ይህም ፍርሃቱ የኤሌክትሪክ መብራት እንዲፈጥር ምክንያት ሆኖታል። እያንዳንዱ ችግር የተሻለ አድል ይዞ ይመጣል የሚባለዉም ለዚህ ነዉ።

"ስኬት ውድቀት የማያጋጥምበት ሂደት አይደለም። ስኬት ማለት የረዥም ጊዜ ዓላማዎቻችንን ከግብ ማድረስ ማለት ነው። ስኬት እያንዳንዱን ውጊያ በተናጠል ማሸነፍ ማለት ሳይሆን፣ አጠቃላይ ጦርነቱን በድል አድራጊነት መወጣት ነው።" ኤድዊን ሲ. ብሊስ።... Success is Winning the war, not every battle.

መርህ - 9 "ሽንፈት ራሱ ስኬት ነው"

11.10 በስኬትህ አትኩራ

"በስኬት መሰላል ወደ ላይ በወጣችሁ ቁጥር ሰዎችን በአክብሮት ቅረቧቸው-ምክንያቱም ወደታች በምትወርዱበት ጊዜ እነሱኑ መልሳቹህ ማግኘታችሁ አይቀርምና።"

የጎመሩ ፍሬዎችን ያዘሉ የአትክልት ቅርንጫፎች ወደታች ዝቅ እንደሚሉት ሁሉ፣ አንተም እየበለልክ በሄድክ ቁጥር ለሌሎች ተናናሽ ሁን። ከስኬት ማማ ላይ ከፍ ብለህ ስትወጣ ትሁትነትን ተላበስ። በጭራሽ በስኬትህ እንዳትኮፈስ፣ ሰዎችን አሳንሰህ እንዳታይ፣ የበታችነት ስሜት እንዲሰማቸው እንዳታደርግ።

መሰላል

ስትወጣ የጨበጥከውን	-	አይቀርምና መርገጥ
ዞረህ ማትመለስ መስሎህ	-	አታበላሽው ያለቅጥ
እንደወጡ መቅረት	-	መቼም የለምና
የጨበጥከውን ልትረግጥ	-	ትመለሳለህ እንደገና
ወደታች መመለስ	-	ስለሆነ ግድ
እጅህ ይበላሻል	-	ዳግም ስትወርድ[157] YN

ህግ - 10 "የጎመሩ ፍሬዎች ወደታች ዝቅ ይላሉ"

[157] የዚህን ግጥም ሃሳብ መነሻ የወሰድኩት ከፕ/ር መስፍን አጭር ግጥም ነበር።

11.11 ሰጪ እንጅ ተቀባይ አትሁን

"ከላይ የምትሰጥ እጅ ከታች ከምትቀበል እጅ ትበልጣለች" (ነብዩ ሙሀመድ ﷺ [158]

በህይወት ላይ ጨማሪ እንጂ ጭማሪ አትሁን። ሰጭ እንጂ ተቀባይ ላለመሆን ጣር። ከላይ ሆና ሌሎችን የምትረዳ እጅ ከስር ሆና እርዳታን ከምትቀበል እጅ ትበልጣለች። የአላህ መልዕክተኛ በህይወት ላይ ለሰው ልጆች መልካምን ነገር አበርክተን እንድናልፍ በዚህ ንግግራቸው ያበረታቱናል። ምድር የሰጠችንን ግልጋሎት ከፍለን ማለፍ እንዳለብን ይገፋፋናል። ቀጣዩ ታሪክ ይህን ሁኔታ የሚያብራራልህ ይመስለኛል። ተከተለኝ፦

የታላቁ ኢማም (ሊቅ) የኢብራሂም ኢብኑል አድሐም ተማሪና ጓደኛ የነበረ አንድ ግለሰብ ለንግድ ወደሌላ ሀገር ያቀናል። በርሃውን እያቆራረጠ መጓዙን ቀጥሏል። መንገዱ አሰልቺና አድካሚ ነበር። ትንሽ እረፍት ለመውሰድ አንድ ዛፍ ጥላ ስር ያርፋል። ከያዛት ስንቅ ትንሽ ዘግኖ ተመገበ። ጉዞውን ዳግም ከመጀመሩ በፊት ግን አንድ አስገራሚ ነገር በቅርብ ርቀት ተመለከተ። ባየው ነገር ተደመመ።

አዎ! አንድ አሞራ ከሩቅ ሲበር መጥቶ ሌላን ማየት የማይችል አሞራን ሲመግበው እና ወደ አፉ ምግብ ሲከትለት ተመለከተ። በአላህ ስራና ጥበብ ተገረመ። ሁሉንም መጋቢና ተንከባካቢ ጌታ መሆኑን በደምብ ተረዳ። ከዚያም ከራሱ ጋር ተወያየ። "ይህን የማያይ አሞራ በዚህ በረሃ ውስጥ የሚመግብ ጌታ እኔን እንዴት ይረሳኛል። አላህ (ሱ.ወ) ቤቴ ሆኜ ሊመግበኝ እየቻለ እኔ ምን በበረሃ አንከለከለኝ?"... ሲል ከራሱ ጋር ተጨዋወተ። በመጨረሻም የንግድ ጉዞውን አቋርጦ ለመመለስ ወሰነ። ወደ ሃገሩ የመልስ ጉዞ አደረገ።

ወደ ሀገሩ እንደገባ ከታላቁ ሊቅ ኢብራሂም ኢብኑል አድሃም ጋር ተገናኘ። በጉዞው ላይ ያየውን ተአምር ነገራቸው። አላህ አማያዩ እንስሳትን እንኳ እንደማይረሳ አጫወታቸው። "እኔ ታዲያ ምን አደከመኝ እንደዚያ አሞራ የሚመግብ ሰው የሚልክ ጌታ እያለኝ" አላቸው።

---

[158] ማሊክ፣ አህመድ፣ ቡኻሪ፣ ሙስሊም ዘግበዉታል

ታላቁ ሊቅ እንዲህ አሉት፡- "ታዲያ አንተ መጋቢው አሞራ መሆን ይሻልሀል ወይስ ተመጋቢውን"? "ሰዎችን የሚንከባከብ መሆን ይሻልሀል ወይስ ሰዎች የሚንከባከቡት? ግለሰቡ ስሜቱ በጣም ተነካ። አዲስ እይታ እንዲኖረው ረዱት። በህይወት ቆይታው ሰጪ እንጂ ተቀባይ ሆኖ መኖር አስደሳች ነገር እንዳልሆነ አስተማሩት። በጣም ተደሰተ። የታላቁን ሊቅ የኢብራሂም ኢብኑል አድሃምን ግንባር በፍቅር ሳመና "አንተ ሁሌም ታላቁ መምህራችን ነህ" አላቸው። ዳግም የንግድ ጉዞውን ለመቀጠል ጓዙን ማዘጋጀት ያዘ።

አዎ! ሰጪ እንጂ ተቀባይ ላለመሆን ጥረት አድርግ። ሪጂ እንጂ ተረጂ ላለመሆን ትጋ። አጋዥ እንጂ ታጋዥ ላለመሆን ጣር። ከላይ የምትሰጥ እጅ ከታች ከምትቀበል እጅ ሁሌም የተሻለች መሆኗን አትዘንጋ።

ሀግ - 11 "ከላይ መሆን ያልቻለች እጅ ከታች ትሆናለች"

11.12 የማይመለከትህ ነገር ውስጥ አትግባ

"የማይመለከተውን ነገር መራቅ የአንድ ሰው አሰልምና ማማር (ጥሩ ሙስሊም መሆን) መገለጫ ነው።"[159] ነብዩ ሙሐመድ ﷺ

ትልቅ አገላለፅ ነው። የአንድ አማኝ ጥሩ የእምነቱ ተከታይነት መገለጫው የማይመለከተውን ነገር መተው ነው። በሚመለከተውና በሚጠቅመው ነገር ብቻ መጠመዱ ነው። የሰው ልጅ በምድራዊ ቆይታው ሁለት ነገሮችን ይጋፈጣል። አንድ የሚመለከተው፣ ለለውጡ የሚረዳው፣ ለአላማው ስኬት ግብአት የሚሆነው... ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የማይመለከተው፣ የማይጠቅመው፣ ካለመረው የህይወት ግብ ተቃራኒ የሆነ ነው። በአንዱ የተወጠረ ሌላኛው ያመልጠዋል።

"በማይመለከተው ነገር የተጠመደ (ቢዚ የሆነ) የሚመለከተው ነገር ያመልጠዋል" ይሉሀል ኢማሙ ኢብኑል ቀይም[160]። ታዲያ አንተም ወደስኬት ስታቀና በሚመለከትህ ነገር ላይ ብቻ አትኩር (ቢዚ ሁን)። በሚጠቅምህ ነገር ላይ ብቻ ተጠመድ። ለእድገትህና ለጀመርከው ጉዞ አጋዥ በሚሆንህ ነገር ላይ ብቻ አተኩር... ያኔ ወደ ስኬት መድረስህ የእርግጠኝነት ጉዳይ ይሆናል።

[159] ቲርሚዚ - 3976

አስራ ሶስት

አንድ ወጣት በአንድ እስር ቤት አጠገብ በችኮላ ያልፋል። ፈጥኖ ሊደርስበት የሚገባ አስቸኳይ ጉዳይ አለው። ትኩረቱን ወደ ጉዳዩ አድርጎ መገስገሱን ይሄል። ድንገት ከእስር ቤቱ የሚሰማው ድምፅ ትኩረቱን ሳበው። ነገር ግን ይህ እኔን "አይመለከተኝም፣ ወደ ሚመለከተኝ ማቅናት አለብኝ" ብሎ መንገዱን ተያያዘው። ከትንሽ እርምጃ በኋላ "አስራ አንድ" የሚል የህብረት ድምፅ ሰማ። "ቅድም "እስር" ብለው በህብረት ሲጮሁ ሰማሁ፣ አሁን ደግሞ "አስራ አንድ" ይላሉ፣ ነገሩ ምንድን ነው? ቢሆንም እኔን አይመለከተኝም" አለና መንገዱን ቀጠለ።

ከጥቂት እርምጃዎች በኋላ "አስራ ሁለት" ሲሉ ሰማ። "ይህ ነገር ምን ይሆን?" ሲል ራሱን ጠየቀ። "ለምን ሄጄ አልመለከተውም" ሲል ከራሱ ጋር አወራ። "አሠ! በፍጥነት ተመልሼ ወደ ጉዞዬ አቀናለሁ፣ ወደ ሚመለከተኝ እመለሳለሁ" ብሎ ወደ እስር ቤቱ ግድግዳ ቀረብ አለ። በግድግዳው ላይ ትንሽ ቀዳዳ ተመለከተ። ጠጋ አለና በቀዳዳው በኩል አጮልቆ ወደ ውስጥ መመልከት ጀመረ። እስረኞቹ ተሰብስበው ቆመው ተመለከታቸው። ድንገት ሳያስበው ከውስጥ ቡተሰነዘረ ቡጢ አይኑን ተመታ። ደንግጦ ወደኋላ እንደወደቀ፣ ከውስጥ የተሰበሰበው እስረኛ እየሳቁ በህብረት "አስራ ሶስት" ሲሉ አስተጋቡ።

ለካስ እስከ አሁን ሲሰማው የነበረው ቁጥሮች በማይመለከታቸው እየገቡ ቡጢ የቀመሱ ሰዎች ብዛት ነበር። እስረኞች እስር መርሻና ጊዜ ማሳለፊያ የተጠቀሙበት ጫወታ ነበር ለካ። እርሱም በዛራው አለት ቡጢ ከቀመሱት አልፎ ሂያጆች አስራ ሶስተኛው ሆነ። በማይመለከተው ገብቶ መመልከቻውን ተመቶ ተመለሰ።[161]

አንተም በማይመለከትህ ነገር አትግባ። ትኩረትህን ሙሉ በሙሉ ግብህ ላይ አድርግ። ሀሳብህን ሁሉ አላማህ ላይ ሰብስበው... ያኔ ወደ ስኬት መድረስህ ግድ ይሆናል።

ሀግ - 12 "በማይመለከተው የተጠመደ የሚመለከተው ያመልጠዋል"

---

[160] ኢጣልያ ቀደም- ከ 700 ዓመት በፊት በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ የነበሩ የተሀድሶ ቀንዲልና ሊቅ።

[161] ዶር ግሪቅ አስሰወይዳን - ፈንል ኢልታአ (ስኮቲት ማስተካከያ ጋር)

11.13 እንዳትጠለፍ

"በትናንሽ ስኬቶች ታይታ (ሪያአ) ላይ እንዳትወድቅ ታላላቅ ግቦች ይኑሩህ"

አዎ! ታላቅ ራዕይን የሰነቁ ሰዎች በትናንሽ ስኬቶች ይዩልኝ ውስጥ ከመጠለፍ ይድናሉ። መቶ መፅሐፍ ለአለም አበርክቼ እሄዳለሁ ብሎ ግብ የቀረፀ ሰው፣ ሶስት መፅሐፍ በማሳተሙ አይኮፈስም። የዶክትሬት ዲግሪ የመማር አላማ የሰነቀ ግለሰብ በመጀመሪያ ዲግሪ አይሸነገልም። እይታችን ሩቅ ካለው ግባችን ላይ ስለሆነ ባለፍነው ጥቂት እርምጃ በራስ መኮፈስ "ኢጎ" ውስጥ አንወድቅም። ገና ምኑ ተነካና... መች ጉዞው ተጀመረና።

ሀግ - 13 "ሩቅ አላሚ ቅርብ አያድርም"

11.14 ሁሉም ነገር መፍትሔ አለው

"መድሀኒትን ፈልጉ አላህ አንዲትንም በሽታ አላሰቀመጠም መድኃኒቱን (አብሮ) ያስቀመጠ ቢሆን እንጂ" ነብዩ ሙሐመድ ﷺ

በሌላም ንግግራቸው ላይ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡- "አላህ አንድንም በሽታ አላወረደም መድኃኒቱን አብሮ ያወረደ ቢሆን እንጂ ያወቀ አወቀው፣ ያላወቀ አላወቀውም።"[163]

ከላይ የጠቀስናቸው የታላቁ መልዕክተኛ ﷺ መልዕክቶች ትኩረትን ይሻሉ። ሁሉም ችግሮች መፍትሄ አላቸው። እነዚህ ችግሮች ዓለማዊም ሆኑ መንፈሳዊ፣ የውስጥ ይሁኑ የውጭ፣ የግል ይሁኑ ዓለም አቀፋዊ... ሁሉም መፍትሄ አላቸው።

ምድር ላይ ያለ የፈለግከውን ችግር ጥቀስ (ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ግለሰባዊ፣ መንፈሳዊም ስጋዊ...) ... ለሁሉም መፍትሄ አላቸው። አላህ የምድር ችግሮችን ከነመፍትሄዎቻቸው ፈጥሯቸዋል። ተግቶ ያወቃቸው ይፈታቸዋል። ተሳንፎ ያላወቃቸው የአሉታዊው ተፅዕኖ ተጠቂ ይሆናል። ... ለዚህም ነው መልዕክተኛው "ያወቀ አወቀው። ያላወቀ አላወቀውም" ማለታቸው።

[163] ኢማሙ አህመድ እንደዘገቡት

ከ1010 ዓመታት በፊት ወደ ዓለም ብቅ ብለው የነበሩት የህክምና ሳይንስ አባት ኢብኑ ሲና፣ ለደረሱበት ከፍተኛ ደረጃ መነሻ የሆናቸው ይኸው ከላይ የጠቀስነው የነብዩ መሐመድ ﷺ ንግግር ነበር። ግለሰቡ ከላይ የጠቀስናቸው ንግግሮችን በማሰላሰል በጥልቅ መልዕክቶቻቸውን ፈተሿቸው። ሁሉም ችግሮች መፍትሄ እንዳላቸው ተረዱ። ለሰው ልጆች አካላዊ በሽታዎች መፍትሄ ለማግኘት እንዲነሳሱ መግፍኤ ሆነላቸው። ከዓመታት ጥናት በኋላ ከ700 በላይ ለሚሆኑ በሽታዎች መድኃኒቶችን የዘረዘሩበትን "ቃኑን ፊ ጢብ" የተሰኘውን ብርቅየ የህክምና ድርሳን ለዓለም አበረከቱ። ይህ ድርሳን ለአውሮፓውያን የህክምና ሳይንስ እድገት የመሰረት ድንጋይ መሆኑን ልብ ይሏል።

ወዲህ ደግሞ ከ600 ዓመታት በፊት ወደ ምድራችን ብቅ ብለው የነበሩት ታላቁ ሊቅና የተሃድሶ ሀየንተ-ሰብዕ (Icon) ኢማሙ ኢብኑል ቀይም፣ ይህን የነብዩ ሙሐመድ ﷺ ንግግር መነሻ አድርገው ለሰው ልጆች የውስጥ መንፈሳዊ በሽታዎች መፍትሄዎችን አስቀምጠዋል። "አዳኑ ወደዋእ" "በሽታና መድኃኒቱ" የሚል ውብ ድርሳን ለዓለም አበርክተዋል።

አዎ! ይህ ፈጣሪ ያስቀመጠው ቋሚ ህግ ነው። ኢብኑ ሲና ይህን መነሻ አድርገው ለአካላዊ በሽታዎች መፍትሄን አስቀመጡ፣ ኢብኑል ቀይም ይህንን መመሪያ ተከትለው ለሰው ልጆች የውስጥ ልቦናዊ በሽታዎች መፍትሄን አሰፈሩ። ታዲያ አንተም ወደ ስኬት ስታቀና ከፊት ለፊትህ ለሚያጋጥሙህ ችግሮች እጅ አትስጥ። ሁሉም ችግሮች መፍትሄ እንዳላቸው ልብ በል።

ብቻ መከራህን እየቀያየርክ ለችግሮችህ መፍትሄ ፍልግላቸው። እንዴ መፍትሄ ማግኘትህ አይቀርም።

"ለሁሉም በሽታ መድኃኒት አለው። መድኃኒቱ በሽታውን ካገኘው በአላህ ፈቃድ ይድናል። ነብዩ ሙሐመድ ﷺ[164]

ህግ - 14 - "ማንኛውም ችግር መፍትሄ አለው"

[164] ኢማሙ ሙስሊም ዘግቦውታል።

11.15 ሁሉንም ማስደሰት አትችልም

"የሰዎችን ሁሉ ውዴታ ማግኘት የማይደረሰበት ድካም ነው።"
የዐረቦች አባባል

ሌሊቱ ተራውን ለቀኑ አስረክቦ ከአድማሱ ራሱን ሲያሸሽ አዛውንቱ ወደ ልጃቸው መኝታ ክፍል አቀኑ። ዛሬ እርሳቸው ለመጨረሻ ልጃቸው ትልቅ ትምህርት የሚሰጡበት ቀን ነው። ረዥሙ እድሜያቸው ያስተማራቸውን፣ በሰፊው የህይወት ተሞክሯቸው ያካበቱትን ልምድ ለማካፈል ወስነዋል።

ትንሹ ልጃቸው ከጎናቸው መጥቶ ቁጭ አለ። "ልጄ" አሉት ርህራሄ እዝነት በተቀላቀለበት ቃና። "ዛሬ ከእኔ ጋር አብረን አንዲትን መንደር ጎብኝተን እንመለሳለን። ስለዚህ ለጉዞ የሚሆነንን ስንቅና መጉጊያ አዘጋጅ" አሉት። ልጁም በፍጥነት ከቤት በመውጣት አንድ አህያና ለጉዞ የሚያስፈልጋቸውን ስንቅ አዘጋጀ።

አዛውንቱ አባትና ትንሹ ልጅ ከመንደራቸው ወጥተው አህያቸውን እየነዱ ጉዞ ጀመሩ። አባትም "አንተ እንዳይደክምህ አህያዋ ላይ ውጣ እኔ በእግሬ እጓዛለሁ" አሉት። ልጁም አህያዋ ላይ ወጣ። ትንሽ እንደተጓዙ በአንዲት ትንሽየ መንደር ጥግ አለፉ። የመንደሯ ነዋሪዎች እየተጠቋቆመባቸው "ምን አይነት ዘመን ላይ ደረስን? እንዴት አዛውንት አባት በእግር እየሄዱ፣ ይህ ሮጦ ያልጠገበ ልጅ አህያ ይጋልባል?" ሲሉ ሰሟቸው። መንደሯንም ትተው እንደወጡ "ልጄ ሰማህቸው እንዴ? እንዲህ ከሚያነውሩን አንተ በእግርህ ብትሄድ ይሻላል" አሉና እርሳቸው አህያዋ ላይ ሆነው፣ ልጃቸው ከፊት በእግሩ እየመራ ጉዟቸውን ቀጠሉ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሌላ መንደር ውስጥ አለፉ። በርካታ ሰዎች ዛፍ ስር ተቀምጠው ሲጨዋወቱ አገኟቸው። ትንሽ አልፈዋቸው እንደሄዱ፣ የመንደሯ ነዋሪዎች "ምን አይነት ጉድ ነው? እንዴት ይሄ አንድ ፍሬ ልጅ በእግሩ እየተጓዘ፣ አባቱ አህያ ይጋልባሉ? ምናለ ለዚህ ትንሽ ልጅ ቢያዝኑለት?" ሲሉ ሰማቸው። አዛውንቱ አባትም ወደ ልጃቸው በመዞር "ልጅ ያሉትን ሰማህቸው እንዴ? ስለዚህ አንተ በእግርህ እየሄድክ እኔ ብቻየን አህያዋን መጋለብ የለብኝም" አሉና ልጃቸውን አብረው አህያዋ ላይ አስቀመጡት።

የአባት ወግ እያወጉት ጉሏቸውን ቀጠሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሌላ ትንሽ መንደር ውስጥ አለፉ። የመንደሯ ነዋሪዎች ከአንድ ትልቅ ዋርካ ስር ሆነው ይጨዋወታሉ። ወሬያቸው ደርቷል። አዛውንቱ አባት ሰላምታ ሰጥተዋቸው አለፉ። የመንደሯ ነዋሪዎች በአግራሞት አፍጥጠው ተመለከቷቸው። ትንሽ አልፍ እንዳሉም እንዲህ ሲሉ ሰማቸው፡- "ምን አይነት ዘምን ላይ ደረስን? እንዴት ለዚህች እንስሳ አያዝኑም? በዚህ ሀር ፀሐይ ለሁለት እንዴት ይጋልባታል?!"

መንደሯን ለቀው እንደወጡም፣ አባት ወደ ልጃቸው በመዞር፡- "ልጄ ሰዎች ያሉትን ሰማሀቸው እንዴ? ስለዚህ ሁሌታችንም በእግር ብንሄድ ነው የሚሻለን።" ብለው አባትና ልጅ በእግራቸው ማዝገም ጀመሩ። ትንሽ እንደተጓዙም በሌላ መንደር ውስጥ አለፉ። ከአንድ ትልቅ የቱምር ዛፍ ስር ተሰብሰበው የነበሩ የመንደሯ ነዋሪዎች በአግራሞት ተመለከቷቸው። "እንዴት ያሉ ሞኞች ናቸው? እንዴት በዚህ ፀሐይ በእግራቸው ይጓዛሉ? የአህያ ጥቅም ታዲያ ለዚህ ሰጓት ካልሆነ ለመቼ ነው?" ሲሉ አባትና ልጅ ነሚቸው።

ትንሽ ከተጓዙ በኋላ አዛውንቱ አባት ልጃቸውን ይዘው ከአንዲት የቱምር ዛፍ ስር ረፍት ወሰዱ። ለልጃቸው እንዲህ አሉት፡- "ልጄ ሆይ! ሰዎችን ሁሉ ማስደሰት አትችልም። ስለዚህ በህይወት ጉዞህ ላይ የሰው ልጆችን ጌታ ማስደሰትን ብቻ ግብህ አድርግ። ይህ ረዥሙ አድሜ ያስተማረኝ ትምህርት ነው። ይህንም ላስተምርህ ፊልጌ ነው ጉዞ እንድንወጣ ያደረኩት። በል አሁን ጓዛችን ሰብስብና ወደ መንደራችን እናቅና" አሉት።[165]

አዎ! ወደ ስኬት ስታቀና ሁሉንም ማስደሰት እንደማትችል ተረዳ። አንተ ልብ ማለት ያለብህ የያዝከው መንገድ የሰው ልጆችን ፈጣሪ የሚያስደስት መሆኑን ብቻ ነው። "የስኬትን ቁልፍ በእርግጥ አላውቅም። እኔ የማውቀው የውድቀት ቁልፍ ሁሉንም ለማስደሰት መጣር እንደሆነ ነው።" ማለታቸው ቢል ኮዝቢ ለዚህ ነው።

---

[165] መሐመድ አል-ሚስሪ - አፕላቱ አር-ረሱል

ስለዚህ በጉዞህ ላይ የአላህን ውዴታ ብቻ ተቅጣጭ። በዙሪያ ያሉ ሰዎች ለሚያቀርቡት ትችት ጀሮ አትስጥ። የያዝከው ጎዳና ሰብዓዊና መለኮታዊ እስከሆነ ድረስ ጉዞህን ወደፊት ቀጥል።

ሀግ - 15 - "ሁሉንም ማስደሰት አትችልም

11.16 ጥበብን ሁሉም ቦታ ፈልገው

"ያለ አርጋታ ትዕግስት የለም ፣ ያለተሞክሮ ጥበብ የለም"[166]
ነብዩ ሙሐመድ ﷺ

ጥበባዊ ንግግሮች ከመለኮታዊ መመሪያዎች አልያም ከህይወት ተመክሮዎች የመነጫሉ። የህይወት ውጣ ውረዶችና ተሞክሮዎች የጥበብ መብቀያ መስኮች ናቸው። የሰው ልጅ በጥልቀት የተመለከተውን ጉዳይ በአጭር ቃላቶች ያሰፍራል። በሚገባ ያጠናውን ነገር በትንሽ መስመሮች ይቋጫል። ረዥሙን የምድር ቆይታውን በተወሰኑ ሀረጎች ያስቀምጣል። ለዘመናት ውስጡን የከነከነውን ብሶቱን፣ በፈንጠዝያ ያቧረቀውን ደስታውን በጥቂት ስንኞች ይቋጥራል።... አዎ! ጥበብ መብቀያው ተሞክሮ ነው።

ታዲያ ይህ የሰው ልጅ የህይወት ተሞክሮ የወለደውን የጥበብ ድልብ ካገኘህበት ቦታ ውሰደው። ታላቁ መልዕክተኛ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ እንዲህ ሲሉ ወደ ጥበብ ይገፋፋናል፦ "ጥበብ የጠቢባን የጠፉ ንብረቶች ናቸው።"[167]... መልዕክቱ ግልፅ ነው። የትም ቦታ የምታገኘው እውቀት አንተን ይመለከትሃል። ንብረትህ ነውና በቻልከው መጠን ዝገን። ከመዝገን ከተሳነፍክ፣ ድሮውንም ጥብና እውቀት አንተን አይመለከትህም ማለት ነው።

አዎ! ጥበብ የጠቢባን ንብር ነው። የትም ቦታ ካገኙት ይጠቀሙበታል። የተናጋሪውን ማንነት ሳይሆን የተናገረው ምንነት ላይ ትኩረት ይሰጣሉ። ጥበብ በማንም ሊነገር ይችላል። ቁም ነገሩ ግን የተናገረው ንግግር ጠቃሚነት ላይ ነው።

---

[166] አል-ሓኪም ዘግበውታል
[167] ቲርሚዚ - ሀዲስ ቁጥር - 2687

"ሰውቀት ከሙሰሚኖች ጠፍታ የሄደች ሀብት ናት። ከአምነት አልባ ሰው አንኳ ቢሆን ውሰዳት" ይሉናል ታላቁ መሪ አሊይ ኢብኑ አቢጧሊብ።

"ከሁሉም ነገር ላይ ያለቸውን መልካም ነገር ተምሪያለሁ ከውሻ እንኳን ጠላቱን እንደት እንደሚከላከል፣ ከአሳማ እንደት በንጋት እንደሚሰማሪ።"

ሙሃደረቱል ኡደባፅ

አይንህን ከፊት አድርግና ጥበብን ፊልጋት። ተፊጥሮን ተመልከትና ግንዛቤን ጨምር። ታሪክን አገላብጥና ተሞክሮን ቅሰም። የእውነት ነው የምልህ! በዙሪያህ ያሉ ነገሮች ሁሉ አስተማሪ ናቸው። እስኪ ቤትህን ተመልከተው፡- "ጣሪያው - ቀና በል ተስፋ አትቁረጥ፤ መሬቱ - ሁሉን ቻል፤ ግድግዳው - ለሁሉም ነገር ልክ አለው። ድንበር አትለፍ፤ መስታወቱ - ወደ ራስህ ተመልከት እራስህን ሁን፤ ሰዓቱ - ጊዜህን በአግባቡ ተጠቀም፤ ቁም ሳጥኑ - አልፎ አልፎ አንጂ አሁንም አሁንም ከንፊርህን አታላቅ... ይሉሀል።"[168]... አንተም ጥበብን ካገኘህበት ቦታ ሁሉ ውሰድ።

ታዲያ ከዚህ ቀጥዩ ከተለያዩ መፅሐፎች ያደንኳቸውን ጥቂት ጥበባዊ ንግግሮችን አስነብብሃለሁ። እነዚህ አባባሎች ከምግብ በኋላ እንደሚበሉ ጣፋጭ ኬኮች ናቸው። "የጥበብ ኩኪሶች" ልትላቸው ትችላለህ። ብቻ አልፎ አልፎ ገለጥ እያደረክ አባባሎችን አስተንትናቸው። ለምትከትባቸው መጣጥፎችህም እንደ ጥሬ እቃ ተጠቀምባቸው። ልብ በል! ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ተከበሩ የፊጣሪ መልዕክተኞች ንግግሮች ስለሆኑ፤ የበለጠ ትኩረትን ይሻሉ። እነሆ፡-

1) ቅድሚያ ውስጥህን ለውጥ

"በሰውነታችን ውስጥ እንዲት ሙዳ ሰጋ አለች፡ አርሷ ከተስተካከለች ሰውነት ሁሉ ይስተካከላል። አርሷ ከተበላሸች ሰውነት ሁሉ ይበላሻል። አርሷም ልብ ናት።

ነብዩ ሙሐመድ ﷺ

---

[168] በረነ - ሙሐመድ ሰዒድ ABX ገፅ - (26-27)

2) ራስህን አታታልል

"ሰዎች የአንተን ውስጣዊ ማንነትህን ባለማወቃቸው ከውጫዊ ማንነትህ በመነሳት የሚሰጡት ምስክርነት አንተ ስለራስህ ያለህን ትክክለና ሰውቀት አንዳይሸፍንብህ።" ኻሊድ ኢብን ሰፍዋን

3) ለውሳኔ አትቸኩል

"አንድ ሰው በአርማጥ አንድ ዓይኑ ጠፍቶ ቢመጣ ዓይኑን ያጠፋው ሰው አስኪመጣ ድረስ አትፍረድለት። ምክኒያቱም ዓይኔን አጠፋኝ ያለው ሰው ሁለት ዓይኑ ጠፍቶበት ሊመጣ ይችላልና።" ዑመር ኢብኑ ዐብዱልዐዚዝ[169]

4) ሳያመልጥህ ተጠቀምበት

"የአያንዳንዱ ዕለት ጎህ ከበሰተምስራቅ ብቅ ባለ ቁጥር፡- "የአደም ልጅ ሆይ! እኔ አዲስ ፍጥረት ነኝ። ስለ ሥራህም መስካሪ ነኝ። ሳላመልጥህ ተሰንቅብኝ። እኔ አንዴ ካመለጥኩ አስከ ዕለተ-ትንሳኤ ድረስ አልመለስም። ብሎ አዋጅ ይናገራል።" ሐሰን አልበስሪ

5) ይህን አስቀድም

"ትምህርት ከመማራችሁ በፊት አውነተኝነትን ተማሩ። ዓላማችሁን አውነተንኝታችሁ ነውና የሚመራው።" ኢማሙ አውዛዒ

6) የግቦችን ግብ አትርሳ

"የሰው ልጅ አግሩ አዚህ ዓለም ከረገጠ ጊዜ ጀምሮ ወደ መጭው ዓለም (አኼራ) መንገደኛ ነው። የጉዞ ቆይታው እድሜው ነው፡ ቀንና ሌሊት ማረፊያው ናቸው።" ኢማም ኢብኑል ቀይም

7) ነገህን ዛሬ ጀምረው

"ነገ ከዛሬ ጋር አብሮ አለ።" ዐሊይ ኢብኑ አቢ ጣሊብ

[169] ነፍሲ ወኒ የተሞላች ናት የሚለውን ይመልከቱ፡- ምዕራፍ 10

9) ጠንካራ ሁን

"በሀይወት እንቅስቃሴ ውስጥ ልፍስፍስ ከሆነ ሰው ይልቅ፤ በእንቅልፍ ውስጥ ሆኖ ቆራጥ የሆነ ሰው በንቃት ውስጥ ነው።" ዐሊይ ኢብን አቢጧሊብ

10) ከእርምጃህ በፊት

"ውሳኔ ሳትሰጥ አስተንትን፤ ወረራ ሳትፈፅም ተዘጋጅ፣ ሳትጀምር አማክር።"
ኢማሙ አሻፊኢይ

11) ትኩረትህን ሰብስብ

"ትኩረትህን ወደፊት አድርግ የኋላህንማ አንድ ጊዜ አልፈኸዋል።"
አል - ሙሐሲብይ

12) በእቅድ ተመራ

"ከተግባር በፊት እቅድ ከፀፀት ያድናል።" ዐሊይ ኢብኑ አቢጧሊብ

13) ታይታን አትናፍቅ

"ለመታየት ብለህ ከብርሃን ላይ መሆን የለብህም። ነገር ግን ለማየት የምትፈልገው ነገር ከብርሃን ላይ መሆን አለበት።" (ዐባስ ሙሐመድ)

14) የሁለት ዓለምን ስኬት ፈልግ

"የዚህን ዓለም ድሎት የፈለገ ሰው አውቀትን ይፈልግ። የመጭውን ዓለም ድሎት የፈለገ ሰው ዕውቀትን ይፈልግ።" ኢማሙ አሽ-ሻፊዒ

15) ፅኑ እምነት ይኑርህ

"... ይህ ልናርለት አና ልቀዳጀው ተሰፋ የማደርገው ዓላማ ነው፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ልሞትለትም የተዘጋጀሁለት ዓላማ ነው።" ማንዴላ

16) ከሱስ ራቅ

"የማልጠጣበትን አንድ ምክንያት ጥቀስ ካላችሁኝ ጥሩ ሰሜት ሊሰማኝ እንዲታወቀኝ መፈለጌ ሊጠቀስ ይችላል።" ሌድ አስተር

17) ራስህን ሁን

"ሌሎችን ሰዎች ለመምሰል ራሱን የሚለውጥ ሰው ብዙም ሳይቆይ ራሱን ሸራርፎ ይጨርሰዋል።" Roymond Hull

18) ከራስህ ጀምር

"አራሳችሁን ታማኝ አድርጉ። የዚያኔ በዓለማችን ላይ ያሉትን ቁጣሬዎች ቁጥር በአንድ ለመቀነሳችሁ አርግጠኛ መሆን ትችሉ ሆናል።" ቶማስ ካርላይን

19) ትልቁ ስጦታ

"አንድ ሰው ለሰው ዘር ሊያበረክተው የሚችለው ትልቁ ስጦታ ራሱን የማሻል ስጦታ ነው።" Frank Herbert

20) በምን አሳለፍከው

"ከረምት መጥቶ በበጋው ወራት ምን ስታደርግ ከረምክ ብሎ የሚጠይቅህ ጊዜ ይመጣል።" Henry Clay

21) በእጅህ ነው

"ለራሳችን ያለንን ከብር አሳልፈን ካልሰጠናቸው በስተቀር ሰዎች ሊወስዱብን አይችሉም።" ማህተመ ጋንዲ

22) ጥሩ ስነ-ምግባርን ተላበስ

"ከፀሐይ በታች ከየትኛውም ችሎታ ይልቅ ከሰዎች ጋር ለመግባባት የሚሰችለኝን ችሎታ ለመቀዳጀት ሰል የቱንም ያህል ገንዘብ አከፍላለሁ።"
ጆን.ዲ. ሮክፌለር

23) የሞኞች ስሌት
"አንድን ነገር ለታይታ ማድረግ ሞኞች የፈለሰፉት የመከበር ሙከራ ነው።"
Bruce Lee

24) ለስኬት ተፈጥረሃል

"ሁሉም የአዳም ልጆች በትክክለኛ ተፈጥሮ ላይ ነው የተወለዱት።"
ነብዩ መ·ሐመድ ﷺ

25) እስከመጨረሻው ድረስ ቀጥል

"ትንሳኤ ልትቆም ባለችበት ቅፅበት ውሰጥ፣ አንዳችሁ አጁ ላይ ችግኝ ቢኖርና ችግኟን ለመትከል አድል ካገኝ ወድያውኑ ይትከላት።"
ነብዩ መ·ሐመድ ﷺ

ሀግ - 16 "ጥበብን ሁሉም ቦታ ፈልገው"

12

ምዕራፍ አስራ ሁለት



የስኬት ተምሳሌቶች

- ቡሻሪ
- ሙሐመድ ዩኑስ
- ታላቁ መልዕክተኛ
  - ንብዩ ሙሐመድ ወደ ሰው ልጆች ከመላካቸው በፊት
  - የኢስላም ፀሐይ ከአድማሱ ላይ ሲፈነጥቅ
  - የጉዞው ጅማሮ
  - ለስኬት የተከፈለ ዋጋ
  - አመርቂ ስኬት (Great Seccess)

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የህይወት ግባቸውን ቀርፀው፣ አልሀ አስጨራሽ ትግልን አድርገው፣ ሁሌም ከአላማቸዉ ጋር ኖረው... በመጨረሻ የስኬት ማማ ላይ ሰለወጡ ታላላቅ ሰብዕናዎች እንመለከታለን።

ተሰጥኦዎቻቸውን ባማከለ መልኩ እንዴት የህይወት ግባቸዉን እንደቀረፁና ግባቸው የሚጠይቃቸውን ክፍያ ሁሉ እንዴት እንደከፈሉ እናወሳለን። በመጨረሻም ከረዥም አመታት ልፋት በኋላ ለአመታት ያለሙትን ዓላማ እንዴት እንዳሳኩ እንዳስሳለን።

12.1 ኢማም አል-ቡኻሪ

"በምቀኝነት ካልሆነ በቀር ማንም ሰው መጥፎ ነገር ሊናገርህ አይችልም። በዓለም ላይ እንዳንተ ያለ ታላቅ ሰው እንደሌለ እመሰክራለሁ"

እውቁ ሊቅ - ኢማሙ መስሊም

ዝናቸው ክፍለ ዘመናትን አልፎ ያስተጋባው እውቁ የሐዲስ ሊቅ ኢማም አልቡኻሪ የተወለዱት በሂጅርያ አቆጣጠር 194 ነበር። የዘር ሀረጋቸውም ከፋርስ ይመዘዛል። ገና በልጅነታቸው አባታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ገና በጠዋቱ የየቲምነትን (የወላጅ አልባነትን) ህይወት ለመጋፈጥ ተገደዱ። እናታቸውም የአባታቸውን ቦታ ተክታ ተንከባከባ አሳደገቻቸው።[170]

ቡኻሪ አዕምሮአቸው ስል ነበር። ነገሮችን በአንድ ጊዜ የመሸምደድ ተሰጥኦ ነበራቸው። የማስታወስ ችሎታቸውም በጣም የተለየ ነበር። አንድ መፅሐፍ ላይ አንድ ገፅ ከተመለከቱ ዳግም ላይፋቅ አዕምሮአቸው ውስጥ ይታተማል። ታዲያ አንዴ ይህን ተሰጥኦዋቸውን የሚያሰልፉበት እድል ተፈጠረላቸው። ተሰጥኦዎቻቸውን ባማከለ የህይወት መስክ ውስጥ የከተታቸው (የመራቸው) አጋጣሚ ተከሰተ።

ነገሩ ወዲህ ነው። ቡኻሪ የ14 ዓመት ታዳጊ እያለ፣ ታላላቅ ዑለማዎች (የሀይማኖት ሊቆች) ሲወያዩ ይሰማል። ውይይታቸው በተመስጦ የተሞላ ነበር። ጭንቀትም ይነበብባቸዋል። መፍትሄ ፍለጋ ይቆዝማሉ። ቡኻሪ የጭንቀታቸው ጉዳይ ምን እንደሆነ ለመረዳት ጆሮውን ጣል አደረገ። "ከነብዩ ሙሐመድ ﷺ የተላለፉ ሐዲሶች (ንግግሮቻቸው፣ አስተምህሮቶቻቸው፣ ትዕዛዛቸው...) የተለያየ ደረጃ አላቸው። ጠንካራውን (ሶሒሑን) ከደካማው (ከዶኢፍ) አበጥሮ የሚለይልን በመጣ።"[171] ሲሉ ሰማቸው። አስከትለውም "ማን ይሆን ጠንካራና ትክክለኛውን (ሶሂሁን) ሰብስቦ በአንድ መፅሐፍ የሚያዘጋጅልን? አላህ ይህን የሚያደርግ

---

[170] መስጦለህል ሐዲስ- መሐመድ ሷሊህ አል-ዑሰይሚን

[171] ከነብዩ መሐመድ ሰ.ዐ.ወ. የተላለፉ ሐዲሶች የተለያየ የትክክለኛነት (Authenticity) የዘገባ ደረጃ አላቸው። የመጀመሪያው ሶሒህ (ትክክለኛና ጠንካራ) ሲሆን፤ ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሐሰን (ጥሩ) የሚባል ነው። በመከተልም ደረጃቸው እየቀነሰ ሲሄድ ዶዒፍ፣ መውዱዕ ይባላሉ። "ዶኢፍ" ማለት ደካማ ማለት ሲሆን በእስልምና ህግጋት ቀረፃ ላይ ጥቅም ላይ የማይውል ነው። "መውዱዕ" ደግሞ ፈጠራ፣ ከነብዩ ﷺ ያልተላለፈ ማለት ነው። ይህ የሐዲስ ደረጃ ምደባ በጣም ከባድና ላይንሳዊ ነው። ጥቂቶች እንጂ ሊካኑበት ይከብዳል።

ቢልክልን::" ብለው ሲመኙ ሰማቸው::

እርሱም ወዲያውኑ "ለዚህማ እኔ አለሁ" አለ::[172] ይህን ተልዕኮ ለመወጣት አሰበ:: ከአላህ መልዕክተኛ ሰ.ዐ.ወ የተላለፉ ሐዲሶችን አበጥሮ ትክክለኛ (ሶሒሕ) ዘገባዎችን ብቻ ያካተተ መፅሀፍ ለማዘጋጀት ወሰነ:: የመሸምደድና የማስታወስ ችሎታው ይህን ግብ ለማሳካት አጋዥ እንደሚሆነው ተረድቷል:: ይህ የማስታወስ ተሰጥኦው በሚሊየን የሚቆጠሩ የነብዩ ሰ.ዐ.ወ ሐዲሶችን በመሰብሰብ ላይ ጉልህ ሚና እንደሚጫወት እርግጠኛ ሆኗል:: ለዚያም ነው "ለዚህማ እኔ አለሁ" ያለቱ::

ለዚህ ታሪካዊ ስኬት ቡኻሪ ተንቀሳቀሱ:: ገና በ 16 ዓመታቸው እርምጃቸውን ጀመሩ:: ሀገራቸውን ኹራሳንን[173] ለቀው ከሀገር ሀገር እየተዘዋወሩ ለአመታት የሐዲስን እውቀት ፍለጋ ማሰኑ:: የሐዲስ ትምህርት ይሰጣል ከተባለበት ቦታ ሁሉም ቀድመው ይገኛሉ:: እውቅ የሐዲስ ሊቅ አሉ በተባሉበት ሀገር ሁሉ ጓዛቸውን ይዘው፣ በርሃውን አቋርጠው፣ የመንገዱን እልህ አስጨራሽና አሰልቺ እንግልት ተቋቁመው እቦታው ድረስ ይገኛሉ:: ሻም (ሶሪያ)፣ ግብፅ፣ ኢራቅ፣ ኩፋህ[174] (የኢራቅ የድሮ ከተማ)፣ ጀዚራህ[175]... ከጎበኟቸውና ለአመታት እውቀትን ፍለጋ ካሳለፉባቸው ሀገሮች ጥቂቶቹ ናቸው:: በራሳቸው አንደበት እንዲህ ይሉናል:- "ወደ ሶሪያ፣ ግብፅ፣ ጀዚራህ ሁለቴ ተመላልሻለሁ:: በስራህን[176] አራቴ ጎብኝቻለሁ:: ባግዳድንና ኩፋህን ከሐዲስ ሊቃኖች ጋር ምን ያህል እንደተመላለስኩባቸው በቅጡ አላስታውስም (በጣም በርካታ ጊዜ ተመላልሼባቸዋለሁ):: ሂጃዝ ላይ ስድስት ዓመት ያህል ተቀምጫለሁ::"[177] በአጠቃላይ "ሐዲስን ከ 1000 ሰዎች በላይ ተምሬ ፅፌ ዘግቤያለሁ"[178] ይሉናል::

---

172 ዶ/ር ዐምር ኻሊድ - ሀታ ዩገይሩ ማቢአንፉሲሂም

173 ኹራሳን - የዛሬዎችን ኢራን፣ አፍጋኒስታንን፣ ታጂኪስታንን እንዲሁም ኡስቤኪስታንን... መዘተ አካባቢዎች ያካተታል::

174 ጥንታዊ የኢራቅ ከተማ ናት::

175 ከኤደን እስከ ሶሪያ በቀም፣ በጎን ከጅዳ እስከ ኢራቅ ገጠራማ ክፍሎች::

176 ደቡባዊ የኢራቅ ጥንታዊ ከተማ ናት:: አሁንም በዚሁ ስሟ ትታወቃለች:: የዛሬውን አያርገውና አውቅ የአውቀት ማእከል ነበረች::

177 ጣሪቅ አስ-ሰዋይዳን - ዐለመትኒል ሀያቱ

178 ታሪኩል በግዳዲ

ኢማሙ ቡኻሪ ሀገራቸውን ኹራሳንን ለቀው በስደት ለዓመታት ተንገላተዋል። የነብዩ ሙሐመድ ﷺ ሐዲሶች አሉ ከተባሉበት ቦታ ሁሉ ተመላልሰዋል። አላማቸውን ለማሳካት ያልተገናኙት የሐዲስ ምሁር የለም። ገና በለጋ እድሜያቸው የሰነቁትን ራዕይ ጥግ ለማድረስ ማስነዋል። ግባቸው የሚጠይቀውን ዋጋ ሁሉ ከፍለዋል። ከዚህ እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ በሚልየን የሚቆጠሩ ሐዲሶችን በቃሉ መሸምደድና በተገቢው ሁኔታ ማስታወስ ቻሉ።

የማስታወስ ችሎታቸው ሲፈተን

ይህ በየሀገራቱ ዞረው፤ ከ1000 በላይ ከሆኑ ዐሊሞች (ሊቆች) የሰበሰቡትን በሚሊየን የሚቆጠሩ ሐዲሶችን ያለ አንዳች እንከን በቃላቸው መሸምደዳቸው (መሐፈዛቸው) በየሀገሩ የህዝብ መነጋገሪያ ሆነ። "እንዴት በለጋ እድሜያቸው ዘገባዎችን (የዘገባ ተዋረዶችን) ያለ አንዳች ስህተት ማስታወስ ቻሉ?" ሲሉ ዓሊሞች ተገረሙ። የበለጠ እግጠኛ ለመሆን ቡኻሪን መፈተን ፈለጉ።

ህያው እውነት

ቡኻሪ በዚያው ዘመን እውቅ የጥናትና የምርምር እንዲሁም የሃይማኖት ልሂቃን መፈልፈያ ወደሆነችው ባግዳድ ጎራ አሉ። ህዝቡም እኒህን የወጣት ሊቅ ለማየት ተመመ። የሀገሪቱ እውቅ ሊቆችም ዝናቸውን ሲሰሙላቸው የኖሩትን የሀዲስ ሊቅ ለመፈተን ወሰኑ። ከባድና ውስብስብ ፈተናን አዘጋጁ።

ነገሩ እንዲህ ነው። የባግዳድ ዑለማዎች (ሊቆች) 100 ሐዲሶችን ከነሙሉ ሰነዳቸው (የዘገባ ሰንሰለት ተዋረዳቸው) አዘጋጁና አስር አስር አከፋፍለው ለ10 ሊቆች ሰጡ። እነዚህ አስር ሊቆች ሰነዶችን ሙሉ በሙሉ አንዱን ከሌላው በማዘባረቅ እንዲያዘጋጁ ተደረገ። በዚህ ላይ የተመረጡት መቶ ሐዲሶች በሐዲስ ሊቆች ዘንድ ለፈተና እጅግ ጠቃሚ የሆኑ መሆናቸው ልብ ይሏል።

ፈተናው ተጀመረ። ይህን ታሪካዊ ትይንት ለመመልከት በሺህ የሚቆጠሩ የባግዳድ ነዋሪዎች ታድመዋል። የሀገሪቱ እውቅ ሊቆችም ከነሙሉ ግርማቸው ፊት ተቀምጠዋል።

ከአስሩ ፈታኞች ውስጥ የመጀመሪያው ተነሳና ሐዲሱን ከነሙሉ ሰነዱ አነበበላቸው። ቡኻሪ ይህን ሐዲስ ከአሁን በፊት በዚህ የሰነድ ፍሰት ሰምተውት የማያውቁት ስለነበር ... "አላውቀውም" ሲሉ መለሱ። ሁለተኛው ሊቅ ተነሳና ሁለተኛውን ሀዲስ ከነሙሉ ሰንሰለቱ አነበበላቸው። ይህንም ቢሆን ቡኻሪ በዚህ መልኩ ሰምተውት አያውቁም። ሐዲሱን ቢያውቁትም ሐዲሱ የተዘገበበትን ሰንሰለት ግን አያውቁትም። ስለዚህ መልሳቸው አላውቀውም ሆነ። እነዚህ ጥያቄዎች ለፈተና ሲባል ሰነዳቸው የተዘባረቁ መሆናቸው ባልተረዱ የፈተናው ታዳሚዎች ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤ ፈጠረ። "ያ ዝናው ዓለምን የናኘው ታላቅ የሐዲስ ሰው እንዴት አላውቅም ይላል?" ሲሉ በግርምት አፈጠጡ። ሶስተኛውም ሐዲሱን አነበበ። የቡኻሪ መልስም "አላውቀውም" ሆነ። ሁሉም እየተነሱ ሐዲሶችን በየተራ ከነሙሉ ሰነዳቸው አነበቡ።... የቡኻሪ መልስ ግን አሁንም "አላውቀውም" ሆነ። መቶውም ሐዲሶች ተነበቡ። ... ከቡኻሪ አንደበት ግን "አላውቀውም" ከሚለው ቃል ውጭ ሌላ ሊወጣ አልቻለም።

በታዳሚው መሀል ዝምታ ነገሰ። ሁሉም ተገርመዋል። ሊቆች የቡኻሪን ታላቅነት በመመስከር፣ በሺህ የሚቆጠሩ ታዳሚዎች ደግሞ ግራ በመጋባት... ሁሉም ተገርመዋል።

"ሊቆቹ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?" ፣ "እንዴት አንድ ሰው ከመቶዎቹ አንዱን እንኳን ሳይሳሳት ይቀራል?" ሲሉ ተደነቁ።... ምድር ላይ የሚራመድ ተዓምር አድርገው ቆጠሩት።

ከዚህ በኋላ ደግሞ የቡኻሪን ታላቅነት ያሳየ፣ የታዳሚውን ህዝብ ብዥታ የገለጠ ንግግራቸውን ቡኻሪ አደረጉ።

ጥያቄዎችን ያቀረቡትን ሊቆችን አንድ በአንድ እየጠሩ የጠየቁትን ሐዲስ እየጠቀሱ ከትክክለኛ ሰነዱ ጋር በማገናኘት ለመቶዎችም ሐዲሶች እርማት ሰጧቸው።

"ቡኻሪ የመቶዎችን ሐዲሶች የሰነድ ስህተት መረዳታቸው ብቻ አይደለም የሚደንቀው እያንዳንዱን ፈታኝ (ሊቅ) የጠየቃቸውን የተዘበራረቁ ሰነዶች እዚያው ሸምድደው እዚያው ማስተካከላቸውና ሐዲሶችን ወደ ትክክለኛ የሰንሰለት ፍሰታቸው መመለሳቸው ነበር ግሩም

የማስታወስ ችሎታቸውን ያሳየው።" ይላሉ እውቁ የሐዲስ ሊቅ-ኢማሙ ኢብኑ ሐጀር።[179]

ሰመርቀንድ ትመስክር

ቡኻሪ በተለያየ ሀገሮች ለነበሩ ህዝቦች ትንግርት ሆነውባቸዋል። በገቡበት ሀገሮች ሁሉ የፊተናን ጥያቄ ያስተናግዱ ነበር። ይኸው አሁን ቡኻሪ ሰመርቀንድ ውስጥ ይገኛሉ።

400 ያህል የሚሆኑ እውቅ የሰመርቀንድ የሐዲስ ጠቢባን፤ የቡኻሪን ትክክለኛ የማስታወስ ችሎታ ለመፈተን ወሰኑ። ለዚሁም ፊተና በርካታ፤ ውስብስብ እንዲሁም ፈታኝ የሆኑ ሐዲሶችን አዘጋጁ። ፊተናውንም የበለጠ ለማከበድ የሐዲሶችን ሰንሰለቶች ማዘባረቅ ያዙ።

በጀዚራ የተዘገቡትን እና ዘጋቢዎችን፤ በየመኖች ዘጋቢዎች ለወጡት። እንዲሁም በኢራቅ የተዘገቡትን ሐዲሶች፤ የሻም ሀገርን ሐዲሶች በዘገቡ የሐዲስ አስተላላፊዎች ለወጡ። በሻም የተዘገቡትን፤ በኢራቅ ዘጋቢያን የሐዲስ አስተላላፊ ሰንሰለቶች ቀየሩ። እጅግ ፈታኝም አደረጉት።

ቡኻሪ ከ 400 ሊቆች ፊት ፊተናውን ተፋጠጡ። አደናጋሪ ጥያቄዎች ተደረደሩላቸው። ይገርማል! ... አንድም ስህተት ሳይገኝ እያንዳንዱን ሐዲስ ወደ ትክክለኛ ሰነዶቻቸው መለሷቸው። ወንዙን ወደ ምንጩ መለሱት። ፊተናው ለዘጠኝ ቀናት ያህል ቀጠለ። ቡኻሪ ላይ ግን አንዳችም ስህተት ሳይገኝ ቀረ። ሊቆችም እጅጉን ተደመሙ። የሰመርቀንድ ህዝቦችም ለቡኻሪ ያላቸው ክብር እጅጉን ከፍ አለ።[180]

በስራን ያየ ያውራ

ቡኻሪ ወደ ታላቁ ስኬት ያደረጉት ጉዞ ረዥም ነበር። ያልረገጡት የመካከለኛው ምስራቅ ቦታ የለም። ይኸው አሁን በስራ ከተማ ተገኝተዋል።

---

[179] ኢብኑ - ሐጀር:- እውቅ የሀዲስ ሊቅ። በቡኻሪ ድርሳን ላይ በበርካታ ቅጾች ሰፊ ትንታኔ የሰጡ ከ 600 ዓመት በፊት የነበሩ ሊቅ።

[180] ኢብኑ ሐጀር - መቀደመቱ ፈትሐልባሪ (መ-ሐመድ ዐሊ 6ቱ የሐዲስ ሊቃውንት)

ቡኻሪ በበስራ ከተማ መድረሳቸው እንደተሰማ፤ በስራውያን ከየቤታቸው ወጥተው እንደጎርፍ እየተግተለተሉ ቦታው ደረሱ። ቡኻሪ ወደሚገኙበት መስጅድ ውስጥ ገቡ።... ያዩትን ነገር ግን ማመን ተሳናቸው። ያ! ዝናውን የሰሙለት ታላቅ የሐዲስ ሊቅ ገና ለጋ ወጣት ነበር። ህዝቡም ቡኻሪን ሐዲስ እንዲያስተምሯቸው ጠየቋቸው። በማግስቱ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ።

በቀጠሮው መሰረት ህዝቡ በጊዜ ታደመ። ቡኻሪም እንዲህ ብለው መናገራቸውን ዩሱፍ ቢን ሙሳ አስተላልፈዋል፦

"በስራውያን ሆይ! ገና ወጣት መሆኔን እያወቃችሁ፤ ሐዲስ እንዳወራላችሁና እንዳስፅፋችሁ ጠይቃችሁኛል። እኔም የሐዲሱ ተራኪዎች (የሐዲሱ ዘጋቢዎች) የዚሁ ከተማ ተወላጅ ሆነው፤ ነገር ግን እናንተ የማታውቋቸውን ሐዲሶች እንግራችኋለሁ።" ብለው ትረካቸውን ቀጠሉ። በርካታ ሐዲሶችን ከነሙሉ የዘገባ ተዋረዶች (ሰንሰለቶች) አነበነቡላቸው።

በስራውያን የሰሙትን ማመን አስኪከብዳቸው ድረስ ተደመሙ። ዘጋቢዎች የዚህ ሀገር ተወላጅ ቢሆኑም፤ እነሱ ግን እነዚህን ሐዲሶች ከአሁን በፊት ሰምተዋቸው አያውቁም። በዚህም የቡኻሪን ታላቅነት አፀደቁ። የማስታወስ ተሰጥኦዋቸው የተለየ መሆኑን መሰከሩ።

ሶሒሓል-ቡኻሪ (ጃሚዑ አስ-ሶሒሕ)

ዓለም ላይ በተለያዩ ሀገራት የተሰራጩትን ሐዲሶች ከሰበሰቡ በኋላ "ሶሒሓል-ቡኻሪ" የተሰኘውንና ከነብዩ ሙሐመድ ﷺ የተላለፉትን ትክክለኛ ዘገባዎችን ብቻ የያዘ ድርሳናቸውን ማዘጋጀቱን ተያያዙት። ከሰበሰቧቸው ሐዲሶች ውስጥ ትክክለኞችን በመምረጥ ላይ ተጉ።

ይህን ታላቅ ድርሳን በማዘጋጀት ዙሪያ በጣም ደክመዋል። የሰበሰቧቸውን ሐዲሶች እንደ አዲስ ቁጭ ብለው አበጥረዋቸዋል። ሰፊ ጥናት አድርገው የሐዲሱን ትክክለኛነት ካረጋገጡ በኋላ የአላህን እርዳታ ይጠይቁ ነበር። ይህንንም እንዲህ በማለት ይነግሩናል፦ "ገላዬን ታጥቤና አላህን የማማከር (የማማረጥ) ሶላት (ኢስቲኻራ)[181] የሰገድኩ ቢሆን እንጂ ምንም አይነት ሐዲስ አልፅፍም።..." አያችሁ ይህ በስኬት ጉዟችን ላይ

ልንይዘው የሚገባን መንገድ ነው። በሰዋዊ አቅማችን የምንችለውን ጥረት እናደርጋለን፣ ከዚያም ጌታችን እንዲያሳውቀንና እንዲረዳን እንማፀናለን።[182]

ኢማም ቡኻሪ ይህን የሐዲስ ድርሳን ሲያዘጋጁ ቀን ብቻ ሳይሆን ሌሊትም እንቅልፍ አልነበራቸውም። ስለራሳቸው ሲናገሩ፡- "እኔ በአንድ ሌሊት ውስጥ ከሀያ ጊዜ በላይ በመነሳት ያስታወስኳቸውን ሐዲሶች አሰፍራለሁ"[183] ይሉናል። ይህ ምን ያህል ትጋትንና የአላማ ፅናትን እንደሚፈልግ ግልፅ ነው። አንድ ሰው በአንድ ሌሊት ውስጥ ሁለቴ ከእንቅልፉ ከነቃ፣ ምናልባት ሙሉ ቀኑን ተረብሾና ንቃቱና ስሜቱ ጠፍቶ ነው የሚውለው። ቡኻሪ ግን በአንድ ሌሊት ከሀያ ጊዜ በላይ ይነቁ ነበር።

በቃ! የዘውትር ስራቸው ይህ ነው። ተኝተው እያለ አንድ የነብዩ ሐዲስ ትዝ ይላቸውና፣ ተነስተው ኩራዝ አብርተው (ጧፍ አቀጣጥለው)፣ ከእንጨት የተሰራውን ብዕራቸውን ቀለም ውስጥ እየነከሩ ብራናቸው ላይ ይፅፋሉ። ከዚያም እንደገና ጧፉን አጥፍተው ይተኛሉ። እስኪ አስቡት አንድ ሰው በአንድ ሌሊት ሀያ ጊዜ የሚነሳና የሚፅፍ ከሆነ ምኑን ተኛሁ ይባላል?[184]

---

[181] ኢስቲኻራ ሶላት- አላህ መልካሙን ነገር እንዲመርጥልን የምንሰግደው ሶላት ነው። ጃቢር ረ.ዐ. እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ ሰ.ዐ.ወ የቁርዓን ምዕራፎችን እንደሚያስተምሩን ሁሉ የኢስቲኻራ (በጎ ነገርን ለመምረጥ ስለሚደረግ ፀሎትም) ያስተምሩን ነበር። አንድ የሚያሳስብ ጉዳይ ሲገጥመን ከፈርድ (ግዴታ) ሶላቶች ዉጭ የሆነች ሁለት ረከዓ ሶላት እንድንሰግድና ተከታዩን ዱዓ እንድናደርግ አስተምረውናል፡- "አላህ ሆይ! በእውቀትህ (ትክክለኛውን ነገር) እንድትመርጥልኝ እጠይቅሀለሁ። በችሎታህም (እተማመናለሁና በጎውንና ትክክለኛውን ምረጥልኝ)። ከታላቁ ትሩፋትህም እጠይቅሃለሁ። አንተ እንጂ እኔ ወሳኝ አይደለሁም። አንተ አዋቂ ነህ እኔ ግን መሀይም ነኝ፣ አንተ የሩቅን ዐዋቂ ነህ። አላህ ሆይ! ይህ ጉዳይ (ጉዳዩን ይጥቀስ) ለኔ፣ ለሀይማኖቴ፣ ለህይወቴና ለመጨረሻዉ በጎ ከሆነ ወስንልኝ፣ አቅልልኝ ረድኤትህንም ሙላልኝ። ይህ ጉዳይ ለኔ ለሀይማኖቴ፣ለህይወቴና ለመጨረሻዉ መጥፎ ሆኖ የሚገኝ መሆኑን የምታውቅ በመሆኑ (መጥፎ ከሆነ) ከኔ አስወግደው። እኔንም ከርሱ አርቀኝ ምንም ይሁን ምን መልካምን ነገር ወስንልኝ ከዛም እኔ (ውሳኔውን) እንድወደ (እንድተበል) አድርግኝ"።

[182] "በጌታህ ተደገፍ/ተመካ" የሚለውን ይመልከቱ- ምዕራፍ - 10

[183] ዶ/ር ዐሊይ አልቀርኒ - The best books of Qarni

[184] ይህን የቡኻሪ ፈለግ በዘመናችን አውቀ የሚዲያ ሰዉ ቻርልስ ቻፕሊን ተግብሮታል። ቻርሊ በልጅነቱ አዉቅ ኮሜዲያን መሆን ይፈልግ ነበር። ታዲያ ሁሉ ሲተኛ አስክርቢቶና ወረቀት ከጎኑ አስቀምጦ፣ መጻራት አብርቶ ነበር። ድንገት አንድ ቀልድ ትዝ ካለው ተነስቶ ይፅፋል። "እኔ በአንድ ሌሊት ዉስጥ ከ20 ጊዜ በላይ እየተነሳሁ ያስታወስኩትን ቀልዶች እፅፍ ነበር።" ይለናል።

ኢማሙ ቡኻሪ በስማቸው የተሰየመውን የሐዲስ ድርሳን ለማዘጋጀት 16 ዓመታት ፈጅቶባቸዋል። (ይህ እንግዲህ ሐዲሱን ለመሰብሰብ ከወሰደባቸው በርካታ ዓመታት ውጭ መሆኑ ነው)። ከዚህ ሁሉ ድካም በኋላ 7397 የተደጋገሙ፣ 2602 ያልተደጋገሙ ሐዲሶችን የያዘውን ድርሳን ለዓለም አበረከቱ። በጣም የሚገርማችሁ እነዚህ 2602 ሐዲሶችን ከስንት ሐዲሶች መሀል መርጠው እንዳወጧቸው ታውቃላችሁ? ቡኻሪ እነዚህን ትክክለኛ ዘገባዎች የመረጧቸው ከስድስ መቶ ሺህ (600,000) ሐዲሶች መሀል ነበር። ከዓለም የተለያዩ አህጉራት ከሰበሰቧቸው በርካታ ሐዲሶች መሀል በአዘጋገብ ፍሰታቸውና ከነብዩ ሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ. በመተላለፍ የትክክለኛነት (Authenticity) መጠን እየመረጡና ለእያንዳንዱ ለሚያስፍሩት ሐዲሶች እስቲኻራ ሶላት እየሰገዱ ታላቁን ድርሳን አዘጋጁ። ልብ በሉ እያንዳንዱ ሐዲስ እስቲኻራ ሶላት ተሰግዶበታል።

ይህንን ዓመታት የፈጀ ድርሳን ከጨረሱ በኋላ በዘመኑ ለሚገኙ እውቅ የሐዲስ ምሁራን ለግምገማ (ለምርመራ) አቀረቡት። እውቁ ዓሊም (ሊቅ) ኢማሙ አህመድ፣ የህያ ኢብኑ መዒን፣ ዐሊይ ኢብኑል መደንይ እና ሌሎችም መፅሐፍን አገላብጠው ፈተሹት። በአግራሞት ተሞሉ። ይህን የመሰለ መፅሀፍ እስከ አሁን እንዳልተፃፈ መሰከሩለት።[185] በየክፍለ ዘመናቱ የመጡ ምሁራንም በክብር ተቀበሉት። ከቁርዓን በኋላም ትክክለኛ የኢስላም ህግጋት የሚቀረፅበት ምንጭ አድርገው ያዙት። ምክኒያቱም የነብዩ ሙሐመድን ሰ.ዐ.ወ. ትክክለኛ ዘገባዎችን ብቻ ያጠናቀረ ግሩም ድርሳን ነውና።

እውቁ የታሪክ፣ የሀዲስ፣ የቁርዓን፣ የስነ-ግጥም ምሁር ዘሀቢ እንዲህ ሲል ውደሳውን ችሯቸዋል፦ "ከእስልምና መፅሐፎች ውስጥ እርሱን የሚያህል የለም። ከቁርኣን በኋላም እንደ እርሱ የተወደደ መፅሐፍ አልተገኘም።"[186]

ኢማሙ አሕመድም "ኹራሳን የቡኻሪ አይነት ልጅ አልወለደችም" ሲሉ አወድሰዋቸዋል። በተመሳሳይ ኢብኑ ኹዘይማህ (እውቅ ኢስላማዊ ሊቅ) እንዲህ ሲሉ ሙገሳቸውን አዝንበውባቸዋል፦ "ከሰማይ በታች የነብዩ

[185] ይህ ውብ ድርሳን - 97 አብይ ክፍሉችንና በስራቸው በርካታ ንዑስ ክፍሉችን የያዘ ነው።
[186] ኢማሙ አዝ-ዘሀቢ - ሲየር አዕላም አን-ነቡላእ
[187] ኢማሙ አሕመድ - ታላቅ ኢስላማዊ ምሁርና በአስልምና ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት ካላቸው አራት መዝሀቦች (School of thought) መካከል የአንዱ መስራች ናቸው።

ሙሐመድ ﷺ ሐዲሶችን ጠንቅቆ የተረዳና በሚገባ የሸመደደ እንደ ቡኻሪ አይነት ፍጡር የለም::"

በዚህ ላይ ቡኻሪ ዛሂድ (ለዓለማዊ ጥቅም ግድ የሌላቸው)፣ አላህን በጣም የሚፈሩ፣ እጃቸውን ላገኙት ሁሉ የሚዘረጉ ቸር፣ ፍርሀት በቀላሉ የማይጠጋቸው ጀግና እንዲሁም የነገስታቶችን በር (ለእርዳታ) የማይረግጡ ክብራቸውን የጠበቁ ሰው ነበሩ::

ቡኻሪ ገና በለጋ እድሜያቸው የቀረፁትን ግብ አሳኩ:: የነብዩ ﷺ ትክክለኛ አስተምህሮቶችን የያዘ ድርሳናቸውን ለዓለም አበረከቱ:: በዚህ ስራቸውም በታሪክ ማንም ሊደርስበት ያልቻለውን ስኬት ተቆናጠጡ::

ቡኻሪ በምድራዊ ቆይታቸው ግባቸውን አስፍረው፣ ለግባቸው ሌት-ተቀን ማስነው፣በመጨረሻም ግባቸውን አሳክተው በ62 ዓመታቸው ዓለምን ተሰናበቱ:: ታላቁን ሰው በማጣታቸው ህዝቡ እንባ ተራጨ:: ለቁጥር የሚታክት ህዝብ በቀብር ስነ-ስርዓቱ ላይ ታደመ:: የታሪክ ምሁራንም በደማቁ ስማቸውን አሰፈሩት:: አላህ ከኒህ የስኬት ተምሳሌት ጋር በጀነት ያገናኘን... አሚን::

ኢማም ቡኻሪ ከራሳቸው በላይ ለሌሎች ኖረው አለፉ:: በህይወት እያሉ 90 ሺህ ተማሪዎች ነበሯቸው:: እንዲሁም እስከ አሁኑ ዘመን ድረስ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች የእርሳቸውን መፅሐፍ ለመለኮታዊ ድንጋጌያቸው አብይ ምንጭ አድርገው ይዘውታል:: አንተስ ቢሊዮኖችን ቀርቶ አንዲትን ነፍስ ታድገሃል? እስኪ ቀጣይዋን ስንኝ መፈክራችን እናድርጋት:-

በአላማ ኑር

አንዲት ፍጡር ካዳንሁ - ባዘን የምትደማ
ናሬያለሁ አላለሁ - ምንም ሳለቅማማ
ውጋት የሰቀዛት - እንዲት ነፍስ አግኝቼ
ከስቃይ ባወጣት - እጆቼን ዘርግቼ
ወይም እንዲት ድንቢጥ - ከመሬት እንሰቼ
ጎጆዋ ባስቀምጥ - አስትንፋስ ዘርቼ
ምንም አላፍርበት
ናሬያለሁ ለማለት[188]

12.2 ሙሐመድ ዩኑስ

የህይወት አጋጣሚ

በምድራዊ ቆይታህ በአንዱ ቀን ተደብቆ የነበረውን ተሰጥኦህን የምትገልጥበት ቀን ይኖራል። በተለይ ማህበረሰቡ ላይ የተፈጠረን ችግር ለመፍታት፤ የሰው ልጆችን ከጥፋት ለመታደግ ውስጥህ በስሜት በነደደ ጊዜ ታላቅ ራዕይ ውስጥህ ይፀነሳል። ሙሐመድ ዩኑስ ባንግላዲሽን ከድህነት ለማውጣት ታላቅ ራዕይ ይዞ ተነሳ። ከእልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ የብዙ ሺህ ሰዎችን ህይወት ታደገ... ዓለም አጨበጨበለት... የኖቤል ተሸላሚ ለመሆን በቃ። ኮቪ ከመሀመድ ዩኑስ ጋር ትንሽ ቆይታ እንዳደረጉ አትተው መፅሐፋቸው ላይ ከትበዋል።

ይህንም ግለሰብ "Find your voice & inspire others to find their voice" "የራስህን እውነተኛ ማንነት ፈልገህ አግኘው። ሌሎችም የህይዎት ጥሪያቸውን እንዲያገኙ አግዛቸው" ለሚለው የመጽሀፍ የአስተሳሰብ መዘውር እንደ ተምሳሌትነት ያወሳዋል። ሙሐመድ ዩኑስ የራሱን የህይወት ጥሪ ፈልጎ ያገኘና የሚሊዮኖችን ህይወት የለወጠ የክፍለ ዘመኑ ታላቅ ሰው ነው።

የኖቤል ተሸላሚው ሙሐመድ ዩኑስ ከ25 ዓመት በፊት በባንግላዲሽ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስ የትምህርት ዘርፍ የተዋጣለት መምህር ነበሩ። የኢኮኖሚክስን ቀመር ለተማሪዎቻቸው ቢያስተምሩም ይህ እውቀት ባንግላዲሽን ከረሀብ ሊታደጋት ባለመቻሉ መማራቸውና ማስተማራቸውን ትርጉም አጥተውበታል።[189]

"ከዩኒቨርሲቲው ዙሪያ ወጥቼ የማያቸው ህልፈተ - ህይወታቸውን የሚጠብቁ ወገኖቼ ሁሌም እረፍት ይነሳኝ ነበር" ሲል የህይወት ተመክሮውን ይጀምርልናል- ሙሐመድ ዩኑስ። እንደ እርግብ ከላይና ከሩቅ ሆኜ የወገኖቼን ሰቆቃ ከምመለከት ታች ወርጄ የማህበረሰቡን የኑሮ ተጨባጭ ሁኔታ ለመረዳትና ቢያንስ አንድ ሰው እንኳን ከሞት ለመታደግ ማድረግ የምችለው ነገር ካለ ለማየት ወደ መንደሮች ጎራ አልኩ።

---

[188] ግጥም - ኤሚሊ ዲክሰን - መንግስቱ ወልደማሪያም እንደተረጎመው
[189] The 8th Habit (from effectiveness to greatness)

እንደመታደል ሆነና ከአንዲት በርጩማ እየሰራች ከምትሸጥ ሴት ጋር ተገናኘሁ። ከእርሷ ጋራ ባደረኩት ቆይታ ብዙ ነገሮችን ተገነዘብኩ። በጨዋታችን መሀል ግን አንድ አስደንጋጭ ዜና አረዳችኝ። የአካባቢው ሰዎች ሙሉ ቀን በርጩማ ሲሰሩ እየዋሉ የሚከፈላቸው 20 ሳንቲም ብቻ ነበር። እንዴት አንድ ሰው እንዲህ የሚያምር በርጩማ ቀኑን ሙሉ ደክሞ ሰርቶ 20 ሳንቲም ይከፈለዋል? ስል በአግራሞትና በሀዘን ተውጬ ጠየኳት። እሷም ፤እኛ በርጩማ የምንሰራበት ቀርከሀ (ሸመል) መግዣ ገንዘብ የለንም። ያለን አማራጭ በርጩማዎቹን ከሚገዙን ነጋዴዎች መበደር ብቻ ነው። እነሱም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ሁለት መስፈርቶችን ይጭኑብናል። አንደኛ ዕቃዎችን የምናስረክበው ለእነሱ ብቻ እንዲሆንና ፤ ሁለተኛ እቃዎችን የምንሸጥላቸው እነሱው ባወጡት የዋጋ ተመን ብቻ እንዲሆን።

ድህነታቸውን በመጠቀም እንደ ባሪያ እየገዟቸው እንደሆነ ተረዳሁ። አስከትዬም አንድ በርጩማ ስንት ይፈጃል ስል ጠየኳት። 25 ሳንቲም ስትል መለሰችልኝ።

ሰዎች 25 ሳንቲም አጥተው ከባርነት በማይሻል ችግር ውስጥ ለመኖር መገደዳቸው እጅጉን አሳዘነኝ።

የለውጡ እርሾ

ለዚህች ሴት 25 ሳንቲም ለመስጠት ከራሴ ጋር ሳወራ ከቆየሁ በኋላ የተሻለ ሀሳብ መጣልኝ። ለምን እንደሷ ያሉትን ችግረኞች ስብስቤ የምችለውን አልረዳቸውም?.... አዎ ይህ ቆንጆ ሀሳብ ነው።

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዬን አስከትዬ ለተወሰኑ ቀናት በመንደሩ ውስጥ እየተዘዋወርን የችግረኞችን ስም ዝርዝር መዘገብን። የስራ ብቃት ያላቸው፤ ነገር ግን 25 ሳንቲም በማጣት በኢኮኖሚ ባርነት ውስጥ የሚኖሩ 42 ግለሰቦችን መዘገብን።

42ቱም የሚያስፈልጋቸውን መጠን ስንደምረው «I got the Biggest shock of my life ... "በህይወቴ ገጥሞኝ ከማላውቀው የድንጋጤ ግምብ ጋር ተላተምኩ።" ጠቅላላ ድምሩ 27 ዶላር ብቻ ነበር። ሀያ ሰባት ዶላር ማውጣት ተስኖኝ ወገኖቼ በችግር ሲማቅቁ እስከዛሬ ዝም ማለቴ

በራሴ ላይ እንዳዝን አደረገኝ።

ከዚህ የተወቃሽነት ስሜት ለመሸሽ ከኪሴ አውጥቼ ለተማሪዬ ብሩን ሰጠሁት። ብሩን ወስዶ ለአርባ ሁለት ግለሰቦች በብድር መልክ እንዲሰጣቸው፤ብድሩንም በፈለጉትና በቻሉበት ጊዜ መመለስ እንደሚችሉና በተጨማሪም የሚሰሯቸውን በርጩማዎች ለሚፈልጉትና ጥሩ ዋጋ ያወጣልናል ብለው ለሚያስቡት ደምበኛ መሸጥ እንደሚችሉ ንገራቸው ብዬ አዘዝኩት። ይህች ብድር ጥሩ መነቃቃትን ፈጠረች።

ብድር ፍሰጋ

የተሰጣቸው ብድር የፈጠረባቸውን ደስታና መነቃቃት ስመለከት ራሴን አንድ ጥያቄ ጠየቅኩ ፤ "አሁን ምን የተሻለ ነገር ማድረግ እችላለሁ?..." እንደ አማራጭ በአካባቢያችን የሚገኘውን ባንክ በብድር ዙሪያ ለማነጋገር ወሰንኩና ወደዛው አቀናሁ።

ለባንኩ ሀላፊ ጉዳዩን በዝርዝር አስረዳሁት። ለእነዚህ ሰዎች የተወሰነ ገንዘብ እንዲያበድራቸው ጠየቅኩት። እሱም አጅግ ተደናግጦ፦ "አብደሃል እንዴ?! ይህ የሚሞከር አይደለም። እንዴት ብለን ነው ገንዘባችንን ምንም መያዣ ንብረት (Collateral) ለሌላቸው ድሆች የምናበድረው? ባንኩ ያስቀመጠውን የተበዳሪነት መስፈርት (Credit worthy) አያሟሉም" ሲል አስረግጦ ነገረኝ።

"እባክህን አንድ እድል ስጣቸው። በዚህ ላይ በጣም ትንሽ ብር ነው።" ስል ተማፀንኩት። "በጭራሽ! ይህ የድርጅታችን ህግ የሚፈቅደው አይደለም። ባንካችን የሚያዝ ንብረት ለሌለው ሰው አያበድርም። በዚህ ላይ ትንሽ መጠን ያለው ገንዘብ ማበደር አዋጭ አይደለም። ትርፉ የወረቀት ኪሳራ ነው።" ሲል ተስፋ አስቆራጭ መልስ ሰጠኝ።

በመጨረሻም ባንግላዲሽ የሚገኙትን የባንኩን የበላይ ሀላፊዎች ባናግር የተሻለ እንደሆነ ጠቆመኝ። ምክሩን ተቀብዬ ወደ እነሱ አቀናሁ። በጣም የሚገርመው የተለዩ ፊቶችን እንጂ የተለየ ሀሳብ ላገኝ አልቻልኩም። ሁሉም ተመሳሳይ መልስ መለሱልኝ። "ድሀን ልናበድር አንችልም።"

ሀላፊነትን መውሰድ

ከቀናት መመላለስ በኋላ አንድ ቁርጥ ውሳኔ ላይ ደረስኩ። እኔው ራሴው የብድሩን ሀላፊነት ለመሸከም ተዘጋጀሁ። ወገኖቼን ለመታደግ እንድፈርም የሚጠይቁኝን ሁሉ ለማድረግ ወሰንኩ።... "Risk taking" የሚባለው ይህ መሆኑን ልብ ይሏል።

የባንኩ ሀላፊዎችም "ይህ ትክክለኛ ውሳኔ አይደለም። ድሆቹ ብድሩን ሊመልሱልህ አይችሉም። እማትወጣበት እዳ ላይ ትወድቃለህ" ሲሉ በተደጋጋሚ መከሩኝ። እኔ ግን የሙከራ እድሉን መጠቀም እንደምፈልግ ፅናቴን አሳየኋቸው። ከባንኩ ያገኘሁትን ብድር ወስጄ ለድሀ ወገኖቼ አከፋፈልኳቸው። በጣም የሚገርመው በየጊዜው ብድራቸውን ይመልሱልኝ ጀመር። በዚህም በጣም ተደሰትኩ። ለባንኩ ስራ አስኪያጅ (ማናጀር) ይህንን ዜና በሀሴት ተሞልቼ ነገርኩት። እሱ ግን ያልጠበኩትን መልስ ሰጠኝ። "እያታለሉህ ነው። አውቀው አዘናግተው ብዙ ብር ከሰጠሀቸው በኋላ አናቅህም ይሉሃል"። ሲል ሊያስጠነቅቀኝ ሞከረ።

ተስፋ አልቆረጥኩም። ተጨማሪ ብድሮች አበደርኳቸው። በሚገርም ሁኔታ ሁሉም ሰርተው ብድራቸውን ከፈሉ። ይህንንም ለባንኩ ስራ አስኪያጅ አሳየሁት። እሱም "ጥሩ ነው። ነገር ግን ከአንድ መንደር ውጭ እንዳትሞክረው። ለሌላ አካባቢዎች ካበደርክ ጉድ ትሆናለህ" አለኝ። በንግግሩ ተስፋ ሳልቆርጥ ወደ ሌላ መንደር ተሸጋገርኩ። ነዋሪዎቿም ብድራቸውን በትክክል እየሰሩ መለሱልኝ።

ይህን ውጤት መሰረት አድርጌ ባንኩ ለአምስት መንደሮች ብድር እንዲሰጠኝ ጠየኩት። ተሳካልኝ። ነዋሪዎችም ብድራቸውን በተገቢው ጊዜ መለሱልኝ። በማስከተል ለአስር መንደሮች አበደርኩ...ይህም የተሳካ ነበር። በማስከተልም በሃምሳ መንደሮች ላይ ሞከርኩት...ውጤቱ አመርቂ ሆነ። በመቀጠልም መቶ መንደሮች ላይ የብድር አገልግሎት ሰጠሁ። ሁሉም እየሰሩ ብድራቸውን መለሱልኝ። ህይወታቸውም መለወጥ ጀመረ። ዳሩ ግን ባንኩ አሁንም አያምናቸውም ነበር። ለነሱ ማበደር ጉም መጨበጥ ነው ብሎ ያምን ነበር። ከኔም ጋር በእያንዳንዱ የብድር ጥያቄ እልህ አስጨራሽ ንትርክ ውስጥ ሁሌ እንገባለን። ለነገሩ በእነርሱ አልፈርድባቸውም ድሀ ለብድር ብቁ (Credit Worthy) አይደለም ተብለው ተምረዋልና። ምኑን ይዘው ገንዘባቸውን ይሰጡታል?!

የግራሚን ባንክ ምስረታ

ባንኩን ለማሳመን የሚደረገው ውጣ ውረድ አድካሚ ስለነበር በነፃነት የብድር አገልግሎት የሚሰጥ ባንክ ለመመስረት ተነሳሁ። ጥናቱን አዘጋጅቼ ለመንግስት አቀረብኩ። መንግስትን ለማሳመን ከሁለት ዓመት በላይ ወሰደብኝ። በመጨረሻም በ1983 ግራሚን ባንክን አቋቋምን። በሂደትም ባንኩን እያስፋፋነው መጣን።

በአሁኑ ሰዓት ግራሚን ባንክ 46,000 የባንግላዲሽ መንደሮች ውስጥ አገልግሎት ይሰጣል። አንድ ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ሰባት (1,267) ቅርንጫፎችን ከፍቷል። 12,000 ሰራተኞች አሉት። እስከ አሁን 4.5 ቢሊየን ዶላር አበድሯል። ባንኩ በየዓመቱ ከአምስት መቶ ሚሊየን ዶላር በላይ የብድር አገልግሎት ይሰጣል። ብድሩም የጎዳና ላይ ለማኞችን ያካትታል። በየዓመቱ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ከሆኑት 3.7 ሚሊየን ህዝብ ውስጥ ዘጠና ስድስት ፐርሰንቱ ሴቶች ናቸው።

ሙሐመድ ዩኑስ የሚሊዮኖችን ህይወት የለወጠ ታላቅ ሰው ስለሆነ አለም አከበረችው። የክብር ኖቤል ተሸላሚ ሆነ። የሀገርና የወገን ፍቅር ላላቸው ሁሉ ተምሳሌታዊ የለውጥ ሀዋሪያ በመሆን በታሪክ ላይ ስሙ ሰፈረ።

ውዷ ሀገራችን ኢትዮጵያ የሙሐመድ ዩኑስ አይነት የለውጥ አርበኞችን ትናፍቃለች። ሁላችንም ለዚህች ሀገር ብልፅግና ቆርጠን ልንነሳ ይገባል። የህዝባችንን ህይወት ለመለወጥ የግድ የመንግስት ወንበር ላይ መቀመጥ የለብንም። ኮቬይ እንደሚለው "Leadership is a choice not a position" አምን መሪነት የለውጥ አራማጅ ለመሆን መወሰን/መምረጥ እንጂ የአመራር ወንበር ላይ መቀመጥ አይደለም። "መሪ መሆን (አመራር) የምርጫ ጉዳይ እንጂ የስልጣን አይደለም"።

የተቃዋሚ ፓለቲካ ፓርቲዎችም በአምስት ዓመት አንዴ ብቅ በማለት ብቻ የወራት የምረጡኝ ዘመቻ በማሰማት መንግስት ስንሆን ችግራችሁን እንቀርፋለን እያሉ መለፈፍ ብቻ አያዋጣም። የሙሐመድ ዩኑስን ገድል ለመድገም የሚያግዳቸው ነገር የለም። በየክልሉ እየተዘዋወሩ ህዝቡ ኑሮውን እንዲያሸንፍ እገዛ ሊያደርጉ ይገባል። ሁሌም ለተፈጠረው ድህነት የመንግስት ፓሊሲ ብቻ ማውገዝ ለህዝብ ቆሜያለሁ የሚል ዜጋ ባህሪ

አይደለም:: የኑሮ ውድነት ንሯል እያሉ ህዝቡን ሰላማዊ ሰልፍ ማስወጣት ብቻውን ትርጉም የለውም:: ኢትዮጵያ ሻማ የሚያበራላት እንጂ ጨለማዋን የሚወቅስ ትውልድ አትፈልግም:: እርግጥ ነው መንግስት ፖሊሲውን እንዲያስተካክል መጠየቁ መልካም ነገር ነው:: ግን በቂ አይደለም::

ሙሐመድ ዩኑስ ድህነትን ከምድረ- ገፅ ለማጥፋት ራዕይ (A vision poverty free world) ሰንቆ ሲነሳ ተጨባጩ ምቹ አልነበረም:: በቁርጠኝነት ተጋፈጣቸው:: ስኬትም ወደሱ አቀናች:: የብዙዎችን ህይወት ለመታደግ በቃ:: የሱን ፈለግ ተከትለው ህዝባቸውን ከድህነት ለማውጣት የተለያዩ ሀገሮች ተንቀሳቀሱ:: ዛሬ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሀገሮች የብድርና ቁጠባን አሰራር በመተግበር ላይ ናቸው::

ኢትዮጵያ ስንት የተማሩ እውቅ ሰዎች አሏት... ዳሩ ግን የእውቀታቸው መዳረሻ ችግርን መውቀስ ብቻ ሆነ:: እንደዚሁም በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይገኛሉ:: ማናቸውም ግን ማህበራዊ አገልግሎት ሲሰጡ አይታዩም:: እስኪ አስቡት የ "X" የእርዳታ ድርጅት የ "A" ፓርቲ የልማትና እርዳታ ክንፍ[190] ቢሆን ምንኛ ህዝብ ልብ ውስጥ ይገቡ ነበር? እንደዚሁም የ "Y" የጽዳት እንቅስቃሴ የ "B" ፓርቲ የማህበራዊ አገልግሎት ክንፍ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ ምንኛ የታደለች ትሆን ነበር? በዕሳት ቃጠሎ ጊዜ ቀድመው ቢገኙ፤ የጎርፉ አደጋ ሲደርስ ፈጥነው ቢደርሱ ህዝቡ የምረጡኝ ዘመቻ ሳያደርጉ ይመርጣቸው ነበር::

ኢትዮጵያን የበለፀገች ማድረግ የሁላችንም ሀላፊነት ነው:: ጎበዝ "ድህነትና ችግር የፈነጨብን ጠንካራ እጆች ለለውጥ ባለመነሳሳታቸው እኮ ነው" በርግጥ ኢድመንድ ይህን ሲል እውነት ብሏል:-

"All that is necessary for the triumph of evil is that good men do nothing" "ተንኮል (ክፋት) ድል እንዲመታ (እንዲያደርግ) የሚያስፈልገው ግብዓት የመልካም ሰብዕናዎች ምንም አለመስራት ብቻ ነው"

[190] ምናልባትም እንደፓርቲ Civic society የማቋቋም ህገ-መንግስታዊ ፍቃድ እንኳን የላቸዉም ካልን፤ እንደ ግለሰብ ግን ሀገርን በመለወጥ ላይ ከመሳተፍና የእርዳታ ድርጅቶችን ከመደገፍ የሚያግዳቸዉ የለም:: እንደ ግለሰብ ፈር - ቀዳጅ የለውጥ ሀሳብ ይዘው ከመውጣት የሚከለክላቸው የለም::

ውዲቷ ሀገራችን የሰጠችንን አገልግሎት ያህል እንኳን ልንከፍላት ይገባል። እኛ አባቶቻችን በገነቡት ጎዳና ባለመጓት መሬት እየኖርን ነው። እኛስ ለመጭው ትውልድ ምን እየሰራን ነው? ሁሌም የምወዳት የቻይናዎች አባባል አለች:- "መልካም ዛፍ ለመትከል ጥሩ ጊዜ የዛሬ ሀያ ዓመት ነበር። የዛሬ ሀያ ዓመት ካልተከሉት ግን ለሚቀጥለው በጣም ጥሩ ቀን ዛሬ ነው"

ስንትና ስንት ሰዎች አሉ ምድር የሰጠቻቸውን አገልግሎት ያልከፈሉ። የተፈጥሮና የአበው ባለዕዳ የሆኑ። እውቁ ‹የክላሲካል ፊዚክስ› አባት፤ ዓለማችን ለደረሰችበት የቴክኖሎጂ እድገት የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው አልበርት አንስታይን ለዓለም ምንም አላበረከትኩም ሲል ይናዘዛል:-

"ሁሌም ራሴን አንድ ነገር አስታውሰዋለሁ ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ የህይወቴ ክፍል የብዙ ሰዎች የላብ ውጤት መሆኑን። ታዲያ ሁሌም የሰጡኝን ግልጋሎት ያህል ለመክፈል እደክማለሁ... ነገር ግን ሁሌም ተገልጋይ ሆኛለሁ"

እውነት ነው። ሰሪዎች እንደሚሰሩ አይሰማቸውም። እኛ ደግሞ ለምድር ብዙ እንዳበረከትን እናስባለን። "ለዚህች ምድር አንዳች ነገር መጨመር ካልቻልክ አንተ ጭማሪ ነህ" ይለናል ሙስጠፋ ራፊዒ። "ከሀገርህ ላይ አንዳችን ሸክም ካላነሳህ በሀገርህ ላይ ሸክም ነህ" እያሉን ነው።

የመኖራችንም ትርጉም ለሰው ልጆች የተሻለ ህይወት መልካምን ማበርከት ነው። በህዝቡ ህይወት ላይ አይነተኛ ለውጥ መፍጠር መታደል ነው። እስኪ ወጣቶች ይህችን ንግግር አዚሟት:-

"I am not here just to make a living, I am here to make a difference"

"እኔ ምድር ላይ የምኖረው ለመብላትና ለመጠጣት ሳይሆን ለውጥ ለማምጣት ነው"

ይህ በርግጥ ትልቅ አባባል ነው። ለሰው ልጅ አዲስ ነገር ያላበረከትንበት ህይወት ትርጉም የለውም። አዲስ ለውጥ ያላስመዘገብንበት ኑሮ ጥፍጥና የለውም። ሁላችንም እናት ኢትዮጵያን ለማስዋብ እንነሳ።

እንካችሁ ይህችን ስንኝ ለናሙና

The secret of living is Giving

I sit in solitude
And contemplate life
I marvel at nature,
I cry at strife,
I ask "what can be done
By only one mind?
The answer comes back
"A goal you must find"
So a goal I must find
One bigger than me.
I decide to give-thoughts
To help humanity.
It is hope I send out
So that all can see,
We are what we are
But we can be what we can be.
So —look up and look out
Give what we can give.
It's your special blessing
Helping others to live.

ታላቁ መልዕክተኛ

አሁን ደግሞ ምድርን ከረገጡ ፍጡራን ሁሉ የበላይና የሰው ልጆች ሁሉ የስኬት ተምሳሌት ስለሆኑት አንድ ሰው አስነብብሃለሁ። ያኔ አለም በዕልመት ተሞልታ እያለ ብቻቸውን በያዙት መለኮታዊ ብርሃን ምድርን ሊያደምቁ ስለተጉ ታላቅ ሰብዕና አወሳልሀለሁ። የሰዉ ልጆችን ፍጡርን ከማምለክ የሰዉ ልጆችን ፈጣሪ ወደማምለክ፡ከዚህች ዓለም ጥበት ወደ ቀጣዩ ዓለም ሰፋት፡ ሌሎች ስርዓቶችና አመለካከቶች ከመጡት በደል ወደ ኢስላም ፍትህ ለማሸጋገር ሲማስኑ ትመለከታቸዋለህ። የአባታቸዉ የኢብራሂም ፋና ዳግም አንዲያበራ አንዲሁም የወንድሞቻቸዉ የሙሴና የኢየሱስ (ዐ.ሰ) አስተምህሮት ዳግም አንዲያብብ ደፋቀና ሲሉ ታያቸዋለህ።

ይዘውት የተነሱት የመለኮታዊ ብርሃን አድማሱ ላይ ሲፈነጥቅ፡ የሰው ልጆች ካጠለላቸው ዕልመት አንዴት አንደወጡና ለከፍለ ዘመናት የተከረቸሙ የህይወት በሮች በእምነት (ኢማን) ቁልፎች እንዴት አንደተከፈቱ እንመለከታለን።

12.3 ታላቁ መልዕክተኛ ﷺ

ብዙ ዘመን ገና

ግርማ ሞገስ ያለው - አጅግ የሚያኮራ
በእጅ ያልተቀረፀ - በሰው ያልተሰራ
ከሶቅራጥስ ሀውልት - በቁመት የለቀ
በአሰራሩም ቢሆን - ይበልጥ የረቀቀ
ሃውልት[191] አቁሜያለሁ - ለመታሰቢያህ
ለሚመጣው ትውልድ - ለወደ ኋላህ
ወደዚህም ሰፍራ - ሰዎች ይመጣሉ
የሐውልቱን መንገድ - እየተከተሉ
የማይፈርሰውና - የማይበሰብሰው
ረቂቅ መንፈስህም - ሰጋ የለበሰው
አንደ መሰንቆ ምት - ወይ አንደበገና
ይኖራል ወደፊት - ብዙ ዘመን ገና[192]

---

[191] ምናባዊ ሀውልት ለማለት ነው። ሀውልት በኢስላም ያልተፈቀደ መሆኑን ልብ ይሏል።

[192] 2005 ዓ.ል አጥቢያ ላይ ታሊቲ ማረሚያ ቤት ዞን ሁለት ውስጥ ለተወሰኑ ወራት ታስራያለሁ። በቆይታችን ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነት ነበረን። መንግስት የእኛን ስም የማጥፋት ዘመቻ ቢከፍትም የታራሚውን ልብ ሊገዛ አልቻለም። ይልቁንም ለእኛ ያላቸው ክብር የላቀ ሆነ። ከዚሁ ዞን ከተዋወኋቸው የእስር ቤት ባልደረባዎቼ ውስጥ ደራሲና ጋዜጠኛ አበበ ተክላ (ታሪኩ) አንዱ ነበር። የእቤ ቶክቻዉ የቅርብ ወዳጅ እንደሆነ አጫውተኛል። ታዲያ አንዱ ይህችን ግጥም ከሌላ ግጥም ጋር አድርጎ ማስታወሻ ሰጠን። ስንለካት ሰፋችን። ቁመቷም እንደረዘመን አስተዋልን። ለነብያችን መሐመድ ﷺ አደረግናት። እናውቃለን! ግጥሟም ቢሆን ያንን ታላቅ ስብዕና ለመግለፅ አትም እንደሌላት።

Lead Like Prophets - እንደ መልዕክተኞቹ ምራ

የነብያትን የአመራር ጥበብ የሚተነትኑ በርካታ መፅሐፍት ለንባብ በቅተዋል። "Lead Like Jesus " "እንደ ኢየሱስ ምራ"፣ "Lead Like Moses" "እንደ ሙሴ ምራ"... የሚሉት መፅሐፍት ይጠቀሳሉ። ነብያት መለኮታዊውን መመሪያ በመከተል ስለሚመሩ፣ ትክክለኛ የአመራር ጥበብ ከእነሱ ነው የሚቀዳው። የመጨረሻው የሰው ልጆች የፈጣሪ መልዕክተኛ የሆኑት ነብዩ ሙሐመድም ﷺ የሙሴንና የእየሱስን ዐ.ሰ. የአመራር ጥበብ ገቢራዊ አድርገውና የሁለት ዓለምን ስኬት ተቆናጠው ምድርን ተሻግረዋል። " The 100 Ranking of the most Influential persons in History" በተሰኘ ድንቅ መፅሐፉ እውቁ የታሪክ ተመራማሪ Micheal Hart[193] ስለ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ የስኬት ጉዞ በስፋት አስነብቦናል። በዚህም መፅሐፍ ውስጥ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ አለም ላይ ታላቅ ተፅዕኖ ፈጥረው ካለፉት 100 ግለሰቦች ውስጥ ነብዩ መሐመድን ﷺ በአንደኝነት አስፍሮ እናገኘዋለን። የስኬት ተምሳሌቶች በሚለው ምዕራፍ ውስጥ የመካተታቸውም ሚስጥር ይህ ነው። የሰው ልጆች ከስኬት ጉዟቸው አስተምህሮትን እንዲወስዱ ለማመላከት።

"Muhammed solves All problems (of the world) the ease of drinking coffee" Bernard Shaw

የአላህ መልዕተኛ ﷺ የሰው ልጆች ሁሉ ተምሳሌት ናቸው። ንግግራቸውም ሆነ ድርጊታቸው የመለኮታዊው መመሪያ ነፀብራቆች ናቸው። ሁለንተናዊ የህይወት ገፅታቸውን ለመዳሰስ በርካታ ቅፆች ያስፈልጋሉ። በዚህ ክፍል ውስጥ አንድ የህይወት ገፅታቸውን ብቻ በወፍ በረር ለማውሳት ተሞክሯል። እሱም የማህበረሰብ መሰረት የሆነውን ግለሰብ በማነፅ ላይ ያደረጉትን የዳዕዋ (ስበካ) ጉዞ በትንሹ ያወሳል።

በመሆኑም የገነቡትን ኢስላማዊ ስልጣኔ፣ የዓለምን የታሪክ ሂደት በመቀየር ላይ የተጫወቱትን ሚና፣ ለሰው ልጆች መንፈሳዊም ሆነ አለማዊ ህይወት ያበረከቱትን ወደር የለሽ አስተዋፅኦ፣ የአረቢያን ዘላን

[193] Micheal Hart – The 100 Ranking of the most Influential persons in History (Golden Book Center – 1979)

ትውልድ ከግመል መሪነት ወደ አለም አስተዳዳሪነት ለመለወጥ የተጠቀሙበትን የአመራር ጥበብ (Leadership Wisdom)... ለማውሳት አልተሞከረም።

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ የስኬት ተምሳሌቶችን ስንዘክር ታላቁን ቡኻሪን ማውሳታችን ይታወሳል። አስገራሚ የስኬት ጉዟቸውንም አይተናል። የታላቁን መልዕክተኛ ﷺ ሀዲሶችን በአንድ ጥራዝ በመሰብሰብ በታሪክ አምድ ደምቀው የሰፈሩበትን ስኬት ተመልክተናል።

ይህ የቡኻሪ ልቅና የተመዘዘው የእኒህን ታላቅ ነብይ ንግግር በመሰብሰብ ከሆነ፤ እኒያ ሀዲሳቸው (ንግግራቸው) እንዲህ ተደክሞ የተመዘገበላቸው ታላቅ ሰው ልቅና ምን ያህል የመጠቀ እንደሆነ ልብ ይሏል።

12.3.1 ነብዩ ሙሐመድ ﷺ ወደ ሰው ልጆች ከመላካቸው በፊት

ዓለም ከነብዩ ﷺ በፊት በጃሂልያ[194] የተሞላች ነበረች። የሰው ልጅ ሀሊናው የሻገተበት፤ መንፈሱ የጠለሸበት፤ እሴቶቹና መስፈርቶቹ የተሳከሩበት፤ ግፍና ባርነት የነገሱበት ሁኔታ ነበር። ዓለም በአንድ በኩል መረን የለቀቀ ቅንጦት፤ በሌላ በኩል ደግሞ አሰቃቂ ድህነት አይሎባት ነበር። ሰማያዊ ሃይማኖቶች የነበሩ ቢሆንም መሰረታዊ ባህሪያቸው ስለተለወጠ፤ ስለተበረዙና ስለተከለሱ እንዲሁም በድክመት ስለተጠቁና በነፍሶች ላይ የነበራቸውን ስልጣን አጥተው መንፈስ አልባ የአምልኮ ክንውኖች (rituals and symbols) በመሆናቸው ሳቢያ ክህደት፤ጥመትና ጽልመት ዓለምን እንደ ብርድ ልብስ ሸፍነዋት ነበር[195]።

ያ ዘመን (ልክ እንደ አሁኑ የ21ኛው ክፍለዘመን "የስልጣኔ" ና የሳይንሳዊ ድንቁርና (Scentific Ignorace) ሁሉ በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን የፅልመት ዘመን እንደሚወክል ይታመናል። የሰው ዘር ለምዕተ-ዓመታት ሲነጉድበት ወደኖረው የገደል አፋፍ የደረሰ ይመስላል። ከፊት ለፊቱ ስልና ዥው ያለ ገደል ተጋርጦበት ነበር።

[194] ጃሂልያ - ከመለኮታዊው አስተሳሰብ፤ የኑሮ ዘይቤ የወጣ ሁሉ ጃሂልያ (ድንቁርና) ይባላል። ድሮስ ሰሰዉ ልጅ ፈጣሪዉ ካስተመጠለት የኑሮ ዘይቤ ከማፈንገጥ በላይ ምን ድንቁርና አለ።

[195] Islam and the world — Pro.Nadwi, foreword by sayid Qutb

በዚህ እንቦርቦስ ውስጥ ተንኮታክቶ ሊጠፋ ወደፊት ይገፋ ይሄል[196]። የሞራላዊና የመንፈሳዊ ድልብ ንቅዘቱን በወቅቱ የነበሩት ሰማያዊ ሀይማኖቶች (Heavenly Religions) ሊያክሙት አልቻሉም።

ያኔ የሰው ልጅ ለምድራዊ ወኪልነትና መሪነት ያበቃውን ሰብዓዊ ማንነት አጥቶ፣ የድንቁርናው ስርዓት አስተሳሰብ (ጃሂልያ) ባሳደረበት አሉታዊ ተፅዕኖ ሳቢያ የህሊና ሚዛኑን ስቶ፣ ውሸትን እንደ እውነት ይመለከት ነበር። "ያልበደለ ይበደላል" የሚል መርህን አንግቦ፣ ሳይቀደም ይበድልና ኢ-ፍትሀዊ ይሆን ነበር።

አዎ! ህይወት በአጠቃላይ የተወሳሰበ እንቆቅልሽ፣ የተዘጋ በር ነበረች። አእምሮ ተቆልፏል፤ ፈላስፎችና ጥበበኞች ሊከፍቱት ተስኗቸዋል። ህሊናም ተቆልፏል። ሰባኪያንና መካሪዎች (የመንፈስ አባቶች) መክፈት አቅቷቸዋል። ልቦናዎች ተቆልፈዋል። ክስተቶችና ተአምራት ሊከፍቷቸው ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። ክህሎቶች ተቆልፈዋል። ትምህርት፣ አካባቢና ማህበረሰብ ሊከፍቷቸው ተስኗቸዋል። የትምህርት ማዕከላት ተቆልፈዋል። መምህራንና አዋቂዎች ሊከፍቷቸው ቢሞክሩም ድካማቸው ከንቱ ቀርቷል። ፍርድ ቤቶች ተቆልፈዋል። የፍትህ ፈላጊዎችና ናፋቂዎች ደጅ መጥናት ሊከፍቷቸው አልቻሉም። ቤተሰቦች ተቆልፈዋል። ምሁራንና የማህበረሰብ ሳይንስ አዋቂዎች ሊከፍቷቸው ተስኗቸዋል። የንጉሣን ቤተ-መንግስቶች ተቆልፈዋል። የተበደለ ህዝብ፣ የተረገጡ ጭሰኞች እና የተሰቃዩ ሰራተኞች ሊከፍቷቸው ተስኗቸዋል። የባለሀብቶችና የገዥዎች ካዝናዎች ተቆልፈው ነበር። የድሆች ረሐብ፣ የሴቶች ሰቆቃ፣ የህፃናት ዋይታ... ሊከፍቷቸው አልቻሉም።

ታላላቅ የተሀድሶ ሰዎችና ምሁራን እነዚህን ቁልፎች ለመክፈት ለዘመናት ታግለው አልሆነላቸውም። ምክንያቱም ቁልፍ ያለመፍቻ አይከፈትም። መፍቻውን ደግሞ ካጠፉት ክፍለ ዘመናት አልፈዋል። ራሳቸው በሰሯቸው ሌሎች መፍቻዎች ሊከፍቷቸው ታገሉ። ከቁልፎቹ ጋር የማይገጥሙ በመሆናቸው ምንም አልፈየዱም። እነዚህን ቁልፎች ሊሰብሩ የሞከሩም ነበሩ። ግን የራሳቸውን እጅ አቆሰሉ። መሳሪያዎቻቸውን ሰበሩ እንጂ ያገኙት ውጤት የለም[197]።

---

[196] Mile Stone — By sayid Qutb , ኢስላም- የማህበራዊ ችግሮች መፍትሄ (ነጃሺ ማተሚያ ቤት 1989)

[197] Islam and the world —By pro.Nadawi,

12.3.2 የኢስላም ፀሐይ ከአድማሱ ላይ ሲፈነጥቅ

ያኔ የሰው ልጅ ከገባበት ፅልመት የሚያወጣው ይመጣ ዘንድ አንጋጦ እየጠበቀ ነበር። ከገባበት የተሳከረ ህይወት የሚያድነው ይላክለት ዘንድ በጉጉት መጠበቁን ይሂል። ነብዩ ሙሐመድ ﷺ በነብይነት ዋዜማቸው ከመካ ቅርብ ርቀት አካባቢ አንድ ተራራ ውስጥ ከሚገኝ ሂራ ከተባለ ዋሻ ብቻቸውን ከሰው ተገልለው በአባታቸው ኢብራሂም (ዐ.ሰ) የአምልኮ ስርዓት መሰረት አላህን ይገዙ ነበር። ቁጭ ብለውም ስለዓለም፣ ስለሰው ልጅች መር-የለሽ ህይወት... ያስተነትኑ ነበር።

ታዲያ በዚህ አልባሌ ስፍራ፣ ከሰለጠነው ዓለም በራቀ ክልል፣ እምብዛም ትልቅ ባልሆነ ተራራ ላይ፣ በታላላቅ የአለም ከተሞች፣ በግዙፍ የጥናት ማዕከሎችና ቤተ-መፅሐፍት ያልተፈፀመ ተአምር ተፈፀመ።

እዚህ ቦታ ላይ ፈጣሪ ሙሐመድን ﷺ ለሰው ልጅች በመላክ ታላቅ ውለታ ዋለ። በእርሳቸው መላክ ያ ጠፍቶ የነበረው ኢማን (በአላህ፣ በመልዕክተኛውና በመጭው ዓለም ማመን) የተሰኘው መክፈቻ ወደ ሰው ልጅች ተመለሰ።

የመልዕክተኛው ﷺ የህይወት ግብ

ነብዩ ሙሐመድ ﷺ የህይወት ግባቸውን፣ በምድራዊ ቆይታቸው ሊያሳኩት የሚጠበቅባቸውን ተልዕኮ፣ የህይወት አላማቸው ከአላህ ነበር የተሰጣቸው። አላህ ከሰው ልጅች ሁሉ መርጦ የሰው ልጅችን ከጥፋት ለመታደግ የተላኩበትን አላማ እንዲህ ሲል ይነግራቸዋል፦

"(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጂ አላክንህም።"[198]

አዎ! የተላኩት ለአለም እዝነት ሊሆኑ ነው። የሰው ልጅ ከገባበት አዘቅት ውስጥ ሊያወጡት ነው። ሰማዩን ያጠለለውን ጥቁር የግፍ ደመና ሊገፉ ነው። የአደምን ልጅ በአጠቃላይ ፍጡርን ከማምለክ አላህን ብቻ ወደማምለክ ለመመለስ ነው። ይህ ግዙፍ ዓላማ ነው።

[198] ቁርአን 21 : 107

ለአለም ህዝቦችም እንዲህ ብለው እንዲያውጁ አላህ አዟቸዋል፦

(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፦ "እናንተ ሰዎች ሆይ እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የተላክሁ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ፤ (አርሱም) ያ የሰማያትና የምድር ንግስና ለርሱ ብቻ የኾነ ነው፤ አርሱ አንጂ ሌላ አምላክ የለም፤ (አርሱም) ሀያው ያደርጋል፣ ይገድላልም። በአላህ፣ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይፅፍና የማያነብ ነቢይ በኾነው መልዕክተኛ አመኑ፤ ቅኑንም መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት።"[199]

ወደርሳቸው የተወረደውን መለኮታዊ መመሪያና መልዕክቱን ይዘው የመጡትን ታላቅ ነብይ እንዲህ ሲል አላህ ያስተዋውቀናል፦

"እናንተ ሰዎች ሆይ! ከጌታችሁ ዘንድ በእርግጥ አስረጅ መጣላችሁ፤ ወደ እናንተም ገላጭ የኾነን ብርሃን (ቁርአንን) አወረድን"።[200]

አዎ! ብርሃኑ ወደናንተ መጥቷል። ካላችሁበት ፅልመት፣ ከተከበባችሁበት ውድቀት የሚያወጣችሁ መመሪያ ወደ እናንተ ወርዷል።

በዚህ የነብይነት አጥቢያ ሁለት መሰረታዊ ትዕዛዝን ተቀበሉ። በመጀመሪያ በራሳቸው ላይ ድልን እንዲቀዳጁ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሌሎችን ወደ ቅናቻ መምራት።

[199] ቁርአን 7 : 158
[200] ቁርአን 4 : 174

12.3.3 የጉዞው ጅማሮ

ታላቁ መልዕክተኛ ﷺ ነብይ በሆኑ ማግስት በ10 ቀናት ልዩነት ከባድ መመሪያና ትዕዛዝ ተሰጣቸው። ትዕዛዙ ታላቅና ከባድ መልዕክት ነበር። የአላህን መልዕክተኛ ﷺ ከተመቸ ቤት አውጥቶ፣ ከሞቀ ፍራሽ አላቆ ወደ ሰው ልጆች የውስጣዊና የውጫዊ ዓለም ትርምስ እና ምስቅልቅል የወረወረ መልዕክት ነበር። መልዕክቱም እንዲህ ይነበባል፦

> "አንተ ተከናናቢው ሆይ! ተነሳ አስጠንቅቅ። ጌታህን አክብር። ልብስህንም አጥራ። ጣኦትንም ራቅ። ማብዛትንም የምትፈልግ ኾነህ (ለውለታህ ምላሽ በመከጀል) አትለግስ፣ ለጌታህም (ትዕዛዝ) ታገስ።"[201]

ይህ ነበር መልዕክቱ "ተነስና አስጠንቅቅ"። የጌታህን መመሪያ ለሰው ልጆች አስተምር። የሰውን ልጅ ከገባበት ዕልመት አውጣ። የውጭም የውስጥም ሰላም አጥተው እየተንገላቱ ነውና ታደጋቸው። ተነስ!

"ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ይህን መልዕክት ተቀብለው ተነሱ። ለ23 ዓመታትም እንደቆሙ ቀጠሉ። ከዚህ መልዕክት በኋላ አላረፉም። አካላዊ መረጋጋት ያለው ህይወት አልመሩም። ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ብቻ አልኖሩም። ወደ አላህ በመጥራት ተጠመዱ። ታላቅ ኃላፊነት ተሸከሙ። በዚህች ምድር ላይ ግዙፉን ኃላፊነት። የሰው ልጆችን ሁሉ የደህንነት ሽክም፣ የእምነትን ሽክም፣ በብዙ መስኮች የሚደረግን ትግል ሽክም። በዕኩና ረፍት የለሽ ትግል ውስጥ 23 ዓመታት ያህል ቆዩ። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ ምንም ነገር ከትግል አላዘናጋቸውም። ለሰው ልጆች ለዋሉት ውለታ አላህ ምንዳቸውን ይለግሳቸው።"[202]

---

[201] ቁርአን 74 : 1-7

[202] ሰይድ ቁጥብ - ፊዚላሊል ቁርአን. (ሰይፉን ፍለጋ- ሐሰን ታጁ ገፅ - 44)

የግለሰቦች እነዓ

መልዕክተኛው ﷺ የታዘዙትን መልዕክት በይፋ ለማድረስ ሲነሱ፣ አንድን ነገር በግልፅ ተመለከቱ። ይህ የተበላሸው ማህበረሰብ የግለሰቦች ጥርቅም ውጤት ነው። የግለሰቦች ስብስብ ማህበረሰብን ይወልዳል። የችግሩም ምንጭ ያለው ከግለሰቦች ነው።

አዎ! የችግሮች ሁሉ ዋነኛው መነሻ የህብረተሰቡ መሰረት የሆነው ግለሰብ ነው። ይህ ግለሰብ በቁስና በሐይል እንጂ የማያምን፣ ስለራሱ እንጂ የማያስብ፣ ስሜቱን የሚያሳድድ ሆኖ አገኙት። በእርሱና በአምላኩ፣ በቀደምት ነብያት መልእክትና በመጭው ዓለም በማመን መካከል ያለው አገናኝ ድልድይ ተደርምሶ ተመለከቱት።

የጃሂልያው ማህበረሰብ ስቃይና መከራ ምንጭ ግለሰብ መሆኑን አስተዋሉ። ነጋደው ስግብግብ፣ ሸቀጦችን አከማችቶ እጥረት የሚፈጥር፣ በርካሽ ሰብስቦ በውድ ለመሸጥ የሚቋምጥ፣ ለረሀብና ለችግር ምክንያት የሚሆን ነበር። ድሃውም አመፀኛ፣ የሌሎችን ድካም ያለ ልፋት መቀማት የሚሻ ነበር። ሰራተኛውም ያልታመነ፣ መብቱን የሚጠይቅ፣ ግዴታውን የማይወጣ ነበር። ሐብታሙ ስስታምና ጨካኝ ነበር። ለድሆች የማያዝን፣ ለምንዱባን የማይራራ፣ ለተራቡ የማያጎርስ፣ ለታረዙ የማያለብስ ነበር።

ገዥው ግለሰብ ቀማኛ፣ አሰሪው በዝባዥ ነበር። ስለራሱ ትርፍና ረፍት እንጂ ስለ ቀጠራቸው ሰራተኞች እንግልት አያስብም። ተቀጣሪው ደካማና አጭበርባሪ ነበር። ንብረት ያዥውም አደራውን የማይወጣ ሌባ ነበር። ሚኒስትሩ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ፕሬዝዳንቱ ቁስ አምላኪና ራስ ወዳድ ነበር። ራሱንና ደጋፊውን እንጂ አያገለግልም። መሪው ጎስኛ ወይም ብሔርተኛ ነበር። አገሩን ወይም ዘሩን ያመልካል። የሌሎች ሐገሮችና ጎሳዎችን እንዲሁም የሌሎች ሀይማኖቶችን ክብርና ነፃነት ማን ይጨፈልቃል። ሕግ አውጭው ግለሰብ በዳይ ህግጋት የሚቀርፅ፣ የሚያማቅቁ ግብሮችን የሚጥል ነበር።

በእንዲህ ዓይነቱ ግለሰቦች ሕብረተሰቡ እንደተገነባ፣ የመንግስት ስርዓቱም በዚህ መልኩ እንደታነፀ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ አስተዋሉ። እናም የነጋደው ራስ ወዳድነት፣ የድሃው ቀማኛነት፣ የሰራተኛው አጭበርባሪነት፣ የሐብታሙ ስስት፣ የገዥው አታላይነት፣ የቀጣሪው አምባገነንነት፣

የተቀጣሪው ክሕደት፣የንብረት ጠባቂው ሌብነት፣ የመሳፍንቱ ራስ ወዳድነት፣ የመሪው ዘውገኛነት፣ የሕግ አስፈፃሚው ርህራሄ የጎደለው... መሆን የሚገርም አልነበረም። ይህን የህብረተሰብ መሰረት የሆነውን ግለሰብ ለማነፅ በአጭሩ ታጥቀው ተነሱ - የአላህ መልዕክተኛ ﷺ።

ጉዞ ወደ አላማ

ከክፍለ ዘመናት በፊት አንድ ታላቅ ሰው በአላህ ተመርጦ የሰው ልጆችን ህይወት በአዲስ መልክ ሲያንፅ እናገኘዋለን። ይህ የህይወት ተሀድሶ እንቅስቃሴ በፈጣሪው ፍፁማዊ አንድነት፣በቀጣዩ የአኼራ (የመጭው ዓለም) ህይወት መኖርና፣ የአላህ መልዕክተኞች ለሰው ልጆች ባደረሷቸው መለኮታዊ ትዕዛዛትና መመሪያዎች ላይ ያተኮረ ነው። እኚህ ታላቅ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ኢስላምን በመካ ለ13 ዓመታት አስተምረዋል። የመካ ቆይታቸው ፈታኝና እልህ አስጨራሽ ነበር። ተልዕኳቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ያደረጋቸውም ኢስላም ለመፍጠር የሚፈልገው የተዋጣለት ኢስላማዊ ስብዕና ባለቤት መሆናቸው ነበር። የመጠቀ አስተሳሰብ፣ የላቀ ባህሪ የተላበሱ፣ ከራስ ወዳድነት የፀዱ፣ለሰብዓዊ ፍጡራን ሁሉ የሚራሩና መስዋዕት ሊሆኑም የተዘጋጁ ነበሩ - መልእክተኛው ﷺ። በአጭሩ አንድ አላህን የሚገዛና የሚታዘዝ አማኝ ሰው ሊኖረው የሚገባው ምሉእ ኢስላማዊ ስብእና ነበራቸው። የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ያስተማሩትን ኖረውታል። ህይወታቸው ራሱ አስተማሪ ነበር። ለሙስሊሙም ሆነ ለሌሎች ህዝቦች የህይወትና የስኬት አርአያ ናቸው።[203]

12.3.4 ለስኬት የተከፈለ ዋጋ

እኚህ ታላቅ ሰው መልዕክቱን አንግበው ሲነሱ የመካ መሳፍንቶች መንገዱ ላይ በመቆም ሁለንተናዊ ጦርነት ከፈቱባቸው። እንደ መጀመሪያ የስነልቦና ጦርነት አራመዱ። ይዘውት የመጡት መልዕክት (ቁርዓን) ተረት፣የቀደምት ህዝቦች አፈ-ታሪክ፣ከሌሎች የተማረው ነው የሚል ፕሮፓጋንዳ በመክፈት ዘመቻ ጀመሩ። እንዲህም ማለታቸውን መለኮታዊው መፅሐፍ

[203] Islam today - አቡልአዕላ አልመውዱዲ

ዘግቦታል፡-

"የመጀመሪያዎቹ (የጥንት) ሰዎች ተረቶች ናት። አስፃፋት (አሰከተባት)።
እርሷም በእርሱ ላይ ሚትና ማታ ትነበብበታለች።"[204]

እንዲህም ሲሉ ተናገሩ፡-

"ይህ (ቁርአን፣ ሙሐመድ) የቀጠፈው በእርሱም ላይ ሌሎች ህዝቦች ያገዙት
የኾነ ውሸት እንጂ ሌላ አይደለም።"[205]

ከዚሁ ጎን ለጎን የመልዕክተኛውን ﷺ መልዕክት ብቻ ሳይሆን የግል ስብዕናቸውን ማውገዝ ተልዕኳቸውን ለማዳከም፣ ጉዟቸውን ለመግታት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ስለገመቱ፣ ትናንት "ታማኙ ሙሐመድ" እንዳላሉዋቸው ሁሉ አሁን ደግሞ ስማቸውን ማጥፋት ተያያዙት። እብድ፣ ደጋሚ፣ ውሸታም፣ ሀሳዊ... የሚሉ ፀያፍ ስድቦችን ያሰሙ ጀመር። ይህም ትችታቸው በቁርዓን ተዘግቧል፡-

"አንተ ያ በእርሱ ላይ ቁርአን የተወረደበት ሆይ! አንተ በእርግጥ እብድ ነህ።"
አሉ።[206]

ድግምትን ከምድረ ገፅ ሊያጠፋ የተላከውን መልዕክተኛ፣ ውሸትን ገፍፎ እውነትን ሊያስተምር የመጣውን የአላህ ነብይ እንዲህ ሲሉ አወገዙት፡-

---

[204] ቁርአን 25 : 5
[205] ቁርአን 25 : 4
[206] ቁርአን 15 : 6

ከየቦታው አፀያፊ ቃላትን እየመዘዙ መልዕክተኛውን ለማውገዝ ተገለገሉበት። ትችታቸው መልዕክተኛውን ዕናትን፣ ውግዘታቸው ብርታትን እንጂ አልጨመሩላቸውም።

የመካ መሳፍንቶች ትግል በመጀመሪያው፣ ግለትም የስነ-ልቦና እና የአእምሮ ጦርነት የሚቆም አልነበረም። ምክንያቱም ጦርነቱን በበላይነት የሚመራው ሰይጣን ስለሆነ፣ ጦርነቱ ዘልዐለማዊ ነው።

መልዕክተኛው ﷺ ይህን ሁሉ መስናክል አልፈው ግባቸውን ጥግ ለማድረስ ጣሩ። "ዳሩል አርቀም" በተሰኘ ቤት ውስጥ ግለሰቦችን በድብቅ መኮትኮቱን ተያያዙት። ከእርሳቸው ሙሉ ስብዕና፣ ከመልዕክቱ ምሉዕነት ጋር ተዳምሮ በአላህ ድጋፍ የተወሰኑ ግን ሁነኛ ሰዎችን በስራቸው አደረጉ። እነዚህ ጥቂት ግለሰቦች ከሰፊው የመካ ማህበረሰብ አንፃር እጅግ አናሳ ቢሆኑም ኢስላምን የተቀበሉት የመልዕክቱን እውነተኛነት አረጋግጠው ስለነበር ሙሉ ህይወታቸውን ለኢስላም በማዋል የህዝቡን መንፈሳዊና ሞራላዊ እድገት ያቀሸሸውን ጃሂልያ ለማስወገድ የቆረጡ ነበሩ።

"ግና ይህ ኢስላማዊ ትውልድ በቀላሉ የተገኘ አልነበረም። ከፍተኛ መስዋእትነት ተከፍሎበታል። የዚህ ትውልድ አባላት አዲስ ላገኙዋቸው ኢስላማዊ እሴቶች ህልውና አያሌ መከራና ስቃይን ተጎንጭተዋል። ይሁን እንጂ የጃሂልያው ስርዓት ላደረሰባቸው እንግልት አንደኛም ተስፋ አልቆረጡም፣ አልተምበረከኩም፣ አላፈገፈጉም ወይም አላጎበደዱም። ሁሉንም መከራ በደስታ፣ በድፍረትና በትዕግስት ተቀበሉ።"

የአላህን መልዕክተኛ ﷺ የተከተሉት ገሚሶቹ ከዝቅተኛው የህብረተሰብ ክፍል የተገኙ ስለሆኑ በአቅመቢስነታቸው ሳቢያ ከፍተኛ ስቃይ ደርሶባቸዋል። ከነዚህ ውስጥ በጥቂቱ፦

ከፍተኛ ግፍ

የዑመይር ልጅ ሙስዐብ የተከበረ፣ የመካ ወጣቶች እንደርሱ ለመሆን የሚመኙት ውብ ወጣት ነበር። ይህ ውብ ወጣት ውቡን ህይማኖት በመቀበሉ እንዲህ ሆነ፦ "የሙስዐብ ቢን ዑመይር እናት መስለሙን

[207] Islam today - አቡልአላ አልመዉዱዲ

ስትሰማ በረሃብ ቀጣችው። ከቤቷም አባረረችው። በቅንጦት የሚኖር ልጅ ስለነበረ፣ ከአንግልት ብዛት ቆዳው ልክ እንደ እባብ ቆዳ ተሰነጣጥቆ ነበር።"[208]

አቡ ጀህል (የመካ ዋና ባላባት) ክብርና ልቅና ያለው ሰው መስለሙን ሲሰማ ሌሎችን በእርሱ ላይ ለአመፅ ያነሳሳበታል። ያዋርደዋል። ይነቅፈዋል። ከፍተኛ የገንዘብ ኪሳራ እንደሚያጋጥመውም በማስጠንቀቅ ያሸማቅቀዋል።"[209]

ይህ እንግዲህ የተከበረ የማህበረሰብ ክፍል ሲሰልም የሚወስዱት እርምጃ ነው። በአንዳሩ ተርታው ህዝብ ውስጥ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ ቅጣትና እንግልት ይደርስበት ነበር።

ኢትዮጵያዊውን ቢላል አሳዳሪው ኡመያህ ከአንገቱ ላይ ገመድ አስሮ ለህፃናት ይሰጠው ነበር። እነርሱም ይዘውት በመካ ተራራዎች ያዙሩታል። ከአንገቱ ላይ የገመዱ ምልክት እስኪወጣ ድረስ ያንከራትቱታል። አሳዳሪው ኡመያህ ያስረውና ይገርፈው ነበር። ጠራራ ፀሐይ ላይ እንዲቆምም ያደርገው ነበር። በረሃብም ይቀጣው ነበር። ከዚህ ሁሉ የባሰው ግን እኩለ ቀን ላይ ፀሀይ እንደ እሳት ሲፋጅ ከመካ አሸዋማ መስክ ላይ ያስተኛውና ቋጥኝ ድንጋይ ከደረቱ ላይ ያስቀምጣል። "በጌታዬ ላአታት) ማምለክ አስክትጀምር ድረስ በዚህ ሁኔታ ትቆያለህ" ይለዋል። እምላለሁ፣ አስክትሞት ወይም በመሐመድ ከደህ ላትንና ዑዛን (የዐረብ ቢላልም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ፡- "አሐድ፣ አሐድ" (አምላክ አንድ ብቻ ነው) ይል ነበር።"... ለስኬት የተከፈለ ዋጋ።

"አማር ቢን ያሲር የበኒ መኽዙም አገልጋይ (ባሪያ) ነበር። ከወላጆቹ ጋር ሰለመ። ጣኦታውያን በዋነኛነት አቡጀህል (የመካው ዋና መሳፍንት፣ የዚህ ኡማ ፊርዓውን) ፀሐይ ሲበረታ ወደ ሜዳ ያወጣቸውና በግለቱ ይቀጣቸው ነበር። በቅጣቱ ላይ እያሉ ነብዩ ﷺ ባጠገባቸው አለፉ። "የያሲር ቤተሰቦች ሆይ! ታገሱ ጀነት ቃል ተገብቶላችኋል።" አሏቸው። (ከዚህ በላይ ምንም ሊያደርጉላቸው አልቻሉም። ያኔ ነብዩ ﷺ አቅም አልነበራቸውም። እርሳቸውም ስቃይ ውስጥ ናቸው)። በቅጣቱ ምክንያት (የአማር አባት) ያሲር ሞቱ። አቡጀህል የአማርን እናት ሱመያህን ብልቷን

[208] ረህመተን ሊልዓለሚን 1/57
[209] ኢብን ሂሻም 1/320

ውስጥ ጦር ወግቶ ገደላት። የመጀመሪያዋ እንስት ሰማዕት (ሸሂዳህ) ለመሆን ታደለች።"[210]

ኽባብ መካዊያን አንድ ቀን ከአሳት ላይ ጣሉትና ጎተቱት። እሳቱን ያጠፋው የጀርባው ስጋ ቀልጦ ነበር።[211]

ታላቁ መልዕክተኛ ﷺ ይህን እንግልት በራሳቸው ላይና በጥቂት ግን ሁነኛ ተከታዮቻቸው ላይ አስተናገዱ። ሁለንተናዊ በደል ተሸከሙ። ግባቸው የሰው ልጆችን መታደግ ስለሆነ፣ ለዚህ ግዙፍ አላማ መሳካት ትዕግስት ወሳኝ መሆኑን ስለሚያውቁ በዕናት ቀጠሉ። አላህም የያዝከው አላማ ግዙፍ ነው፣ የተሸከምከው ሀላፊነት ትልቅ ነው፣ ያነገብከው ተልዕኮ ሁለንተናዊ ነው፣ ስለዚህ በትዕግስት ተዋብ፣ ዕናትን ተላበስ የሚሉ የቁርዓን መመሪያዎችን አወረደላቸው። ከነዚህም ውስጥ፡-

"ከመልዕክተኞችም የቆራጥነት ባለቤቶች የኾኑት እንደታገሱት ሁሉ ታገስ..."[212]

ለደረሰባቸው እንግልት ቁብ እንዳይሰጡና በይቅርታ እንዲያልፏቸው መከራቸው፡-

"ታገስም፤ መታገስህም በአላህ (ማስቻል) እንጂ አይደለም። በእርሱም ላይ (ባያምኑ) አትተክዝ። (ባንተ ላይ) ከሚመክሩትም ተንኮል በጭንቀት ውስጥ አትሁን።"[213]

"[214]

[210] አሱዱል ጋባህ 5/284 ، ሲረቱ አር-ረሱል - ዶ/ር አሊ ሱላቢ
[211] አሱዱል ጋባህ 1/591-92 ، ሲረቱ አር-ረሱል - ዶ/ር አሊ ሱላቢ
[212] ቁርአን 46 : 35
[213] ቁርአን 15 : 85
[214] ቁርአን 16 : 127

እንግልት የበዛባቸውን ተከታዮቻቸውን ሀገር ጥለው እንዲሰደዱ ተደረገ። ለዚህም ለያዙት አላማ ሲሉ ከፊሎቹ ወደ እኛዋ ኢትዮጵያ ተሰደዱ።

ማዕቀብ

ሌላው የአላህ መልዕክተኛ ከነቤተዘመዳቸው የከፊሉት የስኬት ዋጋ ነው። መካዊያን በእርሳቸውና በቤተዘመዳቸው ላይ ለሶስት ዓመት የቆየ ማዕቀብ ጣሉባቸው።[215]

በዚህ ማዕቀብ ውስጥ በበኒ ሐሺም እና በበኒ ሙጦሊብ ጎሳዎች ላይ ማህበራዊ ማእቀብ ለመጣል መካዊያን ተስማሙ። አድማውም ከነርሱ ጋር አለመጋባትን፣ አለመገበያየትን፣ አለመቀራረብን፣ አለመቀላቀልን፣ ወደ ቤቶቻቸው አለመግባትን እና አለማናገርን ያጠቃልላል። ነብዩን ሰ.ዐ.ወ ለግድያ አሳልፈው እስኪሰጡ ድረስ ከበኒ ሐሺም ጋር ምንም ዓይነት የእርቅ ሐሳብ ላይቀበሉ፣ ርህራሄ እንዳይረታቸው በውሉ ውስጥ ሰፈረ።[216]

ማዕቀቡ በረታ። የሚላስ የሚቀመስ ጠፋ። ቅጠሎችንና ቆዳዎችን ለመመገብ ተገደዱ። ህፃናት ከረሃብ የተነሳ የሚያለሙት ለቅሶ የሸለቆውን አድማስ አልፎ ይሰማ ነበር።... ለስኬት የተከፈለ ዋጋ።

"ሷሂፍ" - ከተማ

መካዊያን ለጥሪያቸው ጆሮ ሊሰጡ አልቻሉም። እነሱ አሻፈረን ያሉትን የኢስላም መልዕክት ሌሎች ይቀበሉት ዘንድ ከመካ ቅርብ ርቀት ወደ ምትገኘው ጣኢፍ ከተማ አመሩ። ጣኢፍ ውስጥ ለአስር ቀናት ተቀመጡ። እያንዳንዱን የከተማዋን ባላባት እየተዘዋወሩ አናገሩ። እነርሱ ግን ከመካውያን የባሱ ሆነው ተገኙ። ከሐገራችን ውጣልን አሏቸው። ሕፃናትንም ለቀቁባቸው። እየተከተሉ ይሰድቧቸው፣ በድንጋይ ይደበድቧቸው ጀመር። የሀገሩ ህዝብ ከየቤቱ እየወጣ በመንገዱ ዳር ተሰልፎ ለድብደባው አጋዥ ሆነ። እግራቸው እስኪደማ፣ ጫማቸው በደም እስኪርስ ድረስ አደሟቸው። ከጣኢፍ ሶስት ማይል ርቀት ድረስ

---

[215] ቡኻሪ እንደዘገቡት

[216] ሶሂህ-አል ቡኻሪ - ከፈትሁል ባሪ ማብራሪያ ጋር

አሳደጓቸው። በመጨረሻም ወደ አንድ የአትክልት ቦታ ከለላ ፍለጋ ገቡ። ያኔ ጥለዋቸው ተመለሱ።

መልዕክተኛው ﷺ ከአንድ የወይን ዛፍ ላይ ተጠለሉ። ወደ ጢኢፍ አብሯቸው የሄደው አገልጋያቸው ከእርሳቸው ለመከላከል ሲል በድንጋይ መፈንከቱን ተመለከቱ። እርሳቸውም እግራቸው በደም ታጥቧል። ስውነታቸው ዝሏል፣ አካላቸው ቆስሏል፣ አዕምሯቸው ተረብሿል። የሰው ልጆችን እንዲታደጉ ወደ ላካቸው ጌታ እንዲህ ሲሉ ተማፅኗቸውን አቀረቡ፦

"አላህ ሆይ! የአቅሜን ደካማነት፣ የብልሃቴን ውስንነት፣ ከሰዎች ዘንድም የተናቅኩ መሆኔን ለአንተ ስሞታ አቀርባለሁ። የአዛኞች አዛኝ የሆንከው የደካሞች (መጠጊያ) አምላክ ሆይ! ለማን ትተውኛለህ? ለሚጠሉኝ ባእዶች? ጉዳዬን ከጠላት እጅ አስገባኸውን? (ይሁን) አንተ ካልተቆጣህብኝ ግድ የለኝም። ማህርታህና ይቅርታህ ይበልጥብኛል። ቁጣህ እንዳይሰፍንብኝ ጨለማን በገሰስክበት ብሩህ ማንነትህ፣ ይህችንም ሆነ መጭውን ዓለም ባቆምክበት ሐይልህና ችሎታህ እጠይቅሀለሁ። ውዴታህን እስካገኝ መድከሜን አላቋርጥም። መላም ኃይልም ባንተ ቢሆን እንጂ የለም።"[217]...

ስደት ወደ መዲና

የአላህ መልዕክተኛ መካ ውስጥ በሰላም መቀመጥ አልቻሉም። መካዊያን መሳፍንቶችም ለጥሪያቸው ጆሮ ሊሰጡ ፍቃደኛ አልሆኑም። ከዚህም አልፈው መልዕክተኛውን ሰ.ዐ.ወ ለመግደል ወሰኑ። ያኔ ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ለስደት ተዘጋጁ። ተከታዮቻቸውን ቀድመው ወደ መዲና ላኩና እርሳቸው ከኋላ ከቁርጥ ቀን ጓደኛቸው አቡበክር ጋር ሀገር ጥለው ተሰደዱ።

የአላህ መልዕክተኛ ሰ.ዐ.ወ ወደ መዲና ሲሰደዱ ሁኔታዎች ተቀየሩ። መዲና ውስጥ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ተቃውሞ እምብዛም አልገጠማቸውም። የመዲና ነዋሪዎች የነብዩን ሰ.ዐ.ወ ዳዕዋ ለማዳመጥ ፍላጎት አሳዩ። ጥሪውን ሰምተውም ኢስላምን ለመቀበል ጉጉታቸው ጨመረ። ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ይህን እድል ተጠቅመው የኢስላምን ጥሪ ለብዙሃኑ ህዝብ

[217] ረሒቀል መኽቱም ገፅ 135

ሊያዳርሱ ቻሉ። በጥቂት ግን ጠንካራና ታማኝ ሙእሚን ተከታዮች የተጀመረው የዳእዋ እንቅስቃሴ ጎልብቶ ፍሬ አፈራ። ዓለማዊ፣ መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በኢስላማዊ መርሆዎች ላይ በመቃኘት ለቀጣዩ ኢስላማዊ የህይወት ጎዳና መሰረት ጣሉ።

የመዲና ነዋሪዎች ኢስላም ይዞላቸው የመጣውን በረከት ስለተረዱና በመሃላቸው የርስበርስ ውዴታን፣ ታማኝነትን፣ መረዳዳትን በመፍጠር አዲስ ህይወት እንዲኖር ስላስቻላቸው ኢስላምና ስደተኛ ሙስሊሞች ባለውለታዎቻቸው ሆኑ።[218]

ማሳደድ

ገና ጥሪው መካ ውስጥ እንደተጀመረ፣ በድብቅ ኢስላምን የተቀበሉ አማኞች ይደርስባቸው የነበረውን ግፍ በመሸሽ ባህር አቋርጠው ሁለቴ ወደ ሀበሻ ተሰደዋል። ቀሪዎቹ ደግሞ ከነብዩ ﷺ ጋር የትውልድ ሀገራቸውን (መካን) ጥለው 500 ኪሎ ሜትር አቋርጠው ወደ መዲና ሸሹ።

የመዲና ነዋሪዎች መልዕክተኛውን ﷺ ተቀብለው ማስተናገዳቸው መካውያንን አንገብግቧቸዋል። ለመዲና መሳፍንቶች እንዲህ የሚል ደብዳቤ ላኩላቸው፦

"ወገናችንን (ነብዩንና መካን ጥለው የተሰደዱ የሙሀመድ ተከታዮችን) አስጠግታችኋል። በአላህ እንምላለን ፈጥናችሁ ተዋጉት። ወይም ከአገር አባሩት። ካለበለዚያ ግን ሁላችንም ተባብረን በመዝመት ነዋሪዎቻችሁን እንገድላለን። ሴቶቻችሁን እንማርካለን።"[219]

መካውያን ነብዩን ﷺ ለመግደል ያልቆፈሩት ጉድጓድ፣ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ሁሌም እርሳቸውን ለመግደል ያሴራሉ። በዚህም የተነሳ ነብዩ ﷺ ያለ ጥበቃ አያድሩም ነበር። የአላህ መልዕክተኛ እና ባልደረቦቻቸው ወደ መዲና መጥተው እንሷሮች ባስጠጓቸው ጊዜ አረቦች በሙሉ ስላደሙባቸው ያለ

---

[218] Islam today - አል-መዉዱዲ
[219] አቡዳዉድ እንደዘገቡት

መሳሪያ ውለው አያድሩም ነበር::"[220] ይለናል የቅርብ ባልደረባቸው አቡይ ኢብኑ ከዕብ::

ይህ መልዕክተኛው ﷺ የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለመወጣት ያሳለፉት ውጣ ውረድ ነው:: የቀረዕነው አላማን ለማሳካት ልናልፈው የሚገባንን መስናክል ጠቋሚ ነው:: ያወጣነው ግብ ያለ ድካም አይሳካም:: ሁሉም ለውጦች መስዋዕትነትን ይጠይቃሉና::

ሁለንተናዊ ዘመቻ

የእስልምና ንፁህ ችግኝ ስሩ ወደ ምድር ከመጥለቁ፣ ቀንዘሉ ወደ ላይ ከመዝለቁና ብዙ መስክ ከመሸፈኑ በፊት በእንጭጩ ለመቅጨት ከቋመጡ የአላህና የአማኞች ጠላቶች ጋር በማያባራ ተከታታይ ጦርነት ውስጥ ገቡ:: የዐረቢያን ጦርነት አጠናቀው ፋታ ሳያገኙ ሮማዊያን (The Roman Empire) ይህን አዲስ ማህበረሰብ በስተ-ሰሜን በኩል ለማጥፋት ይዘጋጁ ጀመር::[221] ይህን በኢስላም ላይ የተከፈተውን ጦርነት ለመመከት የአላህ መልዕክተኛ ሰ.ዐ.ወ. ከ28 ያላነሱ ወታደራዊ ዘመቻዎች ላይ ተሳትፈዋል:: አብዛኛውን ራሳቸው የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ሆነው መርተዋል:: ከውጭ በተለያዩ ጦርነቶች ከውስጥ ደግሞ በኑ ቀይኑቃዕ፣ በኑ ነዲር፣ በኑ ቁረይዛ በተባሉ መሰሪ የአይሁድ ጎሳዎች[222] ታምሰዋል:: የስም ማጥፋት ዘመቻ፣ የቤተሰቦቻቸውን ክብር የሚያጎድፍ ወሬ የአለት-ተዕለት ዜና ነበር:: በመሳሪያ አልችል ሲሉ በተመረዘ ምግብ ሊገድሏቸው ያላደረጉት ጥረት የለም:: ነገር ግን መልዕክተኛው ሰ.ዐ.ወ. አንግበውት የተነሱትን ታላቅ ግብ ሊያስጥሏቸው አልቻሉም:: በአላማቸው ፀኑ:: እልህ አስጨራሽ ትግልም አደረጉ::

የመጀመሪያ ሙስሊሞች ቀያቸውን ካስተካከሉ በኋላ ቀጣዩ ተግባራቸው ኢስላምን ለተቀሩት የዓለም ሕዝቦች ማዳረስ ነበር:: ለዚህ አላማም ለአላህና ለመልዕክተኛው ﷺ ቃልኪዳን ገቡ:: የአዲሱ ሙስሊም ማሕበረሰብ ዓላማና ተግባር ኢስላምን ለሰው ዘር ማዳረስ ሆነ:: የነብዩ ሰ.ዐ.ወ. ተጨባጭ ሕይወትና ሞራላዊ ስብዕናቸው ለተያያዙት መንገድ ትክክለኛነት ከምንም ነገር በላይ ማረጋገጫና ተምሳሌት

---

[220] ቲርሚዚ እንደዘገቡት
[221] ሰይድ ቁጥብ - ፊዚላሊል ቁርኣን (29/168-169) ሰይፉን ፍለጋ -ሀሰን ታጁ (186)
[222] ኢብን ሂሻም - (1/518-519)

ሆነላቸው። አፈንግጠው የነበሩ ጥቂት ሕዝቦችም የሙስሊሞችን ልዩ የአኗኗር ዘይቤ ሲመለከቱ በብዛት ወደ ኢስላም ይጎርፉ ጀመር።

በዚህም ፈጣን ኢስላማዊ እድገት ተከሰተ። ጥቂት ስኩዌር ማይልስ የነበረው ኢስላማዊ ግዛት በስምንት ዓመታት ጊዜ ውስጥ መላውን የዐረቢያ ምድር በመጠቅለል ከሚሊዮን ስኩዌር ማይልስ በላይ ሊሰፋ ቻለ። በሂደትም ኢስላማዊ ግዛት ከቱርክ እስከ አፍጋኒስታን ተሻግሮም እስከ ሰሜን አፍሪካ ተስፋፋ። ይህ ታላቅ ኢስላማዊ አብዮት አመራራዊ ይዘት ብቻ አልነበረውም። ከሁሉም በላይ በዋነኝነት በሕብረተሰቡ ሞራላዊና መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ ያመጣ፣ የህይወትን ትርጉምና ዓላማ በጥልቀት ያስተማረ፣ባጠቃላይ የሕዝቦችን የሕይወት ጎዳና በአዲስ አቅጣጫ የቀየሰ እንቅስቃሴ ነበር። ይህ ኢስላማዊ አብዮት ከዐረቢያ ምድር አልፎ የዓለምን የታሪክ አቅጣጫ ቀይሯል። በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ የአኗኗርና የአስተሳሰብ ለውጥ አስከትሏል።[223]

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ በአባታቸው ኢብራሂም ፋና፣ በነብያት ወንድሞቻቸው ሙሴና እየሱስ ዐ.ሰ. የአስተምህሮት ጎዳናን በጠበቀውና ለመጨረሻው የሰው ልጅ ትውልድ ተስማሚ እንዲሆን ተደርጎ የተቀረፀውን እምነት ለዓለም አዳረሱ። ተከታዮቻቸውን በአለም አራቱም አቅጣጫ አሰራጩ። ለዓለም ሀያላን መንግስታት ደብዳቤዎችን ላኩ።

ሌት ተቀን ባደረጉት ጥሪ የሰውን ልጅ ወደ ጌታው መለሱት። ለተፈጠረበት አላማ እንዲኖር አደረጉት። ከማንኑቱ ጋር አስታረቁት። በኢማን ቁልፍ የተከረቸሙ በሮችን ሁሉ ከፋፈቷቸው።

12.3.5 አመርቂ ስኬት (Great Success)[224]

በዚህ የኢማን መክፈቻ የተዘጉ ቁልፎች፣ የተከረቸሙ በሮች ሁሉ በየተራ ተከፈቱ። ይህ ነብያዊ መፍቻ ከዚህ ቀደም ለእውነትም ለሐሰትም ወግኖ ይሟገት ከነበረው አእምሮ ላይ ሲቀመጥ የተዘጋው አእምሮ ተከፈተ። ብርሃን አገኘ። የአላህን ፍጡራን እና ተአምራት ለማየትና ለመጠቀም በቃ። ከአምላክ ጋር ተገናኘ። ከርሱ ጋር ተዋወቀ። የጣኦታትን ከንቱነት ተረዳ። ከእንቶ ፈንቶ አስተሳሰቦች ተላቀቀ።

[223] Islam today - መውዱዲ , ኢስላም ከተናንት እስከዛሬ - ሐሰን ታጁ

[224] The famous thinker Bernard shaw Once said about the prince of the prophets – Muhammed ﷺ "He solves All problems the ease of drinking coffee" (Love and Tolerance- By – Gulen)

ይህ መፍቻ የተኛውን የሰው ልጅ ሕሊና አነቃ። በሞቱ ስሜቶቹ ነፍስ ዘራ። በክፉ የምታዝ ነፍስ ተረጋጋች። ወንጀልን የማትሸከምና ሀጢአትን የማትታገስ ሆነች። ወንጀለኛ ወንጀሉ አላስተኛህ ብሎት (በኢማን የታነፀው አእምሮው ረፍት ነስቶት) ለአላህ መልዕክተኛ ﷺ የሚናገርበትና እጅግ አሰቃቂውን ቅጣት (በድንጋይ መወገርን) እንዲቀጡት አጥብቆ የሚጠይቅና የሚማፀንበት ትንግርት ተፈጠረ።

በገጠር ማንም ሳያያት ሐጢአት የፈፀመች እንስት በፈቃዷ ወደ ከተማ መጥታ ወንጀለኛነቷን ትናዘዛለች። እንድትቀጣም አጥብቃ ትጠይቃለች። ድሃ ወታደር የኪስራን ዘውድ ተሸክሞ በጎ ስራውን ሌሎች አይተው እንዳያደንቁት በልብሱ ጠቅልሎ ለመሪው ያስረክባል። (የምርኮ ገንዘብ) የአላህ ገንዘብ ስለሆነ መንካት ወይም ማጉደል ኃጢአት መሆኑን ያውቃልና።[225]

ደረቅ ልቦች ለዝበው፣ ሸካራዎች ለስልሰው በክስተቶች የሚማሩ፣ ለተበደሉ የሚያዝኑ፣ ለደካማ የሚያጎበድዱ ሆኑ። ይህ መፍቻ ከታፈኑ አቅሞችና ከሀሎቶች ላይ ሲያርፍ በየአቅጣጫው እንደነበልባል ተንቀሳቀሱ። እንደወንዝ ፈሰሱ። ትክክለኛ ፈርና መስመር ያዙ። ግመል ጠባቂ የነበረው የአለም መሪ፣ የአንድ ጎሳ ፈረሰኛ ሀያላን መንግስታትን የሚያንበረክክ፣ የረዥም ጊዜ የክብርና ታሪክ የነበራቸውን ሕዝቦች በስሩ በፍትህ የሚያስተዳድር ሆነ።

ይህ የኢማን መፍቻ መምህራን ከራቁት፣ተማሪዎች ከናቁት፣ የእውቀት ዋጋ ከረከሰበት፣ መምህር ከተዋረደበት ማእከል ላይ ሲያርፍ የእውቀትን ልቅና አጎላ። ደረጃውን አስታወሰ። የተማሪና የመምህር ዋጋ ታወቀ። እውቀት ከሐሂማኖት ጋር ተቆራኘ። ሁሉም መስጊዶችና ሁሉም የሙስሊም ቤቶች የትምህት ማዕከላት ሆኑ። ሁሉም ሙስሊም ለራሱ ተማሪ፣ ለሌሎች ደግሞ አስተማሪ ሆነ። ለእውቀት ትልቁ ምክኒያትና አነሳሽ ሃይማኖቱ ሆነ።[226]

---

225 ማዛ ኸሪረልዓለመ. ቢንሂጧጢል ሙስሊሚን - ፕሮፌሰር ነደዊ
226 አልኢማኑ ወልሐያት - ሼኽ ዶ/ር ዩሱፍ አልቀርዳዊ ገፅ- 270 (ዐረብኛው)

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ አሁንም የማህበረሰቡን ክፍል እነዛ ተግተው ቀጠሉበት። ይህ የኢማን መፍቻ ከተዘጉ ፍርድ ቤቶች ላይ ሲቀመጥ አዋቂ ሁሉ ፍትሃዊ ዳኛ እንዲሆን አደረገው። ሙስሊም ዳኛ ሁሉ በፍትህ ይፈርዳል። ሙስሊሞች ለአላህ ሲሉ ፍትህን ያሰፍናሉ። በሀቅ ፈራጆች ሆኑ። በአላህና በመጨረሻው ቀን ማመን እውን ሆነ። ፍትህ ነግሰ፣ ተከራካሪ ግን ቀነሰ። በሀሰት መመስከርና በግፍ መፍረድ ቀረ።

ቤተሰብ ተቆልፎ ነበር። ጎጆዎች በሰብሰው ነበር። አባትና ልጅ፣ ወንድማማቾች፣ ባልና ሚስት ይበዳደላሉ። ይህ በሽታ ከቤተሰብ አልፎ በህብረተሰቡም ውስጥ ተስፋፍቷል። አሳዳሪና አገልጋይ፣ ትልቅና ትንሽ ይበዳደላሉ። ሁሉም መብቱን ለመውሰድ ይጓጓል። ግዴታውን ለመወጣት ግን አይፈቅድም። ከሰው አክለው ይወስዳሉ። ሲሰጡ ቀንሰው ይሰጣሉ። ነብዩ ሰ.ዐ.ወ. ከዚህ አይነቱ ቤተሰብ ላይ የኢማን መክፈቻቸውን አስቀመጡ። የእምነት ችግኝ ተከሉ። ከአላህ ቅጣት አስጠነቀቁ። የሚከተለውን የቁርአን አንቀፅ አነበቡላቸው፦

"እናንተ ሰዎች ሆይ! ያን ከአንዲት ነፍስ የፈጠራችሁን፣ ከርሷም ተጣማሪዋን የፈጠረውንና ከነኝህ ከሁለቱ በርካታ ወንዶችና ሴቶችን ያበዛውን ጌታችሁን ፍሩ። ያ በርሱ (የጋራ መብቶቻችሁን) የምትጠያየቁበትን አላህን ፍሩ፤ ዝምድናንም (ከመቁረጥ ተጠንቀቁ) አላህ አናንተን ዘወትር ተጠባባቂ ነውና።"[227]

በቤተሰብና በህብረተሰብ ውስጥ ሀላፊነቶችን አከፋፈሉ። እንዲህ አሏቸው፦

"ሁላችሁም ሀላፊነት አለባችሁ። በሀላፊነታችሁ ትጠየቃላችሁ።" በዚህ መልኩ ፍቅር፣ ፍትህና መተሳሰብ የነገሰበት የተቀና ቤተሰብ እንዲሁም ማህበረሰብ ፈጠሩ። በቤተሰቡ አባላት መካከል ትልቅ የሀላፊነትና አላህን የመፍራት ስሜት አሰረፁ። ገዢም ተገዢም አላህን

[227] ቁርአን 4 : 1

ይፈራሉ። ቅጣቱን ይጠነቀቃሉ። ገዢዎች የህዝብ አገልጋዮች ሆኑ። የህዝብ አስተዳዳሪ የሙት ልጅ ወኪል (ንብረት ጠባቂ) መሰለ። የህዝቡን ገንዘብ አያባክንም። ያለአግባብ አያወጣም። ካለው ቤሳቤስቲን ከማንሳት ይቆጠባል። ከሌለው ለእለት ጉርሱ ብቻ ይቀንሳል።[228]

ይህ የኢማን ቁልፍ ከነጋዴዎችና ከባለሀብቶች ላይ በማረፍ በዚህች አለም ፀጋ የማይንጉ፣ መጭውን አለም የሚናፍቁ አደረጋቸው። ገንዘብ የአላህ መሆኑን እንዲህ ሲል አስታወሳቸው፦

"በአላህና በመልዕክተኛው አምኑ፤ (አላህ) በእርሱ ላይ ባለአደራ ያደረጋችሁን ገንዘብን (በእርሱ መንገድ) ለግሱ። ከመካከላችሁ በንዚያ ላመኑትና (ገንዘቦቻቸውን በአላህ መንገድ) ለለገሱት ታላቅ ምንዳ ተዘጋጅቶላቸዋል።"[229]

እንዲህም ሲል አዘዛቸው፦

"አላህ ከሰጣችሁ ገንዘብ ላይ ስጧቸው።"[230]

ገንዘብን አስማችቶ በአላህ መንገድ ላይ ካለመመፅወት አስጠነቀቃቸው፦

[228] ማዛ ሽሊረል ዓለም - ፕሮፌሰር ነደዊ
[229] ቁርአን 57 : 7
[230] ቁርአን 24 : 33

"እነዚያ ወርቅና ብርን የሚያከማቹትን፣በአላህ መንገድም የማይመፀውቱትን በአሳማሚ ቅጣት አበስራቸው፡- በገሀነም እሳት እንዲግሉ በሚደረግበትና ግንባሮቻቸው፣ ጎኖቻቸውና ጀርባዎቻቸው በነርሱ በሚጠበሱበት ቀን፡፡ "ይህ በነፍሶቻችሁ ያከማቻችሁት (ቅጣት) ነው፡፡ ያከማቻችሁትን (የቅጣት ድልብ) ቅመሱ ይባላሉ፡፡"[231]

ጥረታቸው ግቡን መታ፣ የተከሉት የኢማን ችግኝ ፍሬ ለገሰ፣ የታለመለት ግለሰብ ተፈጠረ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ በአላህና በመልዕክተኞቹ ያመነ፣ ቅጣቱን የሚፈራ፣ ታማኝና ጠንቃቃ፣ ከዱንያ (ከምድራዊ ንዋይ) አኼራን (የቀጣዩን ዓለም) ስኬት የሚመርጥ፣ ቁስን በእምነቱና በመንፈሳዊ ጥንካሬው ያሸነፈ፣ይህች አለም ለእርሱ እርሱ ግን ለመጭው ዓለም እንደተፈጠረ የሚያምን ሙስሊም ግለሰብ አነፀ፡፡

ይህ ግለሰብ ነጋዴ ከሆነ ታማኝ፣ ደሃ ከሆነ ጥሮ ግሮ የሚበላ፣ሰራተኛ ከሆነም በታማኝነት የሚሰራ፣ ሀብታም ከሆነ ለሌሎች የሚያዝንና የሚያስብ፣ ዳኛ ከሆነም በፍትህ የሚፈርድ፣ ገዢ ከሆነም ታማኝና ቅን፣ ንጉስ ከሆነ ትሁትና አዛኝ አገልጋይ ወይም ተቀጣሪ ከሆነም ትጉና ታማኝ፣ገንዘብ ያዥ ከሆነም በሙያው የተካነና ታማኝ ሆነ፡፡[232]

በነዚህ ጡቦች (ግለሰቦች) አዲስ ማህበረሰብ ታነፀ፡፡ ህብረተሰቡና መንግስት የግለሰቦች ስነልቦናና ባህሪ ነፀብራቆች ሆኑ፡፡ ህብረተሰቡ መልካምና ታማኝ ህብረተሰብ ሆነ፡፡ ከዱንያ አኼራን የመረጠ ሆነ፡፡ ቁስን አሸነፈ፡፡ ክቁስ ተገዢነት ዳነ፡፡ የነጋዴውን እውነትና ታማኝነት፣ የደሀውን ትጋትና ቁጥብነት፣ የሰራተኛውን ታማኝነትና ጥረት፣ የባለሀብቱን ቸርነት፣ የዳኛውን ፍትህና ጥበብ፣ የገዢውን ጠባቂነት ህብረተሰቡና መንግስት ወረሱ፡፡

ይህ መንግስት የተቀና መንግስት ሆነ፡፡ ከጥቅም ይልቅ መርህን፣ግብር ከመሰብሰብ ይልቅ ሰውን ማቅናትን ያስቀድማል፡፡ በዚህ አይነቱ መንግስት በጎ ተዕዕኖና ስልጣን ህብረተሰቡ ተገራ፡፡ እምነትና በጎ ምግባር፣ ቅንነትና ታማኝነት፣ ጥረትና ትጋት፣ ሲቀበሉም ሲሰጡም ፍትህና ያለመበዳደል ነገሰ፡፡[233]

---

231 ቁርአን 9 : 34-35

232 አልኢማኑ ወልሐያት - ኢማም አልቀርዳዊ ፣ ኢማንና ህይወት ትርጉም፡ ሐሰን ታጁ ገፅ 425

233 Islam and the world - pro.Nadawi

አዎ! ከ23 ዓመት እልህ አስጨራሽ ትግል በኃላ ድካማቸው ፍሬ ያዘ። እስልምና እጅግ በሚያስደንቅ ፍጥነት ተስፋፋ። መላ አረቢያ ለዚህ ሐይማኖት አደረች። ከአድማሷ ላይ የጃሂልያ[234] ጭጋግ ተገፈፈ። የታመሙ አእምሮዎች ተፈወሱ። የጣኦት አምልኮ ተንኮታኮተ። የተውሒድ[235] ጥሪ ከዳር እስከ ዳር አስተጋባ። ኢስላም ሕይወት በሰገሰው በረሃ ውስጥ የአዛን ጥሪ ሕዋውን እየሰነጠቀ ተሰማ። የቁርዓን አዋቂዎች በአራቱም አቅጣጫዎች በመዝመት ቁርዓንን ለሰው ልጆች አነበቡ። አላህን ሕግጋት አስተገበሩ። የተበታተኑ ህዝቦችና ጎሳዎች አንድ ሆኑ።

የሰው ልጅ ፍጡራንን ከማምለክ አንድ አላህን ብቻ ወደ ማምለክ ተሸጋገረ። አሸናፊና ተሸናፊ፣ ጌታና ሎሌ፣ ገዢና ተገዢ፣ በዳይና ተበዳይ የሚባሉ ልዩነቶች ከስመው የሰው ልጆች የአላህ ብቻ ባሪያዎች፣ የሚዋደዱ ወንድማማቾች፣ በአላህ ህግና ስርዓት ብቻ ያደሩ ሆኑ። አላህ በነብዩ ሰ.ዐ.ወ. ሰበብ የጃሂልያን ከንቱ ጉራና ስሜት አስወገደላቸው። አረቦች አረብ ባልሆኑት፣ አረብ ያልሆኑትም በአረቦች ላይ፣ ነጩ በጥቁሩ ላይ አላህን በመፍራት ካልሆነ በቀር ምንም አይነት ብልጫ እንደሌለው ፀደቀ። የሰው ልጆች በአጠቃላይ የአደም ልጆች ናቸው። አደም ደግሞ ከአፈር ነው ተብሎ ታወጀ።

በዚህ አኳኋን በነብዩ ﷺ ጥሪ በረከት፣ የዐረቦች አንድነት፣ ብሎም የሰው ልጆች አንድነትና ማህበራዊ ፍትህ እውን ሆነ። በአለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ጉዳዮች የሰው ልጅ ፍፁማዊ ደስታ ተረጋገጠ። የታሪክ ሂደት ተቀየረ። የምድር ገፅታ ተለውጦ የሰው ልጅ አዕምሮ ቀጥተኛ ሆነ።

አዎ! የነብዩ ﷺ ጥሪ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ተዕዕኖ ሲጀምር ግለሰብ ከድክመትና ከከንቱ አስተሳሰቦች፣ ከባርነት፣ ከብክለት፣ ከእኩይ ድርጊቶችና ባህሪያት ሁሉ ፀዳ። ማህበረሰብ ከግፍና ከአምባገነን ስርዓት፣ ከመበታተንና ከመፈራረስ፣ ከመደብ ልዩነት፣ ከገዢዎች ጭቆናና ከጠንቋዮች ውርደት ፀዳ። የአለም ግንብ ከንዕህና፣ ከበጎነት፣ ከነፃነትና ከተሀድሶ፣ ከእውቀትና ከእምነት፣ ከፍትህና ከክብር፣ ህይወትን ለማጎልበትና ለማሳደግ ከሚደረግ ትግል፣ እንደዚሁም ሁሉም መብቱን

[234] 164 የህዳግ ማስታወሻን ይመልከቱ
[235] ተውሒድ - በአንድ አላህ ብቻ ማመን (Islamic Monotheism)

ከሚያገኝበት በጎ መሰረት ላይ ታነፀ::[236]

በዚህ ለውጦች አማካኝነት አረቢያ ከተፈጠረችበት እለት አንስቶ ያላየችውን ታላቅና ብሩክ ተሀድሶ አየች:: ታሪኳም በየትኛውም ወቅት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በእነዚህ ጊዜያት አንፀባራቂ ገፅታን ተላበሰ::

ተልዕኳቸውን በአመርቂ ሁኔታ ተወጡ:: ግባቸውን በስኬት አጠናቀቁ:: ይዘውት የመጡት እምነትም ያለአንከን ሞላ:: አላህም እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ሰጠ:-

"... ዛሬ ለናንተ ሀይማኖታችሁን ሞላሁላችሁ:: ፀጋዬንም በእናንተ ላይ ፈፀምኩ ለእናንተም ኢስላምን ከሀይማኖት በኩል ወደድኩ:: . ."[237]

አዎ! ብቁ ትውልዶችን አንፀው ወደ አምላካቸው ሄዱ:: ዓለም ዳግም ልታያቸው ያልታደለችውን ምጡቅ ስብዕናዎችን ተመለከተች:: የሰው ልጅ ሁሉ ፈርጦች ተከሰቱ:: አላህም ሱ.ወ. ይህን የነብዩ ሰ.ዐ.ወ. የተሳካ እነዛ እንዲህ ሲል አፀደቀ:-

"ለሰዎች ከተገለፀች ሀዝብ ሁሉ በላጭ ሆናችሁ በፅድቅ ነገር ታዛላችሁ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ፤ በአላህም (አንድነት) ታምናላችሁ...::"[238]

---

[236] Islam and the world - pro. Nadawi , ሰይፉን ፍለጋ በሀሰን ታጁ (186-188)
[237] ቁርአን 5 : 3
[238] ቁርአን 3 : 110

የመሪው ስብዕና

"አንተ በታላቅ ስነ-ምግባር ላይ ነህ"[239]

የአላህ መልዕክተኞች ሁሉ ፊርጥ፣ የአደም ልጆች አይነታ፣ የነብያቶች መደምደሚያ፣ የተሃድሶ ካስማ፣ ሁለንተናዊ የሰው ልጆች ተምሳሌት ናቸው - ነብዩ ሙሐመድ። ስብዕናቸው የመለኮታዊው መመሪያ መገለጫ፣ ሙሉ ህይወታቸው የቅን መመሪያ ምንጭ፣ የሰማያዊው ትዕዛዝ ተግባራዊ ትርጓሜ ነው።

የመልዕክታቸው ዳራ፣ የጥሪያቸው ክልል፣ የተልዕኳቸው ጥግ በየትኛውም ክ/ዘመን የሚመጡ የሰው ልጆችን ሁሉ የሚያካትት ስለሆነ ምጡቅ ስነ-ምግባር፣ ውብና ማራኪ ስብዕና መጎናፀፋቸው የግድ ነው። አዎ! ይህ ነበር ስብዕናቸው።

ታማኝ ትሁት መሪ አንደበተ-ርቱ
መምህር አዋቂ ጣፋጭ አንደበቱ
ቃልኪዳን አክባሪ አስታራቂ ዳኛ
የጦር ሜዳ ጀግና ወታደር አርበኛ
ከቡር የአላህ ነብይ ታላቅ የሰላም ሰው
ዓለም ያወደሰው አላህ ያነገሰው
ቃላት ማይናገር ከራሱ ልቦና
አንዲህ ተዘርዝሮ መች ሰራው ያልቅና
ልተወው ሳልጀምር ችዬ አልዘልቅምና

* * *

[239] ቁርአን 68 : 4

በተከታዮቻቸው ላይ የፈጠሩት ተፅዕኖ

ይዘውት የተነሱትን ሁለንተናዊ ተልዕኮ በአግባቡና በአመርቂ ሁኔታ እንዲወጡ ያደረጋቸውም፤ ኢስላም ለመፍጠር የሚፈልገው የተዋጣለት ኢስላማዊ ስብዕና ባለቤት መሆናቸው ብቻ ሳይሆን አይነተኛ ተምሳሌት መሆናቸውም ነበር። የመጠቀ አስተሳሰብ፣ ምሉዕ ሽብዕና የተላበሱ፣ ከራስ ወዳድነት የፀዱና ከራሳቸው በፊት ሌሎችን የሚያስቀድሙ፤ ለሰብዐዊ ፍጡር ብቻ ሳይሆን ለእንስሳም የሚራሩና ለሰው ልጆች ነፃነት መስዋዕት ሊሆኑም የተዘጋጁ ነበሩ - መልዕክተኛው ::

ይህ ውብ ስብዕና፣ ይህ ምጡቅ ስነምግባር፣ ይህ ሙሉ ርህራሄና ትህትና በተከታዮቻቸው ልብ ውስጥ የፍቅር ጎጆ ቀለሰ። ከነፍሳቸው በላይ ወደዷቸው። ለእርሳቸው መስዋዕት ለመሆን ከፊት ቆሙ።

ፍቅሮት አሸንፈ ፍቅሮ አለምን ገዛ
ሁሉም ቃል ተጋባ የወደዶት ግለ - ለርሶ ሊሆን ቤዛ
ገና ከመነሻው ገና ከጅምሩ
ቢዋሀድ ከገለው ውዴታና ፍቅሩ
ቢሰርፅ ከልቡ ቢገባ ካንጀቱ
ቢዘልቅ ነው አንጂ ከደም ከአጥንቱ
ራሱን አሳልፎ ሀይወቱን መስጠቱ

* * *

አኔ ልሙት አለ
አኔ ልሙት ለርሶ አኔ ልሁን ፊዳ
ይሸው ይፍሰስ ደሜ አካሌም ይጎዳ
ከርሶ አይበልጥብኝም መላው ሰውነቴ
ከፎትን አልየው ካሻው ይምጣ ሞቴ

* * *

በከሀዲያን በትር ከቡር ደምህ ፈሶ
መከራ ሰቃዩ ችግር ባንተ ደርሶ
አይችልም ልባችን ውስጣችን ይደማል
አንተን ከፋ ነክቶህ ጢናስ ኪት ይገኛል

* * *

ለይስሙላ አይደለም አንዲያው ለምለሱ
ሁሉም ያደንቀዋል ሁሉም ያከብረዋል ሁሉም
ያልቀዋል ከሰጋው ከነፍሱ
የኔ አካል አንዳሻው ይረገጥ ይመታ
ይህ ነው የፍቅር ጥግ እንዲህ ነው ውዴታ

***

ለአላማ የተከፈለ ዋጋ - ስደት

መልዕክተኛው ሰ.ዐ.ወ. ይዘውት የተነሱት "ዲን" (ዕምነት) የመጣው የዓለምን ገፅታ ለመቀየር፣ የዓለማት ፈጣሪ በብቸኝነት የሚመለክበትን፣ ኢ- ፍትሃዊነት የሚመክንበትን፣ የሰው ልጅ ሰብዐዊ ማንነቱ የሚረጋገጥበትን አዲስ ዓለም ለመፍጠር ነው። የሰው ልጅ ከሰው ለሰው ባርነት አንድን አምላክ ወደ ማምለክ ነፃነት፣ ከዝህች ዓለም ጠባብ ህይወት ወደ መጭው ዓለም ስፋት... የተሸጋገረበትን ልዩ ዓለም። እጅግ ሰፊና ምሉዕ፣ እጅግ ድንቅና ውብ፣ እጅግ ማራኪ የሆነችን የእምነት ዓለም።[240]

ይህን ሁለንተናዊና አዲስ ዓለም ለመፍጠር ደግሞ እልህ አስጨራሽ ውጣ ውረድን ማለፍ የሚጠበቅ ነው። ከነዚህ ለስኬት ከተከፈሉ ዋጋዎች ውስጥ አንዱ የሚወዷትን ሀገር ለቀው መሰደዳቸው ነበር፡-

የከሀዲያን ብትር እያየለ መጥቶ
ግድ ሆነ መሰደድ ቤት ንብረትን ትቶ
ግድ ነበር እና ሀገር መልቀቃቸው
ከሚወዷት መካ ትተው መውጣታቸው
ተጉዘው ደረሱ ተሰደው መዲና
የአላህ ወዳጅ ቀሩ ብቅ አላሉም ገና

* * *

[240] ቅዱስ ቁርዓን - ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚ ገፅ - 87

የተከታዮች ጉጉት

እንዲህ ርቀን ዛሬ ተለይተን ከንተ
አልቻልነውምና ልባችን ዋተተ
ውስጣችን በሲጋት በናፍቆት ተውጧል
መች ትመጣ ይሆን ሁሉም ይጠብቃል
ምን አግኝቶህ ይሆን ዛሬስ ምን ገጠመህ
በፍቅር በናፍቆት ሁሉም ሰው ተራበህ
ፊራን የአላህ ወዳጅ ከቶ እንደምን አለህ?
ምን አልባት ሚከተል ያን ጋራ ለጋራ
አይጠፋም ከኋላህ የቁረይሾች ጭፍራ
አለ ብዙ ከንቱ ጌታውን ማይፈራ
አላህ ይጠብቅህ ከጠላትህ ተንኮል ከጠላትህ ሴራ

ማባበያ

መልዕክተኛውን ﷺ (ከስደት በፊት) የቁረይሽ መሳፍንቶች የተለያዩ ማባበያዎችን አቅርበውላቸው ነበር። ከቁረይሽ ባላባቶች ውስጥ አንዱ የሆነው ዑትበህ ኢብኑ ረቢዐህ ይህን ተልዕኮ እንዲወጣ ሀላፊነት ተሰጠው። እርሱም እንዲህ ሲል ንግግሩን ከፈተ፦

"የወንድሜ ልጅ ሆይ! በዚህ ባመጣህው አዲስ እምነት የምትፈልገው ገንዘብ ከሆነ ከሁላችንም የበለጠ ሐብታም እናድርግህ። የምትሻው ልቅና ከሆነ በበላያችን ላይ እንሾምህ። ያለፍቃድህ ምንም ነገር አንፈፅምም። የምትፈልገው ንግስናን ከሆነ ንጉሳችን እናድርግህ... ።"[241]

ሚስት እንስጥህ ውሰድ መርጠን ከዘራችን
ገንዘብ እንካ ክበር ብለጥ ከሁላችን
ሰልጣን ካሻህ ንገሰ እዘዝብን በኛ
ግና አንድ አምላክ አትበል ሰላም ሰጠን ለኛ

* * *

[241] ረሂቁል መኽቱም - ገፅ - 108

የአላማ ፅናት

እኒህ ማባበያዎች ሊያማልሏቸው አልቻሉም። ምክንያቱም የህይወት ተልዕኳቸው ከዚህ በላይ ነውና። የሰው ልጆችን ወደ ቅኑ ጎዳና ለማመላከት፣ የሁለት ዓለም ስኬትን እንዲጎናፀፍ ለመምራት፣ ምድርን በፍትህ ለማነፅ ነውና የተላኩት።

ለቁረይሽ መሳፍንቶች በአጎታቸው በአቡ ጧሊብ በኩል የማያዳግም ምላሽ ላኩ። እንዲህ አሏቸው፦ "አጎቴ ሆይ! ይህን ጉዳይ እተው ዘንድ ፀሐይን በቀኜ እጄ፣ ጨረቃን በግራ እጄ ቢያኖሩልኝ እንኳ አላህ ይፋ እስኪያደርገው ወይም እኔ በመንገዱ ላይ እስክሰዋ ድረስ አልተወውም።"[242] ... Stick with your goal.

አውነት ልንገራችሁ ጀሮ ያለው ይሰማ[243]
ጨረቃን ብትሰጡኝ የምትገፍ ጨለማ
ፀሐይን ብጨመር ባሳቡ አንድሰማማ
ትግሌ ይቀጥላል ፍትህ እስኪሰፍን ምድር እስክትለማ

ታላቅ ስኬት- Great Success

ጉዟቸውን በፅናት በጥበብ ቀጥለው
ይኸው ታሪክ ሰሩ ሆነ ያልታሰበው
ፍትህ ተንሰራፋ ፍጡራን ወጡ ነፃ
ኢስላም አምሮ ታየ ምን የሚያምር ህይወት!
ምን የሚያምር ሆነ!!!

"ዛሬ ሀይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ፀጋዬንም በናንተ ላይ ፈፀምኩ። ለናንተም እስላምን ከሀይማኖት በኩል ወደድኩ"[244]

---

[242] ረሂቁል መኽቱም - ገፅ - 90
[243] እስከዚህ ድረስ ያሉትን ስንኞች ተወዳጁ ገጣሚና አርቲስት ሙኒር ሁሴን የከተባቸው ሲሆኑ - ከዚህ በታች ያሉትን ደግሞ እኔው የቋጠርኳቸው ስንኞች ናቸው።
[244] ቁርአን 5 : 3

እንዴ ቁጭ በልና የህይወት ግብህን አስምር

"ጋደም በልና በአይነ ህሊናህ ራዕይህን ተመልከተው፣ ቁጭ በልና ግብህን አስፍረው፣ ቀበቶህን ጠበቅ አድርግና ግስጋሴህን ቀጥል... ያኔ ስኬት ይከተልሀል"

እነሆ ከክፍለዘመናት በፊት አራት ወጣቶች ከከዕባ[245] ፊት ለፊት ተቀምጠው እየተወያዩ ነው። ጨዋታቸው ደርቷል። በመሀል "ለወደፊት ምን መሆን እንደምንፈልግ እንመኝ" ተባባሉ። ከነዚህ ውስጥ ሶስቱ ወንድማማቾች ናቸው። ዐብደላህ ኢብኑ ዙበይር፣ ሙስዐብ ኢብኑ ዙበይር፣ ዑርወት ኢብኑ ዙበይር ይባላሉ። አራተኛውና የቅርብ ጓደኛቸው አብዱልመሊክ ኢብኑ መርዋን ይባላል።

ዐብዱላህ ኢብኑ ዙበይር ምኞቱን እንዲህ ሲል ገለፀ። "እኔ ለወደፊት ሂጃዝ[246]ን በስራ ማድረግ እፈልጋለሁ።"

ከዛም የርሱ ወንድም ሙስዐብ ኢብኑ ዙበይር አስከትሎ፡- "የእኔ ምኞት ደግሞ "ኢራቀይንን"[247] በእጄ ማስገባት ነው።" አለ።

ጓደኛቸው ዐብዱልመሊክ ኢብኑ መርዋን በበኩሉ "እናንተ አሁን ያላችሁትን ግዛቶች በማስተዳደር ከረካችሁ፣ እኔ ግን ከዚህ በላይ እመኛለሁ። እኔ ምድርን በአጠቃላይ ማስተዳደር እፈልጋለሁ።" አለ።

አሁን ደግሞ የወንድማቸው የዑርወት ኢብኑ ዙበይር ተራ ነው። እርሱም እንዲህ ሲል ንግግሩን ከፈተ፡- "እናንተ የተመኛችሁትን ምድራዊ ጉዳይ (ዱንያዊ ግቦች) አላህ ይባርክላችሁ፣ ለስኬትም ያብቃችሁ።" አያይዞም "እኔ እውቅ ዓሊም (ሊቅ)፣ እንዲሁም ባወቀው የሚሰራ መሆን እመኛለሁ። ሰዎች የአላህን ኪታብ (ቁርዓን) የሚማሩበት፣ የነብያቸውን ሱንና የሚቀስሙበት፣ የእምነታቸውን ህግጋቶች ጠይቀው የሚረዱበት እውቅ ዓሊም መሆን እፈልጋለሁ። ከዚያም በቀጣዩ ዓለም የአለማትን ጌታ ውዴታ ማግኘት እመኛለሁ።" ሲል ንግግሩን ቋጨ።

---

[245] ካዕባ - በሳዑዲ አረቢያ መካ ከተማ የሚገኝ፣ ኢብራሂም ከልጃቸው ኢስማኢል ጋር የገነቡት የአላህ ቤት ነዉ። ሙስሊሞች በየስግደት ሰዓታቸው ወደ ከዕባ ይቀጣጫሉ።

[246] የዛሬውን የሳኡዲ ዐረቢያ ምድር የሚያካልለው ስፍራ ነው። ሂጃዝ።

[247] ኢራቀይን - ኢራቅና ኢራንን ማለት ነው።

አዎ! አላማው ግልፅ ነው። የሁለት ዓለምን ስኬት መቆናጠጥ ነው ምኞቱ። በምድራዊ ቆይታው እውቅ ዓሊም (ሊቅ) ብቻ ሳይሆን ባወቀውም የሚሰራ፣ የተናገረውን የሚተገብር፣ የአስተምህሮቱ አይነተኛ ተምሳሌት የሆነ አስተማሪ መሆን ይፈልጋል። ሰዎች ስለ መለኮታዊ መመሪያቸው (ቁርዐን)፣ ስለ መልዕክተኛው ﷺ አስተምህሮቶችና ፈለጋቸው እንዲሁም ስለ ሀይማኖት መመሪያዎችና ህግጋቶች የሚዘገኑበት ማዕድ መሆን ይፈልጋል። ይህን ምድራዊ ስኬት ደግሞ ለዋናው ግቡ (The Goal of Goals) መሰረት ማድረግ ተመኝቷል። በቀጣዩ ዓለም የአላህን ውዴታ ማግኘትን አልሟል።

ዘመናት ነጎዱ። ጊዜ እንደፈረስ ጋለበ። እነዚህ አራት ግለሰቦች በወጣትነት እድሜያቸው የተመኙትን ነገር፣ ከከዕባህ ጥግ ቁጭ ብለው የቀረፁትን ግብ፣ ለወደፊት ቢሆኑ የሚመኙትን አላማ አሳኩ። ዐብዱላህ ኢብኑ ዙበይር-ሂጃዝን (አጠቃላይ የሳዑዲ ዐረቢያን ምድር) አስተዳደሪ ሆነ። ወንድሙ ሙስዐብ ኢብኑ ዙበይር የኢራቀይን ገዥ ለመሆን ቻለ። እንዲሁም ዐብዱልመሊክ ኢብኑ መርዋን የዓለምን አንድ ሶስተኛ ግዛት ለማስተዳደር በቃ። (ያኔ የሙስሊሙ ዓለም ዓለምን በበላይነት የሚመራበት ጊዜ ነበርና የሙስሊሙን ዓለም በአጠቃላይ አስተዳደረ።)። ዑርወት ኢብኑ ዙበይር እንደተመኘው እውቅ ዓሊም ሆነ። ከተለያየ የዓለም ክፍል ሰዎች እየመጡ ከእርሱ እውቀት ይቀስሙ ነበር[248]።

ታዲያ አንተም ጥሩ ተመኝ፣ አንዴ ቁጭ በልና ግብህን አስምረው፣ ተግባራዊ እርምጃን ውሰድ... ያኔ አላህ ያሳካልሀል።

SIT ONCE TO SET YOUR GOAL IN LIFE

[248] ሀያቱታቢኢን - ዶ/ር አብዱረህማን ረአፈት አልባሻ

BIBLIOGRAPHY

እንግሊዘኛ

1. The Noble Quran - Interpretation of the meanings in the English Lan guage, By – Dr. Muhammed Mushin Khan and Dr. Muhammed Taqiudin Al-Hilali. DARUSSALAM- Global leader in Islamic Books 1996
2. How to win Friends & Influence people – Dale Carnegie. Adivision of simon & Schuste,Inc. New York, Ny - 1981
3. Do you have a big Idea – A success story about Thomas Edison
4. Every day Entreprener Dr. Orwin
5. How this Happened - An Analysis how Barack obama Used his Emotional Intelligence and Transformational leadership skills to win his campaign project. By; Dereje Befekadu – 2009. USA.
6. The Road to Success - Dr. Faize seyal
7. The Attract Factor -
8. Be your self - Lienda Field
9. The power of thinking Big - Dr. David Schwartz
10. Islam today- Pro. Al-Mewdodi
11. Principle centered Leadership - Stephen. R.Covey
12. The 17 Principles of success - Napolion Hil
13. Success is Never Ending Failure is Never Final : Robert H Schuller
14. 60 Ways to change your Life - Napolion Hill
15. The 100 Ranking of the most Influential Persons in History – Micheal Hart, Golden Book Center, K L, (1979)
16. The 7 Habits of Highly Effective Teens – SEAN Covey :2014 - USA
17. My vision – Challenges in the race for Excellence – Mohammed bin Rashid Al-Maktoum Published by Motivate Publishing, 2012
18. The difference Maker – Making Your Attitude your greatest Asset John C. Maxwell 2006 – California
19. The 8th Habit from Effectiveness to Greatness - Covey
20. Islam and the world - Abul Hasan Ali Nadwi

21. Your Road Map for success - Maxwell .I
22. The Alchemist – A Magical fable about following your dream, Harper Collins Publishers London 1988
23. World Famous Personality - Roopa Gosain – Good will Publishing Hause India – New Delhi
24. The 7 Habits of Highly Effective People – STEPHEN R. COVEY Published in Great Britain by simon % Schuster UK Ltd, 1989
25. First thing First - Stephen covey – Coping with the ever- Increasing demands of the work place – First Published in Great Britain by Simon & Schuster UK Ltd 1994
26. You Can win - Shiv Khera - Rajiv Beri fer Machillan Indian Ltd New Delhi - 2002
27. The prince: Niccolo Machiavelli, Richard clay Ltd, England - 1981
28. Islam and Management – Dr. Naceur Jabnoun International Islamic publishing House (IIPh), Riyadh Saudi Arabia -2008
29. The 3rd Alternative – Stephen R. Covey, A division of simon & Schuster Inc. 1230 Avenue of the Americas New York, NY 2011
30. Living the 7 Habits – Stories of Courage and Inspiration. Stephen R. Covey By Franklin Covey Co. – 1999
31. Entrepreneurship – Werotaw Bezabih Assefa (Ph.D) – Alpha printers 2010
32. Freedom is not free – Shive Khera – Macmillan India Ltd 2005
33. How to win Friends & Influence people – Dale Carnegie simen & Schuster Inc, 1230 Avenue of Americas, new York, -1982
34. The Beautyful ones anre not yet Born – AYI KWEI ARMAH Cox & Wyman Ltd, Great Britain – 1988
35. Awaken the Giant with in – Anthony Robbins, Simon& Schuster Australia, Sydney – 1991
36. Love and Tolerance - M. Fethullah Gulen New jersey – 2006
37. God is Dead – Fredrich Nitzsche
38. Islam in Nineteenth Century Wollo, Ehiopia – Pro. Hussein Ahmed
39. Imamu Bukhari, his life and works – Maulana Ahmed Ali

አማርኛ

40. በትልቁ የማሰብ ኃይል ትርጉም፡- ሱራፌል ግርማ. ኤች ዋይ ኢንተ. ማተሚያ ቤት፤ ሰኔ 2006 ዓ.ል
41. የአመራር ጥበብ - ጌታቸው በለጠ፤ ርሆቦት አታሚዎች- 2004ዓ.ል
42. የጊዜ አጠቃቀም ጥበብ - ኢዮብ ማሞ፤ 2004 ዓ.ል
43. የስኬት መርህ - ትርጉም ፋሲካ ግዛው
44. እይታ - እዮብ ማሞ፤ 2005 ዓ.ል
45. የስኬት መንገድ - ትርጉም - ቴዎድሮስ አጥላው፤ 2005 ዓ.ል
46. 17ቱ የስኬታማ ህይወት ሚስጥራት፡- ትርጉም ፋንታሁን ሃይሌ - H.K Publishing Plc 2005 ዓ.ል
47. የአሸነፊነት ሀይል፡- ትርጉም ኤፍሬም አበበ
48. ስኬት በ30 ቀናት፡- ትርጉም በዮሀናን ካሳ 2006 ዓ.ል
49. ስኬታማ የጊዜ አጠቃቀም፡- ትርጉም አባተ መንግስቱ፤ 2005 ዓ.ል
50. የቢዝነስ ማሻሻያ ቁልፍ ሙያዎች፡- በ ዶ/ር ወሮታው በዛብህ
51. ትኩረት ፡- በዶ/ር ኢዮብ ማሞ 2006 ዓ.ል
52. ራስን መሆን ፡- ትርጉም በረከት ብርሃኑ - 2001 ዓ.ል
53. በራስ መተማመን ፡- ትርጉም ዳዊት መላኩ- 2005 ዓ.ል
54. የስሜት ብልህነት ፡- ዶ/ር ኢዮብ ማሞ
55. የስኬት በሮች ፡- ትርጉም አበባየሁ ወርቁ - 1995 ዓ.ል
56. የስኬታማነት ጥበብ ፡- ኤፍሬም እንዳለ - 2005 ዓ.ል
57. ስብስብ ግጥሞች ፡- በዕውቀቱ ስዩም
58. መደድ (የግጥም መድብል) ፡- ኑረዲን ዒሳ - 2000 ዓ.ል
59. ለአሸናፊነት መገዛት ፡- ትርጉም ማህሌት ጥላሁን እና ዳኜ መላኩ - 2001 ዓ.ል
60. ሰይፉን ፍለጋ ፡- ሐሰን ታጁ - 2006 ዓ.ል
61. የአሸናፊነት ዳንያ ፡- ትርጉም
62. ኢስላም ከትናንት እስከ ዛሬ ፡- ትርጉም ሀሰን ታጁ 2001ዓ.ል
63. ኢስላም የማህበራዊ ችግሮች መፍትሄ ፡- ነጃሺ ማተሚያ ቤት - 2003

64. ኢንተርፐርነርሺፕ - ራስንና ሀገርን ለማበልፀግ - በዶ/ር ወሮታው በዛብህ አሰፋ 2003 ዓ.ል
65. ምርጥ ኢስላማዊ ታሪኮች - በአወድ አብዱልሰቡር - ነጃሺ ማተሚያ ቤት - 2004
66. የቃየን ፍሰጋ - የግጥም መድብል
67. አብሪልና አዝሪል - የግጥም መድብል በ አክሊሉ ደበላ - 2005 ዓ.ል
68. የስደተኛው ማስታወሻ - ተስፋዮ ገብረአብ - 2006 ዓ.ል
69. የደራሲው ማስታወሻ - ›› ›› - 2004 ዓ.ል
70. የጋዜጠኛው ማስታወሻ - ›› ›› - 2001 ዓ.ል
71. ቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም - እነ ሸይኽ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅ - 1997 ነጃሺ ማተሚያ ቤት
72. ተምሳሌቶቻችን -
73. እይታ - ዶ/ር እዮብ ማሞ
74. መሉነትን መላበስ - ትርጉም - 1999 ዓ.ል
75. እሳት ወይ አበባ - ሎሬት ፀጋዮ ገ/መድህን
76. የስኬት ቁልፎች - ዶ/ር እዮብ ማሞ
77. የፊጣሪ ሀልውና በሳይንስ መነፅር - በሃሩን ያህያ፣ ትርጉም - ሐምዱ ኢድሪስ
78. ማጀሪስ - በጥላሁን ብርሃኑ - 2006 ዓ.ል
79. ከተውሒድ አድማስ - ያሲን ኑሩ ዒሳ - 2006 - ነጃሺ ማተሚያ ቤት
80. የህሊና እረፍት ቁ. 4 - መሐመድ ዑመር - 2006 ነጃሺ ማተሚያ ቤት
81. ኢስላምና የዘመናችን ስልጣኔ - ሰለሞን ክበደ 1436 ዓ.ሂ.
82. በረካ - መሐመድ ሰዒድ ABX 2006

ዐረብኛ

83. አል-ቁርዓኑል አል- አዚም
84. ሰሂህ አል-ቡኻሪ
85. ሶሂህ ሙስሊም
86. ሱነን ኢብኑ ማጃህ
87. ሱነን አቡ ዳውድ
88. ሱነን አት-ቲርሚዚ
89. ሱነን አን-ነሳኢ
90. አል ሙወጦእ
91.አቡል ሐሰን ዓሊ ሐሰን አልነደዊ (ፕሮፌሰር) ፣(1961) - ማዛኽሪረል ዓለሙ ቢንሂጧጢል ሙስሊሚን - ዳሩል ጉርባህ፣ካይሮ
92. ዘሐቢ - ሊየር አፅላመኑበላእ (1985) ሙአሰሰቱ አር-ራሳላህ
93. ሲፈቱ አሰፍዋእ - ኢማም ኢብኑል ጀውዚ
94. ዶ/ር ጧሪቅ አስ-ስወይዳን - ሲናዐቱል ቃዳህ
95. ዶ/ር ጧሪቅ አስ-ስወይዳን - ተግይሩ አን-ነፍስ
96. ዶ/ር አይመን አስዓድ አብዱ - ሰብዑል ዐደህ ሊአክሰሪ ናሲል ፊዐልየህ
97. ዶ/ር ኻሊድ አቡ ሻድ - ሃቢቢ ያ ሪሁል ኢማን
98. ዶ/ር ዓምር ኻሊድ - ሀታ ዩገይሩ ማ ቢአንፉሲሂም
99. ዶ/ር ዓሊ አል-ቀርኒ - ሚን ረዋኢዒል ቀርኒ
100. ዶ/ር ዓምር ኻሊድ - ደዕወቱን ሲተዐዩሽ
101. ጦበራኒ
102. መህሙድ አል-ሚስሪ - አኽላቁ አር-ረሱል
103. ኢማሙ አን-ነዋዊ - ሪያዱ አሷሊሂን
104. ዶ/ር ጧሪቅ አስ-ስወይዳን - ዐለመትኒል ሀያቱ
105. ዶ/ር ጧሪቅ አስ-ስወይዳን - አካዲምየቱ ኢዕዳዱል ቃዳህ

106. ሸህ ሙሀመድ ሷሊህ አልዑሰይሚን - ሸርሁል -ሙስጦለህል ሀዲስ

107. ዶ/ር ጃሲም ሙሀመድ ሱልጣን - አን ነህዳህ - ሚነሰህወቲ ኢለል የቀዛህ፤ ሙአሰሰቱ ኡሚልቁራ ሊተርጀመቲ ወተውዚዓ - አል-መንሱር

108. ታሪኹል ባግዳዲ

One of the founder & CEO of Excellence Leap Training & Consultancy Institute

በድርጅቱ ከተሰጡ ስልጠናዎች በከፊል...:-



Ministry of Transport Ethiopia added 7 new photos.

6 Jan at 10:03 am ·

ለኢፌዲሪ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሠራተኞች ሊሰጥ የነበረዉ የማነቃቂያ ስልጠና ተጠናቀቀ::

****

የሠራተኛዉን የመፈፀምና ሥራን በአግባቡ የመምራት አቅምን ለማጎልበት ታስቦ ለሁለት ቀ... See more





With Transport Minister

CamScanner



የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ
INFORMATION NETWORK SECURITY AGENCY
የምስጋና ምስክር ወረቀት
Certificate of recognition

To YASSIN NURU



Information Network Security Agency - ኢመደኤ

23 Dec 2019 at 7:50 pm

ለኤጀንሲው ከፍተኛ አመራሮች በአመራር ክህሎት እና ማይንድሴት ዙሪያ ሲሰጥ የነበረው ስልጠና ተጠናቀቀ ፡

አዲስ አበባ ታህሳስ 13/2012- ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ከፍተኛ አመራሮች ከታህሳስ 10-12/2012 ዓ.ም በአመራር ክህሎት እና ማይንድሴት (mindset) ዙሪያ ሲሰጥ የነበረው ስልጠና ተጠናቀቀ

ለሶስት ተከታታይ ቀናት በተሰጠው ስልጠና ተቋማዊ ራእይና ውጥ እረዳድ መፍጠር ፣ የአመራሩን የቡድን ስራ ማጎልበት እና በተቋሙ ይረጃ የሚከሰቱ ችግሮች አፈታት ላይ የአመራሩን ሚና ማሳየትን አላማ አድርጎ የተከናወነ ነበር።

ከዚህ ባለፈ ስልጠናው ተቋማዊ ራእይ እና ተልእኮ ፣ ስትራቴጂክ አመራር፣ ለተልእኮ መሳካት ከሃሳብ እስከ ተግባር ያለውን የአመራር እይታ ፣ ስኬታማ አመራር ምንነት እና ተያያዥ ጉዳዩችን የዳሰሰ ነበር።

እያንዳንዱ አመራር ራሱን በስልጠናው ውስጥ ያየበት እና ለአመራሮች ከፍተኛ የሆነ መነሳሳት የፈጠረ መሆኑን በስልጠናው የተሳተፉ አመራሮች ገልጸዋል።



With INSA







With Minister of Peace Ministers and Top Level Leaders

CamScanner

Mana Murtii Waliigalaa Oromiyaa
የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት
Supreme Court of Oromia







With Oromia Supreme Court

CamScanner



A Minister of Peace Good Will Ambassador









የበጎ ፈቃድ አምባሳደርነት
የምስክር ወረቀት

CERTIFICATE OF GOODWILL AMBASSADOR

ለ ኡስታዝ ያሲን ንሩ

To Ustaz Yassin Nuru





- Yassin Nuru Essa
- Masters Degree – Transformational Leadership & Change (Greenwich University England)
- Degree- Organizational Management – ILI (International Leadership institute)
- Diploma – Business Management – Gondar University

- ከ40 በላይ ኢስላማዊ ትምህርቶችን (የሲዲ አልበሞችን) ለህዝብ ያቀረበ::
- ከአሁን በፊት ያዘጋጃቸው መፅሐፎች :
  - ተሰጥኦህን ፊልግ
  - የመንገደኞች ስንቅ
  - ከተውሂድ አድማስ
  - የኡስታዙ ማስታወሻ

ስለመፅሐፉ ምን አሉ? . . . . .

"... እጅግ በርካታ ከሳይንሱም፣ ከመንፈሳዊውም ዓለም የተቃረሙ አስረጅ ምሳሌዎች፣ ማራኪ አቀራረብ...:: ደራሲው እና አንባቢውን ቀጥታ በሚያገናኝ አተራረክ የሊቁንም የደቂቁንም ቀልብ የሚገዛው ፍሰቱ ፀሐፊው ለነገሩ ብቻ ሳይሆን ለአነጋገሩም መጠንቀቁን ያሳያል::"

በፍቃዱ ኃይሉ (የዞን ዘጠኝ ብሎገር)

"ብዙ መፅሐፍትን አገላብጠህ መፅሐፍን በአዲስ Perspective (The west Meets the east በሚል Sense) ማዘጋጀትህ በጣም ያስከብርሃል::"

ዘላለም ክብረት (የዞን ዘጠኝ ብሎገር)

"ገለ ግብ መቅረፅና ራስን ስለመለወጥ የሚያስተምሩ በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ ሀገር ምሁራን የተፃፉ ብዙ መፅሐፎችን አንብቢያለሁ:: ይህ መፅሐፍ ግን ከሁሉም የተለየ እና ሁሉንም የሚያስከነዳ ሆኖ አግኝቸዋለሁ::"

አስማኤል ሐሰን- ሊከቼረር (ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ)